# ሁለተኛ መጽሐፍ

## ሁሉም ለአንድነት - ማስታወሻና ማስተዋያ

መ. ኃ. መስቀል (ዶ/ር)

## ጸሎት

አቤቱ ፈጣሪአችን አምላካችን ቸሩ እግዚአብሔር ሆይ!

የእውር ሰውን ልቦና ባለ አይን ከሚያየው የበለጠ እንዲያይ

ማድረግ የምትችል አንተ ነህና፤

ይህ መጽሐፍ ለአንባብያን የሚጠቅም ሆኖ ይጨረስ ዘንድ፥

ስለአንተ ፈቃድ እለምናለሁ።

አሜን።

ሦስተኛ እትም ታህሳስ 2018

Copyright © 2019 - 2026 by M.H. Meskale (PHD)
መልሶ የማሳተም መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

# መታሰቢያ

**ለባለቤቴ እና ለልጆቼ፥ እንዲሁም ለኢትዮጵያችን መሠረታዊ ለውጥ፦**
**ለዴሞክራሲ፥ ለፍትህ፥ ለአንድነት፥ ለእኩልነት እና ለነጻነት ሲታገሉ ለሞቱ።**

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ከእዚህ ያደረሰኝን ፈጣሪ አምላኬን በከፍተኛ ደረጃ አመሰግነዋለሁ። በእውነት ፍጹምና ኃያል፥ ስሙ ክቡር፥ ለዘለአለምም የተመሰገነ ፈጣሪ አምላካችን የጨለመውን የሚያበራ፥ ቀናውንም መንገድ የሚያሳይ፥ እኔ በእውቀት ሳይሆን፥ በብዙ ዓመታት ጥረትና በጸሎት የተጋሁበትን ሥራ አይቶ እርሱ እንደረዳኝ አምኛለሁ።

በአካላዊነት የማትታየው ባለቤቴን እና በኑሮዬ ደስ እንዲለኝ የሚያደርጉኝ ልጆቼን በጣም አመሰግናለሁ። ለደገፉኝ ለኔ ዘመዶችና ለባለቤቴ ዘመዶች ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

በቅርብም ሆነ በሩቅ ሆናችሁ በመንፈስ ላልተለያችሁኝ ወገኖቼ ሁሉ ሙሉ ምስጋናዬን ከመንፈሳዊ ፍቅር ጋር አስተላልፋለሁ።

በከፊልም ሆነ በብዛት መንፈሳዊ ትምህርትን ላስተማሩኝ (ለተማርኩባቸው) ኦርቶዶክሶች፥ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

በእርማትም ሆነ አስተያየት በመስጠት ለተባበሩኝ ሁሉ፥ በተለይም ለወንድሜ ለአዲስ አለሙ እና ለጓደኛዬ ለተስፋየሱስ መንግሥቱ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

# ማውጫ


ገጽ

ምስጋና: ........................................ vi

ማውጫ: ........................................ vii

የአጻጻፍ መመሪያዎች:........................................ ix

መቅድም: ........................................ xi


# ክፍል አንድ

## ምድራዊና መንፈሳዊ ምልከታዎች


ገጽ

| | | |
|---|---|---|
| መግቢያ: | | 1 |
| ምዕራፍ አንድ | "ሰው ምንድነው?" ጠያቂውስ ማነው?: | 7 |
| ምዕራፍ ሁለት | ቅራኔዎች በሁሉም ሥፍራ: | 49 |
| ምዕራፍ ሦስት | የእንፋረዳለን ቅዠት: | 83 |
| ምዕራፍ አራት | የደረጀና የጨረቃ ውይይት: | 111 |
| ምዕራፍ አምስት | የሙሙዬና የማማዬ ምክር: | 131 |
| ምዕራፍ ስድስት | ኢትዮጵያችን የማትረሳ ዘለአለማዊት: | 159 |
| ምዕራፍ ሰባት | የደረሰብን ስደትና መከራ: | 173 |
| ምዕራፍ ስምንት | ታሪካዊ ኩነቶች በኢትዮጵያችን: | 187 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ | የሶዶቅ ምክር: | 213 |
| ምዕራፍ አስር | የልመና ጥሪ ለእመቤታችን: | 223 |

# ክፍል ሁለት

## ልባዊ እይታዎች - መንፈሳዊ ግንዛቤዎች


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| መግቢያ፡ | | 239 |
| ምዕራፍ አንድ፡ | እውቀትና ሥልጣኔ፥ ማንነትና ድኅነት፡ | 241 |
| ምዕራፍ ሁለት፡ | እምነት ከትንሽ እውቀት | 281 |
| ምዕራፍ ሦስት፡ | መንፈሳዊ ግንዛቤ፡ | 299 |
| ምዕራፍ አራት፡ | ምልከታችን - ወደ ምሥራቅ፡ | 331 |
| ምዕራፍ አምስት፡ | የሰው ብርታቱ ከመንፈሱ፡ | 351 |
| ምዕራፍ ስድስት፡ | ሙሉ ሰው የት አለ?፡ | 377 |
| ምዕራፍ ሰባት፡ | ማመን - አለማመን - ማወቅ - አለማወቅ፡ | 389 |
| ምዕራፍ ስምንት፡ | ማጠቃለያ ሃሳቦች፡ | 401 |
| ዋቢ መጻሕፍት (ለአራቱም መጻሕፍት)፡ | | 413 |

# የአጻጻፍ መመሪያዎች

ይህ መጽሐፍ ለምሁራኑ እንዲሁም ለሠፊው ሕዝብ ቀላል ምንባብ እንዲሆን የሚከተሉትን የአጻጻፍ መመሪያዎች ተከትሏል፡-

- አንዳንድ ቃላት በመጥበቅም ሆነ በመላላት ሲነገሩ የተለያየ (አሻሚ) ፍቺ እየሰጡ እንዳያደናግሩ፥ አንዳንድ ሆሄዎች ላይ በመጥበቅ መነገር ሲኖርባቸው ከሥራቸው ተሰርዞባቸዋል። ሁለት ፍቺ ከሚኖራቸው ውስጥ ለምሳሌ፡- አልለይህም (ሰረዙ አንድ ሆሄ ላይ ብቻ ነው)፤ አይገባም (ሰረዙ ሦስት ሆሄዎች ላይ ነው)። ይህ የተደረገው፥ በተለይ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ሆኖ፥ ወይንም በውጭ ሀገር ብዙ ስለቆዩ፥ ወይንም ከዛ ስለተወለዱ፥ የአማርኛን ስነጽሑፍ ምንባብ ላልተለማመዱ አንባቢያን እንዲቀላቸው ለማድረግ ነው እንጂ፥ በዚህ ረገድ የአማርኛን ስነጽሑፍ ለማሻሻል ታስቦ አይደለም።
- አንዳንድ ቃላት በትእምርተ ጥቅስ (quotation mark) የታጠሩት፥ አረፍተነገሩ ከሚያመለከተው ውጪ ሌላም ትርጉም ሊሰጠው ስለሚችል፥ የመጽሐፉ ስሜት እንዳይዛባ በማሰብ ነው።
- አንዳንድ ፖለቲካዊ ወይንም ሃይማኖታዊ አመለካከቶች ሲብራሩ፥ የሚያነበው ሁሉ ከራሱ ሃሳብ ርቆ የሚሄድ ባለ አንድ አቅጣጫ አክራሪ ሃሳብ እንዳይጎላበትና እንዳይሰናከል ጥንቃቄ ተደርጓል። ምናልባት በግላጭ ወይንም በድብቅ ወገናዊነት ቢታይባቸው፥ የአንባቢ ይቅርታ ይጠየቃል።
- ከተጠቀሱት ዋቢ መጻሕፍት ሌላ፥ ተጨማሪ ማብራሪያዎች በግርጌ ማስታወሻዎች (foot notes) ተካተዋል።
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተጠቀሱት፥ አንዳንድ ሃሳቦችን ከሥጋዊ እና ከመንፈሳዊ ይዘቶቻቸው ጋር የበለጠ ለማብራራት እንደሚጠቅሙ በማሰብ፥ በጥቅሶቹ ለመታገዝ ያህል ነው እንጂ፥ "በግድ" መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያመለከተው መንፈሳዊ ትርጉም ጋር ለማመሳሰል አይደለም። ሆኖም፥ አንባብያንን ለተጨማሪ ማገናዘቢያ እንዲረዳቸው፥ አብዛኛዎቹ ጥቅሶች በግርጌ ማስታወሻ ነው የተቀመጡት።

- ብዙሓኑ ሲያነቡት "የማውቀውን ቀስቅስ እንጂ አትንገረኝ" እንዳይሉ፤ በተቻለ መጠን፥ ገኃድ የሆኑ ሃሳቦች መጠቀሳቸው ለአንዳንድ የአስተሳሰብ ዘገባዎች የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር፥ ተወግደዋል።
- አንዳንድ ጠቃሚ ሃሳቦች ላይ መጠነኛ ትኩረት ቢደረግ፥ አንባቢ የበለጠ እንዲያስብበትና ነገሮችን በራሱ መንገድ በጥልቀቱ እንዲመለከት ነው።
- ይህ መጽሐፍ ብዙ ንኡሳን አርእስቶችን ያቀፈ ስለሆነ፥ በአንድ በኩል አንባቢ እንዳይበዛበት ሲታሰብ፥ በሌላም በኩል ጠቃሚ ሃሳቦች ጥብብ እንዳይሉበት፥ በግርድፉም እንዳይቀሩ ጥንቃቄ ተደርጓል።
- የዚህ መጽሐፍ መርሆ ነገር ማሳጠር እንጂ ነገር ማስረዘም ስላልሆነ፥ በንባብ ብዙ ጊዜ ጠፍቶ ቁም ነገር የማይገኝበት እንዳይሆን፥ የመጽሐፉ ትኩረት በብዛት አጠቃላይ ፍሬ ሃሳቦች ላይ ነው።
- የዚህ መጽሐፍ ግጥሞች ዋና አላማ አንዳንድ ቁምነገሮችን ለማስጨበጥ በመሆኑ፥ በጥንቃቄ የተደከመበት ከግጥሞቹ ውበት ላይ ሳይሆን፥ ጠለቅ ያሉ ሃሳቦችን በማፍታታት እና በማቅለል ላይ ነው።

# መቅድም

ቀደም ሲል የታተመውን ይህንኑ ሁለተኛ መጽሐፍ አሻሽዬ ሳቀርብ፥ ሌሎች ተጨማሪ ስዕሎችና ግጥሞችንም አጃቢ በማድረግ ነው። መቼም የሰው ሃሳቡ ዘወትር ይለዋወጣልና፤ ተጽፎ ሲቀመጥ ግን፥ ያ የተጻፈው ሃሳብ በዚያው ይቆያል። ነገሮች ጊዜ በሚያስከትለው መለዋወጥ ሲለዋወጡ፥ ተጽፈው የተቀመጡ ጽሑፎችንም ከጊዜው ጋር ማራመድ ግድ የሚሆንበት ጊዜ ይመጣል። ይህም መጽሐፍ በዚህ መልክ እንደገና ታይቶ (ታድሶ) በዚህ ባሁኑ መልክ ተቀነባብሮ ቢቀመጥ፥ በጊዜ ውስጥ ባህረ ሃሳቦቻችንን/ትዝታዎቻችን የምንዘክርበት ጥሩ ማስታወሻ፥ ማሳሰቢያና ማስተዋያም እንደሚሆን ታምኖበታል።

የግለሰቦችና የሕብረተሰቦች ሕይወት በምድራዊ ማዕበል ይንገላታል፤ እኛ ግን አላወቅንም። ሰብአዊነት በውስጡ ያቀፋቸውን ደግነቶችና ክፋቶች ይዞ፥ ካለማቋረጥ እንደሚፈስ እንደ ወንዝ ውሃ ይጓዛል፤ የማናያቸው መናፍስትም (ቅዱሳን እንዲሁም እርኩሳን) እኛ በማናውቀውና ልናውቅ በማንችለው ክስተት ውስጥ አልተለዩንም፤ አብረውን (በዙሪያችን) ይጓዛሉ (ይንቀሳቀሳሉ)። እኛም በምድራዊ ሕይወታችን ውስጥ የሚፈጠረውን የማዕበል ሞገድ (እንግልቶቻችንንም) በራሳችን ስንመለከት፥ ምክንያቱ፥ አካሄዱና መጨረሻው ጥፍት ይልብናል።

ከመንግሥታት መሪዎች እና ምድራውያን ጭፍሮቻቸው፥ ወታደሮች እና ሰላዮች፥ በክፋት የተሰማሩ ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞችም በስተጀርባ የሚገፋፉ "ሂድ፤ በል፥ በርታ፥ ግፋ፤ ግደል፤ ጨፍጭፍ.." እያለ የሚያበረታታ የማይታይ ኃይል መኖር አለበት የሚያስብሉ ኩነቶች ውስጥ እየገባን፥ የዚህን የምድራዊ አካላዊ ጉዞአችንን፥ ስደቱን፥ መጀመሪያና መጨረሻውን መመልከት የማንችል እኛ፤ የማይታዩንን ለማየት መፍጨርጨር ጠባያችን ሆነና፥ ስሜቶቻችንን የምንገልጽባችውን መንገዶች አሰፋናቸው (በስዕል፥ በመዝሙር፥ በዘፈን፥ በድርሰት፥ በግጥም)።

እውነት እንደሚታየውም እንደሚሰማውም አይነት ከማይሆንበት አለም ውስጥ ከመሆናችን አንጻር፥ ወደድንም ጠላንም፥ የኛ ግንኙነታችን ከማናውቀው፥ ከማናስበውም ጋርም እንደሆነ ይገባናል። ሁሉም በየቤቱ እምነት ይኖረዋል። ሆኖም፥ የሰው ልጅ ታሪኩ የተሟላ የሚሆነው፥ ከምድራዊ የሕይወት ታሪኩ ጋር መንፈሳዊነቱንም ጨምሮ ስለሆነ፥ ሁሉንም በአይነ ልቦና አጣምሮ ማየት ይገባል። በዚህም መጽሐፍ የተካተቱት ሃሳቦች እና ቁም ነገሮች፡- እይታዎቻችን ከምድራዊ

እሳቤዎቻችን ወጣ እያሉ፥ አጠቃላይ ሰብአዊነትን (ምድራዊና ሰማያዊ ፍጥረቱን) እንዲመለከቱ እና፥ እኛም ሰዎች (ዘር ሳንለይ) በአንድ መንፈሳዊ ሕብረት እርስበርሳችን እንድንተዛዘን የሚያደፋፍሩ ናቸው።

እነሆ! በጊዜ ውስጥ፥ "የማይገባው ሁሉ ሊገባው" እንደማይችል የሚያሳውቅ ማወቂ አበይት ስሜቶችን ብቻ አተረፈልኝ እንዳልል፥ ቀረጥ ከፋዩ ሕዝቤ ያስተማረኝን ውለታ ባልመልስበትም፥ ታግሶ ይህንን ያህል በምድር ላቆየኝ ሉላዊ ሕብረተሰብ ወደማልመለስበት ስሄድ የምተወውን ማዘጋጀት ግዴታዬ መስሎኝ፥ ግጥሞችን መገጣጠም ጀመርኩ (ስዕሎችንም እንዲሁ)።

ግጥሞች ከውስጣዊ የስሜት ግለት የሚፈልቁ ስለሆኑ፥ እነሱንም እንደ ስዕሎች፥ ሁሉንም እንደ አንድ የሙዚቃ መሳሪያ (ክራር፥ ማሲንቆ፥ ወ.ዘ.ተ.) በመጫወት ብዙ ጊዜውን የሚያጠፋ ሰው የታመቁ ውስጣዊ ስሜቶቹን በአፉ በእንጉርጉሮ ወይንም በመሳሪያው እንደሚገልጽ መመልከት ይቻላል።

በአብዛኛው፥ ግጥሞቼ እና ስዕሎቼ ከአለማወቅ የመነጩ መሆናቸውን የሚያስተውሉ፤ አለማወቅ ኃጢአት እንዳልሆነ ይገነዘባሉ። አላውቅም ብሎ ቁጭ ከማለት፥ ከአለማወቅ ተነስቶም ቢሆን ሥራን መሥራት ይሻላልና፤ ይህንን ሁሉ ሠራሁ። በእርግጥ፥ የሰው የሥራው ፍሬ ጣፋጭነት ለሁሉም እኩል ላይሆን ይችላል። ሆኖም፥ በእግዚአብሔር መንፈስ የተፈጠረ የሰው አለማወቅ "ምንም ሳታውቅ" እንደምታገለግል አህያ ላይሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ፥ የአለማወቅ ፍርኃት ሳያግደው፥ እግዚአብሔርን እየለመነ በትጋት የሚሠራ ሰው፥ የሥራው ውጤት ያማረ ይሆናል እንጂ፥ ውጤት አልባ ሆኖ አይቀርም። ለአንድ የተወሰነ መንፈሳዊ ግብ ከሆነም፥ በ"ውጫዊ ኃይል" እየታገዙ ታላላቅ ሥራዎችን በጥቂት ጊዜያት ያከናወኑ እንዳሉ እናውቅ የለም? እግዚአብሔር ሥራዎቻችንን ይባርክልን።

በዚህ መጽሐፍ የተካተቱት ሃሳቦች ከሌሎቹ ሦስቱም (ከምድራዊነታችን ባሻገር ከተሰኙት :- አንደኛ፥ ሦስተኛና አራተኛ መጻሕፍት ጋር የተቆራኙ ናቸው። ሁሉም ልባዊ እይታዎቻችን ላይ ብናተኩር የረቀቀውን ማወቅ፥ የተሻለውንም ማግኘት እንደምንችል የሚጠቁሙ ናቸው።

በዚህ መጽሐፍ፥ ሌሎች ያልሳሉት ስዕል እንጂ፥ በሌሎች ያልታሰበ አልተጻፈም። አንዳንድ ጊዜ የከበሩ እንቁዎች፥ ወርቆችና ጌጣ ጌጦችም እንዳሉት የማያውቅ ሃብታም፥ አናሳ የሆነው ልጁ ከተቀመጡበት ሲያወጣና ሲያሳየው ሃብታምነቱ እንደሚታወቀው፥ ይህም መጽሐፍ እንደዛው ቢታይ፤ መቼም በልሂቃን

ያልተባለ ያልተነገርም የለምና፥ ያንኑ ዞር አድርጎ በግጥም መልክ ማቅረብ አይከፋም በማለት ነው።

ይህ እና  የተቀሩትም ሦስቱ መጽሐፍ የማያወላውል (ቀጥተኛ) ባህሬ፡- በተለያዩ አርእስቶች ያልተቆራረጠ አንድ ልባዊ እይታን  (ከምድራዊነታችን ባሻገር መመልከትን) ብቻ ይዘው በሃሳብ ይመጥቃሉ። በተለይም በዚህ በሁለተኛ መጽሐፍ ውስጥ፥ አንዳንድ ሃሳቦችን ለመግለጽ በተደረገ ሙከራ፤ ተመሳሳይ እና አንድ ወጥ ሃሳቦችን በአንድ ላይ ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፥ በሚከተሉት  በሁለት ክፍሎች ተዘጋጀ፡-

* ክፍል አንድ፡ ምድራዊና መንፈሳዊ ምልከታዎች

* ክፍል ሁለት፡ ልባዊ እይታዎች - መንፈሳዊ ግንዛቤዎች

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሃሳቦች ከሚከተሉት ሦስት መጻሕፍት ጋር የተቆራኙ ናቸው፡-

<u>የአንደኛው መጽሐፍ ይዘት፡- ከምድራዊነታችን ባሻገር - ከግለሰብ እስከ አገር - ማስታወሻና ማስተዋያ።</u>

አባቶች/እናቶች በበኩላችን የሄድንበትን ጎዳና፥ ያሳለፍነውን ክፉውንም ደጉንም ጊዜ ለልጆቻችን እንድናሳውቅ፤ ለሁላችንም ቢሆን እንደ ማስታወሻ፥ እንደ ማስተዋያም እንዲሆን በማሰብ ተዘጋጀ።

ይህ መጽሐፍ በወታደራዊው አገዛዝ (ደርግ) ዘመን፥ ደራሲው በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ውስጥ የነበረውን ወቅታዊ አብዮታዊ ተሳትፎ፥ በዚያውም ስለ አገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ እና በኢሕአፓ ውስጥም ስለተፈጠረው ውስጣዊ የፖለቲካዊ ውዝግብ ያወሳል።

ከንጉሡ ከኃይለ ሥላሴ የአገዛዝ ዘመን ተከትሎ፥ ሀገራችን (ኢትዮጵያችን) በቀጣይ መንግሥታት ውስጥ ያሳለፈቻቸው ጊዜያቶች ለሕዝቦቿ እንግልት፥ ስቃይና መከራ ሆኖባቸዋልና፤ ይኸም መጽሐፍ የመጨረሻውን እትሙን ከማሰራጨቱ በፊት፥ በሃምሳ ዓመታት ሂደት ውስጥ የተፈጠረውን የሀገራችንን ሁኔታ እየተከተለ፥ ባጭር ባጭሩ በማቅረብ፥ ኢትዮጵያችን ካሁን ቀደም የገጠሟት ችግሮች እንዳይደጋገሙባትም በመምከር፥ በሰላም፥ በነፃነትና በእኩልነት አንድነታችንን እንድንገነባ ያሳስባል።

## የሦስተኛው መጽሐፍ ይዘት፡- ከምድራዊነታችን ባሻገር - ሳይንስ፥ እምነት፥ ሥልጣኔ - ማስታወሻና ማስተዋያ

ይህ መጽሐፍ ምድራችን በዚህ በአሁኑ መልክ ከምናያት አስቀድሞ እንዴት እንደነበር ግምታዊ - ሳይንሳዊ ማብራሪያ ያቀርባል። በጂኦሎጂ (ሥነ ምድር) ምርምር ከተገኙ መረጃዎች በመነሳት፥ በምድራችን የተከናወኑትን ተፈጥሮአዊ ክስተቶች - ተፈጥሮአዊ እድገት በአካላዊነቱ ከዝግመተ ለውጥ (evolution) እንዴት ተለይቶ እንደሚታይ ያብራራል።

ለአንዳንድ መሠረታዊ ሳይንሳዊ ጥያቄዎችም ጥንቃቄ በተመላበት መንገድ፥ ሃይማኖታዊ (መንፈሳዊ) አስተያየት ያቀርባል። ቀጥሎም፥ ስለ ሰው ዘር አመጣጥ፥ ስለ ስደቶቻችን እና ስለ ቀደሙ ሥልጣኔዎች፥ ከማንነታችን ጋር ስለሚያያዘው ስለ መንፈሳዊ አንድነታችን ጉዳይም ያወሳል።

ሳይንስ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ እንጂ፥ የሚያርቅ አለመሆኑን ለማስረገጥ ይሞክራል። ሆኖም፥ ይህ እኛ “ሳይንስ - ሥልጣኔ” የምንለው ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ ቢሆንም ባይሆንም፥ ከዚህ ዘመናዊ ሥልጣኔ የተለየ “ሌላም፥ ሌላም” ሊኖር እንደሚችልም ይጠቁማል።

## የአራተኛው መጽሐፍ ይዘት፡- ከምድራዊነታችን ባሻገር - መንፈሳዊ ጉዞ - ማስታወሻና ማስተዋያ

ይህ መጽሐፍ ከምናየው አለም የማናየውን አለም ለማየት ስንሞክር የሚታሰበንን (ፍቅር፥ ደስታ፥ ሃይማኖታዊ - መንፈሳዊ ስሜት..) የሚጠቃቅስ፤ ሁሉም የገዛ እምነቱን ይዞ እንዲጸና ለየት ባለ መልክ የሚያሳስብ ነው።

## ድረ ገጽ፡- https://www.ambscience.org/

ቀደም ሲል፥ ይህ ድረገጽ ተዘጋጅቶ አያሌ ግለሰቦች በአለም ዙሪያ ተመልክተውታል። አራቱም መጻሕፍት ከሌሎች ተጨማሪ ጽሑፎች፥ ግጥሞች እና ስዕሎች ጋር፤ ሳይንሳዊ ጽሑፎችም በዚሁ ድረገጽ ውስጥ ተካተዋል። መጻሕፍቱ እየተሻሻሉ በድግግሞሽ በታተሙ ቁጥር፥ ድረገጹም በዛ ልክ እየታደሰ ቆይቷል።

# መግቢያ

ሰው በደንብ እያወቀ መጥፎም ጥሩም እንደሚሠራ ሁሉ፥ በደንብ ሳያውቅም መጥፎም ጥሩም ይሠራል። ማወቅ የምንችለውን እና የምናውቀውን በቀላሉ የምናምንበት ሲሆን፥ ማወቅ የማንችለውን እና የማናውቀውን ማመን ያስቸግረናል። ሆኖም፥ በአይነ ልቦና ለማየት ስንፈልግ፥ በአካል ባይሆንም በመንፈስ እንድናውቅና እንድናምን "ይደረጋል/ይሆናል"። ነገር ግን፥ ይህ እውነት ስለመሆኑ፥ በምን ማረጋገጥ ይቻላል? ለአንዱ የሚታየው ለሌላው አይታየውም። እያንዳንዳችን በሁለት ጎራ እንድንከፈል በሚያደርገን ሁኔታ ውስጥ እያለፍን የነገሮችን መጨረሻ እንጠባበቃለን። ስለ ሁሉም ነገር "እንድናምን የሚያደርገንን" ማመሳከሪያ የሚሆነንን እውቀት ባናገኝም፥ እምነታችንን የሕይወታችን ባቡር አድርገን እንጓዛለን። መጨረሻችንን (መውረጃ ጣቢያችንን) የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው[1]።

ውስጣዊ ስሜቶቻችንን በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ እንዲሁ እየተንገታገትን ለመግለጽ ስንሞክር፥ እውነት እንደሚታየውም እንደሚሰማውም አይነት ከማይሆንበት አለም ውስጥ በመሆናችን፥ ያዝ ለቀቅ እያደረገ የሚያንገላታን እድል ፈንታችን ወዴት እንደሚመራን አላወቅንም።

አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን ከሃይማኖታዊ እምነቶች የሚያርቁት፥ "ይህ በሳይንስ ያልተረጋገጠ፥ ከእውነትነት የራቀ፥ ወዘተ.." በማለት ነው። ታዲያ፥ "የሰው ልጅ (ሕይወቱ) ይህንን ያህል ጥሩ የሆነው፥ ያንን ያህልም መጥፎ የሆነው እንዴት ነው?" እያልን እራሳችንን ስንጠይቅ፥ መልስ የሚሰጠን ሃይማኖት (ማንኛውም ሃይማኖት) ነው እንጂ፥ ሳይንስ አይደለም።

እነሆ! በስሜቶች ብቻ የሚገባን ከሚመስለን ጋር፤ እንዲሁም በእምነታችን ምሥጢራትን (ከአእምሮ በላይ) የሆኑትን ሁሉ በልባችን ይዘን፥ ይህንን ያህል በመቆየታችን የምናወራው (የምንጽፈውም) አልጠፋንም። ከእልፍ አእላፋት ጠፈራዊ አካሎች ውስጥ እኛ በዚህች ሰዓት ከዚህ ስለተገኘን ለፈጣሪ አምላካችን ምሥጋና የምናቀርብበትን መድረክ በማግኘታችን ደስ ይለናል።

እነሆ! በስዕል መደበኛ ትምህርት ከተገኘ እውቀት ሳይሆን፥ በልምድ የተገኙ የብዙ ዓመታት ስዕሎቼን እንዲሁ በትኜ አላስቀራቸውም በሚል ቁጭት አንድ መልክ ላስይዛቸው ተነሳሳሁ። ይህንን አበርክቶዬን "በተሰጠው ሁለት መክሊት ላይ፥ ሌላ

---

[1] "..ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።" ዮሐ. 20፡29

ሁለት አትርፎ እንደመለሰው ታማኝ አሽከር ይቆጠርልኝ ይሆናል” ብዬ የማስበው ብርታት ሰጥቶኝ ከዚህ ደርሻለሁ።

አብዛኞቹ ስዕሎች ድብቅብቅ ያሉ ስለሆኑ፥ እያንዳንዱ ተመልካች እንደራሱ ስሜት እና አስተሳሰብ ይረዳዋል። አንዳንዶቹ ስዕሎች ሲያዩአቸው ምንም የማይማርኩ ቢሆኑም፥ ከያንዳንዱ ስዕል አብሮት ያለውን ጽሑፍ በጥሞና ለተመለከተው፥ ከዚያ ሥፍራ የታመቁ ሃሳቦች መኖራቸውን ማገናዘብ ይቻላል። እነኚህም፥ ስታገላብጡ የምታዩአቸው፥ በሃያ ዓመታት ገደማ ውስጥ ከተሠሩት የተለቀሙ ናቸውና፤ ፖለቲካ፥ ማሕበራዊ ኑሮ፥ ሃይማኖት እና መንፈሳዊ ስሜቶችን ያስተጋባሉ፤ በኢትዮጵያችንም ያሳለፍናቸውን የውጣ ውረድ ጊዜያቶች በማስታወስ፥ ጥልቅ ትዝታዎችን በመቀስቀስ፥ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ተጨማሪ ንቃትና ብርታት እንደሚሆኑን ታምኖበታል።

በተለይም ግጥሞቹ “በኢትዮጵያችንም ሆነ በተቀረው አለማችን ውስጥ ግለሰብአዊ፥ ቤተሰብአዊና ሕብረተሰብአዊ ኑሮአችን ወዴት ነው የሚመሩን? የኛስ ርዕዮተ አለማችን ወዴት ነው የሚወስደን? የምድራዊ ኑሮአችን እንዴት ካለ መንፈሳዊነት?” እያልን እንድንጠይቅ ያደፋፍራሉ።

ብዙውን ጊዜ ስዕል በመሳል የሚጠመዱ ግለሰቦች፥ በውስጣቸው የታመቁ ሃሳቦቻቸውን (ብሶት፥ ሃዘን፥ ደስታ...) ለመግለጽ ካላቸው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ፣ ለእነርሱ የመንፈስ እርካታ የሚያገኙበት፥ እንደ ውስጣዊ ህመም መርሺያ፥ ማስታገሺያ ሊሆን ይችላል።

አንዳንድ ጊዜ ስዕል መሥራት እንደ ጊዜ ማሳለፊያ፥ እንደ መተከዢያ፥ እንደ ማሰቢያና ማሰላሰያ ሊያገለግል ይችላል። በዚህን ጊዜ ሰአሊው ሳያስበው ከሚነካካቸው ውስጥ ብቅ ብቅ የሚሉ ምስሎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደዚህ ያሉ ስዕሎች በብዛት ይገኛሉ።

ስውር/ድብቅ ስዕሎች (አብስትራክት ወይንም/ እንደ አብስትራክት ያሉ) እንደየተመልካቾቻቸው፥ እውነታን በብዙ የተለያዩ መንገዶች በማንጸባረቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና አላቸው። ስውር/ድብቅ ስዕሎች እጅጉን የተለዩ ናቸው። እነርሱ፤ የሌለን ነገር ያለ ነገር እያስመሰሉ በቀለሞች ቅንጅት ብቻ ቀልብን የሚስቡ ናቸው። ደግነቱ፥ የሰው አእምሮ እጅጉን ሰፊ በመሆኑ ማንኛውም ስዕል (የረቀቀውም/ያልረቀቀውም) እንደየተመልካቹ የተለያዩ ስሜቶችን ማስተጋባቱ አይቀርም። ስለዚህ፥ የስዕል ትምህርት ያላቸውም፥ የሌላቸውም እንዲሁ በልምድ የሚስሏቸው ስዕሎች ሁሉ ውጤት አልባ ሆነው አይቀሩም።

እውቀት ካለ ፍልስፍና ጥልቀት አይኖረውም፤ ስነ ጽሑፍም በስዕል ሲታገዝ ማስተዋልን ይጨምራል (ያሳስባል፥ ያፈላስፋልም)። በዚህ የስዕሎች እና የግጥሞች ስብስብ እና ቅንብር ውስጥ፥ ከምድራዊ አስተሳሰብ ወጣ እያለ፥ ወደ መንፈሳዊነት የሚያመራ ፍልስፍናዊ ምልከታዎችን በአንድ ወጥ እሳቤ (አንድ አቢይ መልእክት) በአንክሮ ለማስተጋባት ተሞክሯል። ይኸውም፡- የማናውቀውና ልናውቅ የማንችለው ኃይል መኖሩን፤ ይህንንም በአካላዊው አለማችን መረዳት እንደማይቻል፤ በሚሰማን በውስጣዊ ስሚቶቻችን (አይነ ልቦና) ማወቅ የምንችለውን አውቀን፥ ከእውቀት በላይ የሆነውን፥ ካለ በቂ እውቀትም ቢሆን፥ እንዲሁ ማመን የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ለማሳሰብ (ለአንዳንዶቻችንም ለማስታወስ) ነው።

## ግጥሞች ግጥምጥሞች - ስዕሎች የአይን ማረፊያዎች

ሃሳብ ሲበራከት፥ ሲከብድ - ለመግለጽ ሲያስቸግር፥

ቋንቋም አልበቃ ሲል - በአፍ የሚነገር፥

ቢነገሩም፥ ተነግረው ተነግረው ለማያልቁ ግትልትል ሃሳቦች፥

ጉራማይሌ ስሜቶች፥

"እንግዲህ በቃ!" የሚሉ፥ ስንኞች፥

"በቃ! ይኸው ነው ባጭሩ" የሚሉ፥ አጫጭር ቃሎች፥

የነገር መቋጥሮች፥ መተከዢያ - ትዝታዎች፥

የሃሳብ ጭማቂዎች፥ የቅርቡን አጉሊዎች፥

የጥንቱን አስታዋሾች - ጊዜን ደምሳሾች - ፈጣን ባቡሮች፥

ቅዠትም ቢመስሉ - እውነታዎች፥

የሰማዩና የምድሩ ንኪኪዎች፥

ተስፋዎች - ልዩ መስተዋቶች፥

አጽናኞች - የእንባ ማድረቂያዎች፥

የናፍቆት አስታጋሾች - የፍቅር መግለጪያዎች፥

ማስተማሪያና ማወደሻ ቅኔዎች፥

መደሰቺያ ዘፈኖች፥

መዝሙሮች - መጸለያ ቅዳሴዎች።

ስዕሎች ማራኪዎች፤ ቀልብ ሳቢዎች፤

ስሜት ጎታቾች፥ ሃሳብ አፍላቂዎች፤
ትዝታን ፈጣሪዎች፤
ቁም ነገርን አሳሳቢዎች፤
ኑሮን የሚያስቃኙ አስታዋሾች።
ስዕሎችም በጠባያቸው፥
ግጥሞችን መሰሏቸው፥
የሰውን ቀልብ የሚስቡ ናቸውና፥
በማራኪ ውበታችው፥
በውስጠ ታዋቂ ሃብታቸው፥
እውቀትን በስሜት በመሰረጻቸው፥
እንደ ከበሩ ማእድናት፥
በእይታ ደስ የሚያሰኙ፥
አዎ! የእውቀት ምንጭም በመሆናቸው፥
ስዕሎችም ግጥሞችን መሰሏቸው።
የደከመ፥ የፈዘዘም ቢሆን፥
እውነትን የሚስብ - የሚያሳስብ፥
የበረታም ቢሆን፥
የሰውን ቀልብ የሚስብ፥
የታመቀ ኃይል ይኖራል፥
በግጥም ወይንም በስዕል።
በመንፈሳዊ እሳቤ ከተጀመረ፥
በመንፈሳዊ ኃይልም ከተቀመረ፥
የሁሉም መጨረሻ ይሆናል፥
ያማረ፥ የከበረ።

# ክፍል አንድ

## ምድራዊና መንፈሳዊ ምልከታዎች



## የክፍል አንድ መግቢያ


በዚህ ክፍል ውስጥ፥ በተለያዩ አርእስቶች የተካተቱት ሃሳቦች፥ በክፍል ሁለት ካሉት ለየት ይላሉ። በዚህ ክፍል ውስጥ፡-

የኢትዮጵያን ሕዝብ ለስቃይና ለመከራ የዳረጉትን ኩነቶች በማስታወስ፥ ምድራዊና መንፈሳዊ ምልከታዎችን (ትእይንቶችን፥ ታሪኮችን) በተለያዩ መንገዶች ይዘረዝራል።

በአጠቃላይ፥ የሰውን ተፈጥሮ፥ መንፈሳዊ ባህሬውንም በማገናዘብ፥ ክፍል አንድ ለክፍል ሁለት እንደ መነሻ - እንደ መንደርደሪያና እንደ ድጋፍ እንዲሆን ተዘጋጀ።

# ምዕራፍ አንድ

## ሰው ምንድነው? ጠያቂውስ ማነው?



ግርምተኞች

**<u>የግርምተኞች ጥያቄ</u>**

ሳር ቅጠሉ፥ አፈር ድንጋዩ፥ እንስሳቱ ሁሉ፥
"ሰው ምንድነው?" ይላሉ።
ሰውም "ሰው ምንድነው?" ብሎ ራሱን ሲጠይቅ፥
መልስ ሰጪው እራሱ መሆኑ ምን ይደንቅ!
"አንተ'ኮ አንተን አይደለህም!" ብሎ ለጥያቄው ምላሽ ቢሰጠው፤
"አዎ! እኔም እኔን አይደለሁም.." ማለቱ 'ማይቀር ነው።

ግን በእውነት ሰው ምንድነው?
በአካል የሚንቀሳቀስ፥ የሰይጣን ቤት ነው?
ሁልጊዜ ሲዋሽ ሲያታልል የሚኖር?
ክፉ ካላሰበና ካልሠራ መኖር የማይችል?
በውስጡ አሉታዊነት እንጂ አዎንታዊነት የሌለበት፥
በእውነት እርሱ ነው ሰው የተባለው?

ሰው በፍጥረቱ ሁለት አይነት - አንዱ ለሌላው ጣውንት፥
ክፉና ደግ በውስጡ - የባላንጣዎች ማደሪያ - ተንቀሳቃሽ ቤት?
ሥጋ ከመንፈስ አንዱን ሰው  ሲጋሩት ለሁለት፥
ባለ ሁለት መልክ ሆነ የሰው ሰው-እነት።

ሰው በሰውነቱ ተመሳሳይ፥
የሃሳቡ መቀመጫያው የማይታይ፤
የሰው ልዩነቱ ብዛቱ፥
ጠባየ ብዙ በየቤቱ።
ሰዎች እርስ በርሳቸው ይተያያሉ በአይኖቻቸው፥
ይለያያሉ በአእምሮአቸው።

ሰው ለሰው አንድ ነው፤ ለእንስሳትና ለአውሬዎች፥ ለእጽዋትም ሌላ ነው፤
ለአንዳንድ ፍጥረታት ሰው ጌታ ነው፥ ለሌሎችም አውሬ ነው።
አውሬዎችም ሰውን ሲያዩ እጅጉን ይፈሩታል፤
የሕልውናቸው ተቀናቃኝ ስለሆነ ይሸሹታል።

በምድራዊና በመንፈሳዊ ተፈጥሮአችን ሁለት ነን መቼም፣

ውስጣዊ ማንነታችን ብናውቀውም ባናውቀውም፥
የምናውቀው ከማናውቀው አይስማማም።
የለሰለሰው ውስጣዊ ማንነታችን እንዳይነካብን፥
በምድራዊ ተጋላጭነት፥ ኃጢአተኛም ላለመምሰል፥
የላይ ላዩን የሕብረተሰብ ግንኙነቶችን ፈጥረን፥
ትርጉም በሌለው ምድራዊ ኑሮ ተሸፋፍነን፤
በተለያዩ ጭንብሎች ራሳችንን እየደበቅን፥
የማንወደውን እየሠራን እንኖራለን።
ሰው ልውጥውጥ የሚለው በአንድ ቅጽበት፥
ፈገግታና ሳቅ፥ ወዲያውም መከፋት፥
ትዝ የሚለው ነገር ቢኖር ይሆን በእውነት?
እጅግ ልዩ መሆኑ ያ ቀድሞ የነበርንበት፥
ያ ደስ የሚለው ሕይወት በሁለትነት ሳይሆን በአንድነት?
ከዘላለም የሕይወት ውሃ እንደተቀዳን፥
ከመሬት ሌላ ማንነት ሲሰጠን፥
ሥጋን ላለማስከፋት ብለን፥
ምድራዊ ማንነታችንን እጅጉን እየገነባን፥
እርሱን የበላይ አደረግን፤
የዘለአለማዊው ማንነታችን ተረሳን፤
ሰዋዊው ማንነታችንን፥ ሳናውቀው ውስጣችንን፥
ሳንወድ እንኖራለን፥ ያልሆነውን ሆነን።
ሰው ምንድነው? ጠያቂውስ ማነው?
መደምደሚያ ማጠቃለያም የሌለው፥
መልስ ቢኖረው፥ ሰው ሊሆን አይችለም መልስ ሰጪው።



የሰው ሁለትነት

## **<u>የሰው ሁለትነት</u>**

ሰው ከራሱ ወጥቶ ቢመለከት እራሱን፥
እንደ ዳኛ ፈራጅም ቢሆን፥
ማየት ቢችል፥ አጥፊውን፥ አልሚውን፥
ለየትኛው ጎኑ ይፈርድ ይሆን?

ወይም መርጠህ ውሰድ ቢባል፥ ከሁለቱ አንዱን፥
የትኛውን ጎኑን መርጦ ይውሰድ?
የትኛውን ጎኑን (የትኛውን የእርሱን እርሱነቱን) ይጥላ፥
የትኛውን ጎኑን (የትኛውን የእርሱን እርሱነቱን) ይውደድ?
　　እንዲህስ ካስመረረ ሁለትነታችን፥
　　መነሻው የባህሬአችን፥
　　ሰው እንዴት ሊያውቅ ይችላል፥
　　ከራሱ ወጥቶ ስለራሱ - የራሱን?
ምንድነው የሁለትነታችን መንስኤው?
ሰው በቁመናው ብቻ ከሆነ የሚለካው፥
ከባቢውን ሁሉ ነው የሚመስለው።
ግን፥ የሰውን የራሱን ሰውነት ብቻ ብናስተውለው፡-
　　ግራ አንጎል፥ ቀኝ አንጎል፥ ግራ ጎን፥ ቀኝ ጎን፥
　　ግራ ፊት፥ ቀኝ ፊት፥ ግራ እጅ፥ ቀኝ እጅ፥
　　ግራ ቂጥ፥ ቀኝ ቂጥ...፤
　　በአብራኮቹ ሁሉ - በውስጦቹም፥ በውጪዎቹም፥
　　መንትያዎች - እንደ ግራ እግር፥ ቀኝ እግር፥
　　በውዝዋዜ እንደ ሰልፈኛ - ግራ ቀኝ እንደሚል ወታደር፥
　　አንዱ ከአንዱ  ውድድር -  ፉክክር።
ሰው ሥጋ እና መንፈስ ሆኖ በመፈጠሩም ምክንያት፥
በውስጡ ሌላ - ልዩ ተቃርኖ አለበት፥
ስለዚህ በዚህ ምድራዊ ሕይወት፥
ከፋትና ደግነት በበዛበት፥
የማያቋርጥ ሙግት ነውና የሰው እድገት፥
በውስጡም በውጪውም ፍትጊያ አልቀረለት፥
በውስጡም በውጪውም ጦርነት -  እስከ ሞት።
　　የ"ይሁን፥ አይሁን" ክስተት - የሕልውና -  የሃሳብ ክርክር፤
　　እንዳው የሚገርም  - የሚደንቅ ነው የሰው ነገር.።



ሰው የሃሳቡ እስረኛ

## ሰው የሃሳቡ እስረኛ

የትም ቢሆን የትም፥ በነጻነት በባርነትም፥

የሰው ልጅ የሃሳቡ እስረኛ መሆን አልቀረለትም።

ግን በተለይ፥ ለሌሎች የኖሩ ከራሳቸው ወጥተው፥


ለፍትህ፥ ለነጻነት የሚታገሉ ናቸው፥

እስር ቤት የሆነ ቤታቸው።

ምንድነው ይህ እውነት የሚሉት፥

ሰዎች በትግል የሚሞቱለት፥
የሰው ልጅ ከውሸት በሽታ ቢድን፥
በእውነታ ውስጥ ብቻ መኖር ይችል ይሆን?
አይ! ምድራችንም'ኮ እስር ቤት ናት፥
የራሷ ሕገ መንግሥት ያላት።
"በአለማዊ መንገድ ካልኖርክብኝ፥
እኔ ከአንተ ጋር ምን አለኝ?..."
እያለች መንፈሳውያንን ስታስቸግራቸው፥
ገዳም መግባት ብቻ ይሆናል የኑሮ ምርጫቸው።
በገዳም የሚገኝ ሰላምና ፍጹም ነጻነት፥
ሰማያዊ ሃሴት በጾም በጸሎት፥
ከቅዱሳን፥ ከጻድቃን ሰማእታት፥
ከመላእክትም ጋር መንፈሳዊ ግንኙነት፥
በምድር እየኖሩ፥ ሰማያዊ ስርአት፥
ይኸው አየነው ሰውን ነጻ ሲያስወጣ ከእስር ቤት።[2]

[2] "እግዚአብሔር በቅዱስ ቦታው ለድሃ አደጎች አባት፥ ለባልቲቶችም ዳኛ ነው። እግዚአብሔር ብቸኞችን በቤቱ ያሳድራቸዋል። **እስረኞችንም** በኃይሉ ያወጣቸዋል፤ በመቃብር የሚኖሩ ኃዘንተኞችንም እንዲሁ።" መዝ. 67፡ 5-65



ሰውና ተፈጥሮ

## ሰውና ተፈጥሮ

ሰውና ተፈጥሮ - እንዴት ነው አንዱ ከሌላው የሚለየው?

የምናውቀው ከሆነ የሚታየው፥

የማናውቀውም ከሆነ የማይታየው፥

ስንቱን ነው አይተን የምንለየው?

ስንቱንስ ነው ሳናይ ቀርተን ያላወቅነው?
እኛነታችንን ከተፈጥሮ ለየን?
ግን፥ በምድራዊነውታችን አንድ ነን።
ሰው ሁሉ ባንድ ላይ (ወታደሩም፥ ቄሱም፥ ጳጳሱም)፥
ሰማያዊ መሳይ ምድራዊ፥
እውቀትም ሁሉ ማቆያ ለሥጋችን፥
እንዳይርበን እንዳይጠማን፥
ሁሉም ሰማያዊ መሳይ ምድራዊ።
የሰውን የአለማወቁን ስፋት እጅጉን አጥብበን፥
በማወቁ ስፋት ተመክተን፥
የጎደለንን ሳናውቅ ተጎዳን።
ግን፥ እጅግ የሚገርመው፥
ብዙ አውቀው እውቀት ከሞላባቸው፥
ትንሽ ብቻ አውቀው የሚኖሩ - እውቀት የጎደለባቸው፥
ደስተኞቹ እነርሱ መሆናቸው።
ምድራዊ ስግብግብነት ፖለቲካን ፈጠረው፤
ፖለቲካም ተፈጥሮአዊ ልዩነቶችን አጋነነው፤
የሃይማኖት ልዩነትም ሰውን ከሰው አራራቀው።
ስለ እውነት የሚፈርድ እውነተኛ ዳኛ በጠፋበት በምድራችን፥
እራሳችንን ለይተን ባለማወቃችን፤
ጥሩነት እያለ ከውስጣችን፥
ክፋትን ከሩቅ በመጋበዛችን፥
እርስ በርስ መተላለቅ ሆነ እጣ ክፍላችን፤
በማወቃችን ተጎዳን።



የእንስሳት አግራሞት

## <u>**የእንስሳት አግራሞት**</u>

ይገርማል! እንስሳትም ሰውን በአግራሞት ያያሉ፥

“ምንድነው እንዲህ አይነት ፍጥረት? እያሉ፤

እንስሳትም በአግራሞት የሚመለከቱን፥

እኛም እነሱን መስለናቸው ይሆን?

ይህቺ ምድር! እርሷ ምግብን ስለሰጠችን፥
በልዩ ልዩ ምድራዊ ባህሬዎች መልሳ ፈጠረችን?
እጅጉን በተራራቁ - በልዩ ልዩ ጠባዮቻችን፥
እንደ ተኩላ፥ እንደ ቀበሮ፥
እንደ ጅብ እንደ አንበሳ፥ እንደ ውሻ፥ እንደ ድመት፥
እንደ አህያ፥ እንደ ግመል፥ እንደ በቅሎ እንደ ፈረስ፥
ውስጠ ጠባዮቻችን
በየአይነቱ የእንስሳ አይነት።

አጥቂና ተጠቂ - ክፉና ደግ በመካከላችን፥
በጉራማይሌ ጠባዮቻችን፥
እርስ በርሳችንም የምንበላላ - እንስሳትን መሰልን?
አዎ! ግን ሁላችንም ሳይሆን፥
አንዳንዶቻችን አውሬዎችም ነን።

አንዱን - ምድራዊ ጠባያችንን አፍነን፥
ሁለተኛውን - ብናጎላ መንፈሳዊነታችንን፥
ደጋጎችም ብንሆን፥
እኛም ቅዱሳን፥ እንደ ሰማያዊ መላእክት እንሆናለን?
ብቻ እንዳው፡-
የተፈጥሮ ምስጢር የማይታወቅ፥
የሚገባን ከማይገባን ትንንቅ።

የሰው ከቁመናው እና ከመልኩ መለያየት በላይ፥ የውስጣዊ ጠባዩ ማንነት ነው እጅጉን የሚልቀው፤ ለዚህም ይሆናል፥ እንደ እንስሳ እንደ አውሬም አይነት የሆነው። ምናልባት፥ ለዚህም ይሆናል ንጉሥ ዳዊት ሰውም እንስሳትን መሰላቸው ያለው።[3]

---

[3] "ሰው ግን ክቡር ሆኖ አላወቀም፤ ልብ እንደሌላቸው እንደ እንስሶችም ሆነ፤ **መሰላቸውም።**" መዝ. 40:20



ከርታታው

## <u>**ከራታታው**</u>

እስቲ የሆነውስ ሆነና፥

አንተ ግመል እስቲ ልጠይቅህ፡-

ለመሆኑ አንተ ከየት ነው የመጣህ?

የት ነው ሀገርህ?

አንተ'ኮ እጅግ የተለየህ ነህ፤

ረጅሙ አንገትህ እንዲሁም እግሮችህ፥

ትልቁ ሻኛ ከጀርባህ፥

ጥቂት በልተህ፤ ብዙ ታኝካለህ፤

ከለስላሳ ቅጠል ይልቅ፥ እሾካማውን ትመርጣለህ፤

ጎንበስ አትል ታንጋጥጣለህ፤

ስትሄድ የምትንቀረፈፍ ትመስላለህ፤

በረጃጅሞቹ እርምጃዎችህ
ሳይደክምህ ብዙ ትሄዳለህ፤
አንተ ትእግስተኛ፥ ሩቅ አስተዋይ፥
ወደ ፊት እንጂ ኋላ ‘ማታይ፥
ስንቶች አሉ የአንተ አምሳያ፥
ባለ ሁለት ሻኛ በመካከለኛው እስያ፥
አንተኑ የመሳሰሉ ዝርያዎችህ
(እነ ላማ እና አልካፓ llamas and alpacas) በደቡብ አሜሪካ፥
ባለ አንድ ሻኛ ግመል፥ በመካከለኛው ምስራቅ እና አፍሪቃ፥
የአርብቶ አደሮች መገልገያ፥
የበረሃ መርከብ - ማጓጓዢያ፥ መነገጂያ፥
ጥቅሙ የጎላ በመላው ኢትዮጵያ፤
የአፋር እና የኢሳዎች መከበሪያ።
የአየር ሙቀት ቅዝቃዜም የማይመክትህ፥
ውሃ የጠጣህበትን ሥፍራ፥
የሄድክባቸውን ጎዳናዎች ሁሉ የማትረሳ፥
አመለ ሸጋ፥ ታማኝ፥ ታዛዥ፥ እሺ እንጂ እምቢን ‘ማታውቅ፥
ቁጭ በል ሲሉህ ቁጭ ትላለህ፥
ተነስ ሲሉህ ትነሳለህ፥
እድሜ ልክህን ሰውን እያስደሰትክ በግልጋሎትህ፥
አንተ ለሰው ሠርተህ ደክመህ ትሞታለህ።
አይ አንቺ ምድር፡- ሰውን የሁሉም ገዢ አድርገሽ፥
ልዩ ልዩ ፍጥረታትን፣
በዱና ተበዱን በጉያሽ ታቅፈሽ፥
በተፈጥሮአዊ ግዴታ
ተቻችሎ መኖርን ታስተምሪያለሽ።
ግመልም የሰውን ልጅ የቀረበው
እንደ ሌሎች የቤት እንስሳዎች ተገዶ ነው።

ሲንቀረፈፍ፥ ሮጦ ማምለጥ አይችል፥
ሥጋ በሊታ አውሬዎች እንዳይመገቡት፥
ወፎች ዝንጀሮዎች እንዳይሰፍሩበት፥
ሳይወድም በግድ ከነጻነት ባርነት፥
ምን ያድርግ? ከሰው መጠጋት ግዴታ ሲሆንበት።
ሰውስ እንዴት ነው፥ አንዱ ለሌላው ባሪያ ሆኖ የተገዛው?
ሰው በቁመናው በቀለሙ እንዲሁም በሥጋው፥
ሰው ያው ሰው ነው የሚባለው፤
ግን በሰዎች መካከል ልዩነቱን ስንመዝነው፥
ሰው በውስጡ ያለና የሚኖር መንፈስ አለው፥
አንዱን ከሌላው ልዩ የሚያደርገው።
አንዱን እንደ ሥጋ በሊታ ገዳይ፥
ሌላውንም እንደ እንስሳ ጌታውን አገልጋይ።
ግን በመሃል፥ "እምቢ አልገዛም!" የሚል፥
ቀን እስኪወጣለትና እራሱን እስኪችል፥
ዙሪያውን በክፉዎች ተከቧልና፤
አይቀርለትም ምድራዊ ፈተና።
እንዴ! እኛምኮ አንዳንዴ፥
ግለሰብን "አፈንጋጭ.." እያልን የምንጠራው፥
የስብእናውን ሚዛን ሳንለካ ነው።
በግድ ሰውን ሁሉ እንደሰው ነው የምንቆጥረው፤
የሰውን ውጪውን እንጂ ውስጡን የሚያውቅ ማነው?
ችግረኛን አይቶ ከልቡ የሚያዝነውን፥
ችግረኛን አይቶ የአዞ እንባ ከሚያነባው፥
እንዴት ነው የምንለየው?
አንድ ከርታታ ሁሉን ተቀብሎ - ራሱን ችሎ ለሚኖር፥
"እንዲህ አድርግ፥ እንዲህ አታድርግ.." አይባል ነገር።
የራሱን ትቶ እንደ ሌላው መሆን ለማይፈልግ፥

በሕይወቱ ጣልቃ መግባት አያስፈልግ።

በሰው ልጆች ታሪክም እንዳስተዋልነው፥

ጊዜ የጣለውን ጊዜ ነው የሚያነሳው።

እድል ፈንታ ወዳልታሰበ ያዘማል፥

ግን አንድ ቀን - ቀን ይወጣል፤

አንድ ትውልድ ይወድቃል - ቀጣዩ ትውልድ ይነሳል።

ውሸት ይጥላል - እውነት ያነሳል።

ለግለሰብ፥ ለሕብረተሰብ፥ ለሀገርም፥

በየተራው - ለሁሉም።

በቀርብ ወይንም በሩቅ ጊዜ፥

ሰው ሁሉ ወደማያውቀውና ወደማይገባው ዘንበል ይላል።

ማንም ካለ እምነት እንዳይኖር ግድ ይላል።



ምጡቅ

## **ምጡቅ**

ሰው በመንፈሱ ምጡቅ፥
ራሱን ለቆ'ሚሄድ ሩቅ፤
በሃሳቡ ራሱን ከራሱ ሲነጥቅ፥

ራሱን ከምድራዊነቱ ሲያላቀቅ፥
ነጻነት የሚሰማው ይሆናል ረቂቅ።
　　አንድ በመንፈሱ የመጠቀ ሰው፥
　　የማይችለው ሥራ፥ የማይደርስበት ሥፍራ የለው፤
　　የጊዜና የቦታ ውሱንነትም አይኖረው።
ሰው ካልሞተ፥ ምን የማይታሰብ ነገር ይኖራል?
ሰውና ሃሳቡ - አንዱ ከሌላው እንዴት ይላያያል?
　　በምኞታዊ አስተሳሰብ
　　እንደ ወፍ ቁበቻ[4] 'ሚልበትንም ሥፍራ፥
　　ሲበር ሲከንፍ ምኞትን ፍለጋ፥
　　ወደ ዛፍ ሲጠጋ፤
　　ጣሪያ ላይ፥ ደመና ላይ፥ ጨረቃም ላይ ሲወጣ፥
　　ከሁሉም ዘንድ መገኘትን የሚመኝ ሰው፥
　　ያው ሞትና መቃብር ነው የሚያሳርፈው።

[4] ቁበቻ - መስፈሪያ ወይም ማረፊያ ማለት ነው በኦሮሚኛ።



እንደ እናንተ

## <u>እንደ እናንተ</u>

የሰው ሕይወቱ ውስብስብ፥

የማይሰፋ የማይጠብ፤

በተፈጥሮ ጠባይ ውስብስብ ሕይወት፥

አንዴ ሰማይ አንዴ መሬት።

ሥጋን ጥሎ ሸሽት፥

መሸሸጊያ ጥግ ፍለጋ፥
ጥሻ፥ ዋሻ መኖሪያ፥ መሞቺያ እና መቀበሪያ።
ሰውም በምድራዊ ፍጥረቱ እንስሳትን እንደመስላቸው፥
ከዚያም አልፎ፥ በውስጡ ሲነድ ሲቃጠል ላስተዋለው፥
አይገርምም እንጨቶችንም ቢመስላቸው።
የሰው ልጅ እንደ በግ፥ እንዲሁም እንደ ጅብ፥
እንደ እባብ፥ እንዲሁም እንደ እርግብ፥
ከሁሉም ፍጥረታት ተመሳሳይ ነውና፤
በመሬታዊ ንጥረ ነገሮች በያይነቱ፥
መንፈሳዊ ጠባዩ ብቻ ነው የሰው ልዩነቱ፤
በማይታየው መንፈሳዊነቱ ብቻ ነው ብርታቱ።
እንግዲህ ሰውን ከሰው የሚያርቀው ማነው?
ማነው ሰውን ከማንነቱ የሚያሳድደው?
ከከፍታው የሚያወርደው
ከሰውእነት ማዕረጉ የሚያስወጣው።
አይ! ከዚህም ከዚያም እኛው መሆናችንን፥
ከዚህ ብንጠፋ፥ ከዚያ የምንገኝ፥
ሥጋውያን ብቻ አለመሆናችንን፥
ይህንን እስክናውቅ ብዙ ጊዜ ፈጀብን።
በምድራዊነት በመጋለጣችን፥
ለሥጋ በማደራችን፥
መንፈስ በራቀው ሰውነት እፍረት ተሰማን፤
ከመንፈስ ስንርቅ፥ መንፈስም እኛን ራቀን፤
እራቁታችንን ቀርተን አፈርን።
ግን፥ ለጊዜው ብንደመርም ከዱር አራዊት፥[5]
እናምናለን - እኛ ሰዎች ሰማያውያንም እንደሆንን።

[5] ዘፍ 2፡ 7፤ ሮሜ 8፡ 9፤ 1 ኮሮ 3፡ 3



ፍጥረት ለሕብረት

## ፍጥረት ለሕብረት

ምድራዊነት ክፉና ደጉን ማበጠሪያ፥

ጊዜያዊ መኖሪያ፥

አዳዲሶችን መቀበያ፥


እንግዶችን ማስተናገጂያና ማቆያ፤

ከርታቶችን መሸኚያ።

እረኞች ፍየሎችን ከበጎች እንደሚለያዩአቸው፥
ሰውንም እንደዚያው ይለየዋል የገዛ ፈጣሪው፤
ግን እስከዚያው፥
የሚታየው ከማይታየው
አንድ ላይ ነው፤
በምድራዊነትም ሁሉም እንዳፈጣጠሩ ይኖርበታል፤
ሁሉም እንደሥራው ይዳኝበታል።

ውጫዊ ጠባይ በምድር ሰውን ከሰው የሚያመሳስለው፥
አይደለምና በኋላም ከልዩ አለም አብሮ የሚያስኖረው፤
የከፉ ሰዎች ስብስብ በነፍሳቸው - ልክ እንደ ከፋታቸው፥
የደጋግ ሰዎችም ስብስብ በነፍሳቸው - ልክ እንደ ደግነታቸው፤
ማን ያውቃል፥ ለሁሉም አንዳንድ አለም ቢሰጣቸው - ለሁሉም እንደየሥራቸው፤
በምድር ላይ ያለቀሱ ለብቻቸው፥ ያስለቀሱም ለብቻቸው፥
ለሁሉም እንደ ተፈጥሮአቸው - እንደ ብጤአቸው።

በዚያም ልዩ አለም መዳረሻቸው፤
ማን ያውቃል፥
ለሁሉም ልዩ ሰማያዊ አቅርቦት ቢኖራቸው?



የሃሳብ ልኬቶች

## <u>የሃሳብ ልኬቶች</u>

ለሃሳብ ትርምስ ልኬት ሲበጅለት፥
ከትርምሱ መሃል አቅጣጫ ሲወጣለት፥
ሃሳብ መስመር ሲይዝ፥

አንድ ሁለት፥ እስከ ህልቆ መሳፍርት፤
ግን፥ ሁሉም  ሲጠቃለል፥
ወይ አንድ ብቻ ወይንም ሁለት፤
ምናልባት በመሃል፤
ምድራዊነት እና ሰማያዊነት።
የሃሳብ ልኬት ከሁለት የማይበልጥ ቀመር፤
አንድም ሰማይ ነው አንድም ምድር።
ግን፥ በሁለትነት ለሚኖር፥
በጥልቅ ግንኙነቶችን - መንፈሳዊ ትስስር፥
ደስተኛ ኑሮን የማያስኖር፥
የሰውን ስሜቱን የሚቆጣጠር፥
አንዱን ሰው ለራሱ መልሶ የሚያደርግ ባይተዋር፤
በሃሳቡ ልኬት አልባነት - ድንግርግር።
በግራም በቀኝም ያለው አስደነገጠን፤
ምድራዊ ኑሮአችን አልሰምር አለን፤
ክፉ አድራጊዎች (አጋንንት) በዙሪያችን፥
መሰናክሎችን አጠመዱብን፤
ሃዘንተኞችም አደረጉን።
ወደፊት በመመልከት ብቻ ሰላም አላገኘን፤
ብዙዎች አሳቾች (ጠንቋዮች) እንደ አጥር ከበቡን።[6]
ግን ተስፋችን ያለው ወደፊት ነው፤
እንደየምነታችን - መጥፎ አይሆንም መጪው።

---

[6] "ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማያምኑ ብዙዎች አሳቾች ወደ አለም መጥተዋልና፤ ይህም አሳቹ ሐሳዊ መሲህ ነው።" 2 ዮሐ. 1፡7




አትጨነቁ

## <u>አትጨነቁ</u>

ሆዴን ባር ባር አለኝ፤

የማውቀው አስጠላኝ - የማላውቀውም ናፈቀኝ።

እያወቀው ውስጤ፥ እያየሁት ባይኔ፥

ግማሽ ተከፍዬ በራሴው ቅራኔ፥

ጎኔን አደቀቀው ጎኔ።

ውስጣዊ ስሜት አስጨነቀኝ፥

ዝብርቅርቅ ያለ ነገር ነው የሚሰማኝ፤

የወደፊቱ ከፊት ለፊቴ ድቅን ብሎ ታየኝ፤

የእኔው እኔ - ጭንቀቴ ሲያጫውተኝ፥

ልክ እንደ እኔው ከጎኔ ሌላ ሰው ያለ መሰለኝ።

ባንድ በኩል ምድራዊነቴ ሲስበኝ፥
ኑሮ ሲከብደኝ፥ ተስፋ ሲያሳጣኝ፥
ሃዘን፥ መከራና ምሬት ሲያመጣብኝ፥
በሌላም በኩል ሰማያዊነቴ ከፍ ከፍ ሲያደርገኝ፥
ብሩህ ተስፋ፥ ደስታ፥ ፍቅር እና ሰላም ሲመግበኝ፥
“ምንድነው ይህስ የራሴው ምቀኛ?
ጎኔና ጎኔ፥ አንዱ ላንዱ የማይተኛ..” እንድል አደረገኝ።


የተቸገረ፥ መሄጂያ ያጣ ሰው፥
የገዛ አይምሮው ነው፥ መሰደጃያው።
እና፥ ምንም፥  ምንም የለም፥ የሰው ልጅ የማያስበው፥
ምድራዊ ችግር ካቅሙ በላይ ሲጫነው፤
ንዴቱም፥ ብስጭቱም ሁሉን የሚያውቅ እየመሰለው፤
ተስፋ ከማያውቀው ውስጥ መኖሩን እየረሳው።

ጭንቀት ራስን ባዶ ያስቀራል - የባጥ የቆጡን ያስቀባጥራል፤
በሃሳብ ብዙ ቦታ ይወስዳል - የሌለ ፍርኃት ውስጥ ይከታል - ያስደነግጣል፤

ይገርማል፤ በዚችው ምድር - ሰዎች ተዝናንተው በሚጨፍሩበት
በሳቅ በጨዋታ በሚደሰቱበት፥
ስቃይ መከራና ጭንቀት  - በአንድ አለም ሁለት አይነት።
በሰው ሁሉ ነው ቅራኔዎች ቤት የሠሩት፥
የመሆን፥ ያልመሆን ትግል ስለሚካሄድ በያለበት፤
ፍጥረትና ቅራኔ - ቅራኔና ፍጥረት፥
በአንድነት ሁለትነት - በሁለትነት አንድነት፤
ጥንት እንደነበረ ይህ ቅራኔ፥ አሁንም መቀጠል አለበት።

ግን የሰው ልጅ ቢደረጅ ቢደኸይ፥ ቢወፍር ቢከሳ፥
ክቡር ሰው በውስጡ እንዳለም አይርሳ
ሰላም ነፍጎ ሌላውን፥ ሰላሙን ያገኘ ማንም የለም፤
ሁሉም እንደ ሥራው መከፈሉ አይቀርም።

**ስለ ሁሉም ነገር እግዚአብሔር ያውቃል፤**
**ሰው ግን፥ በከንቱ ይጨነቃል።**




ጆሮ ፍጥጥ

## **ጆሮ ፍጥጥ**

ከውስጥ ወደ ውጪ የወጡ እስኪመስሉ፥
ጆሮዎችም እንደ አይኖች ፍጥጥ አሉ፣
ፍጥጫው ለመሃለኛው፥

በሁለት ወገን ለሚጨነቀው፤

ኦ! ደግ ነገር ዛሬ ደረሰን፤

ጆሮዎቻችን የውጪ ጫጫታን አስወገዱልን፤

በሹክሹክታም ብዙ አወሩልን፤

ወደማይታወቅ ልዩ አለም እየመሩን፥

ሰላምን ሰጥተው አረጋጉን።

የሰማነው እንዳየነው አይነት ስላልሆነልን፥

መስማትም ማየትም የከበደው አእምሮአችን፥

የእውቀትና እምነትን ሚዛን እንድንለይ መከረን።

ደወል ሲደወል፣ ቃጭል ሲያቃጭል፥

የአለምን ውካታ የሚመክት፥

ከፉ ከፉውን የሚያስወጣ፥

ወደ ውጪ የሚነዳ - የብቸኛ ድምጽ የዝምታ፥

ወደ ስማይ - ወደ ጠፈርም የሚያመጥቅ፥

ከብቸኝነት የሚያላቅቅ።

ከጆሮ ውስጥ ለስላሳ ድምጽ - የአንጎል ውስጥ ትርኢት፥

“አንተ ሰው ነህና አትረፍ!” እያለ ዘወትር የሚወተውት፤

በሃኪሞችም ያልታወቀ የድምጽ ትርኢት፤[7]

ይህ ድምጽ አይደለም አዋኪ፥

ታማኝ ጓደኛ ነው እንጂ፥ ትጉ ዘበኛ፥

ራስን በራስ የሚያጠቃልል - የዘወትር መጽናኛ፥

የውጪውን ውካታ የሚመክት፥

እርጭ ምጭጭ የሚያደርግ ምሥጢረኛ።

የውስጥ ድምጽ ሲሆን መንኮራኩር፥

እስከ ጊዜ ሞት የማይለቅ የሃሳብ ባቡር፥

ምንም እንኳን ቢቆጠር እንደ አንድ ልዩ ነገር፥

---

[7] እንደ ጭውታ (tinnitus)

ጠቀሜታም ይኖረዋል የማያጠራጥር።
አላስፈላጊ የውሸት ድምጽሞገዶችን
የከፉ የከረፉ ሃሳቦችን፥
ሁሉንም እንዳመጣጡ፥
በለሰለሰ ድምጽ የሚያመክን።
የውስጥ ድምጽ ከውጪው ድምጽ ይሻላል፤
የሰውን መንፈሳዊ ባህሬ ያጎላል።
የውጪ ድምጽ የአእምሮን ሃሳብ ይነጥቃል፤
ወደ ምድራዊነት ይጎትታል።
የውስጥ ድምጽ ግን፥ የአእምሮን ሃሳብ ይሰበስባል፥
ከምድራዊ ምኞቶችም ያላቅቃል፤
"የምጠቅ አትቀመጥ" ስሜቶችን ይሰርጻል፤
ወደ ላይ ወደ ላይ ያሰኛል፤
ምድርን በሃሳብ አላቆ ወደ ሰማይ ያወጣል።
"እኔ ምናለኝና ከደረቅ መሬት፥
ይሁና! ምናባቱ፥ ብቸኝነቴም ሃብቴ ነው ከጥንቱ..." በሚል፥
የዝምታ አለም ውስጥ ይከታል፤
ሰውም በሃሳብ ሂድት፥
እብስ፥ እልም ብሎ ይሄዳል።
"እውነትም አለም - ጠፈር የኔ - ቤቴ፥
እኔም ለአለም ጠፈር ቤቱ ነኝ.." ያሰኛል።
***ግን'ኮ! የትም ቢኬድ የትም ቢሮጥ፥***
***ቢጩኸ ቢጮኸም ከራስ ላለማምለጥ፥***
***እንዳው ጆሮ ፍጥጥ - ጆሮ ፍጥጥ።***
አዎ! የሰው ልጅ ምን ጊዜም ጥሩ ጥሩውን ይመኛል፤
ማወቅ የማይችለውን ሁሉ የሚያውቅ ይመስለዋል፤
ውስጣዊ ሰላሙን ሲፈልግ ዝምታን ይመርጣል።
ከምድራዊነት ሲርቅ ሰላሙን ያገኛል።

አዎ! ምንጊዜም የሆኑትን ሆኖ መኖር ከጭንቀት ያወጣል፤
አቅም ሲጎል፥ እርዳታም ሲያስፈልግ፥
እምቅ ኃይል ከውስጥ ይቀሰቀሳል፤
በራስ መተማመን፥ ጾምና ጸሎትም መንፈስን ያበረታል።

ምንጊዜም ከራስ ውጪ ሌላ ሰባኪ - ሌላ አስተማሪ አይገኝም፤
ለህመም መድኃኒቱ ከውጪ ብቻ አይመጣም።

አዎ! ሕይወት ያለው፥ ለሕይወቱ ድምጽ አለው፤
ሕይወት የሌለውም ለመኖሩ ምክንያት የሚሆነው፥
እራሱን ሲያሳውቀው፥ ለሁሉም የራሱ መንገድ አለው።
የሁሉም  ድምፅ በጥልቀቱ - ከትንሹ እስከ ከፍታው፣
የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ ነው።
ዝምታም'ኮ አንጻራዊ ነው፤
መርገብገብ የፍጥረት ሁሉ ባህሬ ነው፤
ድንጋይም በራሱ እንቅስቃሴ - የራሱ ጩኸትና ዝማሬ አለው።
ለድንጋዩ የህልውናው ማረጋገጫ፥
የርሱ የሆኑ ንጥረ ነገሮች የርሱ ሕይወቱ ናቸው።

ለሰውም በአካል የመገኘቱን ምስጢር የሚገልጥለት፥
ጊዜና ቦታ የማይወስነው፥ እጅግ ኃያል መንፈስ አለው።
በእያንዳንዱ መኖር ውስጥ ልዩ ልዩ መልክ ይታያል፤
መልክንም የሚያንጸባርቅ መንፈስ ከውስጡ ይኖራል፤
ተራራን የሚነቅል ነፋስና ዝናብ፥
የባሕሩም ማእበል ከጠፈር አካላት ጋር ይመሳጠራል፥
በጋራ ዝማሬ ሁሉም አምላኩን ከእኛም ጋር ሆኖ ያመሰግናል።

እንግዲህ በሰው ከንፈር ብቻ ካልቴዘመ (ካልተዘመረ) አይባል፤
ትቢያውም፥ ነፋሱም፥ ውሃውም ይዘምራል።
“ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ ነው የሠራዊት ጌታ፤
መሬቱ ሁሉ በክብሩ ተሞልቶአል!”
እያሉ፥ ፍጥረቱ ሁሉ ያዜሙለታል።




የውዴታ ግዴታ

## <u>የውዴታ ግዴታ</u>

*ያንተ የውዴታ ግዴታ ይሆናልና ላንተና ለህብረተሰብህ፥*

*ማድረግ ያለብህን ሁሉ አድርግ፥*

*ሕሊናህ እንዲያርፍ፥ ደስም እንዲልህ።*

*እግዚአብሔር ሰውን እንደ መልኩ ቀረጸው፥*

*ደስ ብሎትም እንዲኖር፥ በኤደን ገነት አኖረው።*

ሰውም ከጥንት ማንነቱ ተነስቶ ነው፥
እራሱን በራሱ እንደፍላጎቱ፥
የዛሬ ማንነቱን የገነባው።
ሰው ኃጢአት ሠርቶ፥ ከገነት ቢባረርም፥
ምድራዊ ሰማያዊም መሆኑ አልቀረም።
ግን እስኪሞት ድረስ፥ በሁለትነት ጠባዩ ይጨነቃል፤
በምድራዊነቱ ይንገላታል፤
በመንፈሳዊነቱም ይጽናናል።
አንድ ግለሰብ ገለል ፈንጠር ቢል ከሕብረተሰቡ፥
ከስምምነቱ ይልቅ፥ እጅግ ገዝፎ ቢታይ ልዩነቱ፥
ግን'ኮ በአለመመሳሰልም ነው እድገቱ።
ስለዚህ፥ ሰው ሆይ! ሰላምህን ለማግኘት ብለህ፥
ፈቀቅ አትበል ከመንገድህ፤
የአንተን አላማ ከሕብረተሰቡ ማስታረቅ ቢያስቸግርህ፥
አሁንም አስብ፣ ለአንድ አፍታ ቆም ብለህ።
ልዩነቶች ሁሉ ከያለበት ቢከስሙ፥
እንቅስቃሴዎች ሁሉ ይደከማሉ፤
ህብረተሰቡም ሁሉም ዝም ይላሉ።
አሳዳጊ፥ አነቃቂ ንፅፅሮችም ይጠፋሉ፤
ልዩነት ሁሉ ከተወገደ፥ ሕብረተሰቡ ሕይወቱን ያጣል፤
ሁሉም ፈዛዛ፥ በድን ይሆናል።
ስለዚህ፥ ሰው ሆይ ስትኖር አንተ አንተን ሆነህ፥
እውነት እና ፈጣሪ ይሁን ማመሳከሪያህ፤
ማድረግ የሚገባህን ሁሉ አድርግ፥
ሕሊናህ እንዲያርፍ፥ ደስም እንዲልህ፤
መጻፍ ካለብህ ጻፍ፤ መናገርም ካለብህ ተናገር፤
እምነትህና ጸሎትህ ይሁንህ፥
ማንነትክን ማጠናከሪያ መሳሪያህ።




**የኔ እውነት**

## <u>የኔ እውነት</u>

እስከ ዛሬ ሳላደርግ የቆየሁት ይቆጨኛል፤

እውነትን በግልጽ አለማየቴ ያሳዝነኛል።

የገዛ ኑሮዬን ለማደላደል ወዲያ ወዲህ ስል፥

በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፥ እውነትን ማጣመሜ ያሳፍረኛል፤

እስከ ዛሬ በውሸት አለም ውስጥ መኖሬንም አለማወቄ ይገርመኛል።

አሁን ፊቴን በፊቴ ሳየው፥ ያሳለፍኩትንም ኑሮዬን ስገመግም፥
ምንጊዜም እንደራበኝ ቆየሁ እንጂ፥ ምንም ምንም አልረካሁም፥
በስግብግብ ኑሮዬ ጻጸት እንጂ፥ ምንም ምንም አላተረፍኩም።
ምድራዊ ኑሮ - ትንሽ ትንሽ እየዋሹ - ደረቅ እውነታዎችን እየረጋገጡ፥
ከአድር ባዮች ጋር ሊስማሙ - እየቀላመዱ - እያለሳለሱ፥
ነገር እያጣፈጡ፥ ለራስ ሲጎርሱ አያሳንሱ።
በአንዲት ምድር ብዙ አለም፡-
የክርስቲያኖች፥ የእስላሞች አለም፥
የሂንዱ፥ የቡድሃ እንዲሁም የሌሎች አለም፤
በውስጣቸውም ክፍፍሉ የሚገርም፤
በእውነት የሰይጣን መንፈስ ባይኖር፥
የሰው ልጅ እንዲህ ሳይከፋፈል፥
በህብረት ተከባብሮ በሰላም መኖር ያቅተው ነበር?
ተፈጥሮአዊ ልዩነቶች ቢፈጠሩም በአንዲት መሬት፥
ዳገት ቁልቁለት፥ ከፍና ዝቅ፥
ሙቀትና ቅዝቃዜ፥ ለምና ደረቅ፥
በእነኚህ የአየር እና የመሬት ወጣገብነት በበዛበት፥
የሰው አይነት ብዛቱ እንደ ውጫዊ መልኩ ልዩነቱ፤
እጅግ የገነነውም የማይታየው ውስጣዊ ማንነቱ፤
በእውነት የሰይጣን መንፈስ ባይኖር፥
የሰው ልጅ እንዲህ በጠባይ ሳይከፋፈል፥
የገዛ ሰላሙን ጠብቆ መኖር ያቅተው ነበር?
ምድሪቱስ ሰውና ሰው አብሮ መኖር እንዳይችል፥
በእነ አዛዜልና በእነ ስማዝያ መንፈስ፥
በውሸት እና በተንኮል፥ በምቀኝነት እና በጥላቻ ስትበከል፥
የአንድ አካባቢ ሕዝብ እንዳይረጋ ባለበት፥
ሥልጣን፥ ምኞት፥ ፍላጎትና ስግብግብነትን በማብዛት፥
አንዱ በሌላው ላይ እንዲዘምትበት፥

በጦርነት እርስ በርስ እንዲተላለቅ፥
ለመኖርም ደም ማፍሰስን ግዴታ እንዲሆንበት፥
ቆስቋሽ ነገረኛ፥ በእውነት የሰይጣን መንፈስ ባይኖር፤[8]
የሰው ልጅ እንዲህ ሳይከፋፈል፥
በህብረት ተከባብሮ በሰላም መኖር ያቅተው ነበር?
ሚካኤልና ገብርኤል፥ ሱሪያልና ዑራኤል
ከሰማይ ሆነው ያዩትን የጥፋት መላእክት ሥራ፤
እኛም ደገምነው፥ ደጋገምነው ማንንም ሳንፈራ።
አሁንስ ተምረናል ስለ ክርስቶስ እውነት፥
ስለ ቃል ሥጋ መሆን፥ ስለ ቃል ቀዳማዊነት፤
ታዲያ እውነትን መከተል ካስፈለገም መስዋዕትነት፥
በሐዋርያት መንፈስ እንደነ ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፥
መኖር ይቻላል በአንድ ወጥ ሕይወት፤
አንድ እምነት፥ አንድ ሃይማኖት አንድ እውነት።
እኔስ ለመኖር ብዬ - አለማወቅን ተገን አድርጌ
"ጨረቃ ዳቦ ጣዬልኝ.." እንደሚል ደጅ ጠናሁ፤
ለሥጋዬ ብዬ  ምድሪቱን ተለማመጥሁ፥
ከዚህ ከብልጭልጭ ኑሮ ምን አገኘሁ - ምን አተረፍሁ?
በምን በምን ተጠቅሜ - በምን በምን ተደሰትሁ?
አይ! እኔስ በከንቱ እራሴን አታለልሁ።
ልክ እንደ ጎራዴ፥ እንደ ጠብ መንጃም መመከቻ፥
ውሸቶቼን ከጎኔ ሻጥ አደረግሁ፤
በትክክል ማውራት እስኪሳነኝ ለውሸት ገብርሁ፤
ሳትኩ፥ ተሳሳትኩ  - ትኩረቴን ከእውነት አራቅሁ፤
የተሰጠኝን መንፈሳዊ ጸጋ ከራሴ ላይ አወለቅሁ፤

---

[8] "ሌባ ግን ሊሰርቅና ሊያረድ ሊያጠፋም ካልሆነ በቀር አይመጣም፤ እኔ ግን የዘለአለም ሕይወትን እንዲያገኙ፥ እጅግም እንዲበዛላቸው መጣሁ።" ዮሐ. 10፡10


በምድር ተደላድሎ ለመኖር ስል፥ እውነትና ውሸትን ግራ ቀኝ እያሰለፍሁ፤
ተቃራኒ የሆኑትን እኔ እና እኔን፥ ታግዬ ታግዬ አስማማሁ፥
ሁለቱንም እኔ፥ መኖርን ለመኖር ብቻ እንዲሆን አደረግሁ።
እና ታዲያ! ከዚህ ከብልጭልጭ ኑሮ ምን አገኘሁ - ምን አተረፍሁ?
በምን በምን ተጠቅሜ - በምን በምን ተደሰትሁ?
በምድር ተደላድሎ ኑሮ አስከፈለኝ ዋጋ፤
እኔነቴን ወስዶ ሊቀይረኝ በሌላ፥
ከፉኛ ታግሎኛል ወደ ጥልቅ ገደል እስከጠጋ፤
አሁን ገብቶኛል፤ አሁን እኔን እኔው አግኝቼአለሁ፤
በጸሎት በምስጋና እተጋለሁ።

ተማርንብሽ አንቺ አለም፥ አስተማርሺን ጥሩ አድርገሽ፥
ከፉና ደጉን አየንብሽ አንቺ አለም፥ ከተከለከለው ፍሬ እያበላሽ፤
"ከእንግዲህ አይለምደኝም" እስከንል፥
በደንብ አሳደግሺን እየቀጣሽ።

እኔስ ላንቺ ላልሆንሽ - ፍሬ አልባ ሆንኩብሽ፤
ያንቺ ቅጣት ለኔ ሆኖልኛልና፥
በቂ ምክንያት እንድከዳሽ፣
ቆርጦልኛልና አጥብቄ እንድጠላሽ፥
ከእንግዲህ ለመኖር (ለሆዴ ብዬ) አልለማመጥሽ፣
ከእንግዲህ ብትገድሊኝም አልፈራሽ።

ከእንግዲህ በሚደርስብኝ መከራ ሁሉ እንዳልፈራ፥
በአምላኬ፥ መጠጊያዬና ኃይሌ ታምኜአለሁ፤
ስለዚህም ስለ እውነት ብዬ፥ ለእውነት እኖራለሁ።[9]

[9] "ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አለው፡- "የእውነትና የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" ዮሐ. 14፡6



ሕልም፥ ቅዠት፥ እና እውነታ

## ሕልም፥ ቅዠት እና እውነታ

ሰው በቀን ያሰበውን በሕልሙ ይኖረዋል ይባላል፤

ኑሮ ራሱ ሕልም ሲሆን ምን ይባላል?

ሌሊቱን ሲያቃዠው ያደረ፥

እራቁቱን ሰው እንዳያየው
ሱሪውንም ለመልበስ ሲታገል፥ ሲታገል፥
እጅጉን የጣረ፥ መልበስ አቅቶት የተቸገረ፤
አይገርምም ኑሮ ይህንንም ቢመስል፤
ትግል፥ ትግል - አለማድረግ - ማድረግ ሲቻል።
ለምንድነው? መሆን ሲቻል የማይቻለው?
ማነው ከልካዩ ማነው ከፉው፥
እንዲህ ሰውን አላስኖር ያለው?
ጎን ለጎን ሳይራራቁ አብረው ያደጉ ዛፎች፥
ከመሬት በታች ሥሮቻቸው ንጥረ ነገሮችን እየመረጡ ወደላይ ያቀብላሉ፤
እነርሱም ከመሬት በላይ በነፋስ ውዝዋዜ ተደስተው ይኖራሉ።
ከላይ ከሰማይ - ከጸሐይ - ከደመናው፥
ከታች ከመሬት - ከአፈርና ውሃው፥
ሁሉም በቅንጅት ጫካውን ሲፈጥረው፥
ሕይወት ከአንድ ቦታ እንዲህ ለዛፎች ሲሰምር፥
ምን ይሆን እኛስ ሰዎች ከዛፎች የምንማር?
ልክ እንደዛፎች ሥሮቻቸውም ቢሆን የእኛ ኑሮ፥
ልብ ለልብ ተሳስቦ፥ ተፈላልጎ አብሮ መኖር ጥሮ ግሮ፥
ምድራዊ እውነታን ተቀብሎ፥ ከላይ ተማጽኖ ከሰማዩም፤[10]
እንዲህ እንዳሁኑ ችግር አይጸናብንም፤
ሕልሞች ቅዠቶችና እውነታዎች አይምታቱብንም።

---

[10] “እግዚአብሔርም ለድሆች መጠጊያ ሆናቸው፤ እርሱም በመከራቸው ጊዜ ረዳታቸው ነው።” መዝ. 9:9



ጀርባና ጀርባ

## <u>ጀርባና ጀርባ</u>

በመንፈስ አንድ ሆነን፥

ግን፥ ሳናውቅ፥ ሳንተዋወቅ፥

መኖርን ኖርን፥ ጀርባ ለጀርባ ተሰጣ ጥተን፤

ተመስገን፤ ይኸው እስካሁን አለን፤

አንድ ቀን እኛ እኛኑ መስለን፥

ከነ ሙሉ ክብራችን ብቅ እንላለን፤

ዳመና ውሃ እንዲሆን፥
እኛም ሰው እንሆናለን፤
ስንወጣ ከነበርንበት፥
ከዱር ከአራዊት የተማርነውን፥
ከእንስሳትና ከእጽዋት የቀሰምነውን፥
መልካሙን ጥበብ ለሰዎች እናካፍላለን።
    የሰው ልጅም እንዲጠጋጋ እንጂ እንዳይራራቅ፥
    ጀርባ ለጀርባ ሆኖ እንዳይኖር - እንደማይተዋወቅ፥
    እሱም ከእሱው ጋር - ሥጋው ከነፍሱ እንዲታረቅ፥
    ውስጡ ሰላም ሲሆን፥ ውጪው እንዳይርቅ፥
    ውጪውም ሰላም ሲሆን ውስጡ እንዳይጨነቅ፥
    በአንድ ሕብረተሰብ፥ በአንድ አገር፥
    በአንድ ባንዲራ - በአንድ ሰንደቅ፥
    ሁሉም ክብሩን ነጻነቱን እንዲያውቅ።
ምክር - ፖለቲካ፥ ትግል - እስከ ሥር ነቀል ጦርነት፥
በከንቱ አይደለም ይሄ - የእውነት እና የውሸት ትንንቅ።
    ሰው ቢያልቅም፥ ሰልፉ ይቀጥላል፤
    እውነት እስኪያሸንፍ፥
    ውሸት ድቅቅ እስኪል።
ዝም ቢልም - ዝም ማለት ለማይችል፥
አንድ ናት አገሬ ለሚል፥
ቀና ብሎ ለሚያስተውል፥
ያውና አርማው - ሰማይ ላይ ይውለበለባል፤
ቀስተ ደመና ነው፤ ሌላም አይደል።
    ቀኑም ቢጨለም - እጅግ ቢበዛ ስቃይ፤
    መጪውን ጊዜ ለሚያስተውል፥
    ተስፋችን ተዘርግቷል ከሰማይ።



**ወደ ላይ**

## <u>ወደ ላይ</u>

ሰው ምንድነው? ጠያቂውስ ማነው?

ሰው ከምድር የተበጀ ሰማይ ቢቱ ነው።

ጌታችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር እንደ አረገ ወደ ሰማይ፥

የሰውም ምልከታ ሆኗል ወደ ላይ! ወደ ላይ።

ተመስገን እንበል፥ ለምድር ሕይወት ኑሮ፥

መቆየት ደግ ነው፥ መቀጣጫም ቢሆን ወይንም አመክሮ፥


ሁሉን አሳይቶ፥ ሁሉን አስመልክቶ፥
ተመስገን እንበል፥ አቆይቶናልና "ረጅም" እድሜ ሰጥቶ፥
ከእንግዲህ ከሥጋ ምን ቀረኝ ይባላል?
አንድ ወፍ በሙብረሯ ድካም ቢሰማት፥
የምታርፍበት ዛፍ ከሩቅ እንደሚታያት፥
ለእኔም የዘለአለም ማረፊያዬ፥
እጅግ ደማቅ ሠፊ ሥፍራ ሆኖ ይታየኛል።
በዚያ መኖር ለኔ ደስ ያሰኘኛል።
በማይጠፋው አለም እኖራለሁ፤
በዚህ በድንቅ ሃሳቤ ታምኛለሁ።
እና፥ ነፍሴ ብረሪ፥ ውጪ ወደ ላይ፥
ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ አትይ።
ምድራዊ ፈተናዎችን አልፈሻቸዋልና ደስ ይበልሽ፤
በከዋከብት በሚያደንቁሽ መካከል ተምነሽነሺ፤
የተውሻቸው ጊዜና ቦታ አይጎትቱሽ፤
ብርሃናት መመላለሺያ ሰረገላዎች ይሁኑሽ፤
ክፉና ደጉን መመዘኛ ምልከታዎችሽ፥
ስነ አመክኖአዊ አስተሳሰብሽ፥
እውቀትሽ እምነትሽም ሰማያዊ ይሁኑልሽ።
ሰው በውስጥ ስሜት ሕይወቱን ይመራል፤
በሃሳቦቹም ብዛት ይንገላታል፤
አንዳንዴም ሳያስበው እርሱ ራሱ በሃሳቡ፥
እንደ ጠፈር ሠፊ ይሆናል፤
ወደ ላይ ወደ ላይ ያሰኘዋል።
በሃሳቡ ብርቱ ነውና እምነቱ፥
አኗኗሩም ተጋምዷልና ከሃማኖቱ፥
በሚያስጨንቅ ሁኔታዎች ውስጥ ቢያልፍም፥
ቢቸግረው፥ ቢሰቃይ በረሃብ በጥማቱም፥

ቀጣዩን ሕይወት ስለሚያስብ፥ በነፍሱ አይረበሽም፤
ሰማያዊ ሃሴት ነውና ተስፋው፥
“ወደ ላይ.. ወደ ላይ..” የሚያሰኝ፥ የውስጥ ስሜቱ አልተሳሳተም።
ስንሞት ወዴት እንደምትሄድ ነፍሳችን፥
ማወቅ ባይቻለንም በምድራዊ እውቀታችን፥
ምንጊዜም ሂደት ከጠባቡ ወደ ሰፊው ስለሚሆን፥
አዎ! ከታች ወደ ላይ ነውና እድገታችን፥
የሙታን ትንሳኤ ነው እምነታችን።
የተቸገሩ የተጨነቁ ይጸልያሉ ይለምናሉ፤
በዛውም መጠን መልስ ያገኛሉ፤
ምድራዊ ሰው ተለምኖ ከሚሰጠው ብዙ፥
ሳይታክቱ የሚጸልዩ፥ ጻድቃን ሰማዕታትንም የሚማጸኑ፥
ቅዱሳኑንም የሚጠሩ፥ ከሰማይ ቤት የበለጠውን ያገኛሉ።
እውነት ነው - የተጨነቀን ሰው አንድ ደግ የምድር ሰው ከረዳው፥
አንድ ደግ የሰማይ ሰው ለምን አይረዳው?
በእምነት እና በመንፈስ ከቀረብናቸው፥
የሚራዱን ብዙዎች ናቸው።[11]
የሚታይ የማይታየውም፥ ሁሉም ሲሳሳብ፥
እውነታ፥ እውቀትና እምነት፥
በመንፈስ መነካካት - ከሰማይ እስከ መሬት፤
“ወደ ላይ.. ወደ ላይ..” የሚያሰኝ የውስጥ ስሜት፥
ከሰው ልጅ አይጠፋም - በእውን፥ በሕልም ወይንም በቅዠት።

[11] “ሰው አለሙን ሁሉ ቢገዛ፥ ነፍሱንም ካጣ ምን ይረባዋል?” ሉቃ. 9፡25

# ምዕራፍ ሁለት

# ቅራኔዎች በሁሉም ሥፍራ



ሕይወትና ቅራኔዎች

## *መግቢያ*

በቅራኔዎች ውስጥ የሚያድግ በቅራኔዎች ውስጥ ይሞታል። በምትኩም ሌላ ፍጥረት ይተካል። ይህ ክስተት ነፍስ ባላቸውም በሌላቸውም ያለ ስለሆነ፤ በዚህ የቅራኔ ሰንሰለት ውስጥ ሳይወለድና ሳያድግ፥ ሳይሞትና ሳይለወጥ ለዘለአለም የሚኖር አንዳች ቁስ አካል የለም።

*[ጥቂት የቃላት ትርጉሞችን እና ተጨማሪ መግለጫዎችን ከዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ይመለከቷል።]*

## ቅራኔዎች በሁሉም *ሥፍራ*

የሁለት ተቃራኒ ውስጠ ጠባዮች እድገት እና ተዛማጅነት የተፈጥሮአዊ እድገት መነሾ፥ መለወጥና መሻሻል መሆኑን ዲያሌክቲካል ቁስ አካላዊነት በሚል ፍልስፍና ካርል ማርክስ እና ፍሪድሪክ ኤንግልስ በሰፊው ያብራሩታል። እነሱ "ግዑዙ ዓለም ብቸኛው እውነታ ስለሆነ፤ ሁሉም ነገር በቁስ አካልና በውስጡ በሚገኝ ቅራኔ እየተንቀሳቀሰ ወደፊት ይሄዳል (ይከናወናል፥ ይለወጣል)" በማለት፤ የሕብረተሰብንም እድገት በዚያው መልክ ይመለከቱታል። "ከአንድ ዝቅተኛ መንግሥታዊ የአስተዳደር ዘይቤ ወደ ከፍተኛ መንግሥታዊ የአስተዳደር ዘይቤ ለመሸጋገር በዚያ ሕብረተሰብ ውስጥ የሚካሄድ እንቅስቃሴ (ቁሳዊ፥ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ) ወሳኝ ነው" ይላሉ። ከዚህም በመነሳት፥ የሰዎችን ምድራዊ ታሪካዊ ሂደቶችን እጅግ ቅልል ባለ መልኩ አስቀምጠውታል።[12]

እነ ካርል ማርክስ የሰው ልጅ በውስጡ መንፈስ እንዳለው ኃጢአትም እየሠራ ሲጓዝ፥ ለታሪካዊ እድገቱ መነሺያ የሚሆን ተፈጥሮአዊ ማንነቱና እምነቱ ወሳኝ መሆኑን በፍልስፍናቸው ውስጥ አላካተቱትም። እነርሱ የሚሉትን የቅራኔዎች መኖር (ከአካል እስከ ሕብረተሰብ) በጥቅሉ የምንቀበለው ቢሆንም፥ በእነርሱ እሳቤ ውስጥ ያልተካተተው የሰው መንፈሳዊ ተፈጥሮው፥ ለምድራዊ ሕይወቱም ወሳኝ መሆኑን በጥልቀት መመልከት ያስፈልጋል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምድራዊ (አለማዊ) ተቃርኖ እንደሚተርክ፥ ስለ መንፈሳዊ ተቃርኖም፥ ከመላእክት መካከል አንዱ ስለነበረው ስለ ሳጥናኤል "እንደ ልዑል እሆናለሁ" በማለት የእግዚአብሔርን ዙፋን ለመንጠቅ ፈለገ በማለት ይተርካል

---

[12] Primitive Communal Society, Slave Society Feudalism, Capitalism (Imperialism), Socialism Communism

(ኢሳይያስ 14፡14)። ይህ ታላቅ ኃይል፥ መሬት ወድቆ፥ ከጥንትም አዳምና ሔዋንን ያሳተ፥ በነፍስና ሥጋችን መካከል ቅራኔዎችን እያባባሰ ቆይቷልና፤ በጴጥሮስ አንደበትም ውስጥ ገብቶ፡-

*“አቤቱ ይህ አይሁንብህ፥ ከቶም አይድረስብህ”* አለው፤ ጌታችን ኢየሱስም፡-

*“አንተ ሰይጣን ከኋላዬ ሂድ አለው፤ እንቅፋት ሆነህብኛል፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና”* አለው። ማቴ..16፡ 22-23

[ኢየሱስ ይህንን የተናገረው ለጴጥሮስ ይመስላል። ግን፥ ጴጥሮስን ላናገረው ለሰይጣኑ መልስ መስጠቱ እንደሆነ ያስታውቃል]።

እኛም በአንድ በኩል የሰይጣንን ምድራዊ እውቀት፥ በሌላም በኩል የፈጣሪአችንን መንፈሳዊ (ሰማያዊ) እውቀት፥ እንዲህ በሁለት አቅጣጫ ከሚመጣ እውቀት እየተመገብን በቅራኔዎች ተወጠርን።

***በምናየው አለም ስንመላለስ፥***

***በማናውቀው አለም ውስጥ ነው የምንኖረው።***

ለምንድነው የሰው ልጅ በቅራኔዎች ውስጥ የሚኖረው?

ለምንድነው ኑሮ ጉራማይሌ የሆነው?

ማነው፥ የዚህችን አለም ጥሩና መጥፎ ጎን መመዘን የሚቻለው?

ህጻን ሲድህ እንደ እንስሳ በአራት እግር፥

አድጎ መቆም ሲጀምር ልዩ ፍጡር፥

ከፍ ብሎም የብቻውን ኑሮ ሲጀምር፥

የግራ እጁ ከቀኝ እጁ የሚከራከር።

የአንዱ ሰው እጆች የሚያፍሱት አመድ ወይንም አፈር፥

የሌላውም ሰው እጆች የሚያፍሱት የወርቅ ጠጠር።

እንዴት አንድ ሰው ኑሮውን ይኑር ተከብሮ በዚች ምድር፥

በሰላማዊ ኑሮ - ሳይቸገር ሌላውንም ሳያስቸግር?

ቅራኔዎች ሳይናገሩ (ሳያናግሩ) መናገርንም ያስችላሉ፤

ድምጽ ሳያሰሙ ያድጋሉ (ያሳድጋሉ)።

ሁላችንም ተፈጥረናልና ለፈለገን አንታጣም፤

መገኛችን ሁሉም ሥፍራ ነው - በዚህ አለም በዚያኛውም።

ግን፥ የሰው ልጅ በሁለት ሃሳቦች እየተንገላታ፥

ኑሮውን ይኖራታል፥ ደስ ሳይለውም፥ በቅሬታ።
አንዳንዴም እየሳተ ማንነቱን፥
ማስታወሱን ይተዋል ፈጣሪውን።

አለማችን በብዙ እውነቶች ተወጥሯል፤
አንዱ እውነት የሌላውን ሥፍራ ለመቀማት ይታገላል።
ባንድ በኩል እስላም በሌላም በኩል ክርስቲያን፥
ሁሉም እንደ እምነቱ ሲወግን፥
ከስምምነት ልዩነት ሲያመዝን፥
ቶርቶራዎች (terrorists) ሲያቀጣጥሉ እሳቱን፥
ክፉ አድራጊዎች ሁሉ ሲያደፍጡ፥ ተደብቀው ከጉያችን፥
የሰው እልቂት ሲሆን ከሁለት ወገን፤
ጤነኛ ሲጠፉ፥ ደስታ ሲተካ በሃዘን።

ሰው ለምን ተጠመደ በክፋው፥
ከጎኑ እያለለት ጥሩው?
ሰላማዊ ኑሮ ሲበላሽ፥ ሲጠፉ ጤንነት፥
ምንድነው ሚናቸው፥ የማይታዩ ኃይላት?
እስቲ ይህንን እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች እንመልከታቸው፤
ምድራዊ፥ ሰማያዊ ሆነን ስለመፈጠራችንም ጉዳይ እናስበው።
የቅራኔዎች መኖር ግዴታዊነቱን (አስፈላጊነቱን)።

ቅራኔዎችም በተቃራኒ ጠባዮቻቸው፥
ክፋትና ደግነትን ይዘው፥
ከየትም ሥፍራ የማይታጡ፥ ጠፈራዊ ናቸው።
ቅራኔዎች ካለማቋረጥ በተቃርኖ ይቆማሉ፥
በእንቅስቃሴዎቻቸው ሁሉ ለዘለአለም ይጣላሉ፥
ይህንን ነው ከአካላዊው አለም በሳይንስ የተማርነው፤
በሃይማኖታችን የተማርነውም'ኮ ይህንኑ ነው የሚመስለው።

ለአንድ ሰው በሁለት አቅጣጫ መካሪ ባይኖረው፥
የሰው እምነቱ፥ ሃይማኖቱ፥ አስተሳሰቡ፥

አንድ አይነት ነበር የሚሆነው።

ግን ለሰው የወዳጁ ጠላት፥ ባላጋራው፥
እውነት እንዲደበቅ ይታገላል በያቅጣጫው።
ሰላም ይሁን ብሎ የሰው ወዳጅ ሲመክር፥
ባላጋራው ይቃወማል - ይተናነቃል፤
የጥሩ ነገር - የይሁን ሃሳብ ሁሉ እንዳይሰምር።

ምድሪቱ እንዳልነበረች ሕይወት መዝሪያ፥
ጊዜው ተለውጦ፥ ስትሆን ሬሳ መልቀሚያ፥
ወደ መኖር የሚመራው ጊዜ ሲያጥር፥
ወደ ሞት የሚመራው ጊዜ ሲረዝም፥
ምድራችንስ "ሊሞትባት እንጂ ሊኖርባት አልተፈጠረቺም" የሚያሰኝ፥
ይህንን ለመሰለ የሰው ምሬት ምን ምላሽ ይገኝ?
ለአጥፊው ቅጣቱን ሰጥቶ የሚዳኝ።

እስቲ እናስበው፥ ከጠፈር ጀምሮ እስከ ሰው፥
ምክንያቱን፥ መሠረቱን፥ የተቃራኒዎችን መኖር፥ ግዴታዊነቱን።

በአይኖቻችን ቢታዩም ባይታዩም፥ ገሃድ ነው ነፍሳማነት፥
በሥፍራዎች ሁሉ፥ ከትንሽነት እስከ ትልቅነት
አሉ በዙሪያችን ነፍሳማዎችም በያይነቱ፥
በባህሩ፥ በአየሩ፥ በመሬቱ፥

ባናያቸውም አሉ፥ ይወጣሉ ይገባሉ፥
አንዴ ሊያጠፉን አንዴ ሊያስተካክሉን፥
አሉ በያይነቱ - መልካቸው ብዙ፥
ከነፋሱ ከዝናቡ ከእሳቱና ከጭሱ የሚዛመዱ።
አዎ! ሁሉ ነገር ከቅራኔ ጋር ተፈጥሯል፤
ለአካልም ጸረ አካል ይኖራል፤
ጥንትም፥ አካል በሕልውናው ሳይከበር፥
የ "ይሁን/አይሁን" ትግል ተካሂዶ ነበር።

በደምሳሳውም ቢሆን፥ እጅግ ጠበብ አድርገን።

ገና ድሮ ድሮ ከዋክብት በጉልህ ሳይወጡ ከተደበቁበት፥
ማንነታቸው ሳይረጋገጥ፥ በብርሃናቸው ድምቀት፥
ጠፈር ጥምልል፥ ጥቅልል፥ የጋስ ጢስ ብቻ በሆነበት፥
ከውስጡ የ“መሆን ሃሳብ” እንዳይጸና፥
እንዳይፈጠሩ አካላት፥
ተካሂዶ ነበር እጅግ ታላቅ ጦርነት፥
በአካላትና በጸረ አካላት (anti-matter) መካከል ታላቅ ግጭት፥
“የይሁን - መሆን” እና “የአይሁን - አለመሆን” ጦርነት።

ግን የ“መሆን” እውነታ “ሲያይል?”፥ የ“አለመሆንን” ሥፍራ ሲወስድበት፥
በጠፈር የአካላት ህልውና ሲከሰት፥
ብቅ ብቅ አሉ ከዋክብት፥
ከመጠፋፋት ባሻገር እንዲኖር መገኘት።
ይህ በሳይንስ ታዋቂ ቢሆን፥ የ“ይሁን” ባዮች አሸናፊነት፥
የ“አይሁን” ባዮች ትግል ከሽፈት፥
ለኛ ግን የእግዚአብሔር የቃሉ መፈጸም - ፈቃዱ የታየበት።

በጊዜ ብዛት፥ ጠፈር ሲገዝፍ በስፋት፥
ዝግጅቱም ሲቀጥል፥ ለመጻኢ ምድሮች ተስማሚነት፥
የጠፈር ቅዝቃዜም ሲሆን ለንጥረ ነገሮች የአይነት ብዛት ምክንያት፥
ማዕድናት ሲከማቹ፥ ለመጻኢው የሰው ልጅ ሥልጣኔና ሃብት፥
ቀስ በቀስ፥ ግዑዛን አካላት ሲዘጋጁ ለምግብነት፥
ምድራችንም ስታፈራ ሕይወት፥
በዚህ መለኮታዊ እቅድ፥ በዚህ ሽግግር ምክንያት፥
ለኛ ለሰዎች፥ “ከሰማያዊ ሕያውነት፥
ወደ ምድራዊ ሰውነት”፥
ሰብእነት - ደቂቀ አዳምነት።[13]

---

[13] በሰማይ የተፈጠሩ ሰማያውያን አዳምና ሔዋን ምድራውያን ሆኑ (ከምድራዊነታችን ባሻገር ሦስተኛ መጽሐፍን ይመለከቷል።

መጨረሻ የለው፥ የጠፈር ምርምር፥
ግሩም ድንቅ ነው የከዋክብት መፈጠር፥
ደስ ያሰኛል፥ የእኛም ከዚያው መደመር።
ግን እንዳው ለመሆኑ! አካል እንዴት በጸረ አካል ላይ በረታ?
እንዴትስ ህልውናው ተረጋገጠ ካለ እርዳታ?
ማንስ አዘጋጀው ለሕይወት ግንባታ?
እኛስ ከየት ተነስተን ነው ከዚህ የደረስን?
ያሰበን ሳይኖር - የፈጠረን።
እንዴት ነው? የአለመሆን እውነታ፥ ለመሆን በር የሚከፍት፥
እንዴት ነው? መትረፍ የሚኖር፥ በግጭት በመጠፋፋት፥
አካላትና ጸረ አካላት ተጋጭተው፥
እነርሱም ተጠፋፍተው፥
በምትካቸው ኃይልን ረጭተው፥
ከዋክብትም ብቅ ብቅ ሲሉ፥ ከመጠፋፋት ተርፈው፥
ሲያበሩ፥ ጠፈርን ሲያሳምሩ፥ እዚያና እዚያ ተበትነው፤
ሰዎችም በአካላዊነት ተባዝተው፥
ምድርን ሞልተው፥ የሚያስፈልጋቸው ሁሉ ተዘጋጅቶላቸው፥
ባለ ሁለት ጠባይም ቢሆኑ በፍጥረታቸው፥
አውቀው፥ አምነው፥ ስለ ፈጣሪያቸውም መስክረው፤
ሁሉንም በያሉበት በአይነ ሕሊና አየናቸው።
ይህስ አይደለም፥ የአንጎል ብቻ - የሃሳብ ክርክር፤
አይደለም የተፈጠረ፥ በኒውሮን (የ ህዋሳት) ኬሚካሎች ቅንብር፥
እስኪ እናስተውለው፥ ቅራኔ ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ መኖሩን፤
ማንኛውም ነገር ከአለመኖር ወደ መኖር ሲሸጋገር፥
በቆይታውም ዘመን ሲኖር፥
ተፈጥሮአዊ እንደሆነ የቅራኔዎች መኖር።
ግን ምን ይደረግ! የተፈጥሮ ንግግሩ ከኛው ጋር ሲሆን፥
መላቀቅ ያስቸገረው የውስጣችን ከዙሪያችን፥

የተፈጥሮ ንኪኪው ከራስ ጠጉራችን እስከ እግር ጥፍራችን፥
ሥጋችን፥ አጥንታችን፥ ነርቫችን፥ ደማችን፤
የተቃራኒዎች ትግል በተቃራኒዎች ጠባይ ይወሰናል፥
በመንትያ እውነቶችም መሃል ቅራኔ ይኖራል።
እውነት ብቻውን ደረቅ ነው፤
በውስጡ አንድ አላማ ከሌለው።
ለበጎ አላማ የተሰለፉ እውነቶች አብረው ያድጋሉ፤
ሰብአዊነት ሰላሙን እንዳያጣ ያድማሉ።
ለጥፋት የተሰለፉ “እውነቶችም” ይደማመራሉ፤
የራሳቸውን አለም ለመመሥረት ይመክራሉ።
መንትያ እውነቶች ሁለቱም  የውሸት ተቃራኒዎች ናቸው፥
በአለማችን አይለዩም፥ በውጪያዊው መልካቸው፥
ይህ ነው አደናጋሪ ጠባያቸው።
በሰማያዊ ጠባያችን፥ ምድራዊው ተደባልቆብን፥
እንዲሁ እንኖራለን፥
በሁለት “እውነቶች” ተወጥረን።
ግን ሁለት እውነት እንዴት? ቢባል፥ መልሱ አንድ ነው፤
ሰውና ሰው በማይተዋወቅበት አለም ነው ያለነው።
አንድ ሰው የራሱን ጥሩነት መግለጥ ቢያቅተው፥
ወይንም ሌላው ባይረዳው፥
ያ ሰው እንደ መጥፎ ነው የሚቆጠረው፤
ጸብና ጭቅጭቅ፥ ግጭትና ጦርነትም
በዚህ አይነትም ነው የሚመጣው።
ስለዚህ አለማችን በብዙ እውነቶች ተጨናንቋል፤
አንዱ እውነት የሌላውን ሥፍራ ለመቀማት ይታገላል።
በውስጠ ጠባይ ተቃራኒ፥
ልክ እንደ አካልና ጸረ አካል፥
አንድ አይነት እውነት እና ሌላ አይነት እውነት ሲጋጭ ይጠፋፋል።

ስለዚህ፡- ሰው ሲኖር ከራሱ ወይም ከሌላው ጋር፥
የመጠፋፋት ውጤቱ ዜሮ ሆኖ እንዳይቀር፥
ከሩቅ ለሩቅም ቢሆን፥ በመተያየት፥
ይሻላል ማባበል፥
“እውነት ነው - ትክክል ነው” ማለት።
　　　ውሸትማ በቀላሉ ይታወቃል፤
　　　በእውነት ይረታል፥ በቀላሉም ይጠፋል።
እንዱን እውነት ከሌላው መንትያ እውነት ማን ይለየዋል?
ውስጠ ጠባዩንስ ማን መርምሮ ይደርስበታል?
　　　እግዚአብሔር ሲፈጥረን እንድናመልከው፥
　　　እኛ ስናፈነግጥ፥ ስንሸሸው፥
　　　እርሱ ሲያስተምረን፥ ሲመልሰን በየጊዜው፥
　　　ይህንን ነው ከታሪክ የተማርነው።
　　　አንድ እውነት ብቅ ሲል፥ ቢከተልም አጥፊው፥
　　　ከሰማይ በመጣ ትምህርት ነው ክፉውን የምንቋቋመው።
　　　ተመስገን፤ ለዚህም ነው እስካሁን ሳንጠፋ የቆየነው።
ውስጥ ውስጡን ሰማያዊነታችን እየታወቀን፥
በምድራዊ የመንትያ እውነታዎች እየተጨናነቅን፥...
ስንጠይቅ፥ ስንጠይቅ፡- “ማነው ከዚህ ውጥረት የሚገላግለን?”
እውነት እምነት እምነትም እውነት መሆኑን ተረዳን።[14]
　　　እንዲህም እያልን ስናስብ፥
　　　የማናስበውም ሲበልጥ ከምናስበው
　　　አንዳንዴም ላለማሰብም እድል ስንሰጠው፥
　　　በሃሳቡ እንደ ውሃ ፍስስ ማለትን የሚሻው፥

---

14 “የእግዚአብሔር ዐይኖች በሁሉ ቦታ ናቸው፤ ክፉዎችንና ደጎችንም ይመለከታሉ።” ምሳ. 15፡3

ለሃሳቡ መንተራሺያ ሥፍራ ፈላጊው፥

ከምድራዊው አለም ይልቅ ሰማያዊው የሚታሰበው፤

እንዲህም እናስባለን፡-

ምን ላይ ተንተርሶ ነው ሰው ያለው?

ሁሉንም "እንዳሻው … እንዳሻው ..

...ሁሉም ያው … ሁሉም ያው..." እያለ፥

በተዳከመ ሃሳቡ የሚዝናናው፥

በስንፍናውም እፎይታ የሚሰማው፥

እርሱ ሲጃጃል - ሲንቀረፈፍ - ጊዜ ከዳው - ሌላው ቀደመው።

ለራሱ ለአካልም ሳይቀር- ለሁሉም'ኮ ተቃራኒ አለው፤

ሳይንቲስቶችም የፖል ዲራክን[15] ግኝት መሠረት አድርገው፥

ጸረ አካል መኖሩን አምነው፥

እና ከዚያም ተነስተው፥

አስበው፥ አስበው፥ ተመራምረው፥ ተመራምረው..

የፒኢቲን[16] መሳሪያ ፈልስፈው፥

በፖዚትሮን፥ ኢሌክትሮን ግጭት፥

የጋማ ጨረሮችን አመንጭተው፥

የካንሰር ህዋሶችን ከተደበቁበት ሲያገኟቸው፥

እያሳደዱም ሲገድሏቸው...፤

---

[15]http://www.nobelprize.org/nobel_prizes/physics/laureates/1933/dirac-bio.html:

*Quantum Theory of the Electron* (1928) and *The Principles of Quantum Mechanics* (1930; 3rd ed. 1947)

[16] http://en.wikipedia.org/wiki/Positron_emission_tomography

ከዚህ የሳይንስ ግኝት የምንረዳው፡-

አንድም የማይተኛ አንጎላችን፥ በውስጡ ቅራኔ እንዳለው፥

እንዲሁም የተቃራኒዎች መኖር አስፈላጊም እንደሆነ ነው።

መነኩሴዎችም ጸረ ሰው መኖሩን አምነው፥

ክርስቶስ የፈጸማቸውን[17] ተከትለው፥

መስቀል መሳሪያቸውን በቀኝ እጃቸው ጨብጠው፥

የማይታዩትን እየገጩና እያቃጠሉ ሲያሳድዷቸው፥

የታመሙትንም ሲያድኑ፥ በጸሎታቸው...።

ከዚህም የተዋህዶ ሃይማኖታችን የምንረዳው፡-

አንድም ምድራዊ ሕይወታችን በውስጡ ቅራኔ እንዳለው፥

ለእርሱም መስቀሉ ፍቱን መድኃኒት እንደሆነ ነው።

---

[17] ማቴ. 8፡28-34፤ ማቴ. 9፡32-33፤ ማቴ. 12፡22፤ ማር.1፡23-26 ሉቃ. 4፡33-36



ቅራኔዎች

## ቅራኔዎች

ቅራኔዎች አንድም ለመኖር አንድም ለመሞት፥
ከድንጋይ እስከ እጽዋት፥
ከታናናሽ ነፍሳት እስከ ታላላቅ እንስሳት፥
ማን አለ ለርሱ ከተሰጠው ውጪ፥
ለራሱ ሕይወት ተመን የሚያበጅለት?
ሞት እና ሕይውት እንጂ እኮ ነው የቅራኔዎች ጥምረት፥
እንደ ኢሌክትሮንና ፕሮቶን ቀዥቀዥ ማለት፥
እንደ ኒውትሮንም ረጋ ማለት፤
እንደ እሳትና እንደ ነፋስ ወደ ሽቅብ መውጣት፥
እንደ ውሃም ታች ታቹን መቃኘት፥
ጎንበስ ቀና፥ በግራና ቀኝ አዞሪት፥

በመብላት እና በመንቀሳቀስ (በመሥራት) ማርጀት፥
ሥጋዊ ሕያዋን ሁሉ ባሉበት፥
መሞት፥ መበስበስ፥ መለወጥ፥
ይህ የማይነጣጠል የዘለአለም ቅራኔ፥
ከጠፈር እስከ መሬት።

በዚህ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ውስጥ ያለ ሰው፥
በአካላዊነቱ (በሥጋዊነቱ) የሚታየው፥
አንዴ ብቻ አይደለም የሚሞተው፥
በየቅጽበተ ሰኮንዱ እየሞተም ነው ያለው።
ሞት ከውጪ አይመጣም፥
መኖር ከመሞት አይለይም፤
በአንድ በኩል እንዲሁም በሌላም፥
ሕይወት ዑደት ነው የማያቋርጥ ለዘላለም፤
በዚህች ምድርስ፥ አንድ ወጥነት የለምና፤
እየኖርን እንሞታለን፤ እየሞትንም እንኖራለን።

በየቀኑ አርጅተው፥ በማይቀር ሞትን ሞተው፥
ፍጡራንን ሁሉ ይመሳሰላሉ - በተቃርኖ ጠባዮቻቸው።

## <u>ሞት በጦርነት - የተቃርኖ ውጤት</u>

ጦርነት የእውነትና የውሸት ግጭት፤
የክፋት ጥግ፥ ሰውና ሰውን የሚያጨራርስ፥
የሁከት ፋብሪካ መጥፎነትን የሚጠነስስ፥
ደስታን የሚያርቅ፥ ሰላምን የሚያደፈርስ።

ጥቂት ሰዎች ከላይ፥ ያሉበት የማይታወቅ፥
ለገዢዎቻቸው ምሥጢረኞች፥
ለፈጣሪያቸው ጠላቶች፥
ሰው በበዛበት፥ የሰው ቁጥር እንዲቀንስ፥
ሰው ሲገደል፥ ሃብታም ሲምነሽነሽ፥

ምቾት አልበቃ ያለው፥
ደም ሲፈስ ደስ እንዲለው፥
እህ! እኛ ግን እነኚህን፥
ሰው መሳይ ሰይጣናትን፥
እንደ ሰዎች ቆጠርናቸው፤[18]
እኛም ሳናስበው እነሱኑ መሰልናቸው፤
ሲያታልሉን ተታለልንላቸው።
እርስ በርሳችን አጨራረሱን፤
እኛም፥ በክፉው መንፈስ ተጠምደን፥
ከሰብአዊ ቁመናችን ወረድን፥
ክብራችንን አጣን፥
እንደ አራዊት ተቆጠርን፤
ከእንስሳትም ዝቅ ያልን መሰልን።
አሁንም ለሆዳቸው ያደሩ፥ ባለ ጊዜዎች ይደሰታሉ፤
ክፉና ደጉን መለየት ስለማይችሉ፤
ከሰይጣኑ ጋር ያብራሉ።
አ! ሰዎች በአለም ዙሪያ ተጨነቁ፥ በመላ እድሜአቸው፤
መፍትሄውን እግዚአብሔር እንጂ፥
ምድራዊ ሰው አይሰጣቸው።


## ክፉዎችን በክፋታቸው አወቅናቸው

ያደረሱብንን ጭንቀትና መከራ ስናስበው፤
የሚጠበቅ መስሎ ስላልታየን ከሰው፥
ድርጊቶቻቸውን እንደ አጋንንት ሥራዎች ቆጠርነው።
ክፉዎች በሚያደርሱብን መከራ፥

---

[18] “ኃጢአትን የሚሠራትም ከሰይጣን ወገን ነው፤ ጥንቱን ሰይጣን በድሎአልና፥ ስለዚህ የሰይጣንን ሥራ ይሽር ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ።” 1ኛ ዮሐ. 38

የከፋታቸውን ክፋት ስናስበው፥
እናውቃለን ምንጩን፥
ያው ከአጋንንት ሠፈር መሆኑን።
እኛ የምናስተውለው የሰውን ውጫዊ መልኩን
በግል ፈቃዱ የሚሠራውን እንጂ፥
አይደለም ተገዶ የሚሠራውን።
አይ! ሞኝነታችን፥
ሰውን ሁሉ እንደሰው መቁጠራችን፤
ይህንን እና የመሳሰሉትን ባለማወቃችን ተጎዳን፥
ከሳይንስ እውቀት በላይ ያለ ስላልመሰለን፥
ክፉውን ማየት ተሳነን።
ክፉ መንፈስ አካላዊ ስላልሆነ፥
አካላዊውን መምሰልና መሆንም ይፈልጋል፤
ሰውን መስሎ፥ ሰውን ሆኖ መገኘትም ሆኖለታል።
የሰውን እጅና እግሩን አእምሮውንም ሲሰልበው፥
በወርቅ (በገንዘብ) በሆዱ ሲገዛው፥
የእርሱ አገልጋይ፥ ባርያውም ሲያደርገው፥
እንዴት ነው ይህንን ድርጊት የማናየው?
የሥራው ብዙ ሥራው ብዙ ነው፤
በአይነ ልቦና ነው፥ እርሱን ማየት የሚቻለው፤
በጾምና በጽሎት ነው፥ እርሱን የምንረታው።



ሕብረትና አንድነት እስከ ሞት

## <u>ሕብረት እና አንድነት እስከ ሞት</u>

*ሰዎችም ከልዩ ልዩ ምንጮች መንጭተው፥*

*እንደ ፈሳሽ ወንዞች ተጠረቃቅመው - ተደራርበው - ተቃቅፈው፥*

*ነጫጭ መጐናጸፊያን ተላብሰው፥*

*በአንድ ላይም በመሆን፥ ክፉና ደጉን አውስተው - አውርተው፥*

*በሃዘን ጊዜ አብረው አዝነው፥*

ደስ ሲላቸውም በአንድነት ዘምረው፥
ለጠላት (ለማይታዩ ኃይላት) ክፍተት ላለመስጠት፤
ነፋስ በማያስገባ ሕብረት አንድነትን ፈጥረው፥
ዋናው መካሪ - የማይታይ መሰሪ፥
እነርሱኑ መስሎ ተመሳስሎ 'ሚኖር በመካከላቸው፣
በማይታይ ጦርነት ቅራኔዎችም አልተለዩአቸው።

ሲገቡ፥ ሲወጡ፥ ሲላኩ፥ ሲወሰዱ፥
በሕይወት ሲኖሩ፥ በምድራዊ እሳት እንዳይነዱ፥
ሲሞቱም በሰማያዊ እሳት እንዳይቃጠሉ፥
በሃሳብ ይደከማሉ፤ በሃሳቦቻቸውም በጋራ ይጨነቃሉ፤

ታዲያ ከመካከላቸው በሃሳብ ያፈነገጡ፥
ራሳቸውንም ማህበረሰቡንም ለመምራት ያልበቁ፥
ከወዲያ ወዲህ ሲዋልሉ፥ በማያውቁት ጉዳይ ክፉኛ የተቀጡ።[19]
እነርሱ ናቸው፥ ፍርኃትና ጥርጣሬ  የማይለያቸው፥
ከማይታወቀው ውስጥም እውቀት እንዳለ ያልታያቸው።
የአለማመናቸውን ዘመን አራዝመው፥[20]
አስቀድሞ በማመን የሚታወቅ ነገር መኖሩ ያልገባቸው።

የተፈጥሮ ባህሪይ ከኢምንት እስከ አበይት፤[21]
የመረረ፥ የከረረ ቅራኔ፥ የሰው ሃሳቡና ባህሬው፥
በቀንም በሌሊትም እረፍት የሚያሳጣው።

---

19 "ባለጠጎች ደኸዩ፤ ተራቡም፤ እግዚአብሔርን የሚፈልጉት ግን፥ ከመልካም ነገር ሁሉ አልተቸገሩም።" መዝ. 33፡ 10

20 "እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱ መጠን፥ እንዲሁ እግዚአብሔር የማይገባውን ይሠሩ ዘንድ ሰነፍ አይምሮን ሰጣቸው።" ሮሜ. 1፡28

21 "በሰው ልቡና ያለውን የሚያውቅ ሰው ማነው? በእርሱ ያለቺው ነፍሱ ናት እንጂ። እንዲሁም ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር፥ የእግዚአብሔርን ሃሳብ የሚያውቅ የለም።" 1ኛ ቆሮ. 2፡11



ወርቅን የሚወዱ

## <u>ወርቅን የሚወዱ</u>

ወርቅን (ገንዘብን) መውደድ የሰውን ጠባይ ለወጠው፤

ምኞቱን ፍላጎቱን አበዛው፤

ሁሉን አፋሽ አግበስባሽ አደረገው፤

የሰው ጠባይ በገንዘብ ኃይል ሲለወጥ፥

ከፍቅር አልባነት አልፎ እጅጉን ሲከፋ፥

ጥላቻና መርዛማነትን አስፋፋ።
ከሕብረሰብአዊነት ወደ ግለኝነት፥
በግለኝነትም ከክፉ መናፍስት ጋር መቆራኘት፥
እስከ ሰው መግደልና ጦርነት፥
በገንዘብ ኃይል እስከ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ጦርነት።

እውቀትም እንደ ገንዘብ፥ ገንዘብም እንደ እውቀት፥
ያለው በሌለው ላይ ዘመተበት፤
በገንዘብና በእውቀት የጎለበተው፥
የምድሪቱን ሃብት ለራሱ አደረገው።
ወርቅን (ገንዘብን) እና ክብርን የወደዱ፥
በምድረ ነዋይ ሞራ በተጋረዱ አይኖቻቸው፥
በተጠናበሩ እይታዎቻቸው፥
ከሕዝቡ እየነጠቁ ለራሳቸው።

ወርቅን የወደዱ፥ በአይነ ልቡናቸው የተንሸዋረሩ አስጨነቁን፥
ብኩርናቸውን ለእንጀራ የለወጡ መሪዎቻችን አንገላቱን፤
እስከ ገደል አፋፍም ድረስ አሳደዱን።
ሃብት ንብረትን ስለአጋበሱ፥ እራሳቸውን እንደ ልዩ ፍጥረት ቆጥረው፥
እኛን እንደ ባሪያ - እንደ ንዑስ ፍጥረት፥
እንደ ትቢያ - እንደ አሮጌ ዕቃም ቆጠሩን።

"ፍሬ መሬት ወድቆ ከዋለ ካደረ፥
ሰው ገንዘብ አግኝቶ መከበር ከጀመረ፥
የመጣ ነውና ቀድሞውን ከጥንት።
ሁለቱም አይድኑም ከመበላሸት።" [ከበደ ሚካኤል - ታሪክና ምሳሌ]

ባንድ ላይ የሚበሩ ወፎች በክንፋቸው እንደሚመሳሰሉ፥
በፍቅረ ነዋይነት የሰከሩ ግሪሳዎችም በአንድነት ይከንፋሉ፤
"እኛ ስለራሳቸን ደስታ እንጂ፥ ስለ ሕዝቡ ግድየለንም.." እያሉ።
ውሸት ካለበት ሥፍራ እውነት ይርቃል፤
ሁሉም ብጤውን እየፈለገ ይጠጋጋል።

የሰውም እውቀቱና ገንዘቡ ምድሪቱን ያሳምራታል፥
ወይንም የሰው እውቀቱና ገንዘቡ ምድሪቱን ያጠፋታል።
ገንዘብ ቢያገኝ ጥሩ ሰው፥
ከራሱ አስቀድሞ ለተቸገሩት ነው የሚያከፋፍለው፤
ኢትዮጵያኖች ወይንም ሌሎች ሃብታሞች፥
ገንዘባቸውን ለልማት የሚያውሉ ደጋጎች፥
ድሆችን የሚረዱ፥ ቤተ እምነቶችን የሚያሠሩ በገንዘባቸው፥
ለእነርሱ ምስጋና ይድረሳቸው፤
እግዚአብሔር ይባርካቸው።
በገንዘቡ ኃይል የሚመካ ክፉ ሰው፥
ሰውንም ሊገዛበት ነው የሚያምረው፤
የሚገዙለትንም ሲያገኝ እንደ እቃ ስለሚቆጥራቸው፥
በእነርሱም ላይ ኃጢአት መሥራት አይታክተው።
ለሃብታሞችና ለግለኞች በተመቸ መንግሥታዊ አስተዳደር፥
የሰው ልጅ ሰብአዊ ክብሩ በቁሳዊ መሥፈርት ሲቆጠር፥
ምድራችንም የኃጢአተኞች መናኸሪያ ሆና እንድትቀር፥
ይህ ነው የክፉ አድራጊው የእርኩሱ መንፈስ እቅድ፥
ሰውን በተንኮልና በክፋት ማጥመድ።[22]
የመላው የምድሪቱ ሃብት ለጥቂቶች መደሰቻ ሲሆን፥
የድሆችም ቤት ሲፈርስ፥
ሃብታም ምድሪቱን ሲገዛ፥ ሰይጣንም ሲነግሥ፥
አ! ያ የኋላ ዘመን ክፉ ጊዜ ቶሎ - ፈጥኖ እንዳይደርስ።[23]

---

[22] "ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፤.." 1ኛ ጢሞቲዎስ 6:10

[23] "ነገር ግን፥ በኋላ ዘመን ክፉ ጊዜ እንደሚመጣ ይህንን እወቅ፤ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ፥ ገንዘብንም የሚወዱ ቀባጣሪዎች፥ ትምክህተኞች፥ ትእቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ ምስጋና የሌላቸው፥ ከጽድቅም የወጡ ይሆናሉ።" 2ኛ ጢሞ. 3፡ 1- 2

በምድሪቱ አዲስ ምድራዊ እምነት ለማስፋፋት፥
ሰይጣንም እንዲቆጣጠራት፥
ይህችን አለም ሮቦቶችና ጥቂት ሃብታሞች ብቻ እንዲራኮቷት፥
እነርሱ ብቻ በፈንጠዝያ እንዲኖሩባት፥
ይህንን እውን ለማድረግ፥ እጅግ ከፍተኛ የገንዘብ ኃይል አስፈልጓል፤
ምድራዊ ሥልጣኔም ወደ ገንዘብ ማከማቺያነት ከተቀየረ ቆይቷል።

የሰው ክብሩ በገንዘብ ሲለካ፥
ትውልድም በሮቦት ሲተካ....፣
አ! የአለም ሕዝቦች ተጨነቁ፥ በመላ እድሜአቸው፤
"እኛን የሚተካ ሰው ላይኖር ነው!" ብለው፤

አ! የሰው ልጅ አጉል ጭንቀት ያዘው፥
የሰው ችግር የፈጣሪውም እኮ ነው፤
ማን ያውቃል አንድዬ ያቀደውን፥
አስቦ አዘጋጅቶ እንዳስቀመጣት ማርያምን፥
አስቀድሞ አዘጋጅቶ እንድሆነ መፍትሄውን።

በተለመደው የጋርዮሽ አኗኗራችን፥
በደስታ ጊዜ አብረን እንደሆንን፥
ሲከፋንም አንድላይ ብንሆን፥
የሰው ፍቅር ከተላበስን፥
ባለ ሃብቶች አይደርሱብን፥
ኑሮአችንን አይቀሙን፥
ከገንዘብ የሚበልጠውን፥
ውስጣዊ ማንነታችንን አይቀሙን፥
ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ደስተኞች ነን።



ዛኒጋባ

## <u>ዛኒጋባ</u>

አይ! የሰው ነገር፥

በሃሳብ ውሎ በሃሳብ የሚያድር፤

ከቀን ወደ ቀን ሳይርገበገብ ሳይናወጥ የማይኖር።

ምንድነው ይህ የሰው የሃሳቡ አጫፋሪ፥

የራሱ ሁለትነት አንሶ ሌላም ተጨማሪ?

ሰው ሲባል እንዲሁ ነው - ማለት ይሆን?

የሆነውን ሳይሆን - ያልሆነውን የሚሆን?[24]

ከፉውና ደጉ ቦታ ሲለዋወጥ፥
በማይረጋ ስሜት፥ በሃሳብ መናወጥ፤
ከመብላት ጋር ረሃብ፥ ጠጥቶም ጥማት፥
ከደስታ ጋር ሃዘን፥ ከዚህ ከዛም ቤት፤
ዝምታ ሲሰፍን እልል ባሉበት።

የሰው ልጅ ኑሮ ሲከብደው ሲቸግረው፥
ማን አወቀ  ቢኖሩ በዙሪያው፥
"አቤት፥ አለን፥ ምን እንርዳ!" የሚለው።
ማን አወቀ እነርሱስ እንደኛ የራሳቸው ሕይወት ቢኖራቸው።

እኛ ግን፥ ከትላልቅ ቤቶች ይልቅ፥
በትናንሽ የሳር ቤቶች፥ በቆርቆሮም ዛኒጋባዎች ውስጥ በዝተን ተገኘን፤
ከውጪም ከውስጥም እንደ ተከበብን - በሕይወታችን ተጠላለፍን።
ማን አወቀ፥ የማይታዩ ፍጥረታት ቢኖሩ?
ባንሰማቸውም እንዲህም እያሉ የሚፎክሩ፡-

"እኛም ምድራውያን ነፍሳት ነን፥
ዘለአለማዊ ሕይወት ያለን።
የጎርፍ የንፋስ አደጋ አያጋጥመን፥
በአገኘነው አካል ላይ ተለጥፈን፥
አይበርደን አይሞቀን።
የሰውን ስሜቱን ሁሉ ተጋርተን፥
የፍቅር፥ የጥላቻ፥ የደግነት፥ የከፋት፥
የደስታ፥ የሃዘን፥ የሰላም፥ የጦርነት ተግዳሮቶችን፥
ሁሉንም እንዳመጣጡ አስተናግደን...።"

---

24 "የማደርገውን አላውቅምና፥ የምወደውንም ያን ምንም አላደርገውምና፥ ያንኑ የምጠላውን ብቻ እሠራለሁ እንጂ።" ሮሜ. 7፡ 15



ጸረ ሰው

## <u>ጸረ ሰው</u>

እነሆ! ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥም፥ ስለ ቅራኔዎች በሥፍራ ሁሉ መኖር፥ በስፋት እና በጥልቀት ተጽፏል። ይህም ከመላእክት መካከል የቅራኔዎች ሁሉ ጠንሳሽ ሆኖ የተገኘ ሰይጣን እንደሆነ ነው የሚያመለክተው።

አካላዊ ያልሆኑ (መንፈሳዊ) ኃይላት በሚታየው በማይታየውም አለም ይመላለሳሉ፤ እኛ ስልለማናያቸው የሉም ማለት አይደለም።

ቅራኔዎችም በመላእክት አለም ሲባባሱ፥ እርኩሳኑ እና ቅዱሳ ኑ ወገን ለዩ[25]።

***በምናየውና በምናውቀው አለም ውስጥ እንመላለሳለን፤ በማናየው እና በማናውቀው አለም ውስጥም እንኖራለን።***

ይህ የኛ ምድራዊ እውቀት መንፈሳዊ እውቀትን የሚያቀጭጭ ከሆነ፥ ጭራሹኑ አለማወቅ ይሻል ይሆን?

በአለማወቅ ውስጥ የሚመላለስ (በምድር ለመኖርም የሚያበቃ እውቀት የሌለው ሰው) የአለማወቅን እውቀት፥ ከዚያ ለየት ካለ አለም ውስጥ ያገኝ ይሆን?

የትም ቢኬድ - ሲሆን የትም እማይደረስ፥

ከሚታወቀው የማይታወቀው ሲብስ፥

ያ ስውር እውቀት ሲሆን የማይቀመስ፥

በአለማወቅ ይገኝ ይሆን ሌላ እውቀት?

በማይታወቅ ጠፈር ውስጥ ያለውን እውቀት የሚዳስስ።

ግን'ኮ አንድ ትሁት አላዋቂ የተባለ፥

በዚያች በትንሿ እውቀቱ - እምነቱ ለእርሱ ሁሉንም የእርሱ ቢያደርግለት፥

አተረፈ እንጂ ምን ጎደለበት?

*አእምሮም በታማኝነት ሥራው፥*

*የውጭ መንፈስ ለመግታት ሲታገለው፥*

*መላስ የብቻውን ነፍስ ሲያወጣ፥*

*የሃሳብ ጉም ሥፍራውን ሲመላው፥*

*ድምጽ ጎርነን ሲል፥*

*ጨለማ በብርሃን ላለመጥፋት ሲክለፈለፍ፥*

*የሰው መልኩ ሲለዋወጥ፥*

*እውነት በመሬት መናፍስት ሲጠለፍ፤*

---

[25] "በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ መላእክቱ እና ሚካኤል ዘንዶውን ተዋጉ። ዮሐ. ራዕ. 12፡7

ጭቅጭቅ ንትርክ ከውስጣዊነት ወደ ውጫዊነት ሲሸጋገር፥
ምድሪቱም በዚህ አይነት ስትኖር፥
ብዙ ሺህ ዓመታት አለፉ፥ ምንም ሳይቀየር።
ለምን? እንዴት ምን ከተተን ከዚህ ቅርቃር?

አዎ! ጠላት አለ በዙሪያችን[26]፥
አፈር እየላሰ የሚኖር፥
ለመናደፍ የሚሽሎከሎክ፥
ሰውን የሚያስት ክፉ ዘር።

በዚች በአንዲት ምድር ስንኖር ከጠላት ጋር፥
ማን አወቀ፥ ለእኛ እንጀራ ምግባችን፥
ለእርሱም ምግቡ ሰው መሆኑን።

ይህ ሕይወት በዚህች ምድር፥
እኛ አለማችን የምንለው፥
ሉሲፈር ከሰማይ ተጥሎ መሬት ከወረደ በኋላ ነው።
በዚህች በኛ አለም፥ ምድሪቱና ቅራኔዎች በአንድነት ተዋህደው፥
ሕዝቦችን ያተራመሳሉ መመሪያ እየተሰጣቸው፥

---

[26] በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘሯም መካከል፥ ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኮናውን ትነድፋለህ።" ዘፍ. 3፡15

"...የብዙዎችን ራሶች ይቀጠቅጣል፡፡" መዝ. 109፡6

"..ዲያቢሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ፥ እርሱም የቀድሞው እባብ ተጣለ፥ …የመሲሁም ሥልጣን ሆነች…"ዮሐ ራዕ. 12፡10

"ያሳታቸውም ዲያቢሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባህር ተጣለ፤ ለዘለአለምም እስከ ዘለአለም ቀንና ሌሊት ይሰቃያሉ።" ዮሐ. ራዕ. 20፡10

"እግዚአብሔርም ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት ሳይራራላቸው ወደ ገሃነም ጥሎ በጨለማ ጉድጓድ ለፍርድ ሊጠበቁ አሳልፎ ከሰጣቸው..." 2ኛ ጴጥ. 2፡4

ከሥራ አስኪያጅ ሉሲፈር ንጉሣቸው።
ለሰው ልጅ በጎ ፈቃድ ቢታወጅም[27]፥
ሉሲፈር ከመጥፎ ምግባሩ አልታቀበም።
ግብረ አበሮቹም አብረው ተሰልፈው፥
ለመጥፎ ሥራ ተጣድፈው፥
በሠለጠኑበት ተሰማርተው፥
ሥፍራና ጊዜ ጠብቀው፥
ሰውን ከሰው ለማጋጨት ተቻኩለው፥
በደረቀ አፈር እንደሚሰርግ ውሃ፥
ሾልከው ተሽሎክልከው፥
ከደቂቅ እስከ ግዙፍ ሁሉን  ነካክተው፤
እነርሱን ፊት ለፊት ተጋፍጦ ማሸነፍ ነው ለሰው ያስቸገረ፥
ግን በእምነት በመስቀሉ ያማተበ፥
እርኩስ መንፈስን ካጠገቡ አባረረ።
ከጥንት ጀምሮ የታወቀ፥ በሁሉም ሃይማኖት፥
ጠንቅ ሆኖ የቆየ፥ ለሰብአዊነት፥
ሥራው ሰውና ሰውን ማጋጨት፥
እያጠፋፋ ወደራሱ አለም መከተት፥
የዚህን የተደበቀ የጠላት ውጤት፥
ለሚያዩ፥ ለሚሰማቸው፥ አይቻልም መርሳት።
ምንም እንኳን አንዳንዶች፥
ይህንን ከቁም ነገር ባይቆጥሩት፥
የማይመስልም ነገር እውነታ ሊሆን እንደሚችል፥
ይህ እና የመሳሰለውን፥

---

[27] "ክብር ለእግዚአብሔር፥ በሰማያት ሰላምም በምድር፥ ለሰው ልጅም በጎ ፈቃድ ሆነ" ይሉ ነበር። ሉቃ. 2፡14

በማመን እና በማወቅ መካከል ያለውን፥
ለማወቅ መሞከር ሞኝነት አይሆን።
ታዲያሳ! የአለማወቃችን ጺጋ ነበር የሚሻለን??

ዛፍ ራሱን መስሎ እንዳይኖር፥
ተፈጥሮ ቅጠል ሲያሳጣው፥
ሰውም ራሱን መስሎ እንዳይኖር፥
ሰይጣን መሃል እየገባ ሥርዓት ሲያሳጣው፥
ከትርምስምሱ ባሻገር፥
ማነው ሥርዓት አልባነትን ሥርዓት የሚያስይዘው?

በምድራዊ የመንትያ እውነታዎች፥
እንዲሁም በእውነቶች እና ውሸቶች መካከል ቅራኔዎች፥
እኛ በመሃል እየተጨናነቅን..፤
ስንጠይቅ፡- "ማነው ከዚህ ውጥረት የሚገላግለን?" እያልን፥
ይኸው እስካሁን አለን።

ሳናውቅ ወደማናውቀው እንገባለን፤
በማናውቀው እናውቃለን፤
በእምነታችን እንድናለን።

በማይታየው አለም ለሚኖሩ እኩዮች፥
መስቀሉ ነው - ጻረ እኩይ - ጠላታቸው፥
ለእኛ መድኃኒታችን ሲሆን - እነርሱን የሚያቃጥላቸው፥
ይህንን ነው - በአይነ ልቡና ከምናየው የምንረዳው።[28]

---

[28] *"ኃጢአትን የሚሠራትም ከሰይጣን ወገን ነው፤ ጥንቱን ሰይጣን በድሎአልና፥ ስለዚህ የሰይጣንን ሥራ ይሽር ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ።" 1ኛ ዮሐ. 3፡8*

## ***መደምደሚያ***

ጠፈራዊ ቅራኔዎች የህያውነት መዘውሮች ናቸው፤
የሚያንቀሳቅሱ ክፋትና ደግነትን ይዘው፤
ለዚህ ነው ቅራኔም (የመሆን ያለመሆን ትግል) የማይጠፋው፤
ለዚህ ነው (ይሆናል) በአንድ ሰው ውስጥም የቅራኔዎች መኖር ያስፈለገው።
ስለዚህ ሰው ይኖራታል ሕይወቱን፥
ግራ ቀኝ ማለት ሳይሰለቸው።[29]
የሰለቸውም ይታመማል፥ ይሸነፋል፤
ተስፋ የቆረጠም እጁን ይሰጣል።
ግን፥ ይህ የሞት ድንፋታ - ሰውን ከሰው ቢገነጥል፥
ዘለአለማዊ ህልውና ይረታዋል፤
ምድራዊ ሕይወትን ሌላ ሰማያዊ ሕያውነት ይተካዋል።
ሰውማ እንዲህ የቅራኔዎች ገፈት ቀማሽ ሆኖ አይቀርም፤
ለዚህማ ነው የጌታችን መሰቀሉ፥ መሞቱ፥ መነሳቱና ማረጉም።
ምንጊዜም አሸናፊ ነውና እግዚአብሔር፥
የእኛም መርመስመሳችን በዚህች ምድር፥
ለጊዜው ነው እንጂ፥ አይቀርም መነጠቃችን በክብር።
ጠፈራዊ ቅራኔም (ጥሩና መጥፎው) ጭራሽ ባይኖር፥
ጥሩው በጥሩነቱ፥ መጥፎውም በመጥፎነቱ፥
እራሱን አስከብሮ ይኖር ነበር።
ይህ አለም አንድ ወጥ (አንድ አይነት) ቢሆን ኖሮ፥
በመጥፎነቱም ሆነ በጥሩነቱ፥
ራሱን የቻለ አንድ አለም ይባል ነበር።
ግን እኛ፥ እንዲህ አይነቱን አለም አናውቀውም፤
ተሳትፏችን ነውና ከጥሩውም ከመጥፎውም።

---

[29] "እነሆ በአመጻ ተጸነስሁ፤ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ።" መዝ. 50(51)፡5

ከምድራዊነት ባሻገር መኖሪያችን፥
ፍቅር የሞላበት፥ የጋራ ሕልውናችን፥
ቅዱስ መንፈስ ነው አንድነታችን።
　　ይህም እንዲሆን መጨረሻው፥
　　ጥሩው እያለልን፥ መጥፎውን አናጉላው።
በመንትያ እውነቶች ተጠምደን፥
አንጎላችን መምረጥ ቢያቅተው ከሁለት አንዱን፥
መሪ ሆኖ ከቤተ ክርስቲያን ይውሰደን እግራችን።
ተምረን፥ ጸልየን፥ ቀድሰን፥ ዘምረን፥
መስቀሉን ተሳልመን፥ ጸበሉንም ጠጥተን፥
ንስሃ ገብተን፥ ቅዱስ ቁርባን ተቀብለን፤
ከአምላካችን አንድነትን መመሥረት ነው የሚበጀን።
　　ጥሩው አንጎል የመሪነት ሥልጣን ሲሰጠው፥
　　ለኃይሉ ወሰን፥ ለእድገቱም ድንበር አይኖረው።
በአንድ አንጎል እየተመራ፥ ለጥሩው፥ የሚተጋ፥
ወደ ፍጹምነት ነው የሚጠጋ።
　　ምድራዊ የተፈጥሮ ባህሬ ሰውን ቢያስጨንቀው፥
　　የሰው መንፈሳዊ የተፈጥሮ ባህሬው ይችላል ሊገታው።
　　በቃ! በእምነት መጽናት ነው የሚያዋጣው፥
　　በቃ! ይህ ነው የሚጠቅመው፥ በጥቂቱ ለሚማር ሰው።
እና፥ እስቲ ደጎች እንሁን፦ በውስጣችን ያለውን ፍጹሙን፣
ከውስጣችን አውጥተን እንስጠው ለራሳችን።
　　ለሰው ልጅም በጎ ፈቃድ ይሁን፥
　　ድኅነት ይግባ ከቤታችን፥
　　ፈውስም በኢየሱስ ክርስቶስ፥
　　በጌታችን እና በመድኃኒታችን።

### የቃላት ትርጉምና ተጨማሪ ማብራሪያ

(ከምድራዊነታችን ባሻገር ሦስተኛው መጽሐፍ የተወሰደ)

### ሕዋስ

ዝቅተኛው (የመጨረሻውና ትንሹ) ባለ ሕይወት አካል፤ ዝቅተኛው የሕይወት ክፍል። አንድ ሕዋስ በውስጡ ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን ፕሮቲኖች በሕዋሱ ሽፋን (cell membrane) ውስጥ አቅፎ ይይዛል። በፕሮቲን ውስጥ ያሉ ኬሚካሎች እንደ ሰንሰለት የተያያዙ አሚኖ አሲድ የተባሉ ናቸው። የአንድ ሕዋስ የሕይወት ተግባራት በጠቅላላ ከዲ ኤን ኤ ጀምሮ እስከ ፕሮቲን ግንባታ ድረስ በዚሁ የሕይወት ሕዋስ ውስጥ ይካተታል።

### የነርቭ ሕዋስ

የነርቭ ሕዋስ ከሌላው ሕዋስ የሚለየው መረጃዎችን በማስተላለፍ ጠባዩ ነው።

### ጸረ አካል፥ የአካል ተቃራኒ። (Anti matter)

ጸረ አካል ከአካል የሚለየው በተቃርኖአዊ ጠባዩ ብቻ ነው። በአካል የተገነባ ብርጭቆ በጸረ አካል ከተገነባ ብርጭቆ ምንም ልዩነት አይኖረውም። ነገር ግን በጸረ አካላት ውስጥ የኢሌክትሮኖችና የፕሮቶኖች ጠባዮች በተቃራኒነት ስለተቀመጡ፥ በጸረ አካል የተገነባ ብርጭቆ በአካል የተገነባውን ብርጭቆ ቢነካው ሁለቱም ብርጭቆዎች በታላቅ ፍንዳታ ይጠፋፋሉ።

በአካል የተገነባ ደበበና አስካለ በአካል በተገነባ ምድር ከተመላለሱ፥ በጸረ አካል የተገነቡ ደበበና አስካለም በጸረ አካል በተገነባ ምድር ውስጥ ሊመላለሱ ይችላሉ (ይሆን?)። የአካልና የጸረ አካል መገኘት እድል መሳ ለመሳ ሊሆን ይችላል።[30]

አንድ ኢሌክትሮን እና አንድ ፖዚትሮን ቢጋጩ፥ ሁለቱም ይጠፉፉና በነርሱ ምትክ የጋማ ጨረር ብርሃኑን ያስተጋባል። እኛ ግን ይህንን ጨረር በአይናችን ለማየት አንችልም። ሆኖም ይህንን ፍሬ ሃሳብ በመጠቀም፥ በጋማ ጨረር ፎቶግራፍ የሚያነሳ

---

[30] Close Frank, 2009: **Anti Matter,** Oxford University Press.


PET Scanner (Positron Emission Temography) በህክምና አለም ውስጥ ከፍተኛ ጥቅም እየሰጠ ነው ያለው።

ከጠፈር ወደ መሬት የሚገቡ ጸረ አካሎች (ፖዚትሮኖች) መሬትን በየጊዜው እንደሚጎበኟት ይታወቃል። የአካል እና የጸረ አካል መጠፋፋቶች በጠፈር ውስጥ በታላላቅ ቦግታዎች ሲካሄዱ፥ እስከ ምድራችን የአየር ክበብም ይደርሳሉ። በጸረ አካላት የተገነባ ሌላ ጠፈር ቢኖር ማን ያውቃል?

በጠፈር ውስጥ በአንድ ወገን ከዋከብት፥ ጸሐዮችና ጨረቃዎች፥ እንዲሁም እኛና መሰሎቻችን በአካል እንደተገነባን ሁሉ፥ በጸረ አካላት የተገነቡ ሌሎች ከዋከብት፥ ጸሐዮችና ጨረቃዎች፥ እንዲሁም እኛና መሰሎቻችን የሉም ማለት አይቻልም።

# ምዕራፍ ሦስት

## የእንፉረዳለን ቅዠት



ውዝግብ

## መግቢያ

ምንድነው የሰው ወቀሳ፥
የተቃራኒዎችን ጦርነት የሚያስነሳ?
አጉል ንጭንጭ ከማይጋፉት ጠላት ጋር ባላጋራ፥
ደስታን የሚቀይር በመከራ፥
ጣፋጩንም በመራራ።

እነሆ! በቅድሚያ፡-
አንድ ምሳሌ ከቅዱሱ መጽሐፋችን፥
የምድራዊ አድሎአዊነትን ነገር ከሚያስረዳን፥
ምሳሌው መማሪያ እንዲሆነን፥
መንፈሳዊ ብርታቱን እንዲሰጠን፥
ተስፋ ቢስ እንዳንሆን፥ አላፊ ጠፊውን እያየን።

ከክርስቶስ ልደት በፊት፥ በአንድ ዘመን[31]፥
ኢየሩሳሌም ስትጠፋ፥
በአንጻሩም ተድላ ደስታ ሲሆን ከባቢሎን፥
ሱቱኤል የተባለ ዕዝራ ሲያሰላስል፥ ክፉና ደጉን፥
የምድራዊ አድሎአዊነት ነገር አስጨነቀው፥
አወከው መንፈሱን።
እንዲህም ብሎ ተናገረው[32] እግዚአብሔርን፡-

"የኛ ኃጢአት ከባቢሎን ሰዎች ኃጢአት ጋር ቢመዘን፥
የማንኛችን ኃጢአት ክብደት ነው  የሚመዝን፥
ለምንድነው መከራ በኛ ላይ የሚጸናው?
የኛ ኃጢአት ሳይበልጥ ከሌላው?"

ዕዝራ እንዲህ በማማረር ሲናገር፥

---

[31] 500 ዓመት አለም አካባቢ።

[32] መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል - ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ - ተጨማሪ (ዲዮትሮካኖኒካል)

ዑራኤል ከተፍ አለ፥ ሊያስተምር፡-
"የእግዚአብሔር ፍርድ መወሰኑን ባለመመርመር፥
ማንም ማወቅ እንደማይችል የፍርዱን ምስጢር።"
ግን ዕዝራ ቶሎ ስላልገባው፥
በጾምና በጸሎት መመራመር አስፈለገው።
ዑራኤልም እየተመላለሰ ለዕዝራ እንዲህ እያለ አስተማረው፡-
"እግዚአብሔር ይህንን አለም ለብዙ ኃጥአን ፈጠረው፤
የሚመጣውንም አለም ለጥቂት ጻድቃን አዘጋጀው፤
ለምንድነው እንደ ፌንጣ የምትፈናጠረው?
ለምንድነው የምድሩን ትተህ፥ መንግሥተ ሰማይን የማትመለከተው?"
የእንፋረዳለን ቅዠት፥
በተፈጥሮ ላይ ቅሬታን ማሰማት፥
"ለምን? ለምን?.." እያሉ ጥያቄ ማብዛት፥
እንደ ዕዝራ ስለ ሰው መከራ መመራመር አይነት፥
አሁንም ሞልቷል በያለበት።
ይህም የሚቀጥለው ምሳሌያዊ ድርድር፥
በሰውና በምድር ተምሳሌት ሲነገር፥
የሚያንጸባርቅ ነው የኛኑ ነገር።
ጀሩዬ የተባለች ምድራችን በሰው ተመስላ ትናገራለች፤
የአካልን ውሱን ጠባይ ከመንፈስ እየለየች።
እንዲሁም ዕዝዬ የተባለ፥ የቀድሞው ዕዝራ ተምሳሌት፥
ሊፋረዳት ቆርጧል ይህቺን ጀሩዬ የተባለች መሬት።
እኛም፥ ከምድሪቱ ጋር ስንኖር አብረን፥
እንደ ዕዝራ ነጭነጭ ማለት ስለማይቀርልን፥
እንደ ዑራኤል መልአክ መጥቶ ባያናግረን፥
የዕዝዬ እና የጀሩዬን ክርክር ሰምተን፥
ፈልፍለን እናውጣ መልካሙን፤
በጥልቀቱም እንመልከት ሁሉን።

**<u>ዕዝዬ</u>**

“ቀድሞም በሴት እየተመሰለች ሰውን እንዳናገረች፥
አሁንም ጠቅላላ ምድሪቱን ወክላ ከፊቴ ቀርባለች፤
ጀሩዬ የተባለች፥
በምድራዊ ውበቷ የደመቀች።
አሁንም እንደ ጥንቱ፥
ጀሩዬ አየሩን እንደ ነጠላ ተከናንባዋለች፤
ከጨረቃ መለስ እሷው ነች፤
ከጸሐይ ሙቀትን ቀልባ፥ ሳር ቅጠሉን ታነደዋለች፤
የአየሩን ሙቀት በማዛባት ታነፍሰዋለች፤
ማዕበሉንም ታማታዋለች፤
ሆዷን ሲጎረብጣት ትቁነጠነጣለች፤
መሬቱን ትሰነጥቀዋለች፤
ከሆዷ እሳት ትተፋለች።

በመሃል ቤት ሰውኮ ተጎዳ፤
ማነው ተጠያቂ ለዚህ ፍዳ?
ይህ አካላዊ ሕይወት ከሆነ መራራ፥
ከመሬት በበቀለ የሙብል ብድር የተገኘ መከራ፥
እንዴት ዝም ይባላል? ሰዎች ሲጠቁ ተራ በተራ።
አንዴ በነፋሱ፥ አንዴ በንዳዱ፥
አንዴ በማዕበሉ፥ አንዴ በጎርፉ፥
በመሬት መንቀጥቀጥ በእሳተ ገሞራ ሲሞቱ፥ ሲረግፉ፥
እንዴት ዝም ይባላል? ሰዎች ሲተራመሱ፤
በእሪታና በጩኸት ሲላቀሱ።

ከዓመት ዓመት ቁጣ ከላይ ሲወርድብን፥
ቅጣታችን ከበደላችን በላይ ሲሆንብን፥
መጠየቅ አለብን መብታችንን፤
“ለምን? ለምን?..” ብለን።

ምን ባጠፋን? ምን በበደልን?
ለምን መከራ በኛ ላይ ጠናብን?
ምግብ ስንበላ፥ ደስ ሲለን፥
ጎርፍ መጥቶ ሲጠራርገን፤
ብንከትም፥ ወደ ባሕር ተጠግተን፥
ማዕበሉ እያንገላታን፤
ድርቅ ሲሆንብንም እየተሰደድን፥
የትም ብንሄድ የትም፥
አልቻልንም መቀመጥ ተደላድለን፤
በሄድንበት ሁሉ ኑሮ በግዴታ ሆነብን።

ሲሪላንካ በሚባል ደሴት፥
ይኖር የነበረ የሰባት ልጆች አባት፥
ሱናሜ የሚባል ማዕበል ዘመዶቹን ሁሉ ጠራርጎ ሲወስድበት፥
የሁለት ዓመት ሕጻን ልጁን ብቻ ካለ እናት ሲያስቀረለት፥
እንዲህ አለ፥ በሃዘን ስሜት፡-

“ዘመድ አዝማድ ሁሉ ካጠገቤ ጥፍት ሲልብኝ፤
ለኔስ ምንም የለ እንደ ሞት የሚመቸኝ፤
ለመሆኑ እኔ “ሳልሞት ቀርቻለሁ፥
አልሞትኩም ብል..” ማነው የሚያምነኝ?
ግን የዚህ ልጅ አይን ሲያባብለኝ፥
“አልሞትክም፥ አልሞትንም” ብሎ እቅጩን ነገረኝ፤
ከአይኖቹ ብሌኖች ውስጥ ሕይወት ሲርመሰመስ፥
ዘመዶቼን ጓደኞቼንም ጭምር አሳየኝ።
የሞቱት ሌሎቹ ልጆቼ፥ ሚስቴም ስትታየኝ፥
ከሞት በኋላ ሕይወት መኖሩንም ተረዳሁኝ።
አዩ!...ሌት ተቀን መሞት እያማረኝ፥
ለዚህ ልጅ ስል ብቻ መኖር ግድ ሆነብኝ፥
ስለዚህ በተስፋ ብቻ እኖራለሁኝ፤

ምነው ሞት መጥቶ በወሰደኝም እያልኩኝ"።
አዎ! የሕዝቦች ሃዘን በምድሪቷ ጥቃት፥
በአለም ዙሪያ ምክንያተ ቢስ ቅጣት፥
የሰው መከራና ጭንቀት፥ ከጊዜ ወደ ጊዜያት።
ከተራራ ጫፍ ብንወጣ፥
ወደ ለምለሙም ሜዳ ብንወርድ፥
የተፈጥሮ አደጋ ይከተለናል እንደ ዘመድ።
ዛፍ በነፋስ ከመሬት ሲነቀል፥
ወዳጅ ዘመድ ድንገት ጥፍት ሲል፥
ጠራርጎ ሲያጠፉ የባህር ማዕበል፥
ሃብት ንብረት ውድም ሲል፥
ሰውም እንደ ዕቃ ከቤት ሲጎል፤
እንዴት ይቻላል፥ ተፈጥሮን ማባበል?
በባህር ዳርቻ እንዲሁም በደሴት የሚኖሩ፥
ኑሯቸውን በማህበር የሚመሩ፥
በሃዘንም ሆነ በደስታ የሚተባበሩ፥
ተመዝኖ ከሌላው በለጠ ወይ?
የነርሱ ኃጢአት፥
ለምን በነሱ ላይ በዛ ጥቃት?
ሰውን መግደል ኃጢአት ነው ከተባለ፥
ከምድሪቷና ከሰው ማነው ኃጢአት የሠራ፥
እጅጉን የበደለ?
የትኛው ነው የሚበልጠው?
ምድሪቷ በሰው ላይ የፈጸመቺው፥
ወይንስ ሰው በምድሪቷ ላይ የፈጸመው።
ምድሪቱ እየቀለበች ስላኖረቺን፥
ዝም ብለን ተቀጣን - ይህ እኮ ተፈጥሮ ነው እያልን።
ግን በየቀኑ ድርብርብ ቅጣት ሲበዛብን፥

ድንገትም ጠራርጋ ስትወስደን፥
ይህ ፍርድ ካለአግባብ መስሎን፥
“እስቲ እውነት ካለ ይፋረደን፥
ስለ እውነት በእውነት እንፋረዳለን..” ብለን ተነሳን።”

**ጀሩዬ**

“ሃ! ሃ! ሃ! እውነት ካለ ጭንቀት!
ሃ! ሃ! ሃ! ከምድሪቱ ውሸት ተነቅሎ ሲጠፋ እውነት!
ድንቅ ነው፥ ይገርማል፥ የዕዝዬ ቅዠት።
“ሰውን ሁሉ የመወከል መብት ሳይሰጠው፥
ሊፋረደኝ ከፊቴ ቆሟል፥ ዕዝዬ የተባለ ሰው።
ይሁና!... እኔም ልናገር፥ የሰው አመጣጡን፥
ምግብ እያዘጋጀሁ ማብላቴን፥
በዚህም ምክንያት መወቀሴን።
ባጠቃላይ ሰው እጅግ አስተዋይ ፍጡር፥
ከነፍስ በስተቀር ሁሉን የሚፈጥር፤
በሁለት እግሩ የሚላወስ፥
በሃሳቡ ጠፈርን የሚዳስስ፥
በዝቶና ተባዝቶ በላዬ ላይ የሚርመሰመስ፥
ሳልገታው ቆይቻለሁ እስከዛሬ ድረስ።
ጨርሶም እንዳልጨርሰው ተይዤአለሁ፥
ይኸው በትእግስቴ ብዛት፥ ለወቀሳ ለመዘባበቻ በቃሁ።
ከሆዴ የወጣው እንዲህ በድፍረት ሲፋረደኝ፥
አዬ! ለኔም ቀኔ ደርሷል መሰለኝ።
ይሁን እስቲ! ይሁና!
ክሴን ልቀበላ! ሳልሞት በቁመና።
እኔም እንደ ሰው፥ ከዕዝዬ እኩል በፍርድ ፊት ቆሜ ልከሰስ፥
የቅዠታም ቅዠት ከውሸት አይብስ።
እንፋረዳለን ከተባለስ፥

ይታያል፥ የማን ከማን እንደሚብስ።
በዚህም ሆነ በዚያ ሞት ላይቀርለት፥
በኔ ሥራ ገብቶ የሚሟገት፥
አቅምን አለማወቅ፥ ከንቱ ልፋት።
ሰውን የማጥፋት ችሎታዬ፥ አቅፎ ከማቆየት ጋር ሲወዳደር፥
በልጦ የሚገኘው ባይሆን ኖሮ የኔ ፍቅር፥
ሰውም አይተርፍ ነበር በዚች ምድር።
እኔም በራሴ ምንም አልፈጽምም፥ ሳልሰማ የበላዬን፥
ሁሉም በሕግ፥ በትእዛዝ ነው የሚከናወን፤
እጅግ በጣም ትንሽ ነው የኔ ሥልጣን።
ሆኖም፥ ለማስታወስ ያህል፥
የምድሪቷንና የሰውን ፍቅር፥
ጥቂቱን ልናገር፥ ከታሪክ ማህደር፦

በቀድሞ ዘመን[33] ገና ብዙ ምግብ ሳይዘጋጅ፥
በውሃ ሰውነቴ ገብተው በሉኝ ጥቃቅኖች።
እኔም በዛን ጊዜ፥ በወጣትነት ስሜት፥
ባሕሩን ገፍቼ ከመሬት ደፋሁት፤
አፈር፥ ደንጊያ ሆነው ቀሩ የባህር እንስሳት።
ቀጥሎም፦ መካከለኛ በተባለው የሕይወት ዘመን[34]፥
የምግብ አይነት በበዛበት፥
እጅግ ተባዝተው፥ እጅግም ገዝፈው ነበር፥ እጽዋትና እንስሳት።
እንደነጻይናዞር ያሉት ሆዳሞች እጅግ በርክተው፥

---

[33] ቀዳማይ ሕይወት (Paleozoic) - ከአምስት መቶ ሰባ ሚሊዮን፣ ዓመት በፊት ጀምሮ፥ እስከ ሁለት መቶ አርባ ሚሊዮን ዓመት ድረስ።

[34] መሐል ሕይወት (Mesozoic) - ከሁለት መቶ አርባ ሚሊዮን ዓመት እስከ ስልሳ አምስት ሚሊዮን ዓመት።

እርስ በርስ ሲጨራረሱ፥ ሌላውንም ሲያጠቁ አይቼአቸው፥
እነርሱንም በተለያየ መንገድ ከምድር ገጽ አጠፋሁአቸው።
እኔም በራሴ ላይ ስሽከረከር፥
በጸሐይ ዙሪያም ስዞር፥
አንዳንድ ጊዜም የመሳሳባችን መጠን ሲቀያየር[35]፥
በመሬት እጅግ ሙቀት፥ እጅግም ቅዝቃዜ ሲፈጠር፥
በአያሌ የእልቂት ዘመናት ብዙ የአካላዊ ሕይወት ጠፍቶ ነበር።
በረዶ ሲቀልጥ በየሞቃቱ ዘመን፥
ወይንም በመሬት መናወጥ፥
ውቅያኖስ ደረቅ መሬትን እየወረረ ሲሸፍን፥
ውሃ ወደ በረዶነት ሲለወጥ፥ በየበራዱ ዘመን፥
ወይንም በመሬት መናወጥ፥
ውቅያኖስ እየሸሸ መሬትን ሲገልጥ፥
አያሌ ፍጥረታት ስለመጥፋታቸው፥
ቅሪተ አካላት ምስክሮች ናቸው።
በተለያዩ ጊዜያት ካጠፋሁአቸው የእጽዋትና የእንስሳት ሰውነት፥
አሁን ጋዝ፥ ዘይት ሆኖ ይቀዳል ከዝቅጠ አለት።
እንዲሁም፥ በደኃራይ ዘመኔ[36] በስተ እርጅና፥
እንቅስቃሴ ቀነስኩ፥ ብዙ ነገር ገባኝና።
የምግቡ ብዛትና አይነት እንደተመጠነ፥
የእንሳሰቱም፥ የእጽዋቱም ጥራትና አይነት ተወሰነ።
እርስ በርስ መበላላት ሲቀንስ፥

---

[35] በጠፈር የእፍጋታ (Gravity) መዛባት ምክንያት፥ መሬት ከጸሐይ እየተንተተች፥ ከጸሐይ ትንሽ ራቅ በምትልበት ወቅት ሁሉ፥ የተለያዩ የበራድ ዘመናት ተፈጥረዋል። (ከምድራዊነታችን ባሻገር አንደኛ መጽሐፍ - ምዕራፍ አራት)።

[36] ደኃራይ ሕይወት (Cenozoic) - ከስልሳ ሚሊዮን ዓመት እስከ ዛሬ ድረስ።

ሰላማውያን ተፈጠሩ፥ አህያና ፈረስ።
በቅርብ ጊዜም፥ ባለ ሁለት እግሮች፥
ሰው መሳይ ፍጥረቶች ተፈጥረው፥
እነኚህ የሰውን የዝንጀሮንም መልክ ይዘው[37]፥
አውሬዎች ስለነበሩ በጠባያቸው፥
ሲበዛ ቂሎች በመሆናቸው፥
የእግዚአብሔር መንፈስ ስላልተሰጣቸው፥
ሥልጣን ተሰጥቶኝ ነበረና፥ በማንኛውም ጊዜ ላጠፋቸው።
በእውነት እኔ እንዳጠፋሁአቸው፥
ምስክር ነው አጽማቸው።
ታዲያ እስከ ዛሬ ድረስ፥ አንድ የወቀሰኝ ሳይኖር በሠራሁት ሥራ፥
የዘመኑ ሰው ሊሟገተኝ ቆሟል፥ የተፈጥሮን ሕግ ሳይፈራ።
በእግዚአብሔር አምሳያ የተፈጠረ የዘመኑ ሰው[38]፥
በዝቶና ተባዝቶ መሬትን ያጥለቀለቀው፥
አጥፍቶ ጠፊ መሆኑን ልቤ እያወቀው፥
ሊወቅሰኝ ተነሳ፥ ታግሼ ባቆየው።
ለፈጣሪ ቅድመ ዝግጅት ሳያስፈልገው፥
እግዚአብሔር በእርሱ ጊዜ (“ባንዴ”) ነው ሰውን የፈጠረው።
በአምሳሉ ፈጥሮም፥
በሰው ጊዜ፥ ብዙ ሚሊዎን ዓመታት ቢያቆየው፥
ለሥጋዊ ሰው እንዲመቸው፤
ምድራዊ ሁኔታዎች ተስተካከለው።

---

[37] የዛሬ 6 ሚሊዮን ዓመታት አካባቢ፥ የቺምፓንዚና የሰዎች ዝምድና ከአንድ ሆሚኖይዲያ (hominoidea) ከተባለ የዘር ግንድ (አንደኛው የዛፍ ቅርንጫፍ) ተጀመረ ተብሏል።

[38] homo sapien

ሰው የተፈጠረው በዚህ ቀን ነው ብለው የሚከራከሩ፥
ድንጋይ ላይ የተጻፈውን ያንብቡ፥
ከኔም የሕይወት ታሪክ ይማሩ።

አዪ! ያሳዝናል፤
አወቅሁ፥ አወቅሁ ብሎ ሰው ይጮሃል፤
ግን እግዜር ለሰው እድሜን ሰጥቶ
ገና ብዙ ብዙ ያሳውቀዋል፥
የዛን ጊዜ ከንቱ ልፍለፋን ይተዋል፤
አርምሞን ይመርጣል።

ይህ የሰው ፍጥረት፥
እጅግ ብልሽት ሲል፥ ፈጣሪውን በመርሳት፥
አመጣጡን ረስቶ፥ ሕሊና ቢስ ደስታን ሲደሰት፥
ከነኃጢአቱ እንዳትጠበው መሬት፥
በዚያ የኖህ ዘመን፥ የጥፋት ውሃ ብለው በሚጠሩት፥
በውሃ አጥለቅልቄ ቁጥሩን ቀነስኩለት።

ከዚያም፥ ከኖህ ዘመን በኋላ፥ አፈሩ በውሃ ሲርስለት፥
ይኸው የዘመኑ ሰው እንደገና ምድርን መላት በመባዛት፤
በተለይም ሰሃራ በሚባል፥ ከአፍሪቃ በስተ ሰሜን፥
ምድሪቱ አንደላቃ አኑራለች ምልአተ ሕዝቡን፥
እንዲሁም ምልአተ እንስሳቱን።

ከድሎት በኋላ መከራ እንዲከተል፥
ሰሃራም በረሃ ሆነ፥ በንዳድ መሬቱ ሲቃጠል።
ሕዝቡም እንስሳቱም ተሰደዱ፥ ውሃ እየፈለጉ፥
በተለይም በአባይ ዙሪያ የተጠጉ፥
አፍሪቃውያን እጅግ ሰለጠኑ፤
ኃያላንም ሆኑ።

ከጊዜ በኋላ፥ ምድራዊ ሥልጣኔ “ለቆ ወጣ?” አፍሪቃን፤

ተሰደደ ወደ ሰሜን[39]፤
ሕዝቡም "ችላ ብሎ?" ቆየ ሥጋዊነቱን፤
እጅግ በማዳበር መንፈሳዊነቱን።
ይህ እጅግ ርቅቅ ያለ መንፈሳዊ ሥልጣኔ፥
የማይታይ ለብዙ ሰው፥
በኢትዮጵያ ምድር፥ በየገዳማቱ ነበር እጅግ ሥር የሰደደው፤
እንዲህ እንዳሁኑ የአለም ሕዝብ ሳይቀምሰው።
ከዚህ የሰው ዘር ከበቀለበት ሥፍራ፥
ጩኸቴን ቀምቶ ከሰሰኝ፥ ዳግማዊ ዕዝራ።
ምን ይደረግ?
ካለማወቅ የሚቀባጥር፥ ይህ የዘመኑ ሰው፥
ባለ አይምሮ፥ ባለ መንፈስ ሆኖ እጅግ የከበረው፥
አጉል ጭንቀት ማብዛት ልማዱም ነው።
መንፈሳዊ ሰው በመንፈሳዊነቱ እኔን ደስ ሲያሰኘኝ፥
ምድራዊ ሰው በምድራዊነቱ እኔን ጎዳኝ።
ሰው እየበላም ሊሆን ሲችል መንፈሳዊ፥
እያወቀም ይሆናል ሰይጣናዊ።
በራሱ የሚላወስ ባለ ነፍስ የተባለ፥
እኔን ሳይቀምስ የሚንቀሳቀስ ማን አለ?
ፈጣሪያቸውን ያወቁ ያላወቁም፥
ከእልቆ መሳፍርት፥ የጠፈር አካላትም፥
እስቲ ማን አለ?
የማይረዳ፥ ስለኔ ባለ ነፍሳማነት፥
ከእኔም ነፍስ እንደተዘራ፥ የእጽዋት፥ የእንስሳት፥
እንዲሁም በእግዚአብሔር መንፈስ የከበረ፥

[39] ለተጨማሪ ማብራሪያ ከምድራዊነታችን ባሻገር ሦስተኛ መጽሐፍን ይመለከቷል።

ጥቁር፥ ነጭና ቢጫ የሰው አይነት።
ስለዚህ እኔን በልተው በአካላዊነት ነፍስ የዘሩ፥
ከጥቃቅን እንስሳት፥ እስከ ሰው በኔ የከበሩ፥
ከፈጣሪ የተሰጠኝን፥ የመግደል ውሱን ችሎታዬንም እንዲያውቁ ይመከሩ።
ታሪክ ጸሐፊም፥ ሳይንቲስትም ቢሆን የሰው ልጅ፥
ሁላችንንም ባንድነት ሊያጠፉን ይችላል፥ የጠፈር ሁሉ ፈራጅ።
ሰው ግን፥.... ከቶ በኔ ጠፍቶ የማይጠፋ፥
በዝቶና ተባዝቶ በሥልጣኔ ቢገፋ፥
ተፈጥሮን መሟገት የሚችል አይምሰለው፥
ተስማምቶና ተቻችሎ መኖር ነው የሚሻለው።
ግን እስቲ እኔም ልቻለው፥
መቼም ዲሞክራሲ - ሰብአዊ መብቱ ከሆነ ለሰው፥
ለፍላፊ - ቀባጣሪ መሆኑ ‘ማየቀር ነው።”

**ዕዝዬ**

“ሃ! ሃ! ሃ! እንዲህ ነዋ! እውነት ሲገለጥ በጭንቀት፥
እንዲህ ከሆነማ የሰውና የምድሪቱ ግንኙነት፥
እርሷ ፈላጭ ቆራጭ እንዳሻት፥
መፋረዱ ሲያንሳት፥ ማን ዝም ሊላት?
በምድራዊ ኃይሏ አሰቃይታ በገደለች፥
እሷ፥ በራሷ ግንዛቤ ራሷን ስታሞካሽ፥
የሰውን አመጣጥ በደንብ አልተረዳች።
እኛ ሰዎች፥ በዚህች ምድር ቆይታችን፥
ከየት ተነስተን ነበር ከዚህ የደረስን?
“ገና ድሮ፥ ድሮ” ብለን ወደማይገባን ነገር መለስ ስንል፥
መንፈሳችንም ሲያሳውቀን ማስታወሱን፥
“ነበርኩ፤ አሁን አለሁ፥ እንዳለሁም እኖራለሁ....” እያለ፥
ሲያካፍለን ምሥጢሩን፥

ጥንት ያልገባን ነገር ሁሉ አሁን አሁን ገብቶን፥
“እንዲህ እኮ ነበረ!...” እንድንል፦
ሁሉ ነገር ፈካ፥ ፈካ ብሎ፥
ቁልጭ፥ ቁልጭ ብሎ ሲገለጥ በአካል፥
አዬ! በማስታወሳችን ብቻ ስናሰላስል፥
የመንፈስን ነገር (አጸደ ነፍስን) ስናሰላስል፥
በምድራዊነቱ ታዋቂ ከሆነው ከአካል ባሻገር፥
የት ነው ያለው፥ ያ ረቂቅ ፍጡር?
አዬ!.... ከመሬት ብንጣበቅ ለሆዳችን ብለን፥
ያሳዝናል፥ በምድራዊ ግንዛቤ ብቻ ሲወሰን ማንነታችን።
ጀሩዬ የሰዎች ህልውና ምድራዊነታችን ብቻ አለመሆኑ አልገባትም፤
“እገለዋለሁ፥ አጠፋዋለሁ” እየተባለ፥
የሰ ልጅስ የማይደነፋበት ሕያው መሆኑን አላወቀችም።

 የሰው ዘር በዝቶና ተባዝቶ፥ ሲታይ አምሮበት፥
 ቆንጆዋ ልጃገረድ አርጅታ ስትሞት፥
 ጎልማሳውም ሸምግሎ ከምድር ሲሰናበት፥
 ያለው ሲጠፋ፥ የሌለው ሲተካ፥
 ምንጊዜም እኛው ነን፥
 ለዘለአለም የምንኖር፥ በጥፍት በግኝት።

ግን ጀሩዬ አሁንም ግር እንዳይላት፥
ይህ አንዴ የተጀመረ ሕያውነት፥
እንደ ቁጫጭና ዘመሚት በሕይወት መበራከት አይነት፥
ይህ ጥፍት ግኝት፥ ይህ ብቅ ጥልቅ፥
ከግዙፍ እስከ ረቂቅ፥ ሕይወት ሲፍለቀለቅ፥
የማያቋርጥ፥ የማያልቅ።

 ሁሉም ከባዶነት ተነስቶ ሲያድግ ሲመነደግ፥
 አብቦ፥ አምሮና ደምቆ የሚታይ ሁሉ እንደ ጽጌረዳ ሲጠወልግ፥
 ለጀሩዬ ይህ ብቻ ቢመስላት ምድራዊነት፥

እርሷ የምታድነው፥ እርሷም የምታጠፋው ሕይወት፥
እኔም ትንሽ ልናገር፥ ስለ ሰዎች ማንነት።
እኛ ሰዎች ልዩ ነን፤
በውስጣችን የፍጹም ሰውእነት ጠባያት ያሉብን፤
እኛው ነን፥ በፊት የነበርን፥ አሁን ያለን፥
ቀድሞ የሞትን፥ አሁን የዳንን[40]፥
እኛው ነን፥ ያለፈው የወደፊቱም አዳምና ሔዋን።
ወይ ጉድ! ምድሪቱም ተገልብጣ ከበላዬ፥
ባንድ በኩል ወዳጄ፥ በሌላም በኩል ባላጋራዬ፤
አሁንስ በደንብ ሰማሁሽ በጆሮዬ፥
ግን ምነው ገና ሳልሞት ጀሩዬ!
አብልተሽ አጠጥተሽ ገዳዬ።
ምነው ተነሳሺብኝ፥ ሟጠጠ ትእግስትሽ፥
የኔ ጩኸት ካለ ምክንያት መሰለሽ?
በአንድ በኩል ፍቅርሽ፥
በሌላ በኩል ጠላትነትሽ፥
አንቺም በሰው ላይ “ውሱን ስልጣን” አለኝ ካልሽ፥
እስቲ ስሚኝ ልጠይቅሽ፡-
ሰው ኃጢአተኛ ነው ይባላል፤
ቅጣቱንም በየጊዜው ይቀበላል፥
ግን ቅጣት ለምን በጅምላ ይሰጣል?
ሕጻን ልጅ በምን ጥፋቱ ይታመማል?
ለምንስ ካለ ጊዜው ይሞታል?
ሳር ቅጠል ሲፈልጉ፥ የደከሙ መጋቢዎች፥
የት ገቡ የኛ ከብት አርቢዎች?
ሃብት ንብረት የተባሉ ከብቶች፥

[40] “በሞቱ ከመሰልነውም በትንሳኤው እንመስለዋለን።” ሮሜ 6፡5

ፍየሎች፥ በጎችና ግመሎች።

በአካሉ ነፍስ የተሰጠው፥ ሁሉም ፍጥረት፥
በምን ኃጢአታቸው ተቀሰፉ እንስሳት?
ሳር ቅጠሉስ ቢሆን ለምን ይሙት?
ከደቂቅ እስከ ግዙፍ፥ ሁሉም ለራሱ፥ የራሱ አለም ሲናጋበት፥
ይሰማዋል ቅሬታ፥ ሃዘን፥
ከፍና ዝቅ ሲበዛበት።

ከአስር ከብት ጋር አንድ ሰው ተዳብሎ ሲሞት፥
ከንብል፥ ከንብል በያለበት፤
ነጫጩ ብቅ ብቅ ሲል፥ በዚህም በዚያም አጥንት፥
ገና የአለም መጨረሻ ሳይሆን፥
የፍጥረታት እልቂት።

ጀሩዬ ሆይ! አንቺም እንደ እናት እንደ አባትም ሆነሽ፥
ልጆችሽን ካለአግባብ ትቀጪያለሽ፥
የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሳይኖርሽ።
እኔም ባጭሩ ልናገር የሰውን - ፍጥረቱን፥
ከዚህ ያደረሰውን - ምድራዊ ሰማያዊ ጠባዩን።

የመብላትና ኃጢአት የመሥራትን ግንኙነትን ያልተረዱ፥
ከምድሪቱ ምግብ ለመመገብ ተንጎዳጎዱ።
ከእልፍ አእላፋት እንስሳት እልቂቶች በኋላ፥
የዘመኑ ሰው መጣ ሊበላ።
ታዲያ፥ ለአዳምና ለሔዋን ምን በጃቸው?
ምግብ አብልታ በላቻቸው።
ሕይወት ቢያልፍ ሕይወት ይተካል ቢባል - ትክክል!
ከሰማይ እየነጎደ መሬት ጥልቅ ይላል፤
እንደ በረሮ የእሳት እራት ሆኖ ይቀራል።

ምድሪቱ ብትገድላቸው እያስራበች፥
ብትጨርሳቸው፥ የተፈጥሮ አደጋን እያከታተለች፥

መኖራቸውን ስለምታውቅ እኮ ነው “በልተን እንኑር” ባዮች።
አይ መሬት! አይ ይህች የተዋበች መሬት!
በፈቃደ እግዚአብሔር ድንገት ጥልቅ አልንባት!
በመብላት ልንገነባ አካላዊ ሕይወት!.......
እኛስ መስሎን ነበረ፥
መሬትን ካለ ክፍያ የምንዳብሳት፥
በየብስና በባህር ሲርመሰመሱ ነፍሳት፥
ሁሉም ባካባቢው፥ በአካላዊነቱ ሲታይበት፥
ወይ ጉድ! ጥርቅም አርጎ ያዘን እኮ!.. ይህ ምድራዊነት፤
ከምግብ፥ ከግብረ ሥጋና ከስልጣን የሚከሰት፥
የሰው፥ የእንስሳቱም መጥፎነት፥
እኔ ብቻ ልኑርበት ባይነት፥
ኃጢአት እንደ መሥራት አይነት።
ሰዎች ለመጥፋት ሲሉ ኃጢአትን ይሠራሉ?
ወይንስ ኃጢአት ሲሠሩ ይጠፋሉ?
ይህቺስ ምድር ኃጢአት አሠርታ የምታጠፋ፥
ኸረ “ያ ሰው” ምን ባጠፋ!!..
ኸረ “ያ ሰው” ምን ባጠፋ!!..
ስንቱ ተነግሮ ያልቃል? የተፈጥሮ ጥቃት፥
የማይገቱት፥ የማይመከቱት።
ማነው ተጠያቂው?
ከእንግዲህስ፥ እባክሽ ጀሩዬ በደንብ ስሚኝ፥
እኔ አንቺን ብፋረድ ምክንያት አለኝ።
ሰውም “ምድሪቱን እንፋረዳለን፥” ብሎ ከተነሳ፥
ያንቺም ሕልውና መናጋቱ አይረሳ።
እኔስ ለብሶቴ ምላሽ ቢኖረውም፥ ባይኖረውም፥
ምድሪቱ አብልቻለሁ ብላ ከምትነሳኝ ሰላም፥
ትቼአት ብሄድ ነው ‘ሚበጀኝ ወደዛኛው አለም፥

ተለማምጦ ኑሮ ጭንቀት ከሌለበት፥
ከዛው ነው ሚሻለኝ፥ ከመጣሁበት።”

**<u>ጀሩዬ</u>**

“ዕዝዬ እኔም ሰማሁህ በዕዝኔ፥
ካለ አቅምህም ስትንጠራራ፥ አየሁህ በአይኔ፥
ምድሪቱንስ እፋረዳታለሁ ከማለት፥
ኑሮን መግፋት ይሻላል በአዎንታዊነት።
በፈቃዳዊ ነጻነትህ በኖርክብኝ፥
ሃዘን አይገባኝም ብትለየኝ።
በትእግስትና በቆይታ ብዙ ነገር መማር ሲቻል፥
አግባብ አይደለም አስራበችኝ ብሎ እኔን መወንጀል።
በፍርድ ቀን ማን ተጠርቶ ማን ይቀራል?
የሁሉም ሥራ ይነበባል፤
የሰው ግፍ መቼ ተነግሮ ያልቃል?
አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ብልጦች ይሆናሉ፥
አንዳንድ ጊዜም ይሞኛሉ።
በተለይ በልተው ሲጠግቡ ከአውሬም ይብሳሉ።
ተስማምተው እንዳይበሉ፥
ካለማቋረጥ እርስ በርስ ይጣላሉ።
በድሮ ጊዜ ጀግኖች ካለ ጦርነት መቀመጥ ሰልችቷቸው፥
ጅራፍ ይዘው ወጡ ይባላል ከቤታቸው፥
መሬትን ሊገርፉ፥  ጦር አምጪ ብለው።
ከኃጢአተኛም ኃጢአተኛ አሳዳጊውን በየቀኑ የሚቀጣ፥
በሞኝነቱና በክፋቱ ተፈጥሮን የሚያስቆጣ።
ወይ ጉድ! እንዲህማ እኮ ነው፥ የሰው ልጅ እጅግ ሲመቸው፥
ወሰን ድንበሩን ለቆ፥ በገዛ ራሱ ነው ገደል የሚገባው።
ከችግር እንዲማር፥ ቅጣት በመጠኑ እየተሰጠው፥

ኑሮውን በራሱ እየታገለ ሲያሸንፍ ስናየው፥
በአንድ በኩል ሠልጥኗል፥ በሌላም በኩል ተበላሽቷል፤
በጦር መሳሪያ ግንባታ የገዛ መጥፊያውን አዘጋጅቷል፤
ሰውን እንደ እንስሳ ሲያጠፋበት ይታያል።
የተፈጥሮ ጣልቃ ገብነት ባይኖር፥
እስካሁን አንድም ሰው በምድር አይኖር።
ዕዝዬ እስቲ ተመልከት የተፈጥሮን ነገር፤
ተፈጥሮ ዙሪያዋ ክብ ናት፥ ባለ ሕግ እና ባለ አጥር፤
“አካላዊ ኃይልን” ሁሉ በራሷ እና ለራሷ የምታስቀር፤
አንተም በደንብ ሳይገባህ፥
አትበል ፈንጠር ፈንጠር፤
ተወስኗልና፥ የሰውና የምድር አብሮ መኖር።”

**ዕዝዬ**

“ከእንግዲህስ ጀሩዬ አድምጪኝ፥ ልንገርሽ፥
መልክ አውጥተሽ፥ በውሃና በቆዳ መሬት ሰውነትሽ፥
እንጨቱን፥ ሳር ቅጠሉን፥ አፈር ድንጋዩን ለብሰሽ፥
ሙቀትና ቅዝቃዜን አጋጭተሽ፥
የነፋስ ሽውታን ፈጥረሽ፥
በየቀኑ ገላሽን እየታጠብሽ፥
እንዲህ አምረሽና ደምቀሽ፥
የሕይወት አይነት በጉያሽ ሲርመሰመስብሽ፥
ሁሉን አብልተሽና አጠጥተሽ፥
በእናትነትሽ እንደተወደድሽና እንደተከበርሽ፥
በፍቅርና በአክብሮት  ስናይሽ፥
አንቺም ባለ ሕይወት ሆነሽ፥ ሰውን ስላሳደግሽ፥
ሕይወታችን አለማችን ተባልሽ።
ግን እስቲ በእውነት ምንሽ ነው አለም?

የከፋትሽ ብዛት ጸሐይ የሚያጨልም፥
የጥቁር ጪስ ጉም።
ልዩነቶቻችን ሲባባስ፥
ሥጋ ሲፈርስ
ወደ ላይ ስትወጣ ነፍስ፥
እስከ መቆረጥና መቆራረጥ ስንደርስ፤
“ምድር ሆይ ደህና ስንብች!” ብለን
የዛን ጊዜ ነው  ስንለያይ፥
በማንነታችን የምንተያይ።
ግን እስከዚያው እስቲ አስቢው!
በዋሻው፥ በጫካውና በሜዳው፥
በተራራውና በሸለቆው፥
ምንድነው ይህ ያንቺ መንፈስ፥
ሰውን የሚሸፍን በከፋት ልብስ።
ምድራዊነት ይቋረጣል፥ አካላዊነት ያረጃል፥
ሰብአዊነት ያለቅሳል፤
አብሮት የተጣበቀ መንፈስም ያዝናል።
ታዲያ ምንድነው ይህ ያንቺ የፍጥረትሽ ጠባይ?
ይህ አንቺ የኮራሽበት የኃጢአትሽ ጸበል፥
ፍጥረታትን በከፋት የሚበክል፥
ምንድነው ይህ በውስጣችን የተደበቀ፥
ግን በእውነት ከአንቺውና ያንቺው የሆነ፥
የልብሽ፥ የውስጥሽ የአንቺነትሽ ምስል።
እራስሽን (እውነተኛ ማንነትሽን) ደብቀሽ ከውስጥሽ፥
የይስሙላ ወሬ ብዙ አወራሽ።
አንቺ ውቢቷ ምድራችን፥  በቃ ስሚኝ ልንገርሽ፥
ብርሃን ባይፈስብሽ ጨለማ ነሽ፤
ጸሐይን ባትሞቂ ትበርጂያለሽ፤

ከአንቺው ከራስሽ የመጣ ምን ሕይወት አለሽ?
በሥጋሽም ሆነ በመንፈስሽ፥ ከውጭ ኃይል ተቀብለሽ፥
የራስሽ እያስመሰልሽ፥
ተመጻዳቂ የውሸት ቋት ነሽ (ልበልሽ?)"።

**ጀሩዬ**

"ሃ!..ሃ!..ሃ!.. አሁን ገና ገባሃ፥
እኔው በራሴ በማንም ላይ ምንም አለማድረሴን አወቅሃ።
"ከአንቺው ከራስሽ የመጣ ምን ሕይወት አለሽ?" በማለትህ፥
እኔም የበላይ አካል እንዳለብኝ ነው የተረዳህ።
አዎን! ከውጪ የመጣ ብርሃን ባይፈስብኝ ጨለማ ነኝ፤
አዎን! ጸሐይን ባልሞቅ በረዶ ነኝ፤
አዎን! ከእኔው ከራሴ የመጣ ምንም ሕይወት የለኝ።
ከእንግዲህስ ክርክሩ ይቁም፥
እርግማንማ የሰው ሥራ አይደለም፤
ተስፋ መቁረጥም በማንም አያምርም፤
ተከባብሮ መኖር ይሻላል ለሁሉም።
ሰው ሲቆረቁረኝ፥ ሲቦጠቡጠኝ፥
ከእኔው ከጉያዬ በሚወጣ ዘይት እያቃጠለ፥
በጢስ ሲያፍነኝ፥
አየሩን ሲያቆሽሽ፥ ውሃውንም ሲበክል፥
እኔ ያበቀልኩትን ሲያቃጥል፥..
ዕዝዬ፥ እስቲ ራስህ ንገረኝ፥
ማን አለ ታጋሽ እንደ መሬት?
ሁሉን ቻይ፥ የማትራገም፥ የማትቆጣ እናት።
ሰው በገዛ አልጋው ላይ ቢጸዳዳ፥ ወዴት ይሄዳል ሽታው?
ምድሪቷን የጎዳ ራሱንም እኮ ነው የሚጎዳው።
ቅድም የነገርኩህን ታሪክ አስታውስ፤

ሲነጋና ሲመሽ፥ አንድ ሴኮንድ ሳይቀንስ፥
በምድሪቷ ሕይወት ሲርመሰመስ፥
ሲፈጠር፥ ሲጠፋ እንዲሁም ሲፈጠር መቆየቱ፥
ይህ ለሥጋ ሰው አይገባውም ይሆናል ምክንያቱ።
ባለ አይምሮ ሰው ማሰብን ማን ከለከለው?
ምድሪቱን ላጥፋ ቢል ራሱን ነው የሚጎዳው።
ከጠፈር አካላት ሁሉ መካከል፥
ሕይወት በምድር የተዘራው፥
እንደ ባልና ሚስት ተከባብሮና ተፋቅሮ እንዲኖር ነው።
　　ከዚህ ሕግ የሚወጣ፥
　　አያመልጥም ሳይቀጣ።
ግን የዛሬውን የሕብረተሰብ ወይም የግለሰብ የተናጠል ቅጣት፥
ከጥንቱ ጋር አወዳድሮ ለተመለከተው፥
በቅጣቶች ብዛት የሰውን ሚዛናዊ መሆን፥
በሥጋም በመንፈም መራቀቀን ነው 'ሚያሳየው።
አሁን የሰው ሕይወት በራሱ በሰው ጥበብ ይመራል፤
ቅጣት ዘር እስከ ማጥፋት እንዳይደርስ በራሱ ይከላከላል፤
ይህም ሆኖ፥ አንዴ ይወድቃል፥ አንዴ ይነሳል፤
እየተቀጣ፥ ከጥፋቱም እየተማረ ከዚህ ደርሷል።
　　ከጥፋት ውሃ በኋላ፥ አለም አቀፍ ቅጣት አልተሰጠም፤
　　ዳግመኛም የጥፋት ውሃ አይመጣም፤
　　የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አይሻርም[41]።
ይህ የምታየው ቅጣት በቁጥ ቁጥ፥
ልክ አባት ልጁን እንደሚቆነጥጥ፤
በየሥፍራዎች አደጋ ቢደርስበት፥
አንዱ ከሌላው እንዲማርበት።

[41] ኦሪት ዘፍ. 9፡12-17

ፍጥረታት ቢጠፉ፥ በመጠነኛ የባህር ሽርሽር፥
ሞኝነት ነው፤ “ለምን ይህ ሁሉ ተፈጸመ?” ብሎ መከራከር።
ይህ በምድራችን የተዘራ ሕይወት፥
ከጠፈር ምድሮች መካከል፥
በደረቅ መሬት ላይ እንደ ወደቀች፥
እንደ አንዷት ቅንጣት የውሃ ጠብታ ይቆጠራል፤
ቁርጥርጡ ሰብአዊነት ይቀጥላል።
ምድሪቱ ስታደልብ ሥጋዊነትን፥
ስታጎለብት የሰውን ምድራዊነቱን፥
እርሷ ስለ ሰውና ኑሮው አላፊነት የለባትም፥
መንፈሳዊነቱን አትነካካውም፤
ሰው የራሱን ማንነት ከተፈጥሮ ይቅሰም፤
ተፈጥሮ ለሰብአዊነት እንጂ፥
ለግለሰብ አይጨነቅም፤
ግለሰብ ቢሞትም ሰብአዊነት አይሞትም፤
ስለዚህ፥ ልቅሶ ማብዛት አይገባም።
ከእንስሳት፥ ከዕጽዋት፥ ከሰዎችም፥
ብዙዎች ናቸው ያስተናገድናቸው፥
ነገር ግን እያንዳንዳቸው፥
ከድግሡ ቤት መቆያቸው፥
እጅግ አጫጭር ነው ዕድሜአቸው።
ስለዚህ፥ ጭንቀት ከማብዛት፥ ለዚህ ለምድራዊ ኑሮ፥
በሰላም አብሮ መኖር ይሻላል፥ ተዋዶና ተከባብሮ።
ወደ ላይ እንኳን ባይወጣ፥ የሰማይ ቤትም ባይኖር፥
ስንት ደስ የሚል ነገር ሞልቷል በዚህቺው ምድር፥
መጥፎው ሲወጣለትና ጥሩው ብቻ ሲቀር።
ክርክሩን ትቶ ጥሩውን ለሚያስብ፥
መፍትሔ አይጠፋም ለችግር።

የተፈጥሮ አደጋ የሚያጋጥማቸው፥
በጥናት ታውቋል፥
ውሱን መሆናቸውና ምክንያታቸው፥
ከነኚህ ሥፍራዎች ሸሽት ሸሽት ማለት ነው፥
ከክፉ አደጋ የሚያድነው።
የደሴትና የባህር ዳር ነዋሪዎች፥
በተፈጥሮ አደጋ በመቀጣታቸው፥
ለዚህም ይሆናል(?) አንዱ የጠባይ ቁንጅናቸው።
በተፈጥሮ በጣም ጥሩዎች ሆነው፥
በምድር ላይ መኖርም ለሚቸግራቸው፥
እግዚአብሔር ጽናቱን ይስጣቸው።
እስቲ ደግሞ ይህንን ልንገርህ ከገባህ፡-
ተፈጥሮ የተስተካከለ አለመሆኑን እያወቅህ፥
ዝብርቅርቆሽነትን እና አለመተንበይን፥
ፍጹማዊነትንም እንደሚያካትት እየተረዳህ፥
"ሕጻን ልጅ ለምን ቶሎ ይሞታል?.." ትላለህ።
እስቲ ተመልከተው፥
ያንተን ሕይወት ከሌላው ጋር ደምረህ፤
በተፈጥሮ ውስጥ ለብዙ ሺህ ዓመታት እንደኖርህ፥
ለወደፊትም ትኖራለህ።
ስለዚህ፥ ካለማገናዘብ ነውና ብሶትህ፥
ከእምነት ጉድለትም ነውና ቅሬታህ፥
ዑራኤል ለዕዝራ የነገረው በደንብ እስኪገባህ፥
በጾም በጸሎት ትጋ ሁሉን ነገር ትተህ።
ዕዝዬ ቅሬታህን ሰምቻለሁ፥
የራሴንም ጭካኔ አውቄዋለሁ፥
እኔም በመሰለኝ ለራሴ ፈርጃለሁ።
ግን የቁም ቅዠት ነው ተፈጥሮን እንፋረዳለን ማለት፥

ሃሳብ በማብዛት የሚመጣ ሞኝነት፤
ለሰው ልጅ ምንም አይነት ቅጣት ባይኖርበት፥
እስካሁን ሙሉ በሙሉ ይጠፋ ነበር በራሱ ክፋት።
ግን፥ መፈራረዱም፥ መተዛዘቡም ይቅር፥
ሁሉንም እንቀይረው ወደ ፍቅር፥
በቃ በመተዛዘን አብረን እንኑር።”

**<u>ከብዙ ጾምና ጸሎት በኋላ</u>**

**<u>ዕዝዬ</u>**
“ምንድነው ይህ የማይታይ ሰብአዊነት?
እንዴት ነው ኑሮ፥ እንዴት?
በሰብአዊነት ያይደለ፥ በአንድ ሰውነት፥
መጠነኛ ኑሮ ጭንቀት የሌለበት፥
በዚች ምድር፥ ፍቅረ ነዋይ በበዛበት፥
አድሎአዊነት በጸናበት።
አይ ምድር! ባንድ በኩል ቁንጅት፥
በሌላም በኩል ብልሽት።
በምድር ላይ መከራ ቢጸና፥
የጠመመው ሰብአዊነት እንዲቀና?
የግለሰቦች ምድራዊ ዕድል ፈንታ፥
ተወስኗል ‘ማይደል? በተወለዱበት ጊዜና ቦታ?
እንዴት ይሊያል የሰው (ግለሰብም ቢሉት ሰብአዊነት)፥
እንቀስቃሴው ከምድር እውነታ?
የኑሮና የኃጢአት መሥራት ግዴታ።
ምን አይነት ሰው ነው?
ከምድራዊ እውነታ ተለይቶ የሚኖር፥
ሰማያዊ ሰው ቢኖርስ እንዴት ነው፥

ከምድራዊነት ጋር የሚጣመር፥
ልቡንና አይምሮውን፥
በበጎ ሃሳብ ምልልስ ብቻ የሚያስተሳስር፥
ጊዜን በሃሳቡ የሚደመስስ፤
ያለፈውን የወደፊቱንም የሚኖር።
ደግሞስ ማነው እሱ ጸረ ሰው?
በሰው ሕይወት ሽር ጉድ የሚያበዛው፥
ሰውን ወደ ኃጢአት፥ ወደ ክፋት የሚገፋፋው።

የምናውቀውስ የማናውቀውን አይሸፍንም፤
ፈራ ተባ የሚያሰኝ የሰቀቀን ኑሮ አይመችም።
እግዚአብሔር ሁለት አለምን ፈጠረ እንጂ፥
አንድ አለምን ብቻ አልፈጠረም።
ታዲያ፥ ምንድነው የሰው ልጅ ተስፋ?
ጭራሽ መጥፋትን እንዳንጠፋ።

አሁንስ ገባኝ ልበል?
አዎ! እጅግ ደስ የሚለው አማራጩ ታውቋል፤
ዑራኤል ለዕዝራ ነግሮታል፤
“ለምን ትኩረታችሁ በምድር ላይ ብቻ ይውላል?
ለምንስ የሰማዩን አታዩትም?” ብሏል።

ሰዎች እየተያዩ እንዳይተዋወቁ፥
የማንነታቸውንም ምንጭ፥
የምድራዊነታቸውንም ባሕሬ እንዳይረዱ፥
የሆነ አዚም ከለላቸው፤
በቀዝቃዛ፥ በሞቃት፥ በሜዳ በገደላማ ሥፍራ፥
በጉራማይሌ አለም የሚኖር ሰው፥
እርስ በርስ እንዳይተዋወቅ ነው የሆነው።
ተስማምቶ፥ በአንድነት የሚኖርበት ሥፍራ ነው የታጣው።

ተፈጥሮ ዙሪያው ከብ፥

ባለ ሕግ፥ ባለ አጥር፥
ጠፊ ሥጋን ለራሱ ወስዶ፥
ሕያው ነፍስን የሚያባርር።
አካል ሥጋ አንድ ሳይቀር፥
ተመልሶ ምግብ እንዲሆን ለምድር፥
ይህ ከሆነ የሞት ምስጢር፥
ግን ከዚህ ሁሉ ባሻገር፥
ሌላ ጣግጭ ሕይወት ባይኖር፥
የሰው ኑሮው፥ ተስፋው፥ ቅዠቱና ሕልሙ ሲደመር፥
ከንቱ ልፋት ብቻ ሆኖ ይቀር ነበር።
ግን ከምድራችንም ጥሩነት መኖሩንም እናውቃለን፤
ታዲያ፥ የምድሩ ይመስላል ቢባል የሰማዩን፥
ጥሩው እጅግ በጣም ጥሩ ሲሆን።
በሕልም እንጂ በእውን እንደማይሰማ፥
እጅግ እንደሚማርክ እንደ ውዳሴው ዜማ።
በራዕይ እንጂ በእውን እንደማይታይ፥
መሠረቱ በጃስፐር፥ በካልሴዶኒ የጸና፥.. በከበረ ደንጋይ፥
አርያም፥ የንጹሕ ወርቅ ከተማ፥
የጠራ ብርጭቆ መሳይ[42]።

አንድ ጻዲቅ የሆነ ሰው፥
ጊዜአዊ ምድራዊ ደስታን ትቶ፥
ዘለአለማዊ ሃሴትን ሽቶ፥
በጾም በጸሎት ራሱን ሲያደክም፥
በሕያዊት ነፍሱ ሲንቀሳቀስ፥
በምድሪቱ ቆየባት እንጂ አልኖረባትም።

[42] ዮሐ. ራዕይ 21፡18 - 19

መሰናበቻ ጊዜውም ሲደርስ፥
እርሱ ወደ ላይ ይወጣል፤
ግን፥ በምድር ቋንቋ "ሞተ - በድን ሬሳ ሆነ" ይባላል።
        እኛም ከዚህ ምድሪቱን ሳይሆን የገዛ ሕይወታችንን ነው የበላነው፤
        ከሰፊው ባሕር ተቀድተን፥
        ቀስ በቀስ ነው የምናልቀው፤
        ከዚያስ ከሰማይ ቤት፥
        ሁሉም እንደ ብጤው፥
        ለሁሉም እንደየሥራው፥
        ከዚያ ነው፥ ሁሉም ደመቅመቅ የሚለው።
        በምድር ካለው በሰማይ ያለው ነው የሚበልጠው።
ስለዚህ  በምድር ተቆርጦ የሚቀረው፥
ይህ ሰው (መንፈሳዊ) እራሱን በርቀት እንዲያስተውለው፥
ምድሪቱ ትምህርት ቤት ትሁነው።
ከዚህ ተሰደን ወደዚያ፥
እስክንሻገር ወደ ጻድቃን - ወደ መላእክት መናኸሪያ፥
በምድራዊ ኑሮ እየተጨነቅን፥
በሃሳብ ጨለማ ከመባዘን፥
ቆይታችን በምድር እጅግ ቀለል እንዲል፥
የክርስቶስን ምክር በጥሞና እንከተል[43]፥
በጎደለውም ሞልቶ እንዲሰጠን፥
"እንፈልግ የእግዚአብሔር መንግሥቱን፥
ከሁሉ አስቀድመን፥ ጽድቁን[44]።"

---

[43] ማቴ. 6፡25 - መጨረሻ

[44] ማቴ. 6፡33

# ምዕራፍ አራት

## የደረጃና የጨረቃ ውይይት



ደረጃ እና ጨረቃ

**መግቢያ**

በኑሮው የሚደከም ለሌላው፥
ምንም ቢሆን ምን - ማንም ሰው የሚሠራው - ሥራው
ከራሱ አልፎ ለሌሎች የሚያደርገው፥
ብርታትና ጤንነት ሲሰጠው፥
ፍቅር፥ ብርሃን፥ ደስታ ሲሆን ነው የምናየው።
ለዚህ ምሳሌዎች ብዙዎች ናቸው፤
ከነርሱም መካከል ደረጀ አንዱ ነው።

ደረጀ ችግር፥ መከራ ቢጸናበት፥
ኑሮ ካቅሙ በላይ ቢሆንበት፥
በሃሳቡ ራሱን ጥሎ ሰማይ ወጣ፤
ጨረቃን በመንፈሱ (በሃሳቡ) ቀረባት፤
ጭንቀቱን፥ ብሶቱን ነገራት፤
መፍትሔ ያገኝ መስሎት።

እስቲ እንስማው፥ የደረጀን ስሜቱን፤
ድካሙንም ሆነ ብርታቱን፤
ከጨረቃ ጋር ውይይቱን።

**ደረጀ**

"ዛኒጋባ - ባለ አንድ ክፍል ቤት፥
ባለ አንድ በርና ባለ አንድ መስኮት፥
ዙሪያው ምርጊት፥
መጋረጃም የሌለበት፥
ሥራ ውዬ በጨለማ የምገባበት፥
ጎህ ሳይቀድ በጨለማ የምወጣበት፥
ድከም ሲለኝ የምተኛበት።

ከእለታት በአንድ ቀን፥ ከወትሮው ደክሜአለሁ፤
ከቤቴም እንደገባሁ፥
ሳላስበው መሬት ላይ ወድቄአለሁ።
ድካሜም እንደጠፋ፥
ከባድ እንቅልፍ ውስዶኝ ሳለሁ፥
ድንገት ከእንቅልፌ ነቃሁ፤
ከዚያም፥ በመስኮቱ በገባ ብርሃን ተደናገጥሁ፤

የቀሰቀሰችኝ ጨረቃ መሆኗንም አላወቅሁ፤
ጣደፍ፥ ጣደፍ ብዬ ተነሳሁ።
እኔ የፋብሪካ ሠራተኛ፥ ጸሐይን የረሳኋት፥
ሥራ የምገባው ጸሐይ ሳትወጣ፥ በጧት፤
ከሥራ የምገባው ጸሐይ ስትጠልቅ በምሽት፤
ጨረቃ ቤቴን በብርሃኗ ጮራ ሞልታበት፥
ደስ የሚል ብርሃን ቤቴን ድምቅምቅ አድርጎት፥
ቆየት ብዬ እንኳን ሳልደሰትበት፥
የረፈደብኝ መስሎኝ ስርበተበት፥
ልብሴን ለብሼ፥ ቁርሴን ሳልበላ ከቤቴ ወጣሁኝ፤
ወደ ሥራ ቦታ - ወደ ፋብሪካዬ ገሰገስኩኝ።
ከመንገዱ አንድም የረፈደበት ላብ አደር አላየሁኝ፤
ላሊበላዎች፥ የኔ ብጤዎች ከአይኔ ጠፋብኝ፤
አልፎ አልፎ ሬሳ ከመንገድ ላይ ሲታየኝ፥
መንግሥት እስረኞችን ከእስር ቤት እያወጣ፥
ድሆች፥ መንገድ አዳሪዎችንም እየሰበሰበ፥
በስብሰው እንዲተሉ፥
ገድሎ ገድሎ የተዋቸው መሰለኝ፤
ይልቅስ እኔ ወደ ሥራዬ ልገስግስ፥
“እኔ ምናገባኝ?.. አለቃዬ እንዳይቆጣኝ፤
ደምወዜንም እንዳይቆርጥብኝ”
ብዬ ገሰገስኩኝ።
እንደምንም ከሥራ ቦታዬ ደረስኩኝ፤
ግን ከዚያም አንድም ሰው አላየሁኝ፤
ከተዘጋው የፋብሪካ በር፥
ጨለምለም ካለው - ከጣሪያው ከፈፍ ሥር፥
እንደ ጅብራ ግትር ብዬ ቆምኩኝ፣
ከወዲያ ማዶም ሰው ተኝቶ ታየኝ፣
አዬ! ዘበኛውንም መንግሥት ገድሎታል አልኩኝ።
ግን ጆሮዬን ምን አደነቆረኝ?
ለምንድነው የፋብሪካ ድምጽ የማያሰማኝ?
እጅግ ግራ ገባኝ፥ ከነከነኝ፤
የማየው ሁሉ እንደ ሕልም ሆነብኝ።

ከዚያ ማዶ፥ ጨረቃ ገላጣውን ሜዳ በብርሃኗ አሳምራዋለች፤
በወርቅና በብር እንዳጌጡ ሙሽራዎች፥
አሽብርቀው ይታያሉ፥ ቁጥቋጦዎችና ሳሮች፤
ሳላስበው እግሬ ወደ ሜዳው ወሰደኝ፤
አንገቴም እራሴን ወደ ሰማይ አቀናብኝ፤
ጨረቃ ጸሐይን መስላ፥
ከወትሮው እጅግ ተልቃ፥
እጅግም ደምቃ ታየችኝ፤
በአናቴ ትይዩ እጅግ ቀርባኝ፥
ጸሐይን በተሲአት ያየኋት ነበር የመሰለኝ፤
ፈዝዤ ቀረሁ፥ ጨረቃ መሆኗን ማመን አቅቶኝ፤
ትንሽ ቆይቶም ሁሉ ነገር ዝብርቅርቅ ሲልብኝ፥
"እኔ ማነኝ?" ብዬ እራሴን በአንክሮ ጠየቅሁኝ።
ገና ሳልሞት፥ ሥጋና መንፈስ ሳልሆን ተከፍዬ፥
እኔ እኔን መሆን ተሳነኝ፥ በሁለትነት ጠባዬ።
ብርሃኔ ሲያበራልኝ፥ ጨለማዬ ዋጠኝ፤
ከፍታዬ ሲያሳድገኝ፥ ዝቅታዬ ቀበረኝ፤
ደግ ደጉን ሲያስመኘኝ፥ ክፉ ክፉው አጠረኝ፤
በጎ ፈቃዴ ሲያስሮጠኝ፥ እድል ፈንታዬ አስሮ ያዘኝ፤
ጥሩነቴ ወደፊት ሲገፋኝ፥ መጥፎነቴ ወደኋላ ጎተተኝ፤
አዎንታዊነቴ ሲያመቻቸኝ፥ አሉታዊነቴ ቆረቆረኝ፤
መልካም ምግባሬ ሲያስደስተኝ፥ መጥፎ ሥራዬ ጸጸተኝ፤
አንዱ ጎኔ ሲክበኝ፥ ሌላው ጎኔ አሳነሰኝ፤
አንዱ ጎኔ ሲያሞግሰኝ፥ ሌላው ጎኔ አሟረተብኝ፤
በሁለት አቅጣጫ ተወጥሬ፥ ማንነቴ ጠፋኝ።
በእውነት እኔ ማነኝ? በእውነት እኔ ማነኝ?
ማንነቱ ያፈነገጠ ከሰው፤
ሕይወት አልሰምር ካለው፥
በልቶ ጠግቦ ደስ ካላለው፥
የኑሮ አለመረጋጋት ካበሳጨው፥
መምሰል ብቻ ይሆናል እውነታው፤
ይጣመማል አቅጣጪያው፤
ይወላገዳል ጉዞው፤

ከራሱም ጋር መሆን ያቅተዋል፤
እሱነቱን ጥሎ መሄድ ያሰኘዋል።
ሰውና ሃሳቡ፥ ምኞቱ፥ ሕልሙ፥ ቅዠቱ፥
እውነታው፥ እምነቱና ሃይማኖቱ፥
ሁሉም መምሰል፥ መምሰል ብቻ፥
ተለዋዋጭ ምስል እንደ ዳመና፥
የማይለይ እሱነቱ፤
ጀርባውና ፊቱ።
እንስሳት ሁሉ፥ እጽዋትም፥
አካላውያን፥ ነፍስ ያላቸው፥ የሌላቸውም፥
ሁሉም ተደማምረው፥ እኔኑ መስለው፥
“ሁላችንም አንድ ነን፥ ሁላችንም አንድ ነን” ሲሉ ሰማኋቸው።
“ሕልውናችን በጠፈራዊ ሕግጋት ተደንግጓል፤
መሠረታዊ፥ ውስጣዊ ኃይል ይመራናል፤
ከማንመለስበት እየነጠቀ ይወስደናል...” የሚሉ ይመስለኛል።
እኔም ልሂዳ! ልደመር ከሌሎቹ፥
ላይቀርልኝ ውህደቱ፤
ልሂድ ራሴን ለቅቄ፥
ከራሴ (ከሥጋዬ) ተነጥዬ፥
ጨረቃን ላናግራት፥
ሰማይ ላይ ተንጠልጥዬ።
ቁንጅናዋን ልግለጽላት፥
በቋንቋዋ፥ በቋንቋዬ።
ቆይ ወደዚያ ራመድ ልበል፥ ነጣ ካለው ሥፍራ፥
ከዚያ ሄጄ ላውራ፤
ምንጊዜም ከማፈቅራት ከጨረቃ ጋራ።
ጨረቃ፥ የጸሐይ ታናሽ ልጅ፥ የእኔም አገልጋዬ፤
ጨለማዬን የምትገፊ ከላዬ፤
በሁለመናሽ አምረሽ ደምቀሽ ከበላዬ፥
ምን ብዬ ልጥራሽ፥ ትዝታዬ?.
ያልተለየሺኝ ከልጅነቴ፥
አንቺኮ ነሽ ዘመዴ፤
እህቴ ልበልሽ እናቴ?

አቤት ውበትሽ፥ ቁንጅናሽ፥
ይማርካል ሽጋው ጠባይሽ፥
ትእግስተኛነትሽና ፍቅርሽ፤
ረድኤትሽ የሚበቃ ለአለም፥
ድምቀትሽ ፍቅር፥ ብርሃንሽም ሰላም፤
እኔስ ደስ የሚለኝ፥ ካንቺ ጋር ጨዋታ፥
ሁሉን ያስረሳኛል፥ ይሰጠኛል ደስታ።
እስቲ ዛሬ አናግሪኝ፥ ላናግርሽ፥
በመንፈስ ቆሜአለሁ ከፊትሽ።”

**<u>ጨረቃ</u>**
“እህቴ ልበልሽ እናቴ ላልከው፥ በስሜ ላይ ዬን ጨምረህ ጨረቃዬ በለኝ፥
እኔም ላብአደርዬ ብዬ እጠራሃለሁኝ።
ወዝ አደር ብዬ እንዳልጠራህ ወዝ የለህ፥
ላብአደር ብዬ ነው የምጠራህ።
ግን ማልልኝ ከሁሉ አስቀድመህ፥
በራሴ ፈቃድና ኃይል እንዳልሆነ የማናግርህ።
ወደ ፍጡራን ማሕበር በመንፈሱ ለሚዘምት፥
ከጎታቹ ሥጋ ተገንጥሎ በሃሳቡ ለሚዋትት፥
ጠፈር ክፍት ስለሆነ ይገባበታል፥
ሁሉም እንደ ደረጃው ይስተናገዳል፤
ያንተም ወደኔ መቅረብ፥ የኔም አንተን ማስተናገድ፥
ለዚሁ ይመስለኛል።
ስለዚህ እሰማሃለሁ፤
ቀጥል።”

**<u>ደረጀ</u>**
“እሺ፥ ስለምወድሽ ጨረቃዬ ብዬ ነው የምጠራሽ፤
መማሉንም ስሚኝ ስምልልሽ፥
“እውነት እውነት ነው የምልሽ፥
ያንቺ እንዳልሆነ አምናለሁ እስትንፋስሽ።”
እኔስ መች የኔ፥ ለኔ ሆንኩ ብለሽ!
ሥጋ ሰውነቴን መሬት ትቼ፥

በሃሳብ መጥቄ፥ በስሜቴ፥ በመንፈሴ ተነጥቄ፥
እዚህ ተገትሬ፥ ከፊት ለፊትሽ፥
ስለ ጭንቀቴ ሳዋይሽ።
ግን፥ ምነው፥ ምነው ጨረቃዬ፥..... ጉድ እኮ አደረግሺኝ!
ከላብ አደርነት እንድታወጪኝ፥
ወይንም መውጪያ መንገዱን እንድትመክሪኝ፥
ልለምንሽ ስቃጣ፥ አንቺም በችሎታሽ እንድትመሪኝ፥
የሆዴን አውቀሽ ቀደምሺኝ፥ ላብ አደር አልሺኝ።
ለላብ አደርነርነት አልተፈጠርኩኝ፤
እስቲ ምናለበት ሌላ ስም ብታወጪልኝ።
ጨረቃዬ ስሚኝ፤
እባክሽ ታደጊኝ፤
እድል ፈንታዬን ቀይሺልኝ፤
ከላብ አደርነት አውጪኝ፤
እናትሽ ጸሐይ ናፈቀችኝ፤
ጸሐይን በጧት በረፋዱም የሚያሳየኝ፥
ሳትጠልቅ ወደቤት የሚያስገባኝ፥
እባክሽ!...ሌላ ሥራ ፈልጊልኝ።”

<u>ጨረቃዬ</u>
“ኸረ አንተ ዝም በል!
ዙሪያህን የከበቡህ ይሰሙሃል፤
ከመቼ ወዲህ ነው፥ ለሰው ሥራ ፈላጊ የሆንኩት?
ካለ ምክንያት ይመስልሃል ከሰው የራቅሁት?
በምድርና በጸሐይ መካከል የተንጠለጠልኩት።
ይልቅስ ላብ አደርዬ መባሉን ከጠላህ፥
ደረጅዬ ብዬ ልጥራህ።
ግን፥ አስቀድሜ ልንገርህ፥ እኔ ምንም ችሎታ እንደሌለኝ፥
ሥራዬን ትቼ መውጣት አልችልም፥ ተደንግጎ ከተሰጠኝ።”

<u>ደረጅዬ</u>
“ጨረቃዬ፥ አልረሳውም፥ ከልጅነት እስከ እውቀት የሚታየኝን፥
በመላው ሰውነትሽ የተሳለውን።

ተራሮችሽ ተጠጋግተው፥
ባንድ በኩል ተቀምጠው፥
እርስ በርሳቸው ተቃቅፈው፥
ሜዳ ከፊትለፊታቸው፥
በእውነት ፍቅርን የሚገልጽ ምስል ነው፥
እኔ አንቺን ሳይ በውስጥሽ የማየው።
እንጃ! እኔ ምን ለበል?
ፈራሁ፥ ቀባጣሪ እንዳልባል፥
ግን፥ ምስሉን፥ የማርያምንና የልጇን፥
አልሰርዘውም፥ አላጠፋውም፥
የሚመስለኝን፥
በአካላዊ ቁመናሽ የማየውን፥
መንፈሳዊ ገጽታ የሚሰርጸውን።
ያንቺ ሥራማ በጥቅሉ ሁለት፤
ምድርን መዞርና ብርሃን መርጨት።
ግን ተነግሮ አያልቅም ያንቺ የመኖርሽ በረከት፣
በላያችን ከሚፈሰው ብርሃንሽ የምናገኘው ምቾት።
ሰውን በሚያስደሰት ችሎታሽ፥
ከላይ በምታዘንቢው ብርሃንሽ፥
ይኸው እያናገርሺኝ እየሰማሁሽ፥
እኔ ምን ችሎታ አለኝ ትዩኛለሽ?
ጨረቃዬ፥ ችሎታም ባይኖርሽ፥
አንቺ ቆንጆ፥ የሰማይ ዳቦ፥
ከእግዚአብሔር ምስክሮች አንዷ ነሽ፤
የአንድዬ ድንቅ ሥራው የሚገለጥብሽ።
ነፍስ አልባ ብትሆኚ፥ አክሲጂን ባይኖር በዙሪያሽ፥
የጠፈር አካላት (ሜቲዎሮች) ቢረጋግጡሽ፥
እሳተ ገሞራ ቢፈላ ከሆድሽ፥
የመጠቃት ምልክቶች (ጉርጓዶች)፥
በምልአት ቢታዩብሽ፥ በቆዳ መሬትሽ፥
ውሃ ባይኖርሽ የሚያቀዘቅዝሽ፥
አይዞሽ፥ አይዞሽ፤
እንዲሁም ሆነሽ፥ እፁብ ድንቅ ነው ግሊጋሎትሽ።

በተቀረው ከመሬት ይወዳደራል ሁለመናሽ፥
በማዕድናት የከበርሽ፥
በአሉሚና፥ በአዛሂትና፥ በብረት ያጌጥሽ፥
በቲታኒዩም እና በክሮሚዩም የከበርሽ።
 በሌላም ማንነትሽን በሚገልጽ፥
 በታላቁ የስበት ባህርይሽ፥
 የምድራችንን ውሃዎች እያናወጥሽ፥
 የባህሮችን ውሃዎች እየገፋሽ፥
 ማእበል እያስነሳሽ፥.....
 ከቶ ማን ይዘነጋዋል ያንቺን ኃያልነት፥
 ከመሃይም እስከ ሳይንቲስት።
 በስበት ኃይልሽም ሆነ በብርሃንሽ፥
 ሙሉ በሙሉ፥ በግማሹ ወይንም በሩቡ ለምናይሽ፥
 በሰዎች ላይ ተጽናኦ የምታሳድሪ 'ማይደለሽ?
 የአይምሮና የስነ ልቦናን ማንነታችንን እየነካካሽ።
በሰባት መቶ ስምንት ሰዓታት ዙረትሽ፥
በከፊልም ሆነ በምልአት እየሳቅሽ፤
የሰዎችን እድል ፈንታ የምትቀይሺ፥ አንቺ 'ማይደለሽ?
ለሰው ሁሉ ባይገለጡ ምሥጢራትሽ፥
የቡድሃ ሊቃውንት እስኪያምኑብሽ፥
በተአምራታዊ ድርጊቶችሽ፥
ተስፋችን ነሽ እኮ፥ ይመቸናል መኖርሽ፤
እኔንስ ማርኮኛል ሕልውናሽ።
ይልቅስ በዪኝ፥ አናግሪኝ፥ ንገሪኝ፤
ጸሐይ ሳትወጣብኝ።
 እኔና አንቺ ዛሬ አንላቀቅም፥
 ቁርጤን ሳላውቅ ርቄ አልሄድም።
እስቲ በቅጡ አዳምጪኝ፤
እጅግ ጭንቅ ነው ያለኝ፤
ቆንጆ ሥራ አሰጪኝ፤
እኔ ዛሬ ከዚህ ብቆይ፥ ለማየት ጸሐይን፥
ታውቂዋለሽ ሥራ ፈት ሆኜ መቅረቴን።
አንቺው ራስሽ፥ ከእንቅልፌ እስክነቃ ቀስቅሰሽ፥

ብርሃንሽን ከቤቴ አፍስሰሽ፥ አፍስሰሽ፤...
ኸረ እባክሽ፥ አታሳፍሪኝ ባክሽ፤
ካለ ዛሬም አልለመንኩሽ፤
እባክሽ አንድ በዪኝ፥
ተስፋ ሰጥተሽ ቶሎ ሸኚኝ።"

**<u>ጨረቃዬ</u>**
"እና ምን ይሁን ነው የምትለው ደረጃዬ?
ልታጣላኝ ፈለግህ እንዴ! ከፈጣሪዬ።"

**<u>ደረጃዬ</u>**
"አላጣላሽም ከፈጣሪሽ፥ ከፈጣሪዬ፥
እርጂኝ፥ ታደጊኝ ነው ልመናዬ፥
ሥጋዊነቴን ከመሬት ላይ፥ ልቤን ላንቺ ጥዬ፥
የምታዪኝ በሰብአዊ - መንፈሳዊ ህልውናዬ፥
እኔምኮ አንቺን ነኝ፥ እምዬ።
እንደ ጓደኛሽ ቁጠሪኝ፤
እዪኝ ተመልከቺኝ፤
ጨረቃዬ አናግሪኝ፤ ጸሐይ ሳትወጣብኝ።
እግዚአብሔርስ፥ ገና ሳላናገረው ነው የሚሰማኝ፤
ግን ሰምቶ ችሮታው ራቀብኝ።
እባክሽ ጆሮሽን ከፍተሽ ብሶቴን ስሚልኝ፤
እባክሽ እንረዳዳ፥ እርሱም ስንረዳዳ ይየን፤
ሲጥር፥ ሲግር ማየት ደስ ይለዋል አባት ልጁን፥
ሁላችንም የእግዚአብሔር ምስክሮች ነን።
አንቺን ግዑዝ አካል ብለው ቢጠሩሽ፥
በውጪያዊ አካልሽ፥
ሳር አልባ፥ ሜዳዎችሽ፥
ወይም እሳት ወለድ ተራሮችሽ፥
አንቺም እኮ ውስጣዊ ሕሊና አለሽ፤
በተፈጥሮአዊ ሕግጋት የሚያንቀሳቅስሽ።
"ይሁን" የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል ስለሰማሽ፥
አንቺንም ጠፈራዊ ሕሊና ገዛሽ፣

እናም፥ ይኸው እስከዛሬ ድረስ አለሽ፥
ምድሪቱን እየዞርሽ፥
በራስሽም ዙሪያ እየተሽከረከርሽ።
እስቲ ልጠይቅሽ፥
"ይሁን" የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል፥
ከሆድሽ ማውጣት ትችዪአለሽ?
እርሱ 'ማይደል ነፍስሽ፥ ሕይወትሽ፥ የሚያንቀሳቅስሽ?
ታዲያ እኔስ ምናለበት? ብጋራ የውስጥሽን፥
ያንን የማይሻረውን፥ የማይለወጠውን፥
ቃሉን፥ "ይሁን" የሚለውን።"

**<u>ጨረቃዬ</u>**

"ደረጅዬ፥ ይገርመኛል የረቀቀው ፍልስፍናህ፤
ግን፥ አንተ ከምድራዊነትህ ተላቀህ፥
ስታናግረኝ በመንፈሳዊው ሕልውናህ፥
ሁለንተናዊ፥ ጠፈራዊ ሕግጋትን ዘነጋህ?
አካላዊ ፍጡራን ቢወጡ ከራሳቸው፥
ሕሊናቸው ብቻ ቢሆን ሕልውናቸው፥
ገዢና ተገዢ ባይኖር በውስጣቸው፥
ሁሉም እየለቀቁ ቢሄዱ እንዳሻቸው፥
ደረጅዬ፥ ትርምስምሱን እስቲ አስበው።
ይህ እንዳይሆን፥
እኛ የእግዚአብሔር ፍጡራን፥
በጠፈራዊ ሕግጋት ተገዛን፤
ስለዚህ እያንዳንዳችን እንኖራለን፥
ውስጠ ጠባያችንን ከሰውነታችን እያጣጣምን።

> አንተ ግን ከአቅምህ በላይ ተንፈራገጥህ፤
> ውስጣዊና ውጪያዊ ጠባዮችህ ቢቃረኑብህ፥
> ከራስህ ውጥተህ ወደኔ መጣህ፥
> ይልቅስ ተመለስ፥ ከኔ ጋራ ወሬ ይቅርብህ።
> ሂድ ወደ ሥራህ፥ ጸሐዩቱ ሳትወጣብህ።"

**ደረጀዬ**

"ጨረቃዬ እወድሻለሁ፤
ሰምቼሻለሁ፤ እሺ በቃ! እሄዳለሁ።
ግን ከዚያ በፊት፥
ብሶቴን፥ ስሜቴን እንድትሰሚኝ እለምንሻለሁ፤
ጸሐዩቱ ሳትወጣብኝ ጣደፍ፥ ጣደፍ ብዬ አወራለሁ።"

**ጨረቃዬ**

"ደረጀዬ፥ እንደምትወደኝ አውቃለሁ፤
በል ተናገር እሰማሃለሁ፤
ሆድ እንደባሰህ ተረድቻለሁ።

**ደረጀዬ**

"ይኸውልሽ ጨረቃዬ! የከባድ መኪና ሹፌር፥
እጅግ ደግ ነበረ አባታችን፤
ቀጥ አድርጎ ያስተዳደረ፥ ቤተሰቡን እንዲሁም ዘመዶቹን።
ከእለታት አንድ ቀን፥
መኪናው ተገለበጠ፥ አባታችንም ሄደ ጥሎን፤
ገንዘብ ሲያልቅብን፥ ረሃብ ገባ ከቤታችን፥
እናታችንም ታመመቺብን።

ደስ የሚል ኑሮ በትውስታ፥
ወይም በወደፊት ተስፋ፥
ለስላሳው ልባችን በችግር ሲበሳ፥
ደስታ ሹልክ ብሎ ከቤታችን ጠፋ።
ከዚህ ነው የጀመረው፥ የኔ አዲስ ሕይወት፥
ከትምህርት ቤት ወጥቼ፥ ልብስ ሠፊ የሆንኩበት።
እናቴን ለማስታመም፥ ወንድሞቼንና እህቶቼንም ለማስተማር፥
ለዚህ ነው የሁለት ሰው ሥራ የያዝኩት።

ዋጋው ከፍ ቢልም፥ ሲሸጥ የምሰፋው ጃኬት፥
ደሞዜ ትንሽ ስለሆነ፥ እጅግ አስጨነቀኝ የኑሮ ውድነት።
የሚወጣው ወጪ፥ ለምግብ እና ለእናቴ መድኃኒት፥
ለልጆቹ መንከባከቢያ፥ እንዲቆዩልኝ ከትምህርት ቤት፥
ሁሉም በኔ ሥራ፥ አስራ ሁለት ሰዓት፤

የማይለወጥ ከዓመት ዓመት፤
ኑሮዬ ወደ ታች የሚያድግ፥ መሻሻል የሌለበት።
ወትትና ሥጋ በዓመት በአል፥
አንድ ቀን ዘይትና ቅባት ሳናይ፤
ሰርክ ጾም - እህል በእህል፥
ማሽላ፥ አተርና ምስር፥
ቆዳችን እስኪመስል ደረቅ አፈር።
በኢትዮጵያችን፥ በድሆች መንደር፥
በከተማም ቢሆን በባላገር፥
ከቆሙት በታች፥ ከሞቱት በላይ ከመንገራገር፥
ሕመምና ስቃይ የሌለበት፥ ሞት ይሻለን ነበር።
እህ!........ተመስገን ልበል፥ ተመስገን፥.... ከችግሮች ሁሉ ባሻገር፥
እስከዛሬ አልደፈረኝም እብደት፥
ከአንጎሌ አልተለየም ንቃት፥
ከሥራዬም አላነሰም ጥራት።
ግን እስቲ ተመልከቺኝ ጨረቃዬ፥
ብጣሽ ጨርቅን ከብጣሽ ጨርቅ ማገናኘት ሥራዬ፥
አስራ ሁለት ሰዓት አቀርቅሬ፥
ከልብስ መስፊያ መኪናዬ፥
ትዳር አለምን ሳላይ፥ ነጎደ እኮ እድሜዬ!......
ለሰለሰ ጡንቻዬ፤
በላዬ ላይ አለቀ ሥጋዬ፥
ከአጥንቴ ተጣበቀ ቆዳዬ፤
ተጣመመ አንገቴ፥ ጎበጠ ጀርባዬ፣
ተጨማደደ ፊቴ፥ ቆሳሰለ ገላዬ፤
ወደ ሕመም ተለወጠ ጤናዬ።
ኑሮዬ እንዳይሆንብኝ ቅዠት፥
ዘወትር የምሰማው ቸክ፥ ቸክ፥
ተኝቼም በእንቅልፌ ቸክ፥ ቸክ፥
የማይለቀኝ የልብስ መኪናው ጩኸት።
ከሮች ብቅ ጥልቅ የሚሉት፥
አይኖቼን አፈዘዙት፤
አይምሮዬንም አሰለቹት፤

የሚሽሎኮለኩ፥
መርፌ በሚበሳሳቸው ጨርቆች፥
በሥራ ቦታ ክሮች፥ ቤቴ ስገባም ክሮች፥
አይምሮዬን የሚወስዉሱ ሃሳቦች፤
እኔ እንዴት ልላቀቅ፥ ከማያሻሽሉኝ ባላጋሮች።
መርፌና ክር የማይጠግቡ ደሜን ጠጥተው፥
እነሱኑ አስመሰሉኝ፥ አክስተው፥ አክስተው፣
እኔ ፈርቼአለሁ፥ እራሴን እንዳልስተው።
እኔ እንዴት ልለውጠው፥ እድል ፈንታዬን?
እንዴት ልጠግነው፥ የከሳው ሰውነቴን?
እንዴት ልመልሰው፥ የጠፋው ጤንነቴን።
እኔም እንደሰዉ፥ እንድመስል ሰውን፥
በረፋዱ ከቤቱ ውጥቶ፥ በጊዜ የሚገባውን፥
ይህ ምኞቴ፥ እንዲሆንልኝ እውን፥
ለዚህ እኮ ነው! ጨረቃዬ ያ...ንቺን ልመና የተመኘሁት፤
በችሎታሽ እርጂኝ ያልኩት።
ግን ይህም ከተቆጠረ እንደ ቅዠት፥
አንቺንም እንደራሴ ቆጥሬ ስለደፈርኩሽ፥
ይቅር በዪኝ እባክሽ፥ አይለየኝ ፍቅርሽ።”

**ጨረቃዬ**

“ደረጅዬ በጣም ተጨነቀሃል፤
በምድራዊ ምሬቶችህም ብዛት እንደ ታማሚ ሆነሃል፤
መቼ ባንተ ብቻ ተወሰነ ይህ ችግር፥
የሰው ልጅ ማህበራዊ ኑሮው ቢቀያየር፥
መጥፎው የሰው ጠባይ አልጠፋም ከምድር።
ሰው አላወቀበት፥ ተቻችሎ መኖርን፥
እንደሚፋቀሩ ባልና ሚስት፥ አብሮ መሥራትን፤
አልገባውም ጣዕሙን፥ የጋርዮሽ ኑሮን፥
እንደ ኮሙኒስት፥ እኩልነትን።
ባሪያ መሸጥ፥ ጭሰኛና ባላባት፥
አሽከርና ጌታ ከጥንት እንደነበር፥
አገልጋይ ተገልጋይ፥ አሁንም እንዳይቀር፥.

በጋርዮሽም፥ ቢሆን በባርያ ስርአት፥
በባላባትም ቢሆን    በካፒታሊስት፥
ክፉት ሲሠራበት፥
በገንዘብ፥ በጉልበትና በብልጠት፥
ትላንትና እንደነበረ፥ ዛሬም አለ ስግብግብነት፥
የጥቂቶች አለም፥  በብዙኃን ጥረት።
አዬ!  አዬ!  አዬ!
ሰው ሞኝ እኮ ነው፥  መጪውን አያውቅ፤
በልቶ የማይጠግብ፥ ከሌለው የሚነጥቅ።
በጠፈር ነጠብጣቦች መካከል፥ ታናናሽ ነጠብጣቦች፥
እናንት ሰዎች፥
በጥበብ እጅግ ልቃችሁ የምትመጥቁ ባለ ነፍስ ጠብታዎች፥
በመካከላችሁ ሰርገው ቢሰገሰጉም መጥፎዎች፣
ተመክሮ፥ ጦርነትም የማይመልሳቸው ሰይጣናሞች፥
በነርሱ ምድሪቱ ስትጠፉ ጠፊዎች፥
መጪው ግን ጥሩ ይሆናል፥  ለናንተ ለጥሩዎች።
ደረጀዬ እወድሃለሁ፤
ችግርህን ተረድቼአለሁ፣
ልመናህንም ሰምቼአለሁ፤
ጽናት ብርታቱን እንዲሰጥህ እጸልያለሁ፤
ግን አንድ ነገር እንድትረዳልኝ እፈልጋለሁ።
እኛ የጠፈር አካላት የምንዞርበት ዑደት አለን፤
የትም አንሄድ ከርሱ ፈቃድ ወጥተን።
አዎ!  ሁላችን የፈጣሪያችን ምስክሮች ነን፣
እኔ መሬትን ብቻ ነው የምዞረው፤
መላው ጠፈር ከኔ ጭምር ሁሉም ዘዋሪ ነው፤
ቁሙ ሲለን ነው የምንቆመው።
እኔን፥  የአለም ሕዝብ እያንጋጠጠ ያየኛል፥
ማየት ብቻውን ሲሆን አይን ያፈዛል፥
ተስፋም ያስቆርጣል፤
በመንፈስ አርቅቆ መሄድ ልብን ያበራል፤
ለሚያስተውል፥ ጨለማው ብርሃን ይሆናል።
ራስ ወዳድነት አላስኖር ሲል፥

የብዙሃን ጩኸት ሲያይል፥
ሰው ባልጠበቀው መንገድ እግዚአብሔር ይፈርዳል።
ለሁሉም እንደየሥራው ይሰጠዋል።
ደረጀዬ፥.....
በመንፈስ አርቅቀህ እየሄድህ፥
ከኔ ጋር ለመነጋገር በመቻልህ፥
ያስታውቃል፥ አስተዋይና ደግ ሰው እንደሆንህ።
አንተኮ ባታውቀው ነው እንጂ፥ ባይገባህ፥
የአምላክህን ፈቃድ ነው እየፈጸምክ ያለህ።
በኋላ ስታስፈለግ ትወሰዳለህ፤
እስከዚያው፥ ግዳጅህን ፈጽም፤
ምንም ቅር አይበልህ፤
ገንዘብ ቢያጥርህ፥ ኑሮም ቢከፋህ፥
መኖርህ ብቻ ይብቃህ፤
እምነትህ ያጠንክርህ፤
ገቢህንም የፈጠረህ አምላክ ይባርክልህ፥
ጤንነቱን ይስጥህ፥
ደስታንም ይሙላ በውስጥህ፤
በል ወዳጄ፥ ደረጀዬ፥
ሂድ፥ ሂድ ወደ ሥራህ፥
በቃ ሂድ፥ ጸሐይ ሳትወጣብህ፥
እኔ ከዚህ በላይ፥ ምንም የለኝ የምነግርህ።"

**<u>ደረጀዬ</u>**

"ጨረቃዬ እወድሻለሁ፤
ሰምቼሻለሁ፤ እሺ በቃ! እሄዳለሁ።
እህ! ሃብታም በሚገዛው - ነጣቂዎች በነገሡበት፥
በልሙጥ ስሜት፥ ምኞትና ፍላጎት ብዛት፥
ሃሪፎቹ ኳስ ሜዳውን እንደሚቆጣጠሩት፥
ሃብታሞቹም ምድራችንን የራሳቸው፥
ብዙሃኑንም የበዪ ተመልካች አደረጉት።
እነርሱ በፈጠሩት የአስተዳደር ጉድለት፥
የሴቶች ጭቆና፥ የሕጻናትና የሽማግሌዎች እንግልት፥

የሰውን ተፈጥሮአዊ መብት፥
ሰላምና ነጻነቱን ነጠቁት።
　　　　አውሮፓ አሜሪካን አረብ አገር ቢሰደዱ፥
　　　　ከዛም አሉ፥ በሰው ቁስል እንጨት የሚሰዱ።
አዎ! ገባኝ፥ ጨረቃዬ! አሁን ገባኝ፥ እሄዳለሁ፤
ልክ አንቺ እንዳልሺው፥ በኋላ ስፈለግ እወሰዳለሁ፤
እስከዚያው ግዳጄን እፈጽማለሁ።
　　　　በቃ ልሂድ አሁን ገባኝ፤
　　　　ሰማይ፥ አድማሱ፥ ቀላ፥ ቀላ አለብኝ፤
　　　　ጸሐይቱ ልትወጣ ነው መሰለኝ፤
　　　　ያንቺም ድምጽ ደከመብኝ፤
　　　　እንግዲህ ልሂድ፥ ልሩጥ ከሥራ እንዳያስወጡኝ።”

**<u>ጨረቃዬ</u>**

“ቆይ! አንዴ! ቆይ! አንዴ!
አድምጠኝ፥ በደንብ አድርገህ፤
አንድ የቀረ አለኝ፥ የምነግርህ።
ምንም ቢሆን የእግዚአብሔር ነህ፤
እኔም ባልረዳህ፤
እንዲህ እንዳሁኑ በመንፈስህ አርቅቅህ ከሄድህ፥
እምነትና ጽናትን በልብህ ከቀረጽህ፥
ብዙ በረከት አለ የሚጠብቅህ።
የሰውና የፈጣሪ እናቱ የሆነች፥
“እነኋት እናትህ” ተብላ ለዮሐንስ የተሰጠች፥
ለፈጣሪዋ ገረድና እናት፥
ለሰዎችም እናት የሆነች፥
በሰብእናዋ ሰውና ፈጣሪን ያቆራኘች፥
ያቺን፥ አንዲት ንጽሕት ሴት፥
የጠፈር ንግሥት፥
ማርያምን አንተ መቼ አጣሃት።
በመንፈስ አርቅቀህ ሂድ፥ እስከታገኛት፤
በእምነትና በጽናት እርሷን ተማጠናት፤
ፍቅርህን ግለጽላት፤

ለምናት፥ "እናትዬ አማልጂኝ!" በላት፤
የኔ፥ የርሷ፥ ያንተም ፈጣሪ ነው የሚሰጥ የሚነሳ፤
ምንም ችግር ቢጠናብህ ፈጣሪህን አትርሳ።
ይህንን ብቻ ነው እኔ የምነግርህ፤
በቃ አሁን ሂድ! ማርያም ትከተልህ፤
የምትወዳት፥ የምትወድህ፥
የባሕርይህ መመኪያ የሆነቺህ፥
እርሷ ናት የምትረዳህ፥ የምትለምንልህ።
ሂድ ልጄ - ደረጀዬ፤
ከእንቅልፍህ ብድግ ብለህ ሥራን ሥራ፤
ብርሃን፥ ደስታ ይኖራል ካንተ ጋራ፤
የደግ ሰው መልካም መንፈሱ ሲዘራ፥
ከፋት ሲሸሽ፥ ደስታም ሲሆን የጋራ፥
ይህ ነው የሰው መድኃኒትነት፤
ከሁለትነት፥ በአንድ ጠባይ መረጋጋት።
እንደሥራህ ሰው ባይከፍልህ፥
ልፋትህን ፈጣሪ ይቁጠርልህ፤
የተመኘኸውን ያድርግልህ፤
እግዚአብሔር ይለመንህ።"

**<u>ደረጀዬ</u>**


"ጨረቃዬ፥ ጨለማ በዝቶብኝ እንዳይከፋኝ ብለሽ፥
ከሰማይ ላይ ተሰቀልሽ፤
ጸሐይ ላንቺ የምትሰጠውን ብርሃን ሁሉ ወስደሽ፥
ወደእኔ አስተላለፍሽ፥
ጨለማም ከብርሃን ሰጪ አካላት ሁሉ ተደብቆ፥
ዙሪያሽን እያንዣበበ ሊቦጭቅሽ፥
ከመሬት ሥር ተደብቆ ሲያደፍጥብሽ፥
እርሱ ከተፈጥሮ ሕግ ውጪ ሊሠራብሽ፥
ሕግ አክባሪዎቹ ተገን ሆኑልሽ፤
ጸሐይ አበራችልሽ፤
ከመሬትም ትንሽ ትንሽ ብርሃን ደረሰሽ።
እኔም አካልሽ አካሌ መሆኑን፥ ይህንን ሁሉ አሰብኩት፤

የአንቺ፥ የእኔ፥ የጸሐይ፥ የአካላውያን ሁሉ ጠባይ፥
አንድ መሆኑን ተረዳሁት።
የሚነዱት ነደው ብርሃናቸውን ሲፈነጥቁ፥
የማይነዱት ከሚነዱት ብርሃናቸውን ሲያንጸባርቁ፥
ጨለማዎችም ከአካላውያን እየሸሹ ሲደበቁ፥
ይህ ’ማይደል ወይ?
የማያቋርጥ የጠፈር አካላት ዙረት።
ይህ’ማይደል ወይ?
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ማለት?
በደስታ ብርሃን፥ ሃዘን ጨለማን ማባረር፥
ክፉውን በደግ መተካት።
አዎ! ጨረቃዬ ሰምቼሻለሁ፤
እሄዳለሁ፤ ጸሐይ ሳትወጣ እደርሳለሁ፤
ደክሜ እስክሞት እሠራለሁ፤
እኔም እንዳንቺ ግዳጄን እወጣለሁ፤
ለአምላኬ እየጸለይኩ፥
የማርያምዬን ምልጃ እየተማጸንኩ፥
በመላእክት ተራዳኢነትም እየተማመንኩ፥
በአዎንታዊነትና በተስፋ እየሠራሁና እየጸለይኩ እኖራለሁ።
እሄዳለሁ፤ ጸሐይ ሳትወጣ ሄጄ በልብሶች ላይ አደፍጣለሁ፤
ከእንግዲህ የመርፌና የክር ንግግር፥
ከች፥ ከች የሚለውም የስፌት መኪና ድምጽ አያስፈራኝም፤
ፈቅጄ የገባሁበት፥ የገዛ ሥራዬ መንፈሴን አያውከውም፤
ከጨረቃዬ ከተቀበልኩት ተስፋ በስተቀር፥
ሌሎች ሃሳቦች እኔን አያንገላቱኝም።
ምድሪቱን ጥዬ ሰማይ ወጥቼ፥
ጨረቃ መለሰችኝ ወደራሴ፥
ሁሉን ልቻለው እንጂ በቤቴ።
አንዱን ሸፍኖ፥ ሌላውን መስሎ፥
ራስን አሳንሶ፥ ሥጋን መሬት ጥሎ፥
ለአንድነቱ ታግሎ፥ ታግሎ፥ ታግሎ..........።
ሕይወት፥ በሰማይ፥ በምድር፥ በባሕር፥
አዙሪት ወይንስ ዑደት፥ መሞትና መፈጠር?

ራሱን ችሎ በራሱ የሚያድር፥
ሰውና ሰው በማይተዋወቅበት መንደር፥
ከዓመት ዓመት እድሜውን ሲቆጥር፥
እርጅና፥ ድካምና ሕመም ሲያብር፥
በአንዱ ሰው ላይ ብዙ አይነት ችግር ሲከመር፥
እጅግ ሲከብድ፥ ራስን ተሸክሞ መኖር፥
በጧት፥ በተሲአት፥ በምሽት ድንብርብር።
ትንሽ - ኢምንት ሆኖ መኖር፥
የሰው ተስፋ መቁረጥ፥
ሁሉን ትቶ፥ መንገድ ላይ እስከማደር፥
በሥጋም በመንፈስም ኩምትርትርርርር፥......
እግሮችን በእጆች እስከማሰር፤
ችግር እስከ መቃብር።
ወይ ጉድ! በሥፍራዎች ሁሉ ትግል፥
ትግል በትግል ውስጥ ሲመሰቃቀል፥
የአለም መጨረሻ እስኪመስል።
ላይችል አይሰጥም ይባላል፥
ግን አይምሮ ስንቱን ይሸከማል?
ተሸከሞስ ምን ያህል ይቆያል?
አይምሮ ዘለአለማዊ ላስቲክ አይደል!
ምድራዊ ችግሮችን ሁሉ መቀበል የሚችል።
እንደ ደረጅዬም የሚጎዱ፥
የብዙሃንን ሕይወት እየለወጡ፥
እንደ ጸሐይና ከዋክብት እየነደዱ፥
ብዙዎች ናቸው፥ ለሌሎች የሚሰው፥
እንደ ሻማ እየቀለጡ።
ብዙኃን ናቸው፥ ራሳቸውን ለሌሎች አሳልፈው የሚሰጡ፤
ከእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዛት ሳይወጡ።
አዎ! እንደማያቋርጥ የጠፈር አካላት ዙረት፥
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እየጠበቁ፥ ደግ መሥራት፥
በዚህ ብቻ ነው ሰይጣን የሚሸነፈው፤
አለማችንም ከጥፋት የምትድነው፤
ሰላም፥ ፍቅርና ደስታ የምታገኘው።

# ምዕራፍ አምስት

## የሙሙዬ እና የማማዬ ምክር



ሙሙዬና ማማዬ

**መግቢያ**

የሚከተለው መልእክት ዋና አላማ፡- ኮናፑን በአርሲ ላይ የተተከለ አኖሌ እየተባለ የሚጠራ ሃውልት እንዲሠራ ሃሳብ ካቀረቡ፥ ከፈቀዱና ካሠሩ ሰዎች ኃጢአት ይልቅ፥ የኛ የተመልካቾች ኃጢአት የከፋ እንዳይሆን፥ ለወደፊት ታላቅ ችግር ውስጥ ሊጥለን የሚችለውን፥ በአገራችን ውስጥ ሥር እየሰደደ ያለውን የዘረኛነት ተውሳክ ለመግታት፥ ተባብረን እንድንነሳ ለመምከር ነው። መካሪዎቹም የአደባባይ ምሁራን፥ ፈላስፋዎች ያልሆኑ፥ ታናናሽ የጓዳ ጠቢባን (ሙሙዬ እና ማማዬ) ናቸው። እስቲ እንስማቸው።

**ሙሙዬ**

"እናቴ መገኚያዬ፥ እወድሻለሁ፥ አፈቅርሻለሁ እማዬ፥ ማማዬ....
ገና ከሆድሽ ሳለሁ ስሜቶቼን ሁሉ ተቆጣጥረሽ፥
ስዘል፥ ስራገጥ፥ በደስታ ስቦርቅ አንቺም ደስ ሲልሽ፥
ዝምም ስል፥ "ልጄ ምን ሆነብኝ?" ብለሽ፥
ለራስሽ ሳታስቢ፥ ለኔ አስበሽ፤
ማማዬ፥ እኔም የሚሰማኝን ላጫውትሽ፤
እስቲ አይን አይኖችሽን እያየሁ ላናግርሽ።
አ! አ! ምነው ጡትሽን ከፍ ከፍ አደረግሽ፥
ራሴን ቀና ቀና ማድረጌ ወተት አንሶኝ መሰለሽ?
አይ ደግነትሽ! አይ ደግነትሽ!
እኔኮ! አፌን ከጡትሽ ላይ ለጉሜ፥ ሳልለቅሽ፥
የደግነትሽን ደግነት ላነብ ፈለጌ ነው ከአይኖችሽ።
አ! አ! ምነው ጡትሽን ጨመቅ ጨመቅ አደረግሽ፥
ወተት አንሶኝ መሰለሽ? ያልመዘመዝኩሽ።
ሆዴኮ ጠግቧል፥ ግን አይምሮዬ ተጨናንቋል፤
አይኖቼ አይኖችሽን ማየት ከጅለዋል።
ቆይ በደንብ ላጫውትሽ፡-

ሁሉን ቻይ ሆድሽ፥ የሚያቅፈኝ ሜዳው ደረትሽ፥
ሙጭሙጭ አርገው የሚስሙኝ ከንፈሮችሽ፥

ሙቀት የሚሰጠኝ ትንፋስሽ፥
የሚያባብሉኝ አይኖችሽ፥
ሁለመናሽ ያንቺነትሽን ስሜት በውስጤ ሰርጾብኛል፤
የሃሳብ ሞገድ ከአይምሮዬ ተነስቶ፥ ባይኖችሽ ውስጥ ገብቶ ይመረምራል።
ይህቺን አለምን እና በውስጧ የሚሠራውን ጉድ ያሳየኛል፤
እኔንም አንቺንም እየሆነ ያናግረኛል።
ምነው ጡትሽን ነካ ነካ አደረግሽ?
በትካዜ የተዋጥሽ መሰልሽ።
ከአይኖቼ ምን ተረዳሽ?
አዎ! ጥቋቁር ብሌኖች የቀለማት ሁሉ ሕብሮች፥
የጠፈርን ብርሃን የሚያስተላልፉ የሕዋሳት መስተዋቶች፥
ሰውንና ተፈጥሮን የሚያገናኙ ልዩ አለሞች፤..........
ሰው ግን የጠፈርና የሰው ዝምድና አልገባውም፤
ወደ አይምሮ ሰሌዳ ገብቶ የሚጻፈው ሁሉ፥
የት እንደሚደርስ አላወቀም።
አንጎል ለብቻው አንገት ላይ ተሰክቶ ቢቀመጠም፤
ሥራው ብዙ ነውና፥ ግልጋሎቱ ለሰው ብቻ አይደለም፤
የሰው ልጅ ይህንን ሳያውቅ መጎዳቱን፥
አካል ሰውነቱ የራሱ ብቻ አለመሆኑን አላወቀም።
ትንሽ የአንጎል ሕዋስ፥ ባለ አእምሮ፥ አእምሮ ቢስ፥
ትርጉም ሰጪ፥ የሰውን ክፋቱንና ደግነቱን የሚያባብስ...
በዚያች በሚጢጢ የአንጎል ሕዋስ ያወቅን መስሎን፥
እራሳችንን አሳበጥን፥ እርስ በርስ ተጣላን።
አአ! አአ! ምነው ማማዬ ዘገነነሽ?
አንቺም እንደኔ ተሰማሽ?
በአይኖችሽ ብርሃን አለምን ስቃኝ ቆይቼ፥
ሩቅ ተጉዤ፥ ከዚች ሥፍራ ቀረሁ ፈዝዤ፥
አንድ አስደንጋጭ ነገር አይቼ።

ምነው ሰቀጠጠሽ ማማዬ?
እኔን ያስደነገጠኝ አንቺንም አስደነገጠሽ?
በአይኖችሽ መሃል የተደነቀረው ሃውልት ነው ያስፈራሽ?
ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተኮልኩለው፥
በውስጡም እጅ ተሰክቶ፥ ጣቶቹም ተነፋፍተው፥
ወደላይ ተቀስረው፥
ማማዬ ጡትሽ እኮ ነው!!
ውይ! ማማዬ ጡትሽ እኮ ነው።
ተሸፋፍኖ መቀመጥ ያለበትን ገልጠው፥
ምግቤን ከደረትሽ ለይተው
ያንቺን ጡት ከሰማይ ላይ ሰቅለው፥
ውይ! ማማዬ ጡትሽ እኮ ነው።
ስሚኝ ማማዬ!
እኔስ በአለም ዙሪያ ያስተዋልኩት ብዙውን ሲያስደስተኝ፥
እኔንስ ይህ ሃውልት ነው ክፉኛ ያስደነገጠኝ፤
እንጃ! ሰው መሳይ ሰይጣን የተፈጠረ መሰለኝ።
ሔዋን ሕይወት ሰጪው አካሏ ወንዶችን መኮነን ሲሆንባት፥
እሷም ስቅቅ ሲላት፥
ወንዶች ሁሉ ጠላቶቿ የሆኑ ሲመስላት፥
ታዛቢዎች፥ ቱሪስቶች ከሃውልቱ ባሻገር በመንፈስ መጥቀው ሲሄዱ፥
የሃውልቱን ሠሪዎችና አሠሪዎች ለመኮነን ሲገደዱ፥
እውነተኛው የሰው ልጅ ታሪክ እንዲህ በአንድ ሃውልት ተጣሞ ሲሠራ፥
ምን አይነት ሕዝብ ነው ይህ - በገዛ ሃፍረቱ የሚኮራ??
የሃውልቱ ሠሪዎቹና ያሠሪዎቹ ኃጢአት፥
ከጡት ቆራጮቹ ኃጢአት እንደሚበልጥ፥
የዚህ አገር ሕዝቦች አልገባቸው፥
የሰብአዊነት ግማሽ ጎኑን - ሔዋንን ማዋረዳቸው፥
“ተዋረድን! አዋረዱን” ብለው ያለቀሱ ብዙዎች ናቸው፤

ለዚህ እኩይ ሥራ፥ ለዚህ ተንኮል ምላሹ ነው የዘገየው።
እስቲ ስሚኝ ማማዬ!
ሰው የተከለውን ውሸት ተፈጥሮ ያጋልጠዋል፤
የአኖሌን ሃውልት አካባቢው ይረግመዋል፤
የፈሰሰበት የራሄል እንባ ደም ሆኖ ያበሰብሰዋል፤
ውሸት እንደ እውነት ተደርጎ ሲደሰኮር፥
ዛፉ፥ ሳር ቅጠሉ፥ ድንጋይና አፈሩ ይታዘባል፤
ሰው ዝም ቢል፥ ተፈጥሮ ዝም እንደማይል፥
ትርክት ታሪክ እንደማይሆን፥ ጊዜ ያሳየናል።
በቱሪስቶች አፍ ዛሬና ነገ የምንሰደብበትን፥
በእጃቸው ጽፈው፥ በአፋቸውም ተናግረው፥
ይህንን የአኖሌ ሃውልት አቆሙልን - የተነገረንን ሁሉ እንዳንረሳው።
በአለም ዙሪያም ያሉትን ሃውልቶች በአይነ ህሊናዬ ቃኝቻለሁ
ግን፥ የኢትዮጵያችን ታሪክ - በጭቃ ለጣፊዎች - ሲበለሻሽ፥
ካለ ዛሬ እንዲህም አላየሁ።
እስቲ ንገሪኝ ማማዬ፣ እንደዚህ ሃውልት አስደንጋጭ የት ይገኛል?
ሃውልት ሁሉ ስለ አገሩ ጥሩ ጥሩውን ይናገራል፤
ይኸኛው ግን፥ ጠቅላላ የሰውን ዘር ለመኮነን ተገትሯል።
እስቲ ሃውልቶችን፣ እየዞርን እንመልከት፤

በቤልጂየም፥ አንድ ሕጻን (ማኒኪን)፥
የእሳት ቃጠሎን በሽንቱ ሲያጠፋ የሚያሳይ ሃውልት፥
በአሜሪካ የነጻነት ችቦ፥
እስታቹ ኦፍ ሊበርቲ የሚሉት።
የሰው ልጅ አብራክ፥
እጅም ቢሆን እግር፥ ወይም የተቀረው ብልት፣
እንዲህ ጥሩ ጥሩውን ሲያስተምሩበት፥
ያሳዝናል፥ አንዲህ የሰው ገላ፥ ባገራችን ሲገተር ለክፋት፤
ልክ እንደ ለፍላፊ፥ ተናጋሪ ጣኦት።

የሰውን ኃጢአቱን የሚያጋልጥ፥ የአደባባይ ፍርድ ቤት፥
ራሱ አቃቤ ሕግ፥ ራሱ ጠበቃ፥ ራሱ ከሳሽ፥ ራሱ ምሥክር፥
የዳኝነትን እና የኮናኝነትን ሥልጣን በራሱ የተቀናጀ የድንጋይ ክምር፥
በጥቂት ዘረኞች የሚከበር፥
የብዙሀን ውርደት፥ እጅግ የሚያስፈራ..
የሰውን አስተሳሰብ ወደ ክፋት የሚመራ።

አ! ማማዬ - አፍ እንኳን ባልፈታ በአንደበቴ ስናገር ስሚኝ፤
ገና አይኔን ስገልጥ ብዙ ነገር አይቼ ተግንዝቤአለሁ፤
አሁንስ አድጌ ብዙ ብዙ ነገር አውቄአለሁ፤
በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ተፈጥሪአለሁ፤
በሴትነትሽ ደግነት አድጌአለሁ።
ልክ ከሆድሽ ልወጣ ስል፥
ሴቶች ተሰብስበው “ማርያም ማርያም...” ሲሉ እንደሰማሁ፥
አሁንም የብዙ ሰዎችን ጩኸት እሰማለሁ።

የሰውም ልጅ በአጥፊው እውቀትና ፍልስፍና ተጠምዷል፤
በኃሳና በሃይማኖት ተከፋፍሎ እርስ በርስ ይጣላል፥ ይጋደላል።
አ! ማማዬ አ! እናቴ መጋቢዬ፥
አንቺም በልብሽ ስታለቅሺ፥ በአይኖችሽም ስታለቅሺ፥
እንባሽ ፈሰሰ ከገላዬ፤....
ባይኖችሽ ብርሃን የታየኝ ርዕዮቴ፣
ይህ ማስተዋሌ፥ ገና በልጅነቴ፥
ስሜትሽ ነውና ስሜቴ፥
በይ አልቅሺ፥ አልቅሺ ማማዬ፥
በንባሽ ይታጠብ ገላዬ።
በኢትዮጵያ ሆድ ገብቷልና ታላቅ ኃጢአት፥
በቀላሉ አይጠፋም ካለ ጾምና፥ ካለ ጸሎት፤
አልቅሺ፥ አልቅሺ ማማዬ፥ ሥራ አትፍቺ፤
ማርያም አለች ካጠገብሽ፥ ትረዳሻለችና በርቺ! በርቺ! በርቺ!።”

**ማማዬ**

“ደስታን የምትሰጠኝ ሆዴ፥
አይኔ፥ ሁለመናዬ፥ እወድሃለሁ፥ አፈቅርሃለሁ፥ ልጄ፥
ሙሙዬ ከልጅነትህ ባይኖርም ያላስተዋልከው፥
ይገባኛል ምክንያቱ፥ በዚህ ሃውልት ላይ ያተኮርከው።
ጡቴ ብቻ አይደለም ሰማይ ላይ የተሰቀለው፥
መላው ሰውነቴ ነው የጠፋው፤
እኔነቴ ነው የተቀበረው፤
ከሴቲቱ ሆድ የወጣ ወንድ ድንቁርናው ጨካኝ አደረገው፥
የብልግናው ብዛት የሴቶችን አብራክ አረከሰው።

ሴቲቱም እኔ ሔዋን፥ አለቅሳለሁ ዛሬ፥
አለቅሳለሁ፥ አንድም ስለራሴ፥ በቁም ስለመቀበሬ፥
ስለ ተገፈፈው ክብሬ፤
አንድም የማለቅሰው ስለ ልጆቼ ነው፤
ያ ጆሌ ኪያ! ያ ጆሌ ኪያ! ያ ጆሌ ኪያ! እያልኩ ነው የማነባው፤
የኦሮሞ ሕጻናት፥ በዚህ ከፊታችን በተገተረው፥
በዚህ አሰቃቂ ሃውልት ዙሪያ ተኮልኩለው፥
ያሳዝነኛል፥ ያስለቅሰኛል፥ እነሱም ሲያዝኑ ሲተክዙ፡-
“ውይ! የናታችን ጡት፥ ተሰቀለ ከሰማይ..” ብለው።
ምክንያቱንም ሲፈልጉ ከክፉዎች አፍ ሰምተው፥
ወይንም፥ ይህ ነው ታሪካችን የሚል ጽሑፍ አንብበው፥
ያሳዝነኛል፥ ምን እንደሚሰማቸው ሳስበው።
“ታሪክ ጸሐፊዎች ነን..” የሚሉትም ክፉውን አጉልተው፥
የሰውን ልጅ ሚዛናዊ አስተሳሰብ አጣመው፥
ለክፉ አሳቢዎች በር ከፈቱላቸው።
አንዳንድ አክራሪ ፖለቲከኞችም እውነትን የጨበጡ መስሏቸው፥
በክፋትና በጥላቻ ተጠምደው፥
የገዛ ወገኖቻቸውን አሳወሯቸው።

ይህንን እና የመሳሰለውን ጽሑፍ እንኳን እንዳያነቡ፥
በዚሁ የአፍሪቃ ፊደል እንዳይጠቀሙ፥
አይቻልም አሏቸው፤
ፊደላቸው ፊደላችን አይደለም ብለው አስጣሏቸው።
ሰፊው የኦሮሞ ቋንቋ በስነጽሑፍ እንዳያድግ፥
ከአማርኛው ጋር በመተጋገዝ፥
የፈረንጁ ይሻለናል ብለው፥ በጠባቡ ወሰዷቸው፤
ከአፍሪቃ የስነ ጽሑፍ ባሕር አስወጧቸው፤
እነርሱ አልገባቸው - ከሞቀ ቤት መውጣት ሥልጣኔ መስሏቸው፥
የኢዮጵያዊነትን ለዛ ዘጉባቸው።
እነኚህ የኦሮሞ ሕጻናት ሲያድጉና ብዙ ነገር ሲገባቸው፥
ዘረኛነትን ተሻግሮ በሚሄድ ንቃተ ሕሊና ሲታነጽ ርዕዮታቸው፡-
ይህንን ኮናኝ፥ በእርኩሳን መናፍስት መሃንዲስነት የተገነባ ሃውልት፥
ከአክሱም ሃውልት ጋር ነው አወዳድረው የሚያዩት፥
የአክሱሙ፥ የአጠቃላይ የሰዎች ኃይል፥ የሥልጣኔ ምልክት፥
ይሄ ግን የጥላቻ፥ የድንቁርና፥ የሸንፈት፤
ኃጢአት መሆኑን የሚያሳይ ይቅር ማለት፥
በተለይ ለታዳጊ የኦሮሞ ልጆች የተሰጠ፥
እኩይ የፖለቲካ ትምህርት፥
በደቡብ ኢትዮጵያ የሰው ውርደት የታየበት፥
የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሚሳቀቁበት፥
የአለም ሴቶች የተዋረዱበት።
ሙሙዬ አንተም "አልቅሺ ማማዬ" አልከኝ - ይህንን ሁሉ ተገንዝበህ፤
አዎን አለቅሳለሁ።
በልቅሶም ብዛት ሲዞር ናላዬ፥
እንዲህ እያልኩ አንጎራጉራለሁ፤
በኦሮሚኛም ቢሆን - በሁለተኛ ቋንቋዬ።
"ያ ኖሌ! ያ ኖሌ! ጆሌን ሃዳ' ወጂ ወሎሌ!

ኦርሚ ኪያ - አማ ማል ጀተኒ - ጆሌን መራቱማ ወጂ ተበደ'ኒ፥
ቢሊሱማ ኬኛ - ጂራቹማ ኬኛ - በሌይሰኒ።"

አንድም የማለቅሰው፥ በእውነት "ያ ጆሌ ኪያ" የምላቸው፥
እነርሱም እንደ አስተማሪዎቻቸው፥
ፈሪዎች፥ ድንጉጦች እንዳይሆኑብኝ ነው።
አንድም የማለቅሰው፥
ያ ታላቅ ኃጢአት በኢትዮጵያ ሆድ የገባው፥
የተቀሩትን ልጆቼን ሁሉ እንዳያጠምድ ነው።"

**ሙሙዬ**

"በኢትዮጵያ ሆድ የገባው ታላቅ ኃጢአት ዘረኛነት መሆኑ ይገባኛል፥
ሌሎች ልጆችን እያጠመደ በክፋት ሲያሳድጋቸውም ይታየኛል፤
እኔም የኢትዮጵያ መጻኢ ያሳስበኛል፤
እንዳው ምን ይሻላል?

የሕዝቡ ዝምታ ዲሞክራሲን ሲውጠው፥
የመንግሥትም ዲሞክራሲ ሕዝቡን ሲወጋው፥
ለጋራ ችግር አብሮ ማሰብ ሲያቅተን፥
ሁሉም የራሱን ብሶት ሲያጋንን፥
ኑሮአችን ብጥብጥና ጭቅጭቅ ሲሆን፥
መፍትሔው ምን ይሆን? መፍትሔው ምን ይሆን።"

**ማማዬ**

"እውቀት ሸመትን፥ ግንዛቤ ሸመትን.....
ክፉውንና ደጉን፥ ድንቁርናን እና ጥበብን ቀላቅለን፥
ከጦር ሜዳዎች እንዲሁም ከትምህርት ቤት ብዙ ብዙ ተማርን።
እውቀት ሸመትን፥ ግንዛቤ ሸመትን.....
የራሳችንን ለቀን፥ ይህንንም ያንንም፥ የባእዳኑንም ጨምረን፥
ከፖለቲከኞች ፖለቲካን፥

ከሃይማኖተኞችም ሃይማኖትን ተማርን፤
ደጉንም ክፉውንም ወሰድን።
ሁሉን አግበስብሰን፥ ሁሉን መስለን፥
ግን፥ መለስ ስንል ወደራሳችን፥
በአሳሳች መነጽር እያየን፥ የገዛ ታሪካችን አሳፈረን፤
ማንነታችንን የሚፍቅ አስተሳሰቦችን ፈጥረን፤
ከሌላውም ጋር በአንጻራዊነት እያወዳደርን፥
ራሳችንን መምሰል አቃተን፥ የኢትዮጵያዊነታችንን ለዛ፥
የወግ፥ የባህል የአብሮነታችንን ጣእም አጣን፤
ማሕበራዊ ኑሮአችንን ትተን፥ ግለኞች ሆንን፤
አዎ! አይምሮአችንን በሆነ ባልሆነው እያጣበብን፥
በምድራዊ እውነታዎች - በከንቱ የጥላቻ ፖለቲካ ታወክን፤
መንፈሳዊ ባሕሬአችንን ለቀቅን።
በመጨረሻም፥ ያወቅነውን፥ የሰማነውን፥ የተነገረንን፥ የተማርነውን ሆንን፥
(መምሰል ብቻ ሳይሆን)።
ዛሬ፥ የገዛ ማንነታችን፥ የገዛ ወገናችን፥ መልሶ እኛን ጎዳን፤
የነገው ምን ይሆን? ምን ይሆን መጨረሻችን? ምን ይሆን መጨረሻችን።

እኛ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረን፥
ክርስቶስን መምሰል ሲገባን፥
የክፋት ተምሳሌዎች እየመሰልን መጣን።

ኃጢአትን ስንጠላ፥ ኃጢአት ሠሪዎችን መውደድ አቃተን፤
ስለ ኢትዮጵያችንና ስለ አንድነታችን ብለን፥
ክፉ አድራጊዎችን፥ ዘረኞችን፥
የፖለቲካ ወይም የድንቁርና ጠባቦችን መውደድ ጠልተን፥
እርስ በርሳችን ተተራመስን፤
የገዛ ደማችን፥ የገዛ ወገናችን፥ መልሶ እኛን ጎዳን።
መንፈሳዊ መሪዎቻችንም አቡነ ጴጥሮስን መምሰል አቃታቸው፤
እነሱ፥ ውሱን ሆኗልና ትኩረታቸው፤

ካልሆነ ሥፍራ ያርፋል ውግዘታቸው።
የፖለቲካ መሪዎቻችንም ስህተቶቻቸውን ሁሉ ማረም አሳፈራቸው፤
ራሳቸውን ቢያርሙ፥ ከሥልጣን የሚፈናቀሉ መሰላቸው፤
እያዩ፥ እየተገነዘቡ፥ በዳተኛነት መቀጠል ሆነ ምርጫቸው።

አዎ! ትእቢተኛነት እና ዘረኛነትማ፥
እጅጉን የሚብሰው ከፍታቸውን በሚያሳዩ፥
በአወቅን ባዮች - ትምክህተኞች፥
የሕሊና ሚዛን በተዛባባቸው  - ታሪክ አዋቂዎች ነን ባዮች፤
በአማራ ብሄርተኛነት ስም ዘመናዊ ጠባቦች።
እነኚህ'ኮ! የተማሩ ደንቆሮዎች ናቸው፤
አስር ተመሳሳይ ሃውልት ቢሠራ ግድ'ማይሰጣቸው።
የእነርሱ ጠባብነት ውጤት ከዚህ እንዳደረሰን አይገባቸው፤
ይህ ሃውልት የታሪካችን ጥቁር ነጥብ መሆኑ አይታያቸው።
እነርሱ ኦሮሞን እንደ አጥፊ እንጂ፥ እንደ አልሚ አያዩትም፤
እነርሱ የኦሮሞ ጥንታዊ ኢትዮጵያዊነት አይዋጥላቸውም፤
"ኦሮሞ መጤ ነው፥ ኦሮሞ ወራሪ ነው..." ይላሉ፤
ቢሆንም ባይሆንም፥
ኦሮሞ የኢትዮጵያ ኢትዮጵያም የኦሮሞ መሆኗን ይክዳሉ።

ምን ይሆን ምስጢሩ፥ መጨረሻው አላማው?
ሰይጣን እንዲህ በኢትዮጵያ ላይ ያተኮረው፤
ጥንትም ሰይጣን ኃይሉን የሚያጠናክረው፥
ከፍተኛ ባላጋራ ካለበት ነው።
ሕጻኑን (ኢየሱስን) ቀምቶ ሊወስድ ነበር፤ የእሳት ግርግዳ ባይጋርደው፤
በውሃ ጥም ሊገድላቸው ነበር፥ ሕጻኑ ምንጩን ባያፈልቀው።
ሰሎሜ፥ ዮሴፍ፥ ማርያምና ክርስቶስ በረገጡት መሬት፥
በአክሱም ጽዮን ትይዩ ይህ ሃውልት?
በአክሱም ጽዮን ትይዩ ይህ ሃውልት?
እንጃ! ልጄ፥ የእኔስ አእምሮዬ ከቶ አልቻለም ሊገባው፤

ያለፈውን ጥሩ በመጥፎ የመቀየር ሂደት ነው የሚመስለው።

ምነው አንተ ሰው፥ ምነው አንተ ሰው፥
በሃውልቱ ትይዩ የቆምከው፥
አንተ አምሃራይ፥ አንተ ትግራይ፥ አንተ ኦሮማይ፥
እስቲ ተመልከተው፥
“የአውሮፓ ሊቃውንት ካልጻፉት፥
ወይንም እነርሱ ካላጸደቁት…”
ብለህ ነው እኔ አላምንም ያልከው?
ተአምረ ማርያምን ያቃለልከው?
ምድራዊት ኢትዮጵያ፥ ሰማያዊም ሆና የተሰጠችን፥
ምግብነቷ ቢሆንም ለሥጋችን
እንዲሁም ነው እኮ! ለመንፈሳዊነታችን።
ነገሮችን በጥልቀቱ ባለመመልከት፥
ከከፍታችን ወረድን ወደ ዝቅጠት።

የሔዋን ድምጽ ይጮሃል፥
ጡቶቼን መልሱ፥
በኔ ስም አትነግዱ፥
የአዳምም አይነሳ ጉዱ ይላል።
እኔም በመሪር ሃዘን እየጸለይኩ አለቅሳለሁ፤
ማርያም እናቴን እማጸናለሁ፤
እባክሽ አስራት የሰጠሽን ልጅሽን አሳስቢ እያልሁ።
ሚካኤል ገብርኤልን እጣራለሁ፥
ለኢትዮጵያ የሚቆም ሰው ቢጠፋ፥
መላእክት ይቆሙላታል ብዬ አምናለሁ።”

**<u>ሙሙዬ</u>**

“እኔስ ምኞቴ፥
ይህ ሃውልት ከፉና ደጉን፥ ወዳጅና ጠላትን መለያ እንዲሆንልን፥

ብሎም፥ መጪውም ትውልድ ከፉውን በደግ የሚቀይር ጻዲቅ እንዲያደርግልን።
ግን እንዲሁ ሳስበው፥ ይመስለኛል ይህ ሃውልት፥
አንዱ ቅድመ ዝግጅት፥
ለመጪው ትውልድ መማሪያ፥
ድልድይ፥ ከክፋት ወደ ደግነት መሸጋገሪያ።

መሆን ያለበት፥ ይሆን ዘንድ ግድ ይሆናል፤
ሰይጣንስ ከእግዚአብሔር እጅ መች ያመልጣል፤
ሁሉም ቀኑ ሲደርስ ዋጋውን ያገኛል።
እስቲ ማን ያስበዋል፣
ከሰው አእምሮ እንዲህ ያለ ተንኮል ሲጠነሰስ፥
እስቲ ማን ያስበዋል፣
ጭቁኑ፥ ደጉ፥ የኦሮሞ ሕዝብ ከጥንስሡ ሲቀምስ።
እስቲ ማን ያስበዋል፣
ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲህ በቂም በቀል ሲታመስ።

ማማዬ ትኩር ብዬ አይኖችሽን ስመለከት፣
በአይኖችሽ ብሌኖች ውስጥ ሲተራመሱ ይታዩኛል፥ የጠፈር አካላት።
ወደ ላይ እየተወረወረ እንደሚወድቅ መሬት፥
እንቅስቃሴ እኮ አይኖርም ካለ ምክንያት።
ባንድ በኩል የጠፈር አካላት ይመሳጠራሉ፤
ትእዛዝ ተቀብለው ያከናውናሉ፤
ያስተካክላሉ፥ ያመቻቻሉ፤
በሌላም በኩል፥ ፖለቲከኞች መርዝ እንደቀመሰ ጅብ ይራወጣሉ፤
የወጣቶችን አእምሮ ይቆጣጠራሉ፤
አንዳንዶቹ የቆየውን ቁርሾ እንዳይረሳ ያሳስባሉ፤
ሌሎቹም ከጎን እሳት ይጭራሉ፦
“እዩት ተመልከቱት የነፍጠኞችን ግፍ…” እያሉ።
ባላገሮች በደግነታቸው ይታለላሉ፤
እናቶች በየዋህነታቸው ያለቅሳሉ፥

አባቶችም ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው ያዝናሉ።

ታዲያ ይህ ሁሉ ካለ ምክንያት አይመስለኝም፥
መነሻችንና መድረሻችን ውሱን ከሆነ፥
ግዳጁን የማይፈጽም ማንም የለም፤
ነፍስ ያላቸው፥ እጽዋቱም፥
እንስሳቱም፥ ሰዉም፥ አውሬውም፤
ነፍስ የሌላቸው ግዑዛኑም።
ካለ ቅራኔ አልተፈጠረችም ይህች አለም፥
በያለበት ሞልቷል፥
እንደ ፍልሚያ ያለ ነገር፥ እንደ ፍትጊያም፤
እንቅስቃሴዎች፥ ከዚህም ከዚያም፥
ከጠፈር ኃይላት፥ ከኮስሚክ ጨረሮችም፥
ከትልቅ እስከ ትንሽ፥ ከጠቢብ እስከ መሃይም፥
አንድም አይኖር ግዳጁን የማይፈጽም።

ይህ እንቅስቃሴ ይኖረዋል ልዩ ምክንያት፥
ግልጽ ሆኖ የማይታይ፥
ሳይንቲስቶችም ሃይማኖተኞችም ያላስተዋሉት ጉዳይ፤
አላማኝ ሳይንቲስቶች በሰውና በጠፈር ያለውን ግንኙነት ያቃልላሉ፤
እነርሱም ግዴታቸውን ሲወጡ(?)
መንፈሳዊ ክስተቶችን ሁሉ አጋጣሚዎች ናቸው ይላሉ።
ሃይማኖተኞች ግን በልባቸው ያስተውላሉ፤
እየደጋገሙ እያነበቡ የዳዊትን ቃል፦
“ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤
የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል...” እያሉ። (መዝ. 18:1)
ምድራውያን ግን ከምድሪቱ አያልፍም ሃሳባቸው፤
አውሎ ነፋስ ሲገፈትራቸው፥
የጸሐይ ብርሃን ሲያደብናቸው፥
የውሃ ጎርፍም ጠራርጎ ሲወስዳቸው፥

ይደነግጣሉ፥ ይፈራሉ፤
እንዳው በችግር ቀን ብቻ፥
ቀና ብለው፥ ወደ ሰማይ ያንጋጥጣሉ።
አንዳንዶችም፥ የተፈጥሮ ትርምስ መቀጪያችን፥
መልሚያችንም እንደሆኑ ያስተውላሉ፤
የሚያስተውሉቱ፥ ዛሬን ሲኖሩ የነገውንም ያስባሉ።
ታዲያ፥ ጠፈራዊ ቅንብር ይኖራል እንጂ ከበስተጀርባችን፤
ጠፈራዊ ክንውን (ዝግጅት) ይኖራል እንጂ፥
ወሳኙ፥ ለመጻኢው እድላችን።

ሁሉንም በጊዜ ውስጥ ስናስተውለው፥
እንቅስቃሴና ጊዜ እረፍት የላቸው፥
ሁሉም ይሠራል በየፊናው፥
ለተወሰነ አላማው።
የገዛ ድርጊታችን ከእድላችን ጋርም ዝምድና አለው፥
የሚሰማ ይስማ፥ የሚገባው ይግባው።
የሰው ልጅ በሰይጣን ተንኮል ሲታለል፥
ለወሳኙ ጦርነት ሲዘጋጅ፥ የሰው ዘር ውድም እንዲል፥
ጊዜም በሩቁና በቅርቡ መሃል ሲንጠለጠል፥
ሰውና ሰው እየተራራቁ፥ ጠላትነት ሲፈጠር በመሃል፥
አዎ! እኛም እኮ ነን ተሳታፊዎች፥
ከጠፈራዊ ክንውኖች ጎን፥
ፈቃዳዊ ነጻነት ተሰጥቶን፥
ጥሩዎች እንድንሆን የታዘዝን[45]፤

እና፥  ወደ ቀድሞው ነገሬ ልመለስና፥
የሰው ኃጢአቱ ከፍ ብሎ፥ ሰማዩ ላይ የተጻፈበት፥

---

[45] “..ታስበው ዘንድ ሰው ምንድነው?................።” መዝ. 8:4

ከነባቢት ሕያው፥ ግዑዝ ደንጊያ - ጣኦት የተመረጠበት፥
ቢኖር ይመስለኛል፥ ሰይጣናዊ ምክንያት።
ይህ ሃውልት ቢሆንም ለጠፈር አካላት የቆመ፥
ለእንቅስቃሴአቸው መነጸሪያ፥
ከፉና ደጉን ማሰለፊያ፥ ለመጨረሺያው ፍልሚያ፥
እኛም የጠፈር አካላት ነን፥
ለጥፋትም ለልማትም ሃላፊነት ያለብን፥
ለእርቅ፥ ለሰላም፣ ለፍቅር፥ ለሕብረትና ለአንድነት ብለን፥
ቶሎ ብለን ይህንን ሃውልት ካላፈረስን፥
መጥፊያችንን ማቅረባችን መሆኑ ይግባን።
ብቻ ሁሉንም ለበጎ ያድርግልን።

ማማዬ! ትኩር ብዬ ሳይሽ ሳሰላስል፥
ከአይኖችሽ ብሌኖች ውስጥ የጠፈር ምስል፥
በውስጡም ፍቅር፥ እጅግ ደስ የሚል የሚያማልል።
እስቲ አንቺስ ምን ይመስልሻል?
እስቲ ንገሪኝ ከኢትዮጵያ ታሪክ ቀድተሽ፥
ብሔረተሰቦቿን (ጎሳዎቿን ቤተሰቦቿን) ሁሉ እንደ አንድ ሕዝብ ቆጥርሽ።"

**ማማዬ**

"የኢትዮጵያን ብሔረተሰቦች (ቤተሰቦች) ሁሉ እንደ አንድ ሕዝብ ስንቆጥር፥
ጥንታዊት ኢትዮጵያን ስናስታውስ ታላቂቷን ሀገር፥
አክሱም እምብርቷ፥ ሜሮምም[46] አናቷ እንዳልነበር፥
እንዲህ እንዳሁኑ ተከርክማ፥ ተከርክማ ሳታጥር - ሳትኮማተር፤
ተከብራና ተፈርታ የቆየች እንደነበር፥
ይህንን ነው የማስታውሰው የጥንቱን ስዘክር።
ዛሬ ነገም ቢሆን፥ አምናለሁ በሕዝቦቿ እንደምትከበር፥

---

[46] http://www.ancient.eu/Meroe

አሁንም ቢሆን፥ ኢትዮጵያችንን የማስባት፥
በአንዲት የሰላም፥ የፍቅርና የነፃነት ባንዲራ ጥላ ሥር፥
ለአለም ተምሳሌት እንድትሆን ነው ለተቀረውም የሰው ዘር።
ማን ይህንን ርዕዮት ይመልከት?
ማንስ ይቆርቆር ለመላው አፍሪቃ?
በአውሮፓ፥ ባሜሪካ፥ ከጃማይካ፥ እስከ ካናዳ፥
ስለ ስመ ጥሩ ባለ ታሪክ ሀገራችን በያለበት ሲወራ፥
ማን መጥቶ ይደመር ከኛ ጋራ።

ከመላው ኢትዮጵያ፥ ከአክሱም፥ ከጎንደር፥
በእስላም - ክርስቲያን ፉክክር ሳትበገር፥
እጅጉን የሚዘገንነውስ በክፉት መታሰር፥
በዚች ቄሶች፥ ሼኮችና ፓስተሮች በበዙባት ምድር።

እኔስ አልገባኝም ልጄ፥
ምሁራን በበዙበት ሀገር፥ ፈላስፋ፥ ተመራማሪ፥
የአገራችን ታሪክ እንዲህ ሲሆን አሳፋሪ።
እኔስ አልገባኝም ልጄ፥
ከክርስቲያኖቹም፥ ከእስላሞችም ሲጠፋ አስተማሪ፥
ከክፋት ጎዳና የሚያስወጣ መሪ፥
ሲጠፋ መካሪ፥ ለኢትዮጵያችን አንድነት፥ ለአገሩ፥ ለወገኑ ተቆርቋሪ፥
ጥሩውን አጉሊ፥ መጥፎውን ቀባሪ፥
የጥላቻን ሃውልት ሠባሪ፥ የፍቅርን ሃውልት ሠሪ።

አዬዬ..አዬዬ..አዬዬ..
እንግዲህ ከራሴ ጋርም ቢሆን ካንተ ጋር፥
የሆዴን ዘርዝሬ ልናገር፥
ስለ ጥቂት ዘረኞች፥ የኦሮሚያ ወንዶች ችግር።
እነርሱ ወቀሳችውን ጀመሩ እንዲህ ብለው፡-
“ይህ ሃውልት፥ መዘከሪያ የጥንቱን፥
የአማሮችን ጭካኔ፥ ግፋቸውን፥..

ለኛ ማስታወሻ፥ እንዳይረሳን፥...
ለነርሱም ትምህርት እንዲሆናቸው፥
ጠባቦች በኛ ላይ የበላይነትን እያሳዩ፥ በኩራት ተወጣጥረው፥
አልበርድ ብሏልና ትምክህታቸው.
ነፍጠኞች እያየለ መጥቷልና ትእቢታቸው፥
እየታደሰ መጥቷልና ተንኮላቸው።
ክፋት፥ ዘረኛነት፥ ሆዳምነት ጠባያቸው፥
ሰው ሲሰቃይ ማየት ነው ደስታቸው፤
ለዚህም ነው ይህንን ሃውልት ከዚህ ያቆምንላቸው፤
እንደ መስተዋት ሆኖ ውስጣዊ ባሕሪያቸውን እንዲያሳያቸው፥
ሕሊናቸው እንዲወቅሳቸው፥
ክፉ ሥራቸው እንዲጸጽታቸው፥
የሚማሩት ተምረው ዳግመኛ ግፍ መሥራት እንዳይለምድባቸው፤
ለዚህ ነው ይህ ሃውልት ከዚህ የተተከለው።
በተቆርቋሪዎች ተጠንቶ መንግሥት ያጸደቀው።”

እኛም ነገርናቸው ከገባቸው ብለን፦
አዎ፥ አከሱማ (እንዲህ ነው)፥ አከሲ፥ ይቅር አለማለት የበደሉትን፥
አዎ አከሲ ይቅር ብሎ በሰላም መኖር ሲያቅተን፥
በዘመኑ ዲሞክራሲ ሲደመሰስ የርስ በርስ ፍቅራችን፥
ይቅር መባባልም ሲጠፋ፥ ሃዝንና ልቅሶ ሲገባ ከቤታችን፥
አዎ፥ አከሱማ፥ አከሲ፥ እንዲህ፥ እፍረትና ውርደት ሲወጣ ከአብራካችን።

አዎ! ፖለቲከኞች ከፉዎቹ አልበረደም እልሃቸው፥
ዳግመኛም እንዲህ ብለዋልና እንስማቸው፦
“ደ’ገዪ (ስማ፥ ስሚ)፥ ደ’ገያ (ስሙ) ብለዋል፥
አዋጅ ሲያሰሙ ለጆሌ ኦሮሚያ..
“ማንነታችን በአምባ ገነኖች ተቀብሮ ቆይቷልና በስመ ኢትዮጵያ፤
ይህ ሃውልት፥ ለኛ ጋሻና ጦር ይሆነናል፥ የወራሪ ሃይላትን መከላከያ።”
“አከሱማ (እንዲህ ነው)” ብለዋል “አከሲ!”

እውነቱ ቁልጭ ሲል በዲሞክራሲ፥
“አከሱማ (እንዲህ ነው)” ብለዋል “አከሲ!”
ተዳፍኖ የቆየው ታሪካችን ሲገለጥ፥
ግፍ በተሠራበት ሥፍራ በአርሲ።”
ልጄ ሆይ ስማ ሙሙዬ፥ ተቆርቋሪ ስለ ሃውልት ሲያወራ፥
ተመልከተው ሌላውንም ድብቅ ሴራ።
ዘረኞቹም፥ ጠባቦቹም፥ ነፍጠኞቹም፥ በአንድ ላይ ሆኑና፥
ከዚህ መለስ የትግራይ፥ ከዚህ መለስ የአምሃራይ፥
ይህ የደቡብ ክልል፥ ይህ ደግሞ የኦሮሞ ክልል አሉና..
ሁሉም ለየራሱ ይሁን (በይኔ ወበይኑ)፥
አትድረስብኝ አልደርስብህም ተባባሉና....
ኢትዮጵያን አይበሉባ (የማይበሉበት እጅ) አደረጓት፥
ሰውም እንደዛው ኋላና ፊት፥ ባለመተዋወቅ ሲንከራተት፥ ሲንከራተት፥
ለሠርቶ ማደር ሲሯሯጥ፥
“ዘር” የሚሉት ልዩ ቋንቋ መጣበት፥
የጎሳ አድልኦ አንጓጠጠበት።
ባንድ በኩል ደስ ሲለን፥ ከቀድሞው ለሚሻል የልማቱ ሥራ፥
በስመ ሕዳሴም፥ ሰዉ ሲንቀሳቀስ፥ ወደ ሥራ ሲሰማራ፥
ከከፋቶች ሁሉ ባሻገር፥ ሕዝቡ ለተሻለ ኑሮ ሲል ደፋ ቀና፤
የተማረውም በሙሉ ልብ ሲሳተፍ በአገር እድገት ጎዳና፥
ከድንጋይ ፈለጣ የተሻለውን፥ የንግድም ቢሆን የግብርና፥
ግን፥ ሁሉም በክልል በክልሉ እንጂ፥ ከዚያ ወጥቶ፥
በዘረኛነት ገመድ ተተብትቦ፣
ሥራ ፈልጎ፥ ሥራ ፈጥሮ እንዳይሠራ፥
ምርጫ ተከልክሎ፥ እድገቱ በብሔሩ ማንነት ተገድቦ፥
ይኸውልህ ልጄ እንዲህ ሆኖ ቀረ የኛ ተስፋ - የኛ ኑሮ።
የተማረውም ያልተማረውም ከአንድ ሥፍራ ተቀምጦ፥
አይኖቹንም ከድንጋዮቹ ላይ ተክሎ፥

አንገት ደፍቶ፥ ድንጋይ ቀጥቅጦ፥
በሃሳብ ብቻ ለተሻለ አልሞ፥
ሥጋዊ ሕይወቱ በዘረኛነት ተውሳክ ታሞ፥
ከመንገድ ዳር ተቀምጦ፥
ድንጋይ ቀጥቅጦ፥ ድንጋይ ከርክሞ፥ የቀኝ እጁን መዳፍ አሳምሞ፥
ከዚያው አቀርቅሮ፥
ድንጋይ ኮርኩሞ፥ የግራ እጁንም መዳፍ አሳምሞ፥
እግሩንና መቀመጫያውን አደንዝዞ፥
አይነ ሕሊናውን አፍዝዞ፥
ይኸውልህ ልጄ እንዲህ ሆኖ ቀረ የኛ ተስፋ - የኛ ኑሮ።
የሰው ልጅ ሰብአዊ መብቱን ተገፎ፥
ትግሉ ተሰነካከሎ፥ በአድርባዮች ተጣሞ፥
መጻኢ እድሉም ጨልሞ።
በአንዲት አገር የብቸኝነት፥ የፍራቻ ኑሮ..
ተሸማቆ፥ ተኮራምቶ ኑሮ.. ።

ሙሙዬ፥ ስማኝ ልጄ፥
እኔም ነፍጠኞች ይውደሙ ባይ ነበርኩ፥
አምባገነናዊ አገዛዝ እንዲደመሰስ የታገልኩ፥
ግን አሁን ሰውንና ኃጢአቱን መለየት ቻልኩ፤
ከተማርኩት ትምህርት ሁሉ የክርስቶስን አስቀደምኩ፤
ኃጢአት መሥራትን፥ ዘረኛነትን፥ ጠባብነትን ጠላሁ፤
ዘረኞቹን፥ ጠባቦቹን ሁሉ፥ መቼም ሰው ናቸው ብዬ ወደድኩ፥
ለዲሞክራሲ፥ ለእኩልነት፥ ለነጻነትና ለአንድነት ብዬ፥
ግብታዊነትን፥ ስሜታዊ ጥላቻን አሽቀንጥሬ ጣልኩ፤
ውዲቱ አገራችን የሁሉም ናት ማለት ጀመርኩ፤
ኢትዮጵያዬንና የነጻነት አርማዋን፥ ሰንደቋን አስቀደምኩ።
አዬ! ምነው ይህንን ሁሉ መአት ሳላይ በሞትኩ፥
አይ! ምነው ጥንቱን ባልተፈጠርኩ።

እስቲ አንተስ ምን ይመስልሃል? ሙሙዬ
እስቲ ንገረኝ ከየት ላይ እንደሆነ ስህተቱ፥
ይህስ ከሰውም የመጣ አልመሰለኝ ከጥንቱ።”

<u>**ሙሙዬ**</u>

“አዬ! ማማዬ.. የሰው ልጅ፥ የገዛ አይምሮው ወዳጁና ጠላቱ፥
ምድራዊ፥ ሰይጣናዊ ፍልስፍናን ባለመለየት መጎዳቱ፥
መልሚያውም መጥፊያውም የገዛ እውቀቱ፤
የሰው መጎዳቱ ሲሆን በገዛ እውቀቱ፤
በእኛ ሀገር ደግሞ የመጎዳቱ ብዛቱ።
ማማዬ አስታውሳለሁ፥ በሶስቱ ቀለማት ስታሽሞነሙኒኝ፤
ኢትዮጵያዬ እያልሽ፥ ባንዲራ ስታለብሺኝ።
ስለ ሰላም፣ ስለ ፍቅርና ስለ አንድነት ብለሽ፥
እንቺም ባቅምሽ ለፋሽ፤
ማን፥ መቼ፥ ይሆን ሰው የሚሰማሽ?
እንዲሁ ድብቅብቅ ብለሽ ከጓዳሽ፤
በስተርጅና “አንተም ተው፥ አንተም ተው፡” ትያለሽ፤
“ዘረኛነትን ጠላሁ፥..ዘረኞችን ወደድኩ..” ትያለሽ፥
ግን ማን ይህ ገብቶት ማን ሊያዳምጥሽ?
“ሥልጣን ከጠብ መንጃ አፈሙዝ ብቻ አይደለም የሚወጣው፤
በንጹሕ ልቡና ከአንደበት በሚፈልቅ ኃይልም ይወጣል” ብትዪ፥
ማን ይህ ገብቶት ማን ሊሰማሽ።
ማምዬ፥ በቃ እኔስ በደንብ ሰማሁሽ፤
ልጅም ብሆን አውቃለሁ፥
ከየት ተነስተሽ የት እንደደረስሽ፥
አሁንም ያሳዘነኛል የምጠባው ጡትሽ።
ማስተማሪያ ሲጠፋ፥ ካንቺ ጡት ሌላ፥
ሰው ከፋትን ሲውድ፥ ፍቅርን ሲጠላ፥

እኔስ ከእንግዲህ ለምን ጡትሽን ልጥባ፥
አንቺ “አይ ኢትዮጵያ! ምነው ባልተፈጠርኩት” ስትዪ፥
እኔስ ለምን ልኑር?
በቃኝ፥ አፌን ከጡትሽ ልንቀል።
ልሙት፥ ድብን ልበል።”

**ማማዬ**

“ተው ልጄ አትሙት፥ እኔም ላንተ ብዬ ልኑር፤
እደግ ላሳድግህ፥ ሰው ቢከፋ አምላክ አለን፣
እርሱ ሲጠራን እንሄዳለን።
እስከዛው ገና ብዙ ብዙ አለ የማስተምርህ።
    ድሮ ድሮ ገና በልጅነቴ፥ ኦሮሞዎች ሲዘምቱብን፥
    ስንጨራረስ፥ ስንጨርሳቸው፥ ሲጨርሱን፥
    አንዳንዶቻችንም ቤተሰቦቻችንን ለማትረፍ ብለን፥
    እንደ ዝንጀሮ ከገደሉ ተንጠልጥለን፥
    ከፍታውን፥ ሜዳ ሜዳውን ለነርሱ ለቀን፥
    መኖሪያችን ቆላ ቆላውን በየሸለቆው ሲሆን፥
    ግን ጦሩ በረድ ሲል አይተን፥
    ሜዳ ሜዳውንም ስንቃኝ፥ ስንማስን ቆይተን፥
    ከኦሮሞው ተጎራብተን፥ አብረን ኖርን፥ በጋብቻም ተሳሰርን፥
    ቀስ በቀስ፥ ሰላምን ፈጠርን።
ታዲያ፥ ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን፥
ደማቸው ከደማችን፥ ቆዳቸው ከቆዳችን፥
ቋንቋቸው ከቋንቋችን፥ ባሕላቸው ከባሕላችን፥
እነሱነታቸውን ከእኛነታችን አዋህደን፥
“ምና ሸዋ?..” እንጂ “ምና ዘርህ?..” ሳንባባል እንዳልኖርን፥
ምን ጉድ ይሆን ልጄ በኢትዮጵያችን የወረደብን?
    አዎ! ጊዜ ከፋና፥ ከዚህም ከዚያም አክራሪዎች ተነሱብን፤

እኛው በእኛው ተከፋፍለን እንድንኖር አደረጉን፤
ታዲያ፥… ከጥንቱም ከሶስት መቶ ዓመታት በፊትም ቢሆን፥
ተጣልተንም ተዋደንም አብረን እንዳልኖርን፥
የእርስ በርስ ግጭቶቻችን፥ እንዳልሆኑ የሁላችን፥
ጠባብ ታሪከኞች ሰይጣናዊ መልክ አወጡለት፥
ለሠፊው ታሪካችን።
የኢትዮጵያን ሥልጣኔ በራሳቸው ብሔር ብቻ አጥብበው፥
ብሔርና ብሔር ቢጋጭ፥
ያ የሁላችንም ታሪክ መሆኑ ሳይገባቸው፥
የብሔረሰቦችን የማያቋርጥ እድገት፥
በስነአመክንዮ መመልከት አቅቷቸው፥
የኢትዮጵያን እድገት ለራሳቸው ብሔር (አማራ) ብቻ ሰጥተው፥
ማሕበራዊ ታሪካችንን ሁሉ ቆራርጠው፥ ቆራርጠው፥
ሰንጥቀው ተርትረው - እንዲህም ብዙ አውርተው፥
በራሳቸው ጉልበት ያላገኙትን ሁሉ፥
በራሳቸው እንዳገኙት ቆጥረው፥
ተፈጥሮአቸውን - የገዛ ጎሳቸውን (አማራነታቸውን)
ወደላይ ከፍ አድርገው፥ የተቀረውን ሁሉ ወደታች ቀብረው፥ አጣጥለው፥
ኢትዮጵያችንን የጎዷት አንዳንድ የአማራ አክራሪ ዘረኞችም ናቸው።
አዎ! እነርሱ አማራነትን መከበሪያ - መመኪያም አድርገው፥
ብዙ ሲያወሩ፥ ሲያቅራሩ፥ በከንቱ ሲሸልሉ፥ ጆሯችንን አደንቁረው፥
እኛ በነርሱ፥ ግብታዊነታቸውን፥
ስሜታቸውን መቆጣጠር ባቃታቸው፥
ምድራዊ እውቀታቸው ባጨለመባቸው፥
እኛ በነርሱ የታሪክ አመለካከት ታናናሾች ሆንን፤
የነርሱ ጠባብነት እኛን ጎዳን።
መራገም በሚቀናቸው ክፉ አሳቢዎች ተወናበድን፤
እነርሱ ያመጡብን መዘዝ እኛን ገደለን፥ ፈጀን፤

የዘመኑ አክራሪዎች፥ ጥብብ ያሉ ምሁራኑም ተነሱብን፣
የነርሱ ስብከት ከሞት አፋፍ ወስዶ ጣለን።
በአንድ በኩል የኦሮሞ ጅብደኞች፥ አክራሪዎች፥
በሌላ በኩል የአማራ ጅብደኞች፥ አክራሪዎች፥
እንዲሁም በመንግሥት ድጋፍ አሽቃባጮች፥ መርዘኞች ፖለቲከኞች።
እነኚህ ሁሉ በዙሪያችን፥ እኛን በመሃል ጨፈለቁን፤
እውነተኛውን ታሪካችንን አጠፉብን፤
ሳያውቁን እኮ ነው፥ እንዳው ሳያውቁን፥
እኛ አማሮች ኦሮሞዎችም መሆናችንን፤
ሳያውቁን እኮ ነው፥ እንዳው ሳያውቁን፥
እኛ ኦሮሞዎች አማሮችም መሆናችንን፥
ለማንነት ማንነትስ - እነርሱ - እነሱ (እነኚያ አክራሪዎች)
እነርሱ አይደሉም መለዮአችን፥
በፍጽም - በምንም መንገድ - በእነርሱ (በጠባቦቹ) አትመተርም፥
በአድርባይ ጠባቦች አትቦጠቦጥም ኢትዮጵያችን፥
ብዙዎች ናቸውና - ቅን አሳቢ - አማራ - ኦሮሞ ልጆቻችን፤
እና ልጄ! አለ ሌላ - ብዙ ብዙ ነገር - ለወደፊት የሚገለጥ፥
እስከዚያው ግን፥ እድል ፈንታችን ሆኗል አላስፈላጊ መጋጋጥ።
ሰው አእምሮ ገዝቶ በራሱ ካልተማረ፥ በመከራ ውስጥ እያለም ካልገባው፤
መጪው ጊዜ የከፋ እልቂት ነው የሚሆነው።
እነኚያም አክራሪ ጠባቦች፥ ሰው እየታረደ ገደል ቢጣል ግድ የላቸው።
አዬ! ሁሉን የሚያይ አምላካችን አይርሳን፤
አንድዬ አይተወን - እርሱ ይቅር ይበለን፥
ይህንን ክፉ ጊዜ ያሳጥርልን።"

**ሙሙዬ**

"አዬ ማማዬ! አሁንስ እንባዬ ፈሰሰ ከገላዬ፥
እውነተኛነትሽና ፍቅርሽ አይጠፋምና ከአእምሮዬ።

አልቻልኩም ላየው አይንሺን፥
ካንቺ አይኖች የፈሰሱ እንባዎች አርሰውታል ሰውነቴን፤
እንጃ! አንቺም የምትጠፊብኝ መሰለኝ፤
አይዞሽ ማማዬ፥ እኔም አልሙት፥ እንቺም ኑሪልኝ።"

**ማማዬ**

"አይዞህ ልጄ አልጠፋም - አንጠፋም፥
ወላዲተ አምላክ ልጆቿን አትረሳም፤
አይዞህ! በልመና ጥሪ እማጸናለሁ ደጓ እናቴን፥
እርሷን የፈጠረ አምላክ አይረሳም ልጆቹን።"

**ሙሙዬ**

"ማማዬ የቅርቡን ታሪክ ስትነግሪኝ ሰማሁሽ፤
እንደዛሬው የሰው ማንነቱ ሳይዘረዘር፥
ከኖሕ ጀምሮ ቅጣት በጅምላ ነበር፤
አሁንም ቅጣት በጅምላ እንዲመጣ እርኩሳን መናፍስት ይቻኮላሉ፥
ይህንን ሃውልት እና የመሳሰለውን ምልክት ያቆማሉ፥
በዚህም የሰውን ጭንቅላት ያናውጻሉ።

በአንጻሩ፥ ሳር ቅጠሉም አውሬውም ሳይቀር ይናገራል፡-
"ሰዎች እባካችሁ መጥፊያችሁን አታቃርቡት" ይላል።

መጪውንስ ማሰቡ ላንቺ ይከብድሻል፤
ሰው ሰውእነቱን ሲያጣ ማየት ምን ደስ ይላል?
በእናትነት አቅምሽ ሰው ከሰው ሲተላለቅ ማየት ያቅትሻል፤
አንቺም እንደኔ ሞትን ያስመኝሻል።
እንግዲህ አንቺም እስቲ አንዴ ታገሺኝ ስሜቴን ሳጋራሽ፥
እንዲህ ልቦናዬ ከአንቺ እሳቤ ጋር አድጎ፥
እኔንም እንዳንቺ አልቃሻ ከምሆንብሽ፥
ምናለ ባላድግ? ከዚሁ ኩምትር ብዬ ብቀርልሽ።

ማደግ መመንደግ፥ ወጣት መሆን፥ ሰው መባልስ ምን ያደርጋል?
እንዲሁ ትንሽ ሆኖ መቅረት የሚሻል ይመስለኛል።"

**ማማዬ**

"ሙሙዬ ትንሽ መሆንማ ምን ከፋት አለው?
የትልቅነት ፋኪቻ 'ማይደል ሰውን ያጋደለው?
ጥቂቶቹ ለትልቅነት ሲታገሉ፥
በመሃል ብዙሐኑን ያቆሳስላሉ፥
መንግሥታትም ታላላቆችን ሲያቀማጥሉ፥
የብዙሐኑን መብት ይጥሳሉ፤
የሚያተራምሱን ጥብብ ያሉት ትላልቆች ናቸው፤
ከሰፊው ሕዝብ (ከትናንሾች) ምንም ዳራ የሌላቸው።
የነርሱ ውስጣዊ ጠባይ ከመጀምሪያውም ልዩ ነው ከፍጥረቱ፥
ገና ጡት ሲጠቡ፥ የእናታቸውን ጡት እያንገላቱ፥
እያመናጨቁ፥ እየነከሱ፥ እየጎተቱ።
ወተቱን የሚያገኙት በጉልበታቸው እየመሰላቸው፥
ገና ከልጅነታቸው፥ የእናት ፍቅር የጎደላቸው፥
ነዝናዛ የሆኑ በጠባያቸው፥ ካውሬ የባሰ ባሕሬአቸው፤
ለእነርሱ ፍቅር ማለት ጥላቻ፥ ሰላም ማለት ጦርነት፥
ለእነርሱ ውሸት ማለት እውነት፥ ጥበትም ስፋት።

የሰው እውቀቱ በጊዜ ውስጥ ፈር ሲለቅ፥
ለአዲስ ትውልድ ጠንቅ።
ግን እውነት ነው መንፈስ - ሕዝቦችን የሚጠብቅ።

ከጥንት ጀምሮ አያሌ ወረራዎች ተካሂደዋል፥
ግን ሁሉም በሃይማኖት ጽናት፥ በፍቅር ተገተዋል፥
አሁንም በሃይማኖት ጽናት ፍቅር ሲያይል፥
ይህ የጥላቻ ሃውልት ይፈርሳል።
በምትኩ የፍቅር፥ የሰላም እና የአንድነት ሃውልት ይቆማል።"

**ሙሙዬ**

“ማማዬ ላንድ ደቂቃም ቢሆን፥ ፍቅር የጥላቻ ምርኮ ሆኖ ማየት ይቀፈኛል፤
መፈጠሬ ከሆድሽ፥ ከሆነ ሳድግ የሰውን ክፋት ለማስተዋል፥
ተጠምቄ፥ ክርስቲያን ተብዬ፥ እስካሁን መቆየቴ ይበቃኛል።
ለኔስ እየታወቀኝ መቆየቱ ያስጠላኛል፥
የምጠባው ጡትሽ ተናንቆኛል።
አኖሌ ድንጋይ ከሰማይ ላይ፥
ምነው ሞቴን ባቀረበው፥ ይህንን ክፉ ቀን፥
ይህንን የውርደት ቀን ሳላይ።
ማማዬ! መቼም እናት ነሽና - የዋህነትና ፍቅርን ደብለቅለቅ ታደርጊያለሽ፤
ይህ ቋሚ፥ ባለ አእምሮ፥ ሰው የተባለ ፍጥረት፥
ካጠፋ ቅጣት እንዳለበት ትዘነጊያለሽ።
ግን፥ የሰው ልጅ ፍዳ ቀላል እንዳይመስልሽ።
እስቲ ባይነ ሕሊና ተመልከቺው፥
መጪው ጊዜ ለማን ምን አይነት እንደሚመስል።
በዚያች ጊዜ፥ በዚያች ቅጽበት እንዲህ ይሆናል፡-
የዚያን ጊዜ ቅዱሱ ሕዝብ ወደተቀደሰው፥
እርኩሱም ወደረከሰው ሥፍራ ይሄዳል።
የዚያን ጊዜ ለሚሞቱት የመጨረሺያው መጨረሺያ፥
ለሚድኑትም የመጨረሺያው መጀመሪያ ይሆናል።”

**ማጠቃለያ**

በአለማዊውም ቢሆን፥ በመንፈሳዊው፥
ሰው አስቦ በአእምሮው፥ ተገንዝቦ በሕሊናው፥
ይህንን ሃውልት ተቻኩሎ ካላፈረሰው፥
አገር አቀፍ ቅስፈት ነው የሚከተለው።

የዚህን ጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ያስተውሷል፥
ሰው በገዛ ኃጢአቱ ይሞታል፤

ስህተቱን አውቆ የታረመ፥ የመቆያ ጊዜው ይራዘማል፤
ይህ ትውልድ ያልፋል፤ ሌላም ይከተላል፤
የሞኞች አገር መባልን ማን ይወዳል?
የሕሊና ጸጸት ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል፥
አእምሮ ያለው በራሱ ስነ አመክንዮ ይመራል፤
አይነ ልቡና ያለው፣ እውነትን ያያል፤
እንዲህም የነገሩንን - እንዲህም የመከሩን፥
ብዙዎችን አልሰማ ብለናል፤
ከጥፋታችን ካልታረምን፥ ሞት ይጠብቀናል።
ሁላችንም የአንድ አገር ሕዝቦች ነን፤ አንድነታችን ነው ብርታታችን፥
መከፋፈል ነው ድክመታችን፥ ዘረኛነትን ሰባኪ ነው ጠላታችን።
አዎ! ሆድ የገባ ኃጢአት ቶሎ አይወጣም፥
የአክራሪዎችም አስተሳሰብ ከጥበቱ ስፋትን እያገኝም፤
ጠላታችን ሰይጣን ነው እንጂ ሰው አይደለም፤
የተጣላን እናስታረቅ፥ ኢትዮጵያን እናስቀድም።
ቅጣትማ አይቀርም፥ ግን ሰዉ ቢማር ተቀጥቶም፥
መጪው መጥፎ ቀን ማለፉ አይቅርም።
ዘረኞቹንም ጠባቦቹንም እንውደዳቸው፥
ሁሉም ወገኖቻችን ናቸው፥
ዋናውን ጠላታችንን ለይተን እንወቀው፤
ይህንን ነው በአንክሮ ለመግለጽ የሞከርነው።
በሦስቱ ቀለማት ሕብረት፥ የነጻነታችን ምልክት፥
ለአንድ ኢትዮጵያ ለአንድ እናት፥
ሁላችንም እንተባበር፥ እንትጋ በጸሎት፥
በፍቅር፥ በሰላም፥ በሕብረትና በአንድነት።

# ምዕራፍ ስድስት

## ኢትዮጵያችን የማትረሳ ዘለአለማዊት



የጦርነት እና የስደት አዙሪት

***መግቢያ***

በዚህ ርዕስ የቀረበ ትረካ ከጥንታዊት ኢትዮጵያ እስከ ዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ድረስ የነበረውንና ያለውን ሁኔታ በማሳጠርና በመገምገም፥ እንደ ትዝታ እንደ ማስታወሻ፤ መጻሕፍቶቻችንን ለማሰላሰል እንዲረዳን፥ ነው።

ቸሩ አምላካችን እግዚአብሔርም ዘወትር እጆቿን ወደ ሰማይ የምትዘረጋውን ኢትዮጵያን እንዳይረሳት፤ በገዛ አገራቸው ጥቃት ስለደረሰባቸው የሚያዝኑትን እንዲመለከትና፥ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ሁሉ በእኩልነት የሚያይ ጥሩ መሪ እና መልካም አስተዳደር ታገኝ ዘንድ፤ ቀናውን መንገድ እንዲያሳያትና እንዲረዳት እንደ መለመኛ፥ መማጸኛ ጸሎትም ነው። አንባቢያንም በዚሁ መንፈስ ሲያነቡት፥ የሁላችንም የልብ ቅንነት ተደማምሮ ኢትዮጵያን ከፍ ያደርጋታል። አንድነት ኃይል ነው።

## ***ኢትዮጵያችን የማትረሳ ዘለአለማዊት***

ከሰማይ የሕይወት ጠብታ ከመሬት ላይ ሲወድቅ፥
በአፍሪቃ ምድር ከወደ ሰሜን ምሥራቅ፥
ሰውም በዝቶና ተባዝቶ እስኪመላ ምድርን፥
እኛ የት ነበርን? ምን ነበረ ሕይወታችን፥
ከጥፋት ውሃ በፊትስ ቢሆን፥
እኛ የት ነበርን? ምንድነው ታሪካችን?
ከየት ተነስተን ከዚህ እንደደረስን፥
እስቲ ለማስታወስ እንሞክር ጥንት የነበርነውን፥
አሁን የደረስንበትንም፥ በጊዜ ውስጥ ተረማምደን።

ይህ የዛሬው በቆዳው ቀለም የተለያየ የሰው ዘር፥
መሠረቱ ከአንድ ቤተሰብ[47] ብቻ እንደነበር፥
ቢሆንም እንኳን የማያጠራጥር፥
በአይነ ሕሊና እንመርምር፤
ከአንድ የጂኦግራፊ ክልል እና ከአንድ የሰው ዘር በመጀመር።

[47] monogenism

እስከ ዛሬ የተረዳነው፥ ከልዩ ልዩ የጥናት ዘርፎች፥
የሰውን ዘር ተንከባክባ ያቆየች፥
አላፊ አግዳሚውንም ያስተናገደች፤
የዛሬዪቱን ኢትዮጵያን፥ ሱዳንን፥ ግብጽንም ያጠቃለለች፥
ኢትዮጵያ ብለው የጠሯት፥ በሰሜን ምስራቅ አፍሪቃ አንድ ሀገር ነበረች።
ይህቺን ሀገር የሰው ዘር ሁሉ በደግነቷ እንዲያስታውሳት፥
ከጥንታዊነቷ ጀምረን እናውሳላት።

አዎ! አንዳንዴም አንዘንጋ ወደ ኋላ መመልከቱን፥
ያልተቀየረውን፥ የተቀየረውን፥ መልሚያችንን፥ መጥፊያችንን።

**<u>ማስታወሻ ከጥንታዊት ኢትዮጵያችን</u>**

በታሪክ የሚነገረው ወይም የተጻፈው፥
ወደኋላ ብዙ አይዘልቅም፥
ከጥቂት ሺህ ዓመታት ዘልቆ አይሄድም።
በሳይንሳዊ ታሪክ ምርመራ፥
ታሪካዊ መረጃዎች ከሌለበት ሥፍራ፥
ሰው ባለ ታሪክ አይደለም።
ግፋ ቢል፥ አንዳንድ ቅርሳ ቅርስ ቢገኝ፥
በቁፋሮ የሚለቀም፥ አብሮት ከተገኘም የሰው አጽም፥
በዚህ ውሱን መረጃ፥ የሩቁ የሰው ታሪክ አልታወቀም።

ግን እስቲ ላንዳፍታ የሰውን ታሪክ በአይነ ሕሊና እንቃኘው፥
ስነአመክንዮአዊ ግንዛቤ ነውና ሁሉንም የሚዳኘው።

ድሮ፥ ድሮ በሩቅ ዘመን፥ ለአገር ድንበር፥ ለሰውም ዘር የለው፥
ሁሉም አንድ ወጥ ሆኖ ነበር የሚኖረው።
የዛሬው የግብጽ፥ የሱዳንና የኢትዮጵያ ክልል ሳይኖር፥
ከሰሜን እስከ ደቡብ፥ ዘመናዊው የሰው ልጅ (ሆሞ ሳፒያን)
ከ“ግዮን” ወንዝ ዳርቻ ጀምሮ፥ ልምላሜ በበዛበት ሰፈር፥
ሁሉም አብሮ ይኖር ነበር።

ታዲያ፥ የሰው ልጅ በአንድ ወጥነት አብሮ ሲኖር፥
እንደ መልኩና ቁመናው፥ በጠባዩም አንድ ነበር።
ግን መንፈሳዊ ያይደለ አካላዊ ጠባይ፥
ውስጣዊ የበራሂዎች (ጂን) ጥርቅም፥
በውስጡ ልዩነቶቹን ሁሉ አምቆም ቢቆይ፥
ለጊዜው፥ ለውጥ ባያመጣና ባይቀየር፥
መራራቅ ሲመጣ፥ ከቦታ ቦታ መዘዋወር፥
የሰው ልጅ በተለያየ የጂኦግራፊ ክልል ተወስኖ ሲቀር፥
ልዩነቶች ተከሰቱ፥ ያ ጥርቅም የበራሂዎች (ጂን) ሲመነዘር።

የሰው ዘር ሲበዛ፥ ጥቁር፥ ቢጫና ነጭ የቆዳው ቀለም በየአይነቱ፥
አንዱ ከሌላው ተለየ፥ በቁመናውና በሰውነቱ፥
ሰውም ከሰው ሲርቅ፥ ሲፈልግ ብጤውን፥
የአካባቢ ተፈጥሮ አባባሰው ልዩነቱን።
ከጦርነቶች በኋላ፥ በመዳቀል ብዛት፥
ልዩ መልክ ብቅ ብቅ ይል ጀመር፥ ተጣቦ ልዩነት፥

ከሥፍራዎችም ሁሉ ቀደም ሲል፥ ልዩ መልክ ከወጣበት፥
ጥንትም የሰው ዘር ከተጀመረበት፥
የቀድሞው ውስጣዊ የበራሂዎች (ጂን) ጥርቅም ከተደበቀበት፥
የሕዝቦችን ሕብረተሰባዊ አስተዳደር ታሪክ እንመልከት፥
ከዚሁ ከምሥራቅ አፍሪቃ በመነሳት።

የሰው ልጅ በአገር ድንበር ራሱን ከፋፍሎ፥
መንግሥታዊ አስተዳደር መሥርቶ፥
በሰላም ሲኖር ውስጠ ሰላሙን አግኝቶ፥
መከራና ጭንቀት ነበረበት ከያቅጣጫው፥
ይህም አንዱ ነበር፥ የ"ሥልጣኔ" ምክንያት፥ ሰውን ከዚህ ያደረሰው።

መንግሥታዊ አስተዳደር ከሥልጣኔ ጋር ቢጀመርም፥
የሕዝቦች እንቅሳቃሴ፥ በፓስፖርት አልተገታም።
ጸሐይ ስታቃጥል፥ ንዳድ ሲሆን አካባቢው፥

ሕዝቦችም ሲሰደዱ፥ መኖሪያ ሥፍራቸውን ለቀው፥
ከምሥራቅ አፍሪቃ የሚፈልቁ ውሃዎች ነበሩ መንገዳቸው።
እግረኞችን የኤርትራ ባህር ቢገታቸው፥
መረከበኞች፥ እያሻገሩ ወደ እስያ አስገቧቸው።
ወደ ሰሜንም ወደ ምሥራቅም የነጎዱ፥
አለምን አዳረሱ፥ በየጊዜው እየተሰደዱ፤
ከተፈጥሮ ሁኔታዎች ጋር እራሳቸውን በማስማማት፥
ብርዱንም፥ ሙቀቱንም ችሎ መኖርን አወቁበት።
ከጊዜ በኋላ የሕዝቦች ቁጥር ሲበራከት፥
መንግሥታት ከሕዝቦቻቸው ጋር በመቀናጀት
ጉልህ፥ አስደማሚ ታሪክ ይመሠረቱ ጀመር በያለበት።
ታሪክ ጸሐፊዎችም መረጃዎችን የሚያጠናክሩበት፥
ሕዝቦች በበዙበትና በከተሙበት፤
የቅርጻ ቅርጽ፥ የስእሎች፥ የመገበያያ መሐለቆች ከታዩበት።
ለምሳሌ በታሪክ ከታወቁት፥ በሄሮግሊፊክስ ተጽፈው ከተገኙት፥[48]
በ 1495 ዓመተ አለም[49] ሃትሼፕሱት የተባለች የግብጽ ንግሥት፥
ወደ ደቡብ ዘልቃለች፥ እስከ ምድረ ፑንት፥
የንግድ ልውውጥን በማጽናት፤
እንዲሁም ከ970 እስከ 930 ዓመተ አለም፥
በንጉሥ ሰሎሞን መንግሥት፥[50]
እንደተጻፈ በመጽሐፍ ቅዱስም፥
በኢትዮጵያ ስለ መርከብ ሥራ መስፋፋት፤

---

48 አያሌ መረጃዎችን ከታሪክ መጻሕፍትና ከድረ ገጾች ይመለከቷል።፡

49 እንደ አውሮፓ አቆጣጠር

50 መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 9፡26 -28 – 10፡11፤ "የኢትዮጵያ ቶጳዚዮ (Topaz) አይተካከላትም።" ኢዮብ 28፡18-19

እስከ ኤርትራ ባህር ዳርቻም፥
ከደቡብ እስራኤል፥ ከኤሎት (ኤላት)፥
በመርከብ ወደ  ኢትዮጵያ ለመዝመት፥
ወርቅ፥ እጣን፥ የሰንደል እንጨት፥
የከበረ እንቁ፥ ሌሎችም ማዕድናት ከሚገኝበት።
ይህ የጥንቱ አብሮ መሥራትና ግንኙነት፥
እስካሁን ያልጠፋ መሆኑን የሚያመለክት፥
እስከ ዛሬ የኤርትራውያን ከኤላት አለመጥፋት።
እንዲህ የታወቀች ነበረች፥
ጥንታዊት ኢትዮጵያ እስከ ክርስቶስ ልደት።
በክርስትና ሃይማኖት - በአንድ እምነት የተሳሰሩ፥
የኢትዮጵያ፥ ወዳጆቿ በዙ፥
የግብጽ፥ የሦርያ የሌሎችም ክርስቲያን ሕዝቦች ተፋቀሩ።
ከጊዜ በኋላም የእስላም ሃይማኖት ሲወለድ፥
ነቢዩ መሐመድም አደረጋት ኢትዮጵያን ውድድ።
"ሂዱ እስልምናን በአለም ዙሪያ አዳርሱ፥
ግን ኢትዮጵያን አትንኩ" በማለቱም፥
በዙሪያዋ የእስላም መንግሥት ቢስፋፋም፥
በውስጧ እስላም ቢበዛም፥
ኢትዮጵያችን ፍቅር እንጂ ጠላት አላፈራችም።
ታዲያ፡- በሜሮዌ፥ በኑቢያ፥ የኖሩ ሕዝቦች፥
ሴማውያን ቢባሉ እንዲሁም ናይሎቲኮች፥
ኩሾች ቢባሉ፥ እንዲሁም አሞዎች፥
ለብዙ ዘመናት የነበሩ፥ ከኢትዮጵያ ተራራዎች፥
በዙሪያዋም በዝቅተኛ ሥፍራዎች፥
እነኚሁ ናቸው፥ በአንድነት ታላቅ መንሥት መሥራቾች።
ሰው ሲወፍርና ሲከሳ ስሙ እንደማይቀየር፥
እኛም ያው እኛው ነን ግዛታችን፥ ቢሰፋ ወይንም ቢያጥር።

የዛሬዎቹ ኢትዮጵያኖች፥ ሱዳኖችና ግብጾች፥
በአጠቃላይ የሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ ሕዝቦች፥
ጥንታዊነትን እና ታዋቂነት ያተረፉ ሥልጡኖች፥
እኛ እነሱ ነን፤ እነሱም እኛ ነን፥
ግብርናን ያስተማርን፥
እንደነ ሄኖክ ያሉ ጻድቃን፥
ሳይንቲስቶች የወጡ ካብራካችን።
ለመሆኑ፡- ኩሽ፥ ኑቢያ ብለው የሚጠሯቸው ሕዝቦች፥
ትሃርካ፥ አስፐልታ፥ ናስታሰን ብለው የሚጠሯቸው ንጉሦች፥
ከየት እስከ የት ነበር የግዛት ክልላቸው?
ወደ ተራራው እንዳይወጡ ምን አገዳቸው?
አንባቢ ያስተውል፥ በራሱ መርምሮ ይወቅ የገዛ ታሪኩን፤
ብዙም ሳይንተራስ አዋቂዎችን ነን ባዮችን፥
በታሪክ አመካኝተው የፖለቲካ አላማቸውን የሚሰብኩትን።
ከላይ ከተራራው የፈለቀ ውሃ ያገናኘው፥
በንግድ ልውውጥ ወንዝን ተከትሎ የተመላለሰው፥
ከጊዜ በኋላ፥ በጂኦግራፊ ክልል የተለያየው፥
አንድ አገር አንድ ሕዝብ እኮ ነው፥
ኑቢያ፥ ኩሽ፥ ኢትዮጵያም ተብሎ የሚጠራው።
በችኮላ ከተጻፉ አድሎአዊ ታሪኮች ባሻገር፥
ያስፈልጋል፥ ጠለቅ ብሎ ማጤን፥ መመራመር፥
ታሪክን በማዛመድ ከሕዝቦች ስደት ጋር።
ተከዜን ተከትሎ፥ እስከ አባይ መጋጠሚያው፥
ቆለኛና ደገኛ፥ እየተጋጨ ነበር ኑሮው፤
የክርስቲያኖች ቅርጻ ቅርስ በኢትዮጵያ የሚታየው፥
በሱዳንም ነበረ፥ እስልምና እስኪያወድመው።
አሁንም በሜሮ እና በሌላም ሥፍራ ይታያል፤
የፈራረሰው የአምልኮት ሥፍራ ይመሰክራል።

የሜሮ ጥንታዊነት ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት፥
ቀዳማዊ ሚኒሊክ፥ የካህኑ የሶዶቅ ልጅ - አዛርያስ እና ጭፍሮቹ ያረፉበት፥
ከሰረገላ ታቦቱን አውጥተው፥
እጆቻቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው፥
ወደ መሬትም እየተደፉ፥ እግዚአብሔርን ያመሰገኑበት፤
ይህንን ታሪክ ማን ይመስክር፥
ማነው ይህንን የሚያውቅ ከታቦቱ በስተቀር።

ታዲያ፡- ቀድሞ የነበረ አይሁድነት፥
ሲተካ በክርስቲያናዊነት፥ እስላማዊነትም ሲታከልበት፥
አክሱማዊነት ተረስቶ ተተካ እንዴ በሱዳናዊነት?
ዛሬ ሱዳን የተባለ መሬት፥
እንዴት ነበረ ከመሐዲና ከዮሐንስ (አራተኛ) ውጊያ በፊት?..

ማን አፋቸውን አፍኖ ያዘው የሱዳኖችን፥
"እኛ እኮ አንድ ሕዝብ ነን!" የሚሉትን።
ሜሮዌ፥ ኑቢያ፥ ናፓታ ወይም ጥንታዊት ፑንት፥
በሰሜን አፍሪቃ አንድ ታላቅ አገር - ብዙ የተወሳላት፥
የአይሁድ፥ የክርስቲያን በኋላም የእስላም መሬት፥
የአሁኗን ኢትዮጵያን አይጨምርም ለሚሉት፥
ለምን እንደማይጨምር መረጃውን ያምጡት።
አሊያም፥ ከአዳምና ሔዋን የጀመረውን፥
የሰውን ዘር እንደ ሰንሰለት፥
የነገሥታቱንም ነገር ይመርምሩት።

ልጅ ኦሪ (አራም) ከ4470 ዓመተ አለም በፊት፥
በዚችው በኢትዮጵያችን የጀመረ መንግሥት፥
ከቀዳማዊ ምኒሊክ እስከ ክርስቶስ ልደት፥
ነገሥታት ቢቆጠሩ፥ በአጠቃላይ መቶ ስልሳ አምስት (?)
ይህ እና የመሳሰለው ታሪክ የሚነገርላት (የሚጻፍላት)፥
ማነች እሷ? ረጅም የታሪክ ሰንሰለት ያላት።

አብርሃና አጽብሐ፥ ከሶፍያም ጋር ከእናታቸው፥
ክርስትናን ተቀብለው፥
ሌሎችም የክርስቲያን ነገሥታት ተከትለው፥
እስከ ኤዛና ድረስ ሰላሳ አንድ ነገሥታት ነግሠው፥
ከኤዛናም ካሌብ ተቀብሎ፥
እስከ አራብያ ግዛቱን አጠናክሮ፥
የልጅ ልጁም፥ ገብረ መስቀል ለክርስትና ተጋድሎ፥
ከዚያው (ከአራቢያ) የተወለደ የልጅ ልጁ ነጋሲ
ነቢዩ ሙሐመድን አስተናግዶ፥..........
ከካሌብ ጀምሮ የተከታተለ ሃያ ሦስት የክርስቲያን ነገሥታት፥
ቢቋረጥም በዩዲት (ጉዲት)?
ቢቃጠሉም ቤተ ክርስቲያናት፥
እንዲሁም ቅዱሳን መጻሕፍት፥
እነ አንበሳ ውድም፥ እነ ድልነአድ፥
ክርስትናን ለኢትዮጵያ መለሱላት።
የሰለሞን የዘር ሐረግ ቢቋረጥም በዛጉኤ መንግሥት፥
በመራ ተክለ ሃይማኖት፥
እጅግ ተጠናከረ እንጂ አልተዳከመም ክርስቲያናዊነት።
የእስላም ሃይማኖት በአለም ዙሪያ በተጠናከረበት ወቅት፥
በቅዱስ ላሊበላ ተገነቡ አስራ አንድ ቤተ ክርስቲያናት።
ከ1270 እስከ 1529 ዓ. ም. ቢቋረጥም፥ የንጉሥ ሰለሞን የዘር ሰንሰለት፥[51]
በይኩኖ አምላክ እንደገና ተቀጠለ፥ የዛጉዌ መንግሥት ሲወድም በጦርነት።

---

[51] ይህንን ነገር በጥልቀቱ እንመልከት፡- ዳዊት በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደነገሠ፤ ልጁም ሶሎሞን በአባቱ እንደነገሠ፤ ንጉሦች ከዚህ ስርወ መንግሥት ጋር ቢዛመዱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዳገኙ ነው የሚቆጥሩት። በዚህም ምክንያት፥ እነርሱ (ነገሥታቱ) በፈሪሃ እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲያስተዳድሩ፥ ታላቅ ሃላፊነት ይሰማቸዋል፤ የአስተዳደር ብቃት፥ መንፈሳዊ ኃይል እና ጽናት ያገኛሉ። ሕዝቡም ይታዘዝላቸዋል፤

ለደሴ ከተማ በምትቀርብ ሃይቅ ከተባለች ሥፍራ፥
ኢየሱስ ሞዓ በተባለ አስተማሪ የተመራ፥
አቡነ ተክለ ሃይማኖት ብዙ ክርስቲያኖችን እንዳፈራ።
እምነትና ጽናት አንዱ ጸባይ የሕዝባችን፥
ዋልታና መሠረት ሆኖ ቆይቷል ያገራችን።
　　　　በዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያችን ተከፋፍላ አልቀረችም፥
　　　　ቴዎድሮስ አንድ አድርጓታል፥ በውድም በግድም።
ኢትዮጵያችንን እንዲህ ያጸናት፥
እንዲህ ለዘመናት አስተሳስሮ ያቆያት፥
የሕዝቦቿ ፍቅር እና አብሮነት።
　　　　ከጦርነቶችም ሁሉ ባሻገር፥
　　　　አሁንም አልጠፋ ብሏል የሕዝቦች አንድነት።
　　　　የሃይማኖት ጦርነት ሕዝቦችን ሲያስመርር፥
　　　　ከየመን፥ ከግሪክና ከሌሎችም አገሮች ግንኙነት ሲቀር፥
　　　　የኢኮኖሚ እድገት ሲገታ፥ በእስላም እና ክርስቲያን ፉክክር፥
　　　　የንግድ፥ የሥልጣኔም እንቅስቃሴ ሲታጠር፥
　　　　ኢትዮጵያም ከአለም ገለል አለች፥ ታዋቂነቷ እስኪሰወር።
ሱዳን በክርስቲያንነቱ ጸንቶ ቢቀር፥
መንፈሳዊ ታሪካዊ አንድነቱም አይለያይ ነበር።
የእስላምና የክርስቲያን ጦር ባይኖር፥
ባልተዘጋ ነበር የኢትዮጵያ በር።
　　　　ከአጼ ካሌብ እስከ ልብነ ድንግል፥
　　　　እስላም ከክርስቲያን ሲታገል፥
　　　　ከሕዝቦች እልቂት ጋር፥
　　　　መንፈሳዊና ሥጋዊ ሥልጣኔም ወድም ሲል፥
　　　　ቤተ ክርስቲያናት አያሌ መጻሕፍትም ሲቃጠል፥...
　　　　ሃይማኖት የምድራዊነት መሳሪያ ሲሆን፥
　　　　ታላቅ ፈተና ሲገባ፥

የሰውም ምድራዊ ኑሮ ብልሽት ሲል፥
በዳዊት እና በይስሃቅ፥
እንዲሁም በፈላስፋው ዘርዓ ያዕቆብ ብርታት፥
ሳይገታ ቀረ የክርስቲያን ሃይማኖት፥
እንዲህም ነውና እምነትና ጽናት።
መቼም የአንድ አገር ታሪክ ስለሆነም ነውና፥
እንደ ግለሰብ ታሪክ ወጣ ገብ የበዛበት፥
ኢትዮጵያን የአክራሪ እስልምና ተከታዮች ወረሯት፤
ኢትዮጵያ የነቢዩ መሐመድን ቤተሰቦች እንዳላስተናገደች፥
ባልተፈቀደላቸው የጀሃድ ጦርነት፥
ብዙ ጉዳትም አፈረሱ የግራኝ መሐመድ ጭፍሮች።
የግራኝ መሐመድ መገደል፥
ኢትዮጵያን ከከፋ ጉዳት ሲያድናት፤
የካቶሊክና የኦርቶዶክስ እምነት ልዩነት አናወጣት፥
ግን የሕዝቦች ጠንካራ ኦርቶዶክሳዊ እምነት፥
ከቅዱሳን እንደ ክርስቶስ ሳምራ፥
ከንጉሥም እንደ ፋሲለዳስ፥
ካቶሊካዊነትን ተቋቋሙት፥
በጽኑ የእምነት ጥንካሬ መንፈስ።
የባእዳኑ እምነት ሳይበግራት፥
የሀገራችን ተዋህዶ ኦርቶዶክሳዊነት፥
እስልምናም ቢሆን ፖለቲካ ያልገባበት፥
የሕዝቦች ጠንካራ እምነትና ጽናት፥
ኢትዮጵያችንን አቆየልን በፍቅር እና በአንድነት።

**<u>ማስታወሻ ከቅርብ ጊዜ ኢትዮጵያችን</u>**

በቁንጽሉ ካቀረብናቸው የእምነት ግጭቶች ባሻገር፥
እጅግ የከረረ ነበር፥
የባላባቶችና የሥልጣን ፉክክር።

ባላባቶች አሽከር ቀጥረውና ጠብመንጃ አስታጥቀው፥
በውትድርናም አሰልጥነው፥ ለኃይል ክምችት በዙሪያቸው፥
ከድሃው ሕዝብ እየነጠቁ ሲወስዱ ለራሳቸው፥
በዚህም ክፉ ሥራቸው ሲበለጽጉ፥
ሲገን ስማቸው፥
አሽከር፥ ጭሰኛ፥ ጥገኛ ወታደር ሲበዛላቸው፥
ኢትዮጵያን ከፋፍለው ወሰዷት ለግላቸው።

በአጼ ቴዎድሮስ አንድነት ቢገነባም፥
በዳግማዊ ሚኒልክ፥ የአገር ድንበር ቢሰፉም፥
በአጼ ኃይለ ሥላሴ የባርያ ስርአት ቢጠፉም፥
ሕዝቡ ከባላባቶች አምባገነናዊ መንፈስ አልተላቀቀም።

ነፃነት በኢትዮጵያ ምድር እስኪነፍስ፥
ታጋይ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ እምነተ ጠንካራ እንደነ አቡነ ጴጥሮስ፥
ፋሺሊስቶችን ከመጡበት የሚመልስ፥..
ግን ኋላ ቀርነት ሲነግሥ፤
ሕዝቡም ነፃ እውጪ ነን በሚሉ ባላባቶች ማነቆ ሲያዝ፥
የመሻሻል ጊዜው ሲዘግም፥
አርሶ አደሩ፥ ላብ አደሩ በልቶ አልጠገበም፥
ጭቁኑ ሠራተኛ፥ ወታደሩ፥ ተማሪው ሲያጉረመርም፥
የዲሞክራሲን ጥያቄ በኃይል መግታት አልተቻለም።
እውን በመሆኑ፥ የለውጥ ጊዴታዊነት፥
አብዮታዊ ትግል ተቀጣጠለ ከያለበት፤
ተገረሰሰ የፊውዶ ካፒታሊስት ስርአት።

**ዳግመኛ ማስታወሻ ከዛሬዪቷ ኢትዮጵያችን**

በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል የፊውዳሎች ስርአት ቢወገድም፥
የፊውዶ ካፒታሊስት አስተሳሰብ በሶሺያሊስታዊነት ቢተካም፥
የቀድሞው ባላባታዊነት አይነት አምባገነናዊነት አልቀረም።
　　ሕዝቡም ያልደረሰበትን እንዲያውቅ ነፃነቱን፥
　　በእኩልነት አንድነቱንና ሰብአዊ መብቱን፥
　　በግንባር ቀደሙ በኢሕአፓ (ኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ) መሪነት፥
　　በየጊዜው ይበተን ነበር የዲሞክራሲያ መጽሔት፥
　　ስለ ለውጥ የሚያስተምር፥
　　ስለ ሕዝባዊ መንግሥት አስፈላጊነት፥
　　ሕዝቡ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት።
ኢሕአፓዎች በሕቡእ እየተደራጁ፥
ሕዝቡን እየቀሰቀሱት፥
ለከፍተኛ አብዮታዊ ንቃት አደረሱት።
ሌሎች ፓርቲዎችም እንዲሁ፥ ታግለዋል በመሰላቸው፥
ለኢትዮጵያችን የተሰዉላት፥ የሞቱላት ብዙዎች ናቸው።
　　ግን የወታደራዊው (የደርግ) መንግሥት፥
　　በኢሕአፓም በሕዝቡም ላይ ሲዘምትበት፥
　　ኢትዮጵያ ብዙሃን ወርቅዬ ልጆቿን ተነጠቀች በሞት።
የኢትዮጵያ ምሁራን፥ ጊዜ ያፈራቸው፥
በተራቀቀው ርዕዮተ አለማቸው፥
በሳል በሆነው ፖለቲካዊ እውቀታቸው፥
አብዮታዊው ፍልስፍናቸውና አለም አቀፍ ርዕዮታቸው፥
ቢታገሉ፥ ቢቆስሉ፥ ቢደሙ፥ ቢሞቱም፥
ጊዜን ተሻግሮ፥ ፈጥኖ መጣ ልዩ አይነት ሶሻሊዝም፥
በጠመንጃ አፈሙዝ የሚገዛ፥ ሰብአዊ ርህራሄ የሌለው፥
በግፍ፥ በኃይልና በጭካኔ፥ ደርግ ሕዝቦችን ገዛቸው፤
ወደ ጦርነት መራቸው፥ በእስር አሰቃያቸው፥

እስኪሟሽሽ አብዮታዊው መንፈሳቸው።

የአገር ኢኮኖሚም በጦርነት ድቅቅ ሲል፥
አገራችን በድህነት፥ በጭንቀት፤
ስትነድ፥ ስትቃጠል፥ ኤርትራ ስታዝን፥ ትግራይም ስትከተል፥
ወጣት ባላገር ከግብርና ሥራው ሲፈናቀል፥
ተገዶ ከቤተሰቡ፥ ከትዳሩ ሲነጠል፥
ምሬትና ሃዘን፥ ከአባትና ከእናት፥
ከወንድምና ከእህት፥ ከባልና ከሚስት፤
ሰቆቃና ጭንቀት ሆነ በያለበት።

አይረሳም ይህ (ያ) የደርግ ሞኝነትና ጀብደኛነት፥
የኢሕአፓና የሌሎችም ፓርቲዎች አንድነትን ማጣት፥
በደርግ ዘመን ለተፈጸመ ኢሰብአዊ ድርጊት የሆነ ምክንያት፤
ወገንን በወገን ላይ በማዝመት የደረሰ ጥፋት።

ከጥንትም አሳድጋ ያቆየች፥ ሰው እና እንስሳትን፥
ተንከባክባ ያስተናገደች ስደተኞችን፥
ጠብቃ ያቆየች፥ ሕዝቡን ነፃነቱን፥ ሃይማኖቱን፤
በሶሻሊስት የተዳቀለ አጓጉል ፍልስፍና አደቀቃት ኢትዮጵያን።


እንዲሁም ታስቦላት ነበረ አቴይስትነት፥
የእግዚአብሔር የለም ትምህርት፥
መንፈሳዊ ጎኗንም ጭራሽ ለማጥፋት።
ግን ተመስገን፤ በመንፈሳዊነቱ ጸንቶ ቀረ ሕዝባችን፥
ተምሳሌት ይሆን ዘንድ፥ ለአለማችን።

ኢትዮጵያውያን ቢሰደዱ፥
ቃሉን - የእግዚአብሔርን እንዳይረሱ፥
ታቦቱን ይዘው በአለም አዳረሱ።

አላካቸውም እንዳይረሳቸው፥
“ኢትዮጵያን ጠብቅልን” ነው፥
የዘወትር ጸሎታቸው።

# ምዕራፍ ሰባት

## የደረሰብን ስደትና መከራ



ስደት ከኢትዮጵያና ከኤርትራ

**መግቢያ**

ስደት፥ በክፉ ኃይላት የመገፋት ውጤት፥
ከአላስኖር ባዮች፥ ከጦርነቶች፥
ከድህነት እስከ ሰብአዊ መብት ማጣት፥
ስደት ከሰይጣናዊ ጠላት ሽሽት።

እየተቀየረ መጥቷልና ይዘቱ፥ መጠኑ፥ እጅግ ገዝፎ የስደታችን፥
አሳሳቢ ሆኗልና፥ የአኗኗር አቅጣጫችን፥
እስቲ የጊዜውን ሁኔታ እንመልከተው አብረን፥
አብረንም እንጩህ እንዲሰማ ጸሎታችን።

እናንተም የቀድሞ ስደተኞች፥
ተሰዶ፥ ተሳዶ መኖርን የቀመሳችሁ፥
ምንም እንኳን ዛሬን ቢደላችሁ፥
ከዛሬዎቹ ስደተኞች አይራቅ መንፈሳችሁ፤
የዛሬው ስደት ሆኗልና የሞት ሽረት፥
ቋሚና ሟቹ መሳ ለመሳ የሆነበት።

ከየትም አገር ቢሆን ከየት፥
ከፍቶት ካገሩ የተሰደደን ሰው እንዘንለት፤
በአካልም ባይሆን በመንፈስ እንድረስለት።

## የደረሰብን ስደትና መከራ

ችግር፥ መከፋትም ከጭንቀት ጋር፥ ሰተት ብሎ ሲገባ በየቤቱ፤
ለስደት ሲዳረግ ጎልማሳ፥ ወጣቱ፤
ያገር ሽማግሌ ባልቴቱ፤
አገር ለቆ፥ ተከታትሎ ሲሄድ፥
ዲያቆን መድረሳው፥ እስላም ክርስቲያኑ፥
ሼኩ፥ ካህኑ፥ ጳጳሱ ሳይቀር፥ ፓትሪያርኩ።

ስደት፥ ፍልሰት፥ እንደማይደርቅ የወንዝ ውሃ፥
ሠራተኛውንም ምሁሩን ካገር የሚያስወጣ።

እናት ልጇን “ሂድ እንተም ተሰደድልኝ” ብላ ስትመክር፥
አባትም የገዛ ልጆቹን “እናንተም ሂዱ...” እያለ ሲያደፋፍር።
መቼስ ካለ ተስፋ አይኖር ሰው፤
ባለ አገር ሆነን ሳለ፥ አገር እኮ ነው ያጣነው፤
አንድም ኖሮ፥ ኑሮን ለማስኖር ነው'ኮ ካገር የሚወጣው።
አይኖች ብዙ አይተው ፈዘዘዙ፥
ጆሮችም ብዙ ሰምተው ደነዘዙ፥
ልብና አንጎል ለየብቻ ዋሉ፥
ኢትዮጵያና ኢትዮጵያ ተከፋፈሉ፤
አብራኮቻችን እየቆሰሉ ተለያዩ፥
ማንነታቸውን ተነጥቀው ስለቆዩ።
ገና አፍ ሳንፈታ፥ በልቅሶ ብቻ ነበር መከፋታችንን የምንገልጠው፤
እስቲ አሁን ደግሞ በሰው ቋንቋ እንሞክረው፤
ስደታችን በውስጡ ያዘለውንም ጩኸት እንጻፈው።
ለሚሰማው፥ ሁለት አይነት ጩኸት ነው ያለው፡-
አንደኛው፥ ወደ ፈጣሪ ብቻ የሚጮህ፥ እጅግ ክብድ ያለ፥
የዝምታ ጩኸት ነው፥ መሬት የማይችለው።
ሁለተኛው፥ ባለአእምሮ ወደ ሆነ ሰው የሚጮህ፥
እጅግ ኃይለኛ ጩኸት ነው፥
ሰሚ ጆሮ ያለው ሁሉ ብቻ የሚሰማው።
እንዲህ ጩኸት በሁለት አቅጣጫ ሲያይል፥
የሰው ስሜቱ ይግላል፥ ይፈላል፥
እስከመቼ ታግሶ - ዝም ተብሎ ይቻላል?
የግፍ ሠሪዎች ሥራ እየተጻፈ ይቀመጣል፤
እግዚአብሔር ጩኸቶቻችንን ሁሉ ይሰማል፤
ለጊዜው ምህረቱ እንደ ሰማይ ይርቃል፤
ግን ጊዜ የወለደውን ጊዜ እንዲወስደው ያደርገዋል።
ኑሮ ሲወደድ፥ እያነሰ ሲመጣ ተካፍሎ የሚበላው፥

እንጀራና ወጥ ሲናፍቅ፥ ደግነትም ከፍት ሲለው፤
ጩኸት በዝቷል በያለበት ለሚሞተው።
አብሮ መኖር፥ አብሮ ማዘን፥ አብሮ ማልቀስም ሲያቅት፥
ሩጫ ሰላምና ነፃነት ወደሚገኝበት፤
ስደት - ከኢትዮጵያ፥ ከኤርትራም ሽሽት።

ስደትም አንዳንዴ አልሞት ባዩን የሚያሳድደው ይመስላል፤
ከሄዱበት ከደረሱበት አሳዶ ይይዛቸውና ይገድላቸዋል።
የሩጫው መነሺያ ሞት፥ መጨረሺያውም ሞት፥
የአሟሟቱም አይነት እጅግ የሚያስደነግጥ፥
ከማሳዘንም አልፎ የሚሰቀጥጥ።
ሕዝቡ አገር ለቆ ሲወጣ፥
ሲፈልግ፥ ሌላ አገር መጠለያ፥
በልዋጩ ሃይማኖቱን እንዲለውጥ ሲገደድ፥
“አልለውጥም፥ አልሰልምም” በማለቱ ብቻ፥
እጆቹን የኋሊት እየታሰረ ሲታረድ፥
“ኸረ የኔኮ ነው” ባይ እንደሌለው፥
እንደ አሮጌ እቃ ሲጣል መሬት፥
ተረካቢ ያጣ ሬሳ፥
ለሰማይ አሞራ ሲተውለት፤....
ይህ ዘግናኝ ጭካኔ፥
ሰይጣን ለምክንያት የፈጠረው፥
የሰውን ልጅ በቁሙ፥ በሞቱም አዋረደው።

አዛኝ - ደጋግ የኢትዮጵያ/የኤርትራ ልጆች አለቀሱ፥
የገዛ ደረትን እንደ ከበሮ እየደለቁ፥
እንደ ጭፈራ ወደላይ ወደላይ እየዘለሉ፥
እየተራወጡ እየተንፈራገጡ፥
መሬት ላይ እየወደቁ፥ ከዚያም እየተንከባለሉ፥
እራሳቸውን እየጎዱ አለቀሱ፤ አነቡ።

"ምን መጣ በሕዝባችን? ምን ተፈጠረ በአገራችን?" ብሎ የማይጠይቅ፥
በውስጡ ርህራሄ የሌለው፥ ከሆዱ ዙሪያ አልፎ የማይጨነቅ፤
ይህንን በአለም ያስተጋባ ጩኸት የማይሰማው፥
ሰምቶም የሃዘን ተካፋይ የማይሆን፥
በክህደት አለም ውስጥ የሚኖር፥
ወይንም ከዳተኛ፥ ከጠላት የሚወግን።
የሰውማ ነፍሱ ጠፍቶ አይጠፋም፤
እንደ ቅቤ በጸሐይ አይቀልጥም፤
እንደ ውሃ ጠብታ መሬት አይሰርግም።
ግን፥ አሸዋ ውስጥ ሰርጎ ስለገባ የአበሻ ደም፥
የኢትዮጵያ የኤርትራም ተራሮች ወሬውን አላስተጋቡም፤
መርዶው ስላልተሰማ ደም መላሽ አልተገኘም።
እንዳው እርር ድብን ብሎ ዝም።
ስደተኛ በሰይፍ ሲታረድ፥ በጥይት ሲገደል፥
ወደ ገደል ሲጣል፥ በእሳት ሲቃጠል፥
አመድና ጢስ ሆኖ ስለቀረው የአበሻ ሰውነት ብዙም አልተነገረም፤
ከራሳቸው አልፈው የማያስቡ፥ አፋቸው እንደተለጎመ ነውና ከጥንትም።
በአገራችን እንደ አብርሃም ደግ፥
እንደ ሄኖክና እንደ ኤልያስ ጻድቅ አልጠፋም፣
ግን ችግራችን፥ ጭንቀታችን አልታወቀም፤
መርዶው ለታዛቢዎችና ለተቆርቋሪዎች አልተዳረሰም፥
ስለዚህ፥ ሬሳ ቀባሪ አልተገኘም፤
ሰብእናችን በቁምም በሞትም አልተከበረም።
እንዳው እርር ድብን፥
ዝም የሚያሰኝ ሃዘን።



ንዳድ

## ንዳድ

ስደተኛ ድንበር ሲሻገር፥ ጎረቤት አገር ሲሰፍር፥

እንደ ድርጭት ወፍ እሽ እየተባለ ካገር አገር ሲባረር፥

ዱር አዳሪ ሲሆን፥

ጸሐይ ስታቃጥል መሬቱም ሲነድ፥

የግር ጉዞ በድብቅ፥

የቀን ሃሩር የሚያቃጥል፥
የበረሃ አሸዋ ፊት የሚያጮል፥
የሌሊት ውርጭ የሚጋረፍ፥
የስደተኞች ሰቆቃ፥ እንደ ስንቅ፥
ወይንም ሠርቆ እንደሚጠፋ ሌባ ፍርኃት።
ከባሕር ወደብም መድረስ የተቻለው፥
በሰአታት የሚቆጠረውን ጉዞ፥ በዓመታት አከናውኖ፥
በመርከብም የተጫነ፥ እንደ እቃ፥ በጠባብ ስፍራ ታጭቆ፥
በአየር እጥረት ታፍኖ፥
በማዕበል ተንገላቶ፥
የተረፈው ተርፎ፥ የሞተውም ሞቶ፥...
በገዛ ተስፋው እየተገፋ፥ አውሮፓም የደረሰ እድለኛ፥
የመሸበት መንገደኛ፥ ማደሪያ ያጣ ስደተኛ፥
አሁንም ሙሉ እንቅልፍ የማይተኛ።
ከባሕር የሰጠሙ ጓደኞቹ ትዝ ሲለው፥
ሆድ ሲብሰው፥ ሰውነቱን ሲከፋው፥
አእምሮውም በራሱ ሃሳብ ሲጨንቀው፥
ከሁለት ሃሳብ ተከፍሎ ሲሟገተው፥
የሞቱትን ጓዶቹን እድል ሲያስመኘው:-

> "እኔ ማን ነኝ?" ይላል፥ "ማነኝ እኔ ለብቻዬ?
> ተለይቼ ከጓደኞቼ፥ ከወገኖቼ።
> ይህ የማየው በገዛ አይኔ፥
> እኔን የሚመስል ሰው በዙሪያዬ፥
> መንፈሴን ገንጥሎ ከሥጋዬ፥
> በግድ የሚያናግረኝ፥ እንድዋሽለት "አልሞትኩም ብዬ"።
> ታዲያ እኔስ መሞቴን ካልረሳሁት፥
> በየትኛው አለም ነው ያለሁት?
> ይህስ፥ ይህስ፥ ከየት የመጣ ነው?፥ ይህ ቅጣት፥

ከእናትና አባቴ በወረስኩት ኃጢአት?
ወይንስ እኔው በሠራሁት።
መኖር ማለት እንደ ቆመ ዛፍ ባለ ሕይወት፥
ወይንም ተንቀሳቃሽ እንደ ድመት፥...
እንዲሁ፥ በሕይወት መቆየት፥
በሰው አገር ገብቶ መቃተት፤
እንዲህ ብቻማ ከሆነ፥ በሕይወት መቆየት፥
ቢታዘንም ቢለቀስም ለውጥ ካላመጣ፥
እንዲህስ ከምሰቃይ ከራሴ ውስጥ ልውጣ።”

ወገኔ ስነአይምሮውን አስተካክሎ መቀመጥ አቅቶታል፤
ኑሮው ከራስ ለመላቀቅ የሚደረግ ትግል ሆኖበታል፤
ፈዛዛ ደንጋራ አድርጎታል።
ግን ተስፋውና እምነቱ ተዋህደው ያጸኑታል፤
ሳያስበው በእጁም በልቡም ያማትባል።

ውይ! ሕመሙ፥ ጉዳቱ የስደቱ፤
ትዝታው፥ ፍቅሩ፥ ናፍቆቱ።

መጽናናትን የሚሹ ጽናትን ያገኛሉ፤
ተስፋና እምነትን ከልባቸው ያኖራሉ።
ደስታም የሚቀርበውንና የሚርቀውን ያውቃል፤
በውስጡ ተስፋን ይዞ የሚያዝን የሩቁን ያስተውላል፤
ተስፋ መስቀሉን ከፊት ለፊቱ ያስቀድማል።
የሃዘናችን መርዶ ከሰማይ ሰማይ ይዳረሳል፤
ጩኸታችን ከጠፈር ጠፈር ይስተጋባል፤
ልቅሷችንን መላእክት ይሰሙታል፤
ፈጣሪያችንም ይረዳናል።

ምድራዊ ኑሮ ከቶ አይገፋም ካለ ተስፋ፥
ጨለማው እስኪገፍ እጅግ የሚያለፋ።
ግን ማን ያውቃል? ለሁሉም ምክንያት ቢኖረው፥

ዛሬን ለኛ የማይገለጥ፥ የወደፊቱ ትውልድ የሚያየው።
ጥንትም፥ ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት፥
ከአብራካችን የወጣ የሰው ዘር፥
በአራቱም ማእዘን እየተሰደደ ነበር፥
አለምን ያዳረሰው ከዳር እስከ ዳር።
ጥንትም፥ ከምሥራቅ አፍሪቃ መነሻችን፥
ከአዳምና ከሔዋን ጀምረን፥
ይኸው እንዲሁ አለን፥ በአለም ዙሪያ እንደተዘራን።

ታዲያ፥ ይህም አነሰና ጥንት በየብስ የተዘራን፥
ዛሬም ከኤርትራ፥ ከኢትዮጵያ አገራችን፥
ስደት ሆኖ ቀርቷል እጣ ክፍላችን።
ከፊታችን ድቅን እያለ፥ ተስፋ መስቀላችን፤
በሄድንበት የራሳችንን፥ ማንነታችንን የሚያስንቅ አላገኘን።

የአለም ፖለቲካ ለአድር ባዮችና ለሃብታሞቹ አድልቶ፥
ሃይማኖትም ተወሳስቦ፥ በምድራዊነት ተነካክቶ፥
ከዚህም ከዚያም ጩኸት በረከተ፥ የስደተኛው ቁጥር እጅግ በዝቶ፤
ሕዝቦች ተቁነጠነጡ፥ ዘመን ከፍቶ።

ስሙን ስደት ቢሉት፥ እንደ ጥንቱ ሰላም ወዳለበት ሽሽት መስሏቸው፥
ምኑን ስደት ሆነ፥ መጠጊያ ሲሻ ሞት ለጠበቀው።
ከጥንት ጀምሮ እኛ እንደምናውቀው፥
ሰው የገደለ ብቻ ነበር ካገር የሚሰደደው፥[52]
ስደተኛው ጊዜያዊ መጠጊያ ሥፍራ ቢሰጠው፥
ለፍርድ እስኪቀርብ ተበቃይ እንዳያጠቃው።
ግን ጩኸት ሲቋማ በተቃራኒው፥

[52] “ነፍሰ ገዳዩ በማህበሩ ፊት ለፍርድ እስኪቆም ድረስ እንዳይሞት፥ ከተሞች ከደም ተበቃይ የመማፀኛ ከተሞች ይሁንላቸው።” ዘኍ. 35፥15

ገዳዩ (አሳዳጁ) እኮ ነው ባለአገር ሆኖ የቀረው።

እኛም ስደተኞች፥ ሥጋችን ከባዕድ አገር፥ ህልማችን ከሕዝባችን፥
ተምረን እንዳንደርስላት ለአገራችን፥
ያገር ዘመድ ናፍቆቱን በግዳችን ችለን፤....
እህ! ተመልሶ መግባቱንም እንዳናስበው አደረጉን።
በውስጥም በውጪም ወገኖቻችን ሲጎዱብን፥
መጥፎውን ስንሰማ ጆሮዎቻችንን ብንደፍን፥
ይወቅሰናል አእምሮአችን።
በእውን ያየነውን፥ እያስታወስን ታሪካቸውን፥
በሃዘን ላይ ሃዘን እየተደራረበብን፥
እንባዎቻችንን መግታት አቃተን፤
በየቀኑ ስናለቅስ አይኖቻችን ደከሙብን።

ሰውም ብቻውን ሲቀር፥
ከድቶት ሲሸሽ፥ ያ የሚያጽናና እንጉርጉሮ፥
ያ ዋሽንት፥ ማሲንቆና ከበሮ፤
ለሙታን እንደሚለቀስ ሙሾ፥
ሆድ የሚያባባ ሲሆን፥ ቅኝቱ ተቀይሮ፤...
ግጥም ገጣሚ ወንዱ ሴቱ፥
በወደድኩህ፥ በወደድኩሽ ፋንታ፥
ወደ ነጻነት፥ እኩልነትና አንድነት፥
ወደ አገሩ ሕልውና ሲሆን ትኩረቱ፥
አይ ስደት! ተረዳድቶ አብሮ በመኖር ፋንታ፥ እንግልቱ፥
ርህራሄና ፍቅሩ ተሸፍኖ በምድራዊነቱ፥
ውስብስብ የሰው ጠባይ ምክንያቱ፥
ከንቱ ፍላጎቱ ስግብግብነቱ።


እንጉርጉሮም ብሶቱን መግለጫያ ስሜቱ፥
እንደ ዋዜማ አይነት ሲመስል፥ ምልክቱ፥
የአዲስ አለም መለወጫያው፥ የምጽአቱ።

**<u>መራር እንጉርጉሮ</u>**

አገሬ እባክሽ የምትሄጂበትን ሥፍራ፥ መጨረሺያሽን ንገሪኝ፤
ለኔም ተስፋዬ እውነታ መሆኑን አሳውቂኝ።

ውሃ ሰውነቴ እስኪያልቅ ድረስ ተጠማሁኝ፤
አንጀቴም እስኪጣበቅ ተራብኩኝ፥
በመንገድ ብዛት ሰውነቴ ደከመብኝ፥
ቀኑ ጨለምብኝ።
አምላኬ እባክህ አትተወኝ፥
በቅዱስ መንፈስህ ምራኝ።
የመሸብኝ መንገደኛ ሆንኩኝ፥
ማነው ከቤቱ የሚያስገባኝ?
በኩባያ ውሃ የሚሰጠኝ?
ግማሽ እንጀራ የሚቆርስልኝ?
አምላኬ እባክህ ድረስልኝ፥
ረሃብና ጥማት ከሌለበት ውሰደኝ።
የሕዝቤ ተፈጥሮአዊ ደግነቱ ናፈቀኝ፥
አብሮ በመሆን መደሰቱ ታወሰኝ፥
አስደሳች መስተንግዶው ትዝ አለኝ፥
ርህራሄና ፍቅሩ ታወሰኝ፥
ምነው ሁሉም ነገር በቀረብኝ፤
መንፈሳዊ ጣዕምን ባጣጣምኩኝ።

አገሬ እባክሽ የምትሄጂበትን ሥፍራ፥ መጨረሺያሽን ንገሪኝ፤
ለኔም ተስፋዬ እውነታ መሆኑን አሳውቂኝ።



የሰሜን ተራራ

## ባቢሎን አይደለንም

እኛ'ኮ! ብንሰደድም ባላአገሮች ነን እንጂ፥ ባቢሎን አይደለንም። በሄድንበት ሁሉ የሚያጋጥሙን ሕዝቦች እኛን እንደራሳቸው የመቀበል ኃላፊነት አለባቸው። ማንም ሰው ተፈጥሮን የኔ (የራሴ) ነው ማለት አይችልም፤ ሁሉም የፈጣሪው ነውና።

ማንም ሰው "የሰሜን ተራሮች የኛ ናቸው፤ በውስጣቸው ያሉትም እነ ጃላዳ፥ እነ ዋልያ፥ ተኩላዎችና ቀበሮች፥ እነ አበበ እና ዘሪቱ፥ ሁሉም የኛ ናቸው.." እያለ መደንፋት የለበትም፤ ሁሉም የእግዚአብሔር ናቸውና። እነርሱ (ተፈጥሮ) ግን፥ አንድ ላይ ሆነው በጋራ መናገር ይችላሉ፤ እንዲህ እያሉ፦

"እኛ በተፈጥሮ የገዘፍን፥ የሰሜን ተራሮች ነን፤

ባቢሎን አይደለንም፤

እኛ ገበሬዎችን የምናጠግብ ማሳዎች ነን፤

በክፉዎች መንፈስ አልረከስንም፤

እኛ አክሱም እና ጎንደር ኢትዮጵያ ነን፤
ከፈጣሪያችን ፈቃድ ውጪ፥ ምንም ነገር አናደርግም።
በዚህም አካባቢ ያለ ሕዝብ ለየት ያለ ቢመስልም ከሌላው፤
ይህ በምድራዊነቱ የደረሰበት የሥልጣኔ እና ኢኮኖሚው፥
ለኩራት፥ ለግብዝና፥ ለእብሪት፥ ለመታበይ እና ለውዳሴ ከንቱ ካደረገው፤
በጦርነት ሰላሙን ማስከበሩ፥
አካባቢውን ለጥቂት የሰው ዘር ብቻ ማድረጉ ኃጢአት ነው።
ሰው ምንም ማድረግ አይችልምና፥ በገዛ ጉልበቱ ወይንም በጉብዝናው፥
ሰው በተገኘበት፥ በሁሉም ሥፍራ፥ የሰው ልጅ ቅዱስ ነው።
የእግዚአብሔር ነውና ሁሉም፤ ሥፍራውም ቅዱስ ነው፤
ተፈጥሮም (መሬቱ፥ ሳር ቅጠሉ..) ይከበርለት ዘንድ መብት አለው።

<u>የተሰወሩ ስዱዳን</u>


እህህህ! አገር ድንበር አቋርጠው፥ ስለተሰደዱ ብቻ አወሳን፤
የስደት መነሺያውን፥ ምክንያቱን ደባብቀን - ለአንባቢ ትተን።
"ሂዱ ያባታችሁን አገር ፈልጉ..." እየተባሉ የሚፈናቀሉ፥
ከኖሩበት ሥፍራ በየጊዜው፥
መጠጊያ አጥተው የሚንከራተቱ በገዛ አገራቸው፥
የእነርሱም የአገር ውስጥ ስደት መራራ ነው።
የተለያዩ ችግሮች ደርሶባቸው ስለሚማረሩ፥
ወደ እስር ቤት ለመታጀር ስለሚፈለጉ፥
በገዛ አገራቸው ስለሚሰደዱ፥
አንዳችም አላነሳን፤
አንባቢ ያውቀዋል ብለን።
አዎ! አንባቢ ያውቀዋል፥ ለመሰደድም አቅም አንሶት፥
ጊዜ ሞቱን የሚጠባበቅ መብዛቱን፥
የረሃብተኛው ቁጥር በየቀኑ እየጨመረ፥
በብዙ ሚሊዎን የሚቆጠር መሆኑን።

እኛም የተሰወርን ስዱዳን፥
ስለተሰወረን እንደ ሙታን ተቆጥረን - ተረሳን፤
በመሬት እምብርት በባህሮች ውስጥም የተጣልን፥
ማንነታችን ተቀይሮ የሰው አይን ያላየን፥
አዎ! እንዲህ ከቋሚዎችም ጋር የተደመርን - የምንመስል ሙታን፥
ብዙዎች'ኮ ነን - የማንታይ በሰዎች የተረሳን።
አዎ! እኛ የነፍሳት ነጠብጣብ፥
ጥቃቅን ብርሃናት ነን - ቦግ ቦግ የምንል ለሚያዩን።
እንደ እርግብ በሰማይ
በመሬት እንደ ጉንዳን።
ምን ትርጉም አለው፥
በአካል ምንስ ብንሆን ምን፤
ለማይቀር ሞት፥ የሉም ለመባል እያለን።
የሰው ልጅ ነፍስ ምንጊዜም ሕያው፥
ቢሞትም ሕይወት አለው፤
እኛም የተሰወርን፥ የማያቃጥል ሞቃት እሳት፥
ሰውነት ሳይኖረንም ነፍሳማ ሕይወት ያለን፥
ምንጊዜም በልበ ሕሊናዋ ታስበናለች ሀገራችን።

***አ! ቸሩ ፈጣሪ አምላካችን፥***
***እባክህ ማረን ይቅርም በለን፤***
***ከስደት ኑሮ አውጣን።***
***በአንድነትና በሕብረት ሠርተን የምንበለጽግበትን፥***
***ኢትዮጵያችንን/ኤርትራችንን ባርክልን፤***
***መልካሙን አስተዳደር አምጣልን፤***
***በሰላምና በፍቅር እንኖር ዘንድ እርዳን።***
***አሜን።***

# ምዕራፍ ስምንት

# ታሪካዊ ኩነቶች በኢትዮጵያችን



ትስስር

**መግቢያ**

መቼ አመማትና ትድናለች አይባልም፤
የኢትዮጵያችንስ ህመም አይካድም።
በእውነቱ ታማለችና ኢትዮጵያችን
እናድናት በፍቅር ተሳስረን።

## ታሪካዊ ኩነቶች በኢትዮጵያችን

የፈጣሪያችን ፈቃዱ ሆኖልን፥
የትግሉም መንፈስ ስላልተለየን፥
ደርግን አሽቀንጥሮ የሚጥል ኃይል ላከልን።
በኤርትራና በትግራይ የኃይል ቅንጅት፥
ኢትዮጵያም ኤርትራም ነፃ ወጡ ባንድነት።


ለኢትዮጵያችን ቀን ወጣላት ሲባል፥
አዙሪት መጣባት፥ ከድጡ ወደማጡ የሚጥል፥
ዳግማዊ ወያኔ ቢገለብጥ መንግሥት፥
መመሪያው ዘረኛነትና አድሎአዊነት፥
በጥላቻና በክፋት የበለዘ ርዕዮት።
ለብሔረሰብ ክልል ሲያወጡለት፥
ለ“ነፃነት” ኬላ ሲበጅለት፥
እጅግ ጥልቅ ሆነ የዘረኛነት ክፋት።
ኢትዮጵያችን ተከፋፍላ እንድትጠፋም እንደሆነ እቅዱ፥
ይህንን ታላቅ ሴራ ያልተረዱ፥
ብዙዎች ናቸው፥ ሳያውቁት የተጎዱ።

በዚህች ምድር የሰፈነ የ“ነፃነት” ጮራ፥
በማይፈለግ አቅጣጫ አመራ፥
ሕዝቡም የተደበቀ ክፋት መኖሩን ሳያውቅ፥
ነጻነቱ ከእኩልነቱ ጋር በአንድነት እውቅና ያገኙ መስሎት
ከፉኛ ተጎዳ፤ እጅጉን ተሰቃየ ባልሠራው ኃጢአት።

የዘረኛነት ጦርነት ተዳርዳር ተዳረሰ፥
ቀስ በቀስ "ነፃነት" እንደገና ደፈረሰ።
በእጅ አዙር ሰይጣናዊ ቅስቀሳ፥
ወንድም በወንድሙ ላይ እጁን አነሳ።
በአንዲት አገር ወዳጅ ዘመድ በበዛበት፥
ጥላቻ ነገሠ፥ እርስ በርስ ተጨራረሰ።

በወያኔዎች ሥራ ሕዝቡ አሁንም ደስ አላለውም።
ግን እግዚአብሔር ኢትዮጵያን አይተዋትም፤
ጥሩውን መንግሥት እስኪያመጣላት፥
ሕዝቡ ጸሎቱን አያቋርጥም - እስላሙም ክርስቲያኑም።

ከነኃጢአታችን እግዚአብሔር ቢወደን፥
የሰብአዊነት መንፈሳዊ እድገቱ እንዲፋጠን፥
አንድያ ልጁን ለኛ ሰጠን።
የእግዚአብሔር ሥራውና ስኬቱ፥
የመጨረሻውን ሰብአዊነት ለፍጹም ሰውነት ማብቃቱ፥
ቀኑም ሲቃረብ ምልክቱ፥
እግዚአብሔር በፍጥረቱ መደሰቱ፤
"ይህ" የታሰበልን አይቀርም፤
ለምን በኀሳና በሃይማኖት መከፋፈልን አንተውም?



ሰላማዊ ሰልፍ

## <u>ሰላማዊ ሰልፍ</u>

ከወያኔ የባሰ፥ ሲተካ ሌላ መንግሥት፥
ጥቂት ሰዎች ኢትዮጵያችንን የግላቸው አደረጓት፤
ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ይህ የቅርብ ጊዜ ክፉ ዘመን፥
የሰዎች እልቂት፥ ስደትና እንግልት፤
በሁሉም ሥፍራ በኢትዮጵያችን ላይ መከራ አበዙባት።


ስለ ኢትዮጵያችንስ ዝም ማለት ስላልቻልን፥
አደባባይ ወጥተን ጩኸቶቻችንን አሰማን፤
ስለ አንድነታችን ታገልን፤
ሰላማዊ ሰልፎችን በከተማዎች ሁሉ አቀጣጠልን፤
በኑሮአችን ለራሳችን ብለን ስንደክም፥
ለዘመድ ወገኖቻችን ማሰቡን አልተውነም፤
ሁላችንም ስለሁላችንም ብለን ተነሳን፤
ብልሹ አስተዳደርን ተቃወምን፤
አድርባይነትን፥ ዘረኝነትን እና ክፉነትን አወገዝን፤
ስለ በጎነት፥ ስለ ሰላም፥ ስለ ፍቅር እና ስለ አንድነትን ሰበክን፤፤
ለሌሎች ብለን ሕይወቶቻችንን እስከ መሰዋት ደረስን።

“ኢትዮጵያን ኬኛ፤ ቢሊሱማን ኬኛ፤
ኤኙ አዳ ኑባሴ? ደቺ ሁንዳ ኬኛ፤
ነምኒ ሁንዳ ተኩቹማ፤ ወጂ ወልቀብኔ ዴምና...” እያልን፥
ቅሬታዎቻችንን ሁሉ በተለያዩ ቋንቋዎች አሰማን፤
የሚሰማን አጥተን፤ ተመልሰን፤
የታደልን ስንገባ ከቤታችን፤
ያልታደልን ከእስር ቤት ተወረወርን።[53]

“ኢትዮጵያ ለኛ ካልሆነች ትፍረስ” ብለው የተነሱ፥
እርሷ ከጥንትም መንፈስ መሆኗን ናቸውና የረሱ፥
የነርሱን ንቃተ ሕሊና ስናከም ዓመታት አሳለፍን፤
ትግላችንም በሠፊው ሕዝብ እስኪታቀፍ በመቆየታችን፥
የከፈልነው ዋጋ ከአቅም በላይ ሆነብን።

---

[53] “አምላኬ ሆይ! ልመናዬን ስማኝ፤ ጸሎቴንም አድምጠኝ፤ ልቤ ተስፋ በቆረጠ ጊዜ፥ ከምድር ዳርቻ ወዳንተ እጮሃለሁ....።” መዝ. 60፡ 1-2



አልቃጠልም

## **አልቃጠልም**

ከዚያ ማዶ ቤት ይነዳል፤

አልቃጠልም የሚል ደፋር ቤት ከሩቅ ይታያል፤

የብርሃን ውጋጋን፥ ከቤቱ ውስጥ በደጃፉ ይሾልካል፤

አዎ! ቤታችንም ነዶ ተቃጥሎም አመድ ሆኖም፥

ተስፋ አለመቁረጥን አስተምሮናል፤

ያልሞተ ሰው እስካለ ድረስ፥ ታግሎ የመኖር ተስፋ ይኖራል፤

አዎ! የቢቶቻችን ቃጠሎ ብሩህ ተስፋን ሰንቋል;

እኛም እጸ ጳጦስ ሆነናል። [ዘጸአት 3፡1-15]

አዬ! መኖሪያ ቤቶቻችንን አቃጠሉብን፤
ትምህርት ቤቶቻችንን፥ ቤተ እምነቶቻችንን
ሰብሎቻችንን፥ ምርቶቻችንን፥
ሁሉንም አጠፉብን፤ በፈጸሙብን ግፍ፥ በደረሰብን መከራ እጅጉን ተጎዳን።
ኢትዮጵያችንን ክፉ ሰዎች ዘመቱባት፤
በውጪም በውስጧም አስጨነቋት።
ጠላቶቿ ሁሉ በአንድነት ተነሱባት፥
ሰይፋቸውን መዘዙባት።
አብረን እንዳልኖርን እኛን እንደ ባይተዋር ሲቆጥሩን፤
ሃብት ንብረታችንን ቀምተው፥
ነፍሳችንን ሊነጥቁ ሲያሳድዱን፥
ሕይወታችንን ለማዳን ብለን ጫካ ገባን።
ሕይወት ለማጥፋት ሲሯሯጥ፥ ወንድም የወንድሙን፥
"የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ፥ የእናቶች እርግማን፥
ማን ላይ ያርፋል? መጨረሻው ምን ይሆናል?" እያልን ስናዝን፥
በሕይወት መኖርና አለመኖር ትርጉሙ ጥፍት አለብን።
"እኛን አትግደሉን፥ አታቃጥሉን.." እያልን፥
ብሶታችንን በልቅሶና በዋይታ እናሰማለን፣
ተፈጥሮም በዙሪያችን ጆሮ ሆኖ ይሰማናል፤
አፍ አውጥቶም ከኛ ጋራ ይጮሃል፤
"አንቃጠልም.." ይላል።
እኛም ጠፍተን እንዳንጠፋ፥
እንደ እጸ ጳጦስ ሆነናል፤
በአካልም በመንፈስም ሥራ ጀምረናል።[54]

---

[54] "የጦር ዕቃችን ሥጋ አይደለምና፥ ጽኑ ምሽግን በሚያፈርስ፥ በእግዚአብሔር ኃይል ነው እንጂ። ልብ ሁሉ ይማረክ ዘንድ፥ ሕሊናም ለክርስቶስ ይገዛ ዘንድ፥ በእግዚአብሔር ላይ የሚታበየውንና ከፍ ከፍ የሚለውን እናፈርሳለን።" 2ኛ ቆሮ፤ 10፡ 4 - 5



እንባዎቻችን

## **እንባዎቻችን**

እስቲ እዩኝ የምታውቁኝ፥

አይታችሁ እዘኑልኝ።

እስቲ እዩት ተመልከቱት፥ አፈር የመሰለ ደም ግባቴን፥

እንባዬንም ተመልከቱት፥ እንደ ወራጅ ውሃ የሚፈሰውን።
　　መፍሰሱን እስኪያቆም፤ እንባዬ ይፈሳል፤
　　ስለ ክፉው ዘመን ማስታወሻ ይሆናል።
መልካችን ሳይጠፋ ከውስጣችን - አፈር መሰለ ቆዳችን፥
ቁንጅናችን ሳይረግፍ - ሳይለወጥ ማንነታችን፥
ወዛችን ተሟጠጠ፥ ቆረፈደ ገላችን።
ደስታችን ተሟጦ ኑሮ ሲከብደን፥
ሃዘን ምርጫችን መሰለብን።
ስናንጎራጉር፥ ስንዘፍንም እያለቀስን፥
የጥንቱን እያስታወስን።
"ስለ ሁሉ ክበር ተመስገን" ብቻ እያልን፥
ይኸው እስከ ዛሬ ኖርን፤
ለቀሪውም ዘመን እግዚአብሔር አምላካችን አለልን[55]።

[55] "ጻድቃን ጮኹ፤ እግዚአብሔርም ሰማቸው፤ ከመከራቸውም ሁሉ አዳናቸው፤ እግዚአብሔር በልባቸው የዋሃን ለሆኑ ሁሉ ቅርብ ነው፤ በመንፈስ ትሁታን የሆኑትንም ያፍናቸዋል። መዝ. 33፡ 17-18



ወንድ አልባ ቤት

## ወንድ አልባ ቤት


ዘመን ከፍቶ በዚህ ዘመን፥ ወንድ ጠፍቷል ከቤታችን፤
ቤት፥ ቤተሰብ፥ እናትና አባት ልጆች፥ አብሮ መሆን፥
ጥሩ የተባለ ሁሉ “ድሮ ቀረ..” የሚባልበት ጊዜ ደረሰን።
አዎ! በዚህ ዘመን፥ እንዲህ ሆኖ ቀርቷል የኛ ዘመን።

ሰው እንዳይሆን ብቻውን፥
በዝቶም እንዲባዛ - እንዲሞላ ምድሪቱን፥
አንድ አድርጎት ወንድና ሴቱን፥
ገና ከጥንቱ - ከአዳምና ከሔዋን፥
እንዲህ መልክ አውጥተን - ዥንጉርጉር ብለን
እንደመልካችንም ተለያይቶ መንፈሳዊነታችን፥
ሰው በሰው ላይ ሲዘምት አየን።

አዬ! አለመዝመትም እንደ ኃጢአት ተቆጥሯል፤
ነፍስን ለአገር መሰዋት መስዋእትነት ሆኗል፤
አቅመ ቢሶች ብቻ ከቤት ቀርተዋል።
አገር ለማዳን ሲባል፥
አባት ከቤት ወጥቶ ሄዷል፤
ወጣት ወንዶችም ዘምተዋል፤
እናትና ትንሿ ሴት ልጅ ብቻ ከቤት ቀርተዋል።

እኛን የሚያስተውሉ መላእክት አሉ፤
ዘመን ዘመናትም እኛን ያስተውላሉ፤
ጥቅልል ብራናዎች (scrolls) ይዘረጋሉ፤
ፎቶዎቻችን ከግርግዳ ይሰቀላሉ፤
ታሪኮቻችን እንደ ማስታወሻ፥
ለወደፊቱም ትውልድ እንደ ትምህርት ይሆናሉ[56]።

[56] "እግዚአብሔርም ለድሆች መጠጊያ ሆናቸው፤ እርሱም በመከራቸው ጊዜ ረዳታቸው ነው።" መዝ. 9፡9



ጦርነት

## <u>ጦርነት</u>

*ሳንወድ ጦርነት ውስጥ ገባን፥*

*መቋጫውን በጎ መንፈስ እየናፈቅን።*

*የጦርነትን መጥፎ ገጽታ ለማን ይነግሯል፤*

*ዝንጉርጉር ገጽታውንስ ማን ይረዳዋል?*

በሞት ጥላ የተከበበውስ ከየት ያመልጣል?
መልካሙን ስናልም ቀኑ መሽቶ ይነጋል፤
እውነት፥ ፍትሕ፥ ሰላምና ነጻነትን ሁሉም ሰው ይመኛል።
በጦርነት ውስጥ ጀግና ይበቅላል፤
ከጀግና ልብ እውነት ይፈልቃል፤
መሞትና አለመሞት ትርጉም ያጣል።

አንዱ አልሞ ሲገድል፥
አውሬ አድኖ የገደለ ይመስለዋል፤
የቆሰለ ሲወድቅ፥ በሕመሙም ሲያጣጥር፥
ጓደኛው ያነሳዋል፤ ወስዶም ያሳክመዋል፤
በጦርነት ለሞቱት ሁሉ ይለቀሳል፤
የአገር ገዢዎች የነገስታትም ልብ ይቀልጣል፤
ሕብረተሰብ ጭንቀትን ያረግዛል፤
በጦርነት ማን ይከስራል? ማን ያተርፋል?

ከጦርነት በኋላ ምን ይከሰት ይሆን?
ጥላቻ ተዘርቶ፥ ጦርነት ተወልዶ፥
ብዙ ሰዎች ሞተው፥ ሃብት ንብረት ወድሞ፣
ጦርነት መሬት እንደሚታረስ፥
የማይታይ ዘር እንደሚዘራ....።

ዘሩን የሚያበቅለው ዝናሙ የታለ፤
የፍቅር ቡቃያው ሲያቆጠቁጥ አልታየ።

የሕመም አይነቱ ብዙ ነው፤
ብቻ እንደካንሰር ያለ - የማይድን እንዳይሆን ነው የምንፈራው፤
ውሸት ተሸንፎ እውነት ነግሦ ማየትን ነው የምንሻው።

አዎ! ጦርነት አስቀያሚ ነው በራሱ፥
እልቂትን ፈጣሪ ነውና ሰውና ሰውን - ፍጅት እርስ በርሱ፤
ግን፥ የጦርነቶች ሁሉ መነሻቸው፥
ጠብና ጭቅጭቅ ስለሆነ፥ በጥሩውና በመጥፎው፤

የአንዱ እጅ መስጠት ለሌላው ግዴታ ነው።
ስለ እውነት የቆመ ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥም፤
ታግሎ ታግሎ፥ ደክሞ፥ ቆስሎ ቢሞትም፥
በታጋይ ስም ‘ሚታገል ቆራጥ፥
ተተኪ ታጋይ አይታጣም።
እውነትን በውሸት የሚመክት፥
ቢበረታ ጠላት፥
ለጊዜው ነው እንጂ አይቀርለት ሽንፈት።
አንዳንዴም ጦርነት፤ ሲቀሰቀስ፥
ካለ በቂ ምክንያት፥
እውነትም ውሸትም ይኖራል፥
ከዚህም ከዚያም ቤት።
እና! ከዚህም ሆነ ከዚያ - አንድ ሰው ሲገደል፥
የሰው ውሸታምነቱም አብሮ አይገደል፤
ደግሞም! ከዚህ ሆነ ከዚያ - አንድ ሰው ሲገደል፥
የሰው ክፉነቱም አብሮ አይገደል፤
ውሸታምነትና መጥፎነት ተገድለው፥
እውነትና ጥሩነት ብቻቸውን አይቀሩም፤
ቅራኔዎች እና ሰዎች አይነካጠሉም፤
ሰይጣን ሰውን በቀላሉ ለቆ አይሄድም።
ግን፥ በጦርነት መቋጫ፥
መጥፎነት ጠፍቶ (ተዳክሞ) ጥሩነት ቢያይል፥
ማን ነበር ልክ ማን ነበር አጥፊ አይባል፤
ያው ሰይጣን ነው እንጂ፥
ክፉ መሠሪ - ሰውን በከንቱ የሚያጋድል።
ታጋይ እና አታጋይ መንፈስ፥
ምንጊዜም ይኖራል በሰው መሃል፥
ለጦርነትም ቅድመ ዝግጅት ይከናወናል፤

የሰው አስተሳሰብ በሁለት ጎራ እንዲከፈል ይደረጋል፤
ይህ ምንጊዜም የነበረ፥ የረቂቃን ተንኮል፥
አስፈላጊ/አላስፈላጊ ጦርንርት አይባል፥
መሆን ያለበት፥ በሥጋዊ ሰው ብቻ ሳይሆን፥
እኛ በማናውቀውም ይወሰናል፤
ይኸም እስከ አለም መጨረሻ ስለሚቀጥል፥
ከፉውንም ከደጉ መለየት ያስፈልጋል።

እንግዲህስ  እኛም ስንቃረብ ወደ ድል፥
በይቅርታ እንጂ፥ በቂም በቀል አንቀጥል።
በሰው ሬሳ ልክ አይደለም ደስ የሚያሰኝ ድል፤
ከጥንቱም ግዴታ እየሆነበት ነው፥
የሰው ልጅ እርስ በርሱ የሚጋደል።

ትግል፡- እውነቱን እውነት ውሸቱን ውሸት ለሚል።
ስልጣን፡- አንድነትን ለሚጠብቅ የሕዝብ ወገን።
በረከት፡- ፈሪሃ እግዚአብሔር ላደረበት።
እውቀት፡- እግዚአብሔርን በመፍራት።
ደስታ፡- በክፋት ለማይረታ።
ሰላም፡- በእኩልነት፥ በነጻነትና በአንድነት፥
ምድራዊ ሕይወትን በዲሞክራሲ ለሚያጣጥም።
እድገት፡- በአዎንታዊነትና በምስጋና፥ በረከት ሲጨመርበት።[57]
አሜን፥ መፃኢያችን ጥሩ ነው የሚሆን፥
ጠባቂ አለ ለሁላችን።

---

[57] “እናንተስ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል” ማቴ. 6: 33



ሰላምን ፈጣሪዎች

## <u>ሰላምን ፈጣሪዎች</u>

"ሰላም ነው?" አትበሉ ሰላም የለም ባገር፤

ከማይመስል ወሬ፥ ስብከት እና ምክር፥

ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ - ማስመሰሉም ይቅር!

እስቲ ምናለበት ሰው ሃቁን ቢናገር!

ሰላም ሲናፈቅ፥ ፍቅር ሲጠራ ከሩቅ፥
ሰው እና ሰው እንዳይተላለቅ፥
በአንድ ባንዲራ - በአንድ ሰንደቅ፥
ሁሉም ክብሩን ነጻነቱን እንዲያውቅ።

እርስ በርሳችን እየተያየን፥
መተዋወቅ፥ መለማመድ አብሮ መኖር ኢቃተን፤
"እኛም" ሰላምን የምንፈጥር ሰላም አጣን
የሰው ልጅ ለሥጋው ባያደላ እጅጉን፥
በጾም በጸሎት ቢያጠናክር መንፈሳዊ ጎኑን፥
ሰላምን ማምጣት እንዲህ ከባድ አይሆን።
እንኳን ሰውና ሰው፥ ሰውና አንበሳም አብሮ መኖርን ይችላል፤
የዳናኤልን ታሪክ ያስታውሷል።[58]

*"ተኩላ ከበግ ጠቦት ጋር ይሠማራል፤*
*ነብርም ከፍየል ጠቦት ጋር ይተኛል፤*
*ጥጃና በሬ የአንበሳ ደቦልም በአንድነት ይሠማራሉ፤*
*ታናሽም ልጅ ይመራቸዋል።" ኢሳ. 11፡6*

[58] "አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ፤ እነርሱም አልቧጨሩኝም" ዳን. 6፡22



የአርበኝነት ጅማሬ

## የአርበኝነት ጅማሬ

ነፋስ እንደሚነፍስ፤

የሚመጣበትና የሚሄድበትም እንደማይታወቅ፥


የሰው ሃሳቡም ከወዲያ ወዲህ ሲነፍስ፥

የሃሳቦች ማዕበል እንደ ውሃ ሲፈስ፥

ህብረተሰቡን ሁሉ ሲያምስ፥ ሲያተራምስ፥
የከፋት፥ የጥላቻ ነፋስ በየመንደሩ፥ በየቀዬው ዙሪያ ሲነፍስ፥
ሰው ሁሉ ከዳር ዳር በጦርነት ወሬ ሲታመስ፥
ከፋትና ደግነት ሲንገዋለል፤
የማይታየው የመንፈስ ሥራ ሲያይል፤
እስላም የለም፥ ክርስቲያን የለም፤
አይሁድ የለም፤ ሂንዱ የለም፤
የሰው ልቡ ሃይማኖቱን ይነግረዋል፤
ከእውነት እንዳይርቅ ይመክረዋል፤
ሳጥናኤል ከሰማይ በታች ወድቋል፤
ፍቅር ብቻውን ያሸንፍ ዘንድ ተሰናድቷል።

        የሃሳቦች ሸክም እጅግ ሲከብድ፥
        ለአቅመ አዳም የደረሰ በማይቋጭ ሃሳቡ ሲጠመድ፥
        የአንጎል መደበኛ ሥራው ስለ ጦርነት ማሰብ ሲሆን፥
        የአናሳ ወንድ ልጅም ማንነት ሲፈተን፥
        ከእናቱ ከእህቱ ጋር እንዳይውል  ከቤት፥
        ከሞቀ ቤቱ ወጥቶ ዱር እንዲገባ፥ ሳር ቅጠሉ ሲፈርድበት፥

የማይችለውን ሸክም እንዲሸከም ሲታዘዝ፥ በለጋ እድሜው፥
ጊዜያዊ መጠጊያ መሰደጃያም ሥፍራ ሲጠፋው፥
“እኔም ባቅሜ፥ የት ሄጄ ልታገል?” እንዲል፤
በእርግጥ ጦርነት የሃሳብ ሸክም እንደሚያቀል፥
ከጠብ መንጂያ አፈሙዝ ነጻነት እንደሚወጣ ይታየዋል፤
ታዲያም! ሀገር ለማዳን ቆርጦ ይነሳል፤
የወንድ ልጅ የማንነቱ እሳቤ፥
የጭንቀቱም መንሳኤ፥
በዚህ የአርበኝነት - የጀግንነት ጅማሬ በፋኖነት ይቋጫል።



ተስፋ

## ተስፋ

ከሩቅም ከቅርብም ሳስተውል፥
ከተራራው ተቀርጾ ልክ እንደ ስዕል፥
ታየኝ የመርከብ ምስል።
አዎ! እርሷው ነች፤
ተሰብራ፥ ተሰባብራ፥ ህልውናዋ ጠፍቶ፥
መላው አከላቷ ወደ አፈርነት ተለውጦ፥
አዎ! እርሷው ነች - በእርግብ አይን እይታ የታየች፤
ጊዜ ጠብቃ የተከሰተች፤
ለሰው ልጅ ደግ እንዳልሰራች፥
ዘመን አሻግራ ለወሬ ነጋሪ በትንሹ የተረፈች፤
ከአንድ አጣብቂኝ ሥፍራ ተወስና የቀረች፥

ያቺ የኖህ መርከብ ተብላ የምትጠራዋ፥
አዎ! እርሷው ነች።
ሰውም እንስሳም እንዳይጠፋ፥
ሁሉንም በጉያዋ ታቅፋ፥
መጥፎውን ዘመን አሳልፋ፥
ለሰው ልጅ የሆነችው ተስፋ፤
ለፍጥረታት ሁሉ የምህረቱ ምልክት የሆነች፥
ሰላምና ምህረትን ከአውደ ምህርቱ ያወጀች፤
አዎ! እርሷው ነች።
ታዲያ፥ እንዲህም ሆኖ፥
ያ የጥንቱ ሰው ከመርከቢቱ ጉያ ወጥቶ፥
ወደ ሜዳው ዘልቆ ሲኖር ተንሰራፍቶ፥
እህል ዘርቶ ያመረተውንም በልቶ፥
ከመደሰቱ እና ከመባዛቱ፥
እጅግ ተበራከተ ኃጢአቱ።
ከሰው ጋር እንስሳት፥ ከአእዋፋት ጋርም እጽዋት፥
ሁሉም እንዲጠበቅ - እንዲኖር በህብረት፥
ከሰማይ አካላት - ሰላም በምድሪቱ፥
ላመነበት ተስፋ ተሰጥቶታል - በቀስተ ደመናው ምልክቱ።
እኔም እርግቢቱ ጥንት የሕይወት ተስፋ'ሚሆን፥
ቅጠል በጥሼ ለኖህ እንደሰጠሁ፥
ዛሬ ደግሞ የሰላም ተስፋ'ሚሆን፥
ቅጠል በጥሼ 'ምሰጠው ሰው ባገኝሁ፥
እያልኩ በስሜታዊ ጉጉት ተጠመድሁ።
ከአእዋፍ መካከል እኔ ተመርጬ፥
መንፈስ ቅዱስ ያደረብኝ፥
የሰላም ምልክት መሆኔ ትዝ - ትዝ እያለኝ፥
የምድር ሰላም እጦት እጅጉን አሰጋኝ።

ከኖህ መርከብ እስከ መስቀሉ፥
ምህረት ተሰጥቶ ለሰው ልጅ ሁሉ፥
ሰውም ካልተዛዘነ እርስ በርሱ፥
ዝም አይሉም ነፍስ ያላቸው ሁሉ፥
ይንቀሳቀሳሉ ለህልውናቸው ሲሉ።
ስለ እውነት መስካሪ፥
የአምላካችንን ተስፋ አብሳሪ፥
መቼ ጠፋና አስተማሪ፥
ተስፋ ሰጪ እንደ እርግቢቱ፥
እንዲባረክ እንዲቀደስ ሕይወቱ።

ከወዴት ነው ተስፋችን የሚገኘው?
ምነው የሰው ልጅ ትምህርቱ አልገባ አለው?
ህመምተኛ ሲሆን - በምድራዊነት በጭንቀቱ፤
ለምን አይማርም ከስህተቱ?
የሰው ልጅ በውሃ ካልጠፋ፥
እኔ በኑክሊየር እሳት ላጥፋው ብሎ መነሳቱ፤
የአዝማሚያው አስጊ መሆን በዛሬ እና በነገ ሂደቱ፥
በየአገሩ፥ በየክልሉ፥ በየመንደሩ፥
ለሰው ልጅ ራሱ ሰው ሲሆን ጠላቱ፥
በዚሁ ከቀጠለ - በመጥፎው ድርጊቱ፥
እጅጉን ያሰጋል፥ ተሰባብሮ እንዳይቀር እንደ መርከቢቱ።

**ያውና ምልክቱ**

አ! የቀስተ ደመናው ተስፋ ምልክቱ፥
መስቀሉንም ይዞ መምጣቱ፤
ከሩቅ ይታያል - ሰባቱ ቀለማቱ፤
እንዲሁም ጎልቶ የሚታየው፥
በተለይ አረንጓዴ፥ ቢጫና ቀይ፥

ሦስቱ ቀለማቱ፥
እጅግ ድምቅ ያሉቱ፥
ብሩህ ተስፋ ለኢትዮጵያ እንዲሁም ለአለም፥
ሰላምን ወዳድ ለሆኑቱ።


    ቀስተ ዳመና ለሰው ልጅ የተስፋ - የድኅነት ምልክት፥
    ከጥንትም ነቢያት እንደተነበዩት፥
    ከሰማዩ አልጠፋም፤ ከልባችንም ጨርሶ አልተሰወረም፤
    መጥፎ ጊዜ ቢመጣም፥  ዘመኑ እጅግ አስከፊ ቢሆንም፥
    በሰላሙ ንጉሥ (ኢየሱስ ክርስቶስ) የተሰጠን ሰላም፥
    ለኛ ላመንበት ምንጊዜም አይጠፋም።

ከኖሕ የጥፋት ውሃ ዘመን በኋላ የነበረ፥
የእርግቢቷ ሰላም፥ የቀስተዳመናው ተስፋ፥
እንዴት አሁን ከኢትዮጵያችን ይጥፋ?

    አይቀርም ከፉው ቀን መጥለቁ።
    አለ፤ ይታያል፥ ብርሃን ይሰርጻል በስንጥቁ፤
    ቀስ እያለ ቦግ ይላል ደማቁ።[59]

---

[59] “ጻድቃን ጮኹ፤ እግዚአብሔርም ሰማቸው፤ ከመከራቸውም ሁሉ አዳናቸው፤ እግዚአብሔር በልባቸው የዋሃን ለሆኑ ሁሉ ቅርብ ነው፤ በመንፈስ ትሑታን የሆኑትንም ያድናቸዋል።” መዝ. 33፡ 17-18





የእንባችን ማህተም

## የእንባችን ማህተም

እማዬ አልቅሺ! አልቅሺ!

እንኳን ሰው ሰማይ ያለቅሳል፤

በምድር ላይ ግድያ በዝቷል።

እማዬ አልቅሺ! አልቅሺ! ይውጣልሽ፤
ዘጠኝ ወር በሆድሽ፥
እስከ አቅመ አዳም በእቅፍሽ፥
የሰው ዘር እንደ ነፋስ ሽው አለ ከፊትሽ፤
ሃዘን ትካዜን ላንቺ ለሴቲቱ ተወልሽ።

የወንድ ልጅ እንባ በሆዱ ነው፤
ለኃጥአን የመጣ ቅጣት አያልፈው።
እማዬ አልቅሺ! አሁንም አልቅሺ!
ሰውን ለማስለቀስ ሰበቡ ብዙ ሆነ፤
ሰው በሰው ላይ ጨከነ፤
ምድራዊ ሕይወታችንም በከንቱ ባከነ።

በአእምሮአችን ሃሳብ ተጨነቅን፥
በሥጋችንም ጉዳት ተሰቃየን፤
በሃሳቦቻችን አንድነትን ፈጠርን፤
የጋራ መፍትሄ በመፈለግ ደከምን፤
“እኛ እናውቃለን” በሚሉ ልሂቃን ተሰላቸን፤
የልባችንን ተናግረን በእንባችን ማህተም እንቋጫለን፤
ሰው ባይሰማን፥
የሰው ያልሆኑ ጆሮዎችም አሉ በዙሪያችን።

በውስጥ እና በውጪ ሴረኞች፥ በክፉ ኃይላት ርብርብ እና አንድነት፥
በምድራዊ ሥልጣኔ ሂደቱና ግስጋሴው ፍጥነት፥
በሚታይና በማይታዩ ጦርነቶች ውስጥ ብዙ ስለቆየን፤
ነፍሳችን ከሥጋችን እንዳትለያይ፥
የስጋት ኑሮ ብቻ ሆነ ኑሮአችን።
ግን፥ የብዙ ራሄሎች እንባ በአለም ዙሪያ የሚፈሰው፥
ወደ ሰማይም የሚረጨው፥
እናውቃለን አንድ ቀን ምላሽ እንደሚኖረው።



መልእክት ከጨረቃ

**<u>መልእክት ከጨረቃ</u>**

አ! የኢትዮጵያ ልጆች ተጨነቁ በመላ እድሜአቸው፤
ከጀርባቸው ጠላት (ሰይጣን) የሚሠራባቸው አልገባቸው፤
ግን ተስፋ አይቆርጡም - ስለ እውነት ሲታገሉ ያልፋል ሕይወታቸው፤
ለቀጣይ ትውልድ ይሸጋገራሉ እውነቶቻቸው።

በአለም ዙሪያ ስለ ጦርነት ብዙ ወሬ ይሰማል፤
ኢትዮጵያችን በጦርነቶች ተቃጥላለች፤
ፖለቲከኞች አፋቸው ያለማቋረጥ ይለፈልፋል፤
የኢትዮጵያኖችም ስሜት እርር ብግን ብሏል፤
እውነቶች ከውሸቶች ጋር ተናንቀዋል፤
ከአንዳንድ ሥፍራም ተጣምረዋል - እንዲሁም ተዛምደዋል፤

ነገር ሁሉ በምንደኞች ተጣሟል፤
አንዱን ከሌላው መለየት አስቸግሯል፤
ጀግናው፥ አዋቂ ነኝ ባዩም ብዙ ያወራል፤
የኢትዮጵያ ገበሬ ጦሙን ያድራል።
አሸናፊው እስኪለይ ሰው ሁሉ ግራ ተጋብቷል፤
በሰውና በመናፍስት መካከል፥
የሰልፍ ልውውጥ ይደረጋል፤
ይህም ለሚታየው ብቻ በገሃድ ይታያል፤
ለማይታየውም የግለሰብ መንፈስ፥
ከሀገር መንፈስ በላይ የሆነ ይመስለዋል፤
ሰው ሁሉ (ሃብታሙም ድሃውም) መጨረሻውን እስኪያውቅ ይቁነጠነጣል፤
ክርክር እና ጭቅጭቅ  እንደ ተራ ንግግር፥
እንደ የጧት ጸሎት ተቆጥሯል።

ነቢዮችን ጠየቅናቸው፥
ጨረቃ ቀድማ ነገረችን
የጨለማ ብርታቱ ጸሓይ እስከትጠልቅ መሆኑን።

ጨረቃ ስትወጣ ጨለማ ይረታል፤
እውነት ግልጽ ይሆናል፤
የበላይ ገዢ የመንፈስ ኃይል መኖሩን፥
ምንጊዜም አሸናፊው ጥሩው መሆኑን፥
ይህንን አውቀው ተገንዝበው ያልተረዱ፥
የሰልፉን ልውውጥ ሲመርጡ ተወናበዱ፥
ከፉዎች ያልሆኑም ያላወቁ፥ ስላላወቁ ተጎዱ።[60]

የባለ ጊዜዎች ሰርግና ምላሽ - እንዳው እችክ፥ ምንችክ፤
የአስረሽ ምቺው የተቀማጠለ ኑሮ፥

---

[60] ምስጉን ነው፥ በዝንጉዎች ምክር ያልሄደ፤ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፤ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ።

ለውጪ ተመልካች- የሚሰቀጥጥ፥ የሚታክት።
ምድራችን በክፉው መንፈስ ብትወጠርም፥
በየአህጉራቱ ሥቃዩአን ቢያሳያትም፥
የሰው ጭንቀቱ እየከፋ ቢሄድም፥
የመዳናችን ቀኑ መዳረሱ (መምጣቱ) አይቀርም።

እንደ ጧት ጸሐይ የእውነት ብርሃን፥
በሥፍራዎችና በአህጉራቱም ሲፈነጥቅ የምናየው፥
በእውነት ኃያሉ እና ቅዱሱ መንፈስ እውነት ነው።
በማያቋርጥ ጦርነት ህዝቡ ሁሉ ሲማረር፥
ለማን ይቻለዋል፥ ክፉውን ወደ በጎ መቀየር?
እባክህ አምላካችን ፊትህን ከኢትዮጵያችን አታዙር።

የእኛ የሁላችን የዝምታ ንግግር፥
ወደ ላይ ከፊ ከፍ ሲል፥
እንኳን እግዚአብሔር ጨረቃ ትሰማለች፥
ከብርሃኗ ጋር አዲስ ተስፋ ትረጫለች፤
ለሚሰማት በጎ ምሥጢር ታበስራለች፤
በደማቅ ቀለሟ እውነታዎቿን ታፈሳለች፤
በድምጽ አልባ ንግግሯም ታጽናናለች፤
የወደፊቱንም ስትናገር እንዲህ ትላለች፡-

“የጦርነቱን መጠናቀቅ በተስፋ ጠብቁ፤
የኢትዮጵያን መሬት ሁሉ የሚረግጡ፥
የሰው ልጅ እግሮች ሁሉ መሆናቸውን እወቁ።
ከኢትዮጵያ ክልል ተፈጥሮ፥ ከዚያም ለቆ የወጣ፥
ጠቅላላ የሰው ልጅ በፍጥረቱ፥
አይቀርም አንድ ቀን እናት አገሩን መሻቱ።”

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የሶዶቅ ምክር



ሶዶቅ

**<u>መግቢያ</u>**

ትዝታና ታሪክ ወደ ኋላ ባይመልስም ጊዜን፥

እናስተውል የዛሬ ሶስት ሺህ ዓኣመት የተመከረውን፥

ዛሬም ለኢትዮጵያችን የሚጠቅማትን።

አገራችንን እግዚአብሔር እንዲጠብቃት፥

ሕዝቦቿም እንዲያገኙ በረከት፥

የካህኑ የሶዶቅ ምክር ለኛም ይሁነን ትምህርት።

የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን ያሠራውን፥
ናቡከደናጾር ቢያቃጥለው ቤተ መቅደሱን፥
ዋናው ታቦት ከዚያ ቀደም ብሎ ወጥቷል፤
ለታቦቱ ታማኝ - አንድ አይሁድ ቄስ ሶዶቅ ወስዶታል፤
ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ይዞት፥ ወደ ኢትዮጵያ ምድር አመጥቶታል፤

ከዚያ ከአንድ ሥፍራ - ከአክሱም ተቀምጧል።

እና፤ ይኸው እስከዛሬ አለ ከኛ ጋራ፥

ስራዓተ አምልኮን የምናከናውንበት፥

እምነታችንን የምናጸናበት፤

የአኗኗራችንም መሠረት ሆኖ የቆየበት፥

የፈጣሪአችን የቃል ኪዳኑ ታቦት።

ሀገር እንዳይፈርስ በኃጢአት ክምር፥

ሥር በሰደደ ሰይጣናዊ አስተዳደር፥

በጥሞና እናስተውል፥

ታቦቱን ይዞ ያመጣልንን - የቀሲስ ሶዶቅን ምክር።

## የሶዶቅ ምክር

ካህኑ ሶዶቅ እና ነቢዩ ናታን ሰሎሞንን ቀብተው እንዳነገሡት፥[61]
ለቀዳማዊ ሚኒሊክም (የማክዳና የሰሎሞን ልጅ) እንዲሁ ተደረገለት።
ያኔ (ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት)፥
እንዲህ እያለ ነበር ሶዶቅ
ቀዳማዊ ሚኒሊክን የሚመክር፦[62]

“ልጄ ሆይ፦
ኑሮህ በእግዚአብሔር እምነት የፀና ይሁን፤
ሥራህ ሁሉ ስኬታማ እንዲሆን።
አንተ ጥሩ ስትሆን፥ ሕዝቡም አንተን ተከትሎ ጥሩ ይሆናል፤
ባንተ ሳቢያ ሕዝቡም አገሩም ይባረካል።
ድሆችን ከሚጨቁኗቸው፥ ከግፈኞች ነፃ አውጣቸው፤
በቀናውም መንገድ ምራቸው፤
በእኩልነት ተመልከታቸው፤
ዳኝነትህም አድሎአዊ እንዳይሆን ተጠንቀቅ፤
በሕግ ፊት፥ ማንም ከማንም እንዳይበልጥ እወቅ።”

የሶዶቅ ልጅ (አዛርያስ) እና ጓደኞቹም ተማክረው፥
ታቦቱን አወጡ ካገራቸው።
ሕዝቡም እንዳያውቅ፥ ቅዱሱ ለቆ መሄዱን፥
አቻኮሉት ሰረገላውን።

ታቦት አልባ ሆኖ የቀረን ሕዝብ፥
ያልታወቀ በሽታ አራወጠው ድንገት፤
የቤት እንስሳት፥
የዱር አውሬም የታቦቱ መለየት ገብቶት፥

---

[61] መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 1:32

[62] ክብረ ነገሥት - http://www.yorku.ca/inpar/kebra_budge.pdf

ተቅበዘበዘ በጭንቀት - በድብርት።
ሁሉም ሲያለቅስ በያለበት፦
አገር ሲተራመስ፥ ሲብስ ጨኸት፥
አህያው፥ ከብቱ፥ ሲቁነጠነጥ፥
ውሻ ራሱን ደፍቶ ሲተከዝ፥
ጅብም ከጩኸቱ ማላዘኑ ሲበልጥ።
የዚያን ጊዜ፦
ንጉሡም (ሰሎሞን) በድንጋጤ በድን ሁነዋል፤
ቤተ እስራኤል ጠባቂያቸውን (ታቦቱን) ይዘው ወደ ደቡብ ገስግሰዋል።
ሰሎሞንም ህልሙን፦
ፀሐይ ከእስራኤል ወጥታ ወደ ደቡብ ስትሄድ ያየውን፥ አስታውሷል፤
የአባቱም (የዳዊት) ትንቢቶች ትዝ ብለውታል።[63]
ይሄ ሁሉ ትዝታ፥ ታሪክም ነው፤
መቆየት ያለበትን ማቆየት ምርጫችን ነው።
እኛም እንደ እስራኤል ልጆች
እንደፈለግን እንሆን ዘንድ ተለቀቅን፤[64]
በምርጫችን ንጉሣዊ ስርዓትን ገረሰስን፤
ስዩመ እግዚአብሔርን ትተን፥ ስዩመ ጠብ መንጃን ተካን።
ንጉሣችንን ስናባርር፥
ቤተ እስራኤልም (ፈላሻም) ወጣ ከአገር።
ጥንትም ንጉሥ ሰሎሞን ወደ ኢትዮጵያ የላከው፥

---

[63] “በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ፤ ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ።” መዝ. 72: 9 “ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።” መዝ. 68: 31

[64] “በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን ናቁ እንጂ አንተን አልናቁምና፥ በሚሉህ ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ፤ . . . . ነገር ግን ጽኑ ምስክር መስክርባቸው፤ በእነርሱም ላይ የሚነግሠውን የንጉሡን ስርዓት ንገራቸው።” ሳሙኤል ቀዳማዊ 8: 7-9

የተከበረ የቀሳውስት፥ የመኳንንት የበኩር ልጅ እንዳልነበረ፥
ዛሬ እንደ ባይተዋር ተቆጠረ።

ከጥንት እስከ አሁን የነበረውንና ያለውን
የግንዱን መሠረቱን፥ እስራኤልን፥
እንዲሁም ኢትዮጵያን፥ ያሳደገች እናቱን (አገሩን)።
ቤተ እስራኤል (ፈላሻ) ያስታውሳል፥
ትዝታው እየቆሬቆረው፥
የገዛ ወገኑ እሱን ሲያሳንሰው፥
ታቦቱ (ሕዝበ ክርስቲያን ወገኑ) ተናገረው፡-

"ከክርስቶስ ልደት በፊት እኮ ነው አገር የለቀቅከው፤
እባክህ ተመለስ፤
ታቦቱ ያለበትም (ኢትዮጵያም) አገርህ ነው፤
ክርስቲያንነትም ያንተው ነው።"

"እኛ"ታቦቱን አምጥተን፥
ኢትዮጵያን በስዩመ እግዚአብሔር እያስጠበቅን፥
አገራችንንም በቅዳሴው እየባረከን (እያስባረከን)፥
ጸልየን፥ "ዝናቡን አዝንብልን፤
ወንዞቹንም እስከ ልካቸው ሙላልን" እያልን፤....."
የኢትዮጵያ ሕዝብ አንዴ ሲመቸው፥
አንዴ ሲከፋው፥
ይህ ጉራማይሌ ኑሮ እኮ ነው ፍቺ ያጣው።

የእድገታችን ማነቆ የሆነውን ነው ማወቅ ያቃተን፤
ዝናቡም ይዘንባል፥ ወንዙም እስከ ልኩ ይሞላል፤
ግን ውሃ ወደ ተጠማው ሳይደርስ ይፈሳል፤
ሕዝቡም አገር ለቆ ይወጣል።

እስላምና ቢገባ ካገራችን፥
ሕዝቡ ተቀበለው ሰላሙን፤
እያስወገደ በሃይማኖቱ የሚነግደውን።

ከመሳፍንት አገዛዝም ወጥተን፥
በነገሥታትም ተገዝተን፥
ይሄው አለን ኢትዮጵያ ተብለን፥
በውጪ ጠላት ሳንበገር - ክፉውንም ደጉንም እያስታወስን።
ትዝታና ታሪክ ወደ ኋላ አይመልስም ጊዜን፥
የቅርብ ጊዜያት ለውጦች ናቸው እኛን ያንገላቱን።
ኃይለ ሥላሴን ገልብጠን፥
ደርግን ተካን።
ግን ትግሉ ስላልበቃን፥
እውነቶችን ከመጠን በላይ (ሕዝቡ ከሚችለው በላይ)
አጉልተንና አብዝተን፥
ረቂቃን ርዕዮቶችን ገንብተን፥
ኢሕአፓ፥ ኢኮፓ፥ ማሌሪድ፥ መኢሶን፥ ወዘተ..ብለን፥
ገና ትግሉን ስንጀምር፥
ጥቃቅን የውሸት ተውሳኮች (ጀርሞች) ገቡብን።
እኽ!....
ትንሿ ውሸት (የታክቲክ ጉድልት፥ አንጃነት) ከጉያችን ገብታ በላችን።
በጥቃቅን የሃሳብ ልዩነቶች እርስ በርስ አጣላችን፥
ለታላቁም ውሸት (የሰይጣን መልእክተኛ) ዳረገችን።
እኽ! የለየለት ዲክቴተር፡-
ተፈጥሮን በቁጥጥር ውስጥ እናደርገዋለን ብሎ የፎከረ፥
የልማቱን ሥራ አጣደፈ፥ በጠብ መንጃው እየቆፈረ፤
ሰውን እየገደለና እያሰረ፥.....
መንግሥት ለራሱ እንደ እስፖርት ቢቆጠረው ጦርነትን፥
ሞት ጨረሰው ወታደሩን፥ ሠራዊቱን፤
ገበሬ፥ ሚሊሺያውን።
በኢኮኖሚ አደቀቃት አገሪቱን፤
ረሃብ ገባው ሠርቶ አዳሪ - ላብ አደሩን።

እንዲህ እና ይህንን ይመስል ነበረ፥
ያ ያሳለፍነው ጊዜ፡-
ጉልበተኛው እኔ ብቻ ልብላና ልጠጣ፣
ኢትዮጵያ የኔ ብቻ ነኝ ሲል፥
አቅመቢሱ በረሃብ ሲቃትት፥
ኢትዮጵያችንም፥ "ኸረ እኔ ለሁላችሁም እበቃለሁ.." ስትል፤
ራስ ወዳዶች አልጠግብ ባዮች፥
ኢትዮጵያችንን እርስ በርሳቸው ተከፋፈሏት፤
ሰፊውን ሕዝብ የበዪ ተመልካች አደረጉት፤
የኢትዮጵያም ሕዝብ ተዘናግቶ፥
ቅድስናውን ከታቦቱ ለይቶ፥
በሥራው (በኑሮው) ሁሉ በረከትን አጥቶ፥....
እኸ! እግዚአብሔር የለም ማለትን እንደለመደ፥
ክብሩን ማእረጉን አጥቶ ተዋረደ፤
ሴቱም ወንዱም ተሰደደ።
ትዝታና ታሪክ ወደ ኋላ አይመልስም ጊዜን፥
ከዲክቴተር አገዛዝም ወጥተን፥
ደርግን በጠብ መንጃ አባረን፥
ለዓመታት ተሰቃየን፤
ሌላ ባለ ጠብ መንጃ ተከተን፥
በጎሳ ልዩነቶች ሳቢያ
ውስጣዊ ክፋቶቻችንን አጉልተን፤
ይኸው መኖርን ኖርን፥
"ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል" ብለን።

ግን ሕዝቡ በዚህ ታላቅ ውሸት ቢታፈን፥
ማነው ታሪካዊ ፍቅራችንን የሚቀማን?

በማንኛውም ሥፍራ፥
በማንኛውም ሁኔታ፥

በማንኛውም ጊዜያት (ሰዓት)፥
እንደ አንድ የትግል ታክቲክ፥
አንድን ብሔረሰብ (አማራን) ለይተው ቢያስጠሉበት፥
የልጆቿን ፍቅር ነጥቀው ሲወስዱባት፥
ጉዳት ላይ የምትወድቅ እናት ኢትዮጵያ ናት።
ሕዝቡ በመሰናክሎች ብዛት ግራ ተጋብቶ፥
በራሱም ላይ ተቆጥቶ፥
ባሳለፈው ሃይማኖት አልባነትም ተፀፅቶ፥
ሃይማኖቱን (እውነቱን) ይዟል፥ አጥብቆና አብዝቶ።

የሕዝቡ ሃይማኖተኛነት ይህንን አሳጣው፥
ያንንም አስገኘለት ለማለት አይደለም፤
ጊዜ ጠብቆ ይመጣል ሁሉም።
ውሸትን ታቅፎ ለቆየ፥ በጊዜአዊ አሸናፊነት፥
እጅግ ታላቅ ይሆናል የሚከተለው ውድቀት።

ጸጉር መሰንጠቅ፥ የሰውን ሃሳቡን ማኘክ፥ መገዝገዝ፤
በውሸት እና በክፋት በጨቀየ የፖለቲካ መርዝ፥
እውነትን በስሜታዊነት ማደንዘዝ፥
ይህ ነው የብልሹ አስተዳደር መዘዝ።

የትግል አጋርን በጎሪጥ መመልከት፥ ጠላትነትን ማፍራት፥
በሆነ ባልሆነው መጣላት፥ የቆሙለትን አላማ መርሳት፥
ጀብደኝነት፥ በሥልጣን ጥም ግፊት፥ ግብታዊነት፥
ልዩነቶችን አለመቀበል፥  በጊዜያዊ አለመግባባት መረታት፥
መቻቻልን፥ መከባበርና አብሮ መሥራትን መጥላት፥
ከኔ በላይ ማን ያውቃል ማለት፥
ይህ ነው ጊዜያችንን ያጠፉብን፥
በእኛው ውስጥ ያለ፥ ያላወቅነው ጠላት።

ወሳኝ ታክቲክ መስሎት የውሸት መሳሪያን የሚጠቀም፥
ለጊዜው ቢያሸንፍም፥ መጨረሺያው አያምርም።

ባለ ጠብ መንጂያ ቢራገጥም፥
እናት (ኢትዮጵያ) ጡቶቿን ከልጆቿ አትደብቅም።

**መደመደሚያ**

የልማት እንቅስቃሴን፥
የሰብአዊ ግንኙነቶችን፥
የጋራ ደኅንነትን፥
ለአንድ ብሔር የሚያስፈልጉትን፥
ሁሉን በጠባቡ የሚወስን፥
ከፉ መንግሥት ዘላቂ አይሆን።
እንዳው ድካም...
የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲህ በቀላሉ አይረታም፤
ተላላፊ መንገደኛን ሲያስተናግድ የኖረ፥
በደግነቱ የሚኖር ነውና እንዳለፈው ለወደፊቱም።

ጥላቻ ካልተወገደ ይቅር በመባባል፥
ሰብአዊነት ይታመማል በማይድን ቁስል።
ይህ የእኛነታችን መለዩ - ኢትዮጵያዊነታችን፥
አብሮ የመሆን ጸጋ በሥፊዋ አገራችን፥
ብንሰደድም የሚሰደድ አብሮን፥
እንደገናም ወዳገራችን የሚመልሰን፥
ይህ መልካም፥ ልዩ ጠባያችን፥
ተገንጥሎ ከሄደ ከላያችን፥
ከባዶነት በቀር ምንም አይተርፈን።
የአገር ፍቅር ስሜት፥ የኢትዮጵያዊነት፥
የጋራ ደስታ በሃብታምነት፥ በድህነት፥
በሥጋዊነትና በመንፈሳዊነት፥
ምንጊዜም አይለየንም የፈጣሪያችን ጸጋና በረከት።

አሉታዊነት ወደ ኋላ ያስቀረናል፤

ውሸት ትግላችንን ያሰናክልብናል።
ከእውነት ተነስቶ የቆመ ለእውነት፥
አንድ ታላቅ ኃይል፥ ፈጣሪው አለለት።
ለዚችስ ለቅድስት አገራችን መሪ የሚሆናት፥
በቅዱሳን ሕዝቡ ገፉፊነት፤
በአምባገነኖች ፋንታ እግዚአብሔር እንዲነግሥባት፥
መንፈሳዊ፥ ፈጣሪውን ፈሪ፥
ሕዝቡን፥ አገሩን የሚያስቀድም መሪ፥
ይህንን ነው ማንም ታጋይ (ፖለቲከኛ) እንዲያውቅ፥
እንዲያስብበትም የፈለግነው።
ይህንን ምክር ነው፥
የታናናሾችን ምክር ለማይሰማም፥
የሶዶቅ ምክር ብለን ያቀረብነው።

ይኸው ነው ዛሬም በየቤተክርስቲያኑ፥ በየመስጊዱ የሚሰበከው፤
የሶዶቅን ምክር ምስጢሩን የአገር መሪ (ተቆርቋሪ ሁሉ) ቢረዳው፥
መሪነቱንም እንደ ንጉሥ ዳዊት፥ ከእግዚአብሔር ረድኤት ጋር ቢነፀረው፥
ይህንን ነው ቅዱስ ሕዝብ የሚቀበለው።
እንዲህ ሲሆን ነው አገር የሚባረከው፤
ረሃብና ጥማት የሚጠፋው፥ መሰደድም የሚቀረው።

# ምዕራፍ አስር

# የልመና ጥሪ ለእመቤታችን



ተማጽኖ

**መግቢያ**

በምድር ያለው በሰማይ ካለው ጋር ቢቀራረብ በፍቅር፥
አይቶና ሰምቶ ዝም አይልም፥
ጥሩ ምላሽ ይኖረዋል ቸሩ የኛ እግዚአብሔር።
ይህ የልመና ጥሪ ነው፥ ለእመቤታችን፥
ስናስታውሳት በፍቅሯ ስበት ለምታባባን፥
ከሰማይ ሆና ለምታየን።
እንባ ሲንጠባጠብ፥ ሲነገር በስሜት፥
እንዲታወቅ በእውነት፥
ከእኛ ከሰዎች ሁሉ፥ የኢትዮጵያን ደግ ደጉን ከምንመኝላት፥
ይህ ለእመቤታችን የልመና ጥሪ - ልባዊ የጋራ ጸሎት፥
"እመቤታችን እባክሽ አማልጂን ከልጅሽ.." እያልን የምንጸልይበት፥
ይነበብ በትጋት - የልመናችን ብዛት ለኢትዮጵያችን እንዲሆን በረከት።

## የልመና ጥሪ ለእመቤታችን

አ! ቅድስት ማርያም፥ በወርቃማው ጸባይሽ - በጥሩነትሽ ፍጹም ሆነሽ የተገኘሽ፥
አ! ማርያም፥ ሰው ሆነሽ - ጺጋን የተመላሽ፥
ኢትዮጵያም "ማርያም፥ ማርያም.." ብላ፥
ከምን ጊዜውም በበለጠ ጩኸት ጠራችሽ፤
በቋፍ ላይ ናቸውና የአስራት ልጆችሽ።
አ! እመቤታችን ልዩ ነው ያንቺ ጺጋ፥
የመለኮት እናት መሆንሽም የመመረጥሽ - የጥሩነትሽ ዋጋ።
አክሱም ጽዮን ማርያም፥ የታቦቱ መኖሪያ፥
ማነው የሚለያት እምዬን ከኢትዮጵያ።
አ! ማርያም ወላዲተ አምላክ፥
አ! ቤዛይት አለም፥ የፍቅር እናት፥
ኢትዮጵያስ ካላንቺ  ማን አላት?
ማን አላት እንዳንቺ ደግ እናት።

የሥጋ ሞት እስኪለየን - በቃችሁ እስኪለን፥
በጥዑም ዝማሬ እየቀደስን፥ እየዘመርን፥
“እሰይ ስለቴ ደረሰ፥ ለማርያምዬ ነግሬአት ነበረ..” እያልን፥
እየሞትንም እስክናልቅ ድረስ ስምሽን እንጠራለን።
ምንጊዜም ማርያም፥ አንቺ አትጠፊምና ከሕይወታችን፤
አንረሳውምና ውለታሽን - ፍቅርሽን፥
ደግነትሽን፥ ተአምራትሽን።
ከአበቦች መካከል ጽጌረዳ፥
ከሴቶች መካከል፥ ማርያም ፍቁር ወልዳ፥
እባክሽ ተመልከች የልጆችሽን ፍዳ።
የማንነታችን ተምሳሌት - ማርያም እናታችን፥
እሜበታችን ምንጊዜም አትረሺንም፥ ይህንን እናውቃለን፤
ማን ለያይቶ ያገናዝባል? አንቺንና ኢትዮጵያን።
የዘወትር ጸሎታችንን ለፈጣሪያችን እያቀረብን፥
ከልጅሽ፥ ከወዳጅሽ እንድታማልጂን፥
አንቺንም እንማጸናለን።
ልጅ ሲርበው እንደሚያስጨንቅ እናቱን፥
እኛም አንቺን መጭቅጨቅ ልማዳችን፥
ደጋግመን እንጠራሻለን፥ አንቀጸ ብርሃን፥
ኢትዮጵያን አልረሳኋትም እንድትዪን፥
ተአምራትሺን እንድታሳዪን።
ምን እናድርግ? ከላይ እስከታች፥ በጣረ ሞት ትግላችን፥
ግቢ ነፍስ፥ ውጪ ነፍስ ሲሆንብን።
እባክሽ ፈጣሪያችንን ለምኚልን፤
ትንንቁን ወደ ሰላም እንዲቀይርልን፤
ከወደቀቺበት እንዲያነሳት ኢትዮጵያን፤
ሕዝቦች ናፍቀዋልና ለውጥን፥
ለድሆች የተመቸውን - መልካሙን።

በምድር ዙሪያ ከሁሉም አገር፥
ታያለሽና የሁሉንም ችግር፥
የእኛም ተስፋችን በጨለማ ዳመና ሲታጠር፥
ሞት እየገባ ከድሆቹ መንደር፤
ጭንቅና መከራ ስለበዛ በኢትዮጵያ ምድር፥
እዛኚቱ አድምጪን፤ ብሶታችንን ስንናገር።
ወንዝና ሸንጥሮ መረብ ሰርተው፥
ድንጋዩም አፈሩም ሳሩም ተመሳጥረው፥
ሜዳና ደኑ በየተራ ተሰልፈው፥
ደጋ ወይናደጋ ግንባር ገጥመው፥
ልዩ አይነት መሬትና አየር እስከ ቆላው፥
ትዝ ይበልሽ ምሥራቅ አፍሪቃ - ኢትዮጵያ፥
ከላይ እስከ ታች የቃኘሺው።
ግን ያ መሬት ከልጅሽ ጋር ሆነሽ የባረክሺው፥
አሻፈረኝ ብሏልና፥ እስቲ እንደገና ጎብኚው።
ከምድር ብቅ ብሎ ከሚታይ ከፍታው፥
ዳሸን፥ የሰሜን ተራራ ከሚባለው፥
በደመና ከሚከናነበው፥
ሰማይ በፀበል ከሚረጨው፥
እስከ ቁልቁል እስከ ዝቅታው፥
ከገደሉ ሥር ከረባድው፥
እስከ ዱብቲ፥ ዳሎል አሳይታ ንዳድ ከሚያጠቃው፥
ከላይ ባህረ ኤርትራን ተከትሎ፥
ቁልቁል በኤደን ሰላጤ በተከፈለው፤
በመሃል የስምጥ ሸለቆ የሚሰነጥቃት፥
በግራና በቀኝ፥ ተራሮች በሰንሰለት የተሳሰሩባት፥
እንዲህ ከፍታና ዝቅታ የበዛባት፤
ለልጅሽ ገጸ በረከት - ወርቅ፥ እጣንና ከርቤ የተገኘባት፤

ያቺ የኢትዮጵያ ምድር - የልጆችሽ መኖሪያ፥
ከዚህም ከዚያም ምድኛና ጣርያ፥
የሰውም የአውሬውም መሸሸጊያ፥ መጠለያ፥
መፈጠሪያ፥ መኖሪያ፥ መሞቺያና መቀበርያ፥
ይህቺ እኮ ናት አገራችን - ኢትዮጵያ።
እናታችን ማርያም፥ እባክሽ ስሚን፥
በጣር ላይ ብዙ ቆይታለች'ኮ አገራችን።
ከተፈጥሮም ይሁን ከሰው እንጃ - አየሩ ተለውጦ፥
ዝናብ ጠፍቶ፥ ዳመናም ከሰማዮ ተሟጦ፥
ወንዙ ሲደረቅ፥ የተዘራውም በጸሐይ ሙቀት ሲቃጠል፥
የደረቀው መሬት፥ ለሰውም ለእንስሳም አልሆን ሲል፥
የሚበላ የሚቀመስ ለዓመታት ሲጠፋ፥ ሞትም ሲከተል....፥
ሁሉን አስተካክሎ ለዘማናት ያቆየ አምላካችን፥
“ኢትዮጵያን ተቆጥቶ ሊቀጣት ይሆን?”
ብለን እንደንጠይቅ፥ ሁናቴዎች አስገደዱን።
ግን፥ የሰው ልጅ የገዛ ሥራው እንዲያስለቅሰው፥
ይህ ከሆነ ተፈጥሮአዊ ሕግ የተደነገገው፥
“ይበለው! ይበለው!...” ነው'ኮ የሚያሰኘው፤
ሥራችንን - ኃጢአታችንን መለስ ብለን ስናየው።
ሆኖም ለችሮታው - ለትእግስቱ ወሰን የሌለበት አምላካችን፥
ይቅርታውና ቸርነቱ እንደማይርቅ ከኢትዮጵያችን፥
ይህንን እናውቃለን - እናምናለን።
አዩ! ምንም ይሁን ምን፥ ብቻ በቃችሁ እንዲለን ለምኚልን፥
ሃዘን በዝቷልና በአለማችን - ባገራችን፥
እባክሽ ማርያም ይህንን ልመና - ይህንን ጸሎት አሳርጊልን።
ከአበቦች መካከል ጽጌረዳ፥
ከሴቶች መካከል ማርያም ፍቁር ወልዳ፥
እባክሽ ተመልከች የልጆችሽን ፍዳ።

በዚያች ሥፍራ፥ በጥንታዊት፥
ምድራዊያን ነፍሳት እንዳልፈነጩባት፥
አሁን ፍጥረታት ረገፉባት።
በዚች ሥፍራ፥ ዘመናዊት፥
ስንድህ፥ ስንሮጥ፥ ስንጫወት፥
በፍቅርና በደስታ እንዳላደግንባት፥
ዛሬ ተለውጣ፥ የሃዘን ቤት ሆና አየናት፤
ሰው እንደ እንጨት ሲነድባት፥
እንደ ከሰልም ሲከሰልባት፥
ምድሪቱን ረሃብ ሲረጋግጣት፥
ቋሚው ሲደፋባት፥ ሙታን ሲረባረቡባት።
አዬ! ምነው እመ ብርሃን?
ችላ አልሻት እንዴ ኢትዮጵያን?
ምነው የማትሰሚያት፥ ጩኸቷን ልቅሶዋን?
ሰቀቀኗን፥ ሰቆቃዋን፥ የሞት ሽረት ጣሯን።
ውሃ ባይጣፍጥ አይመር፥
መጥፋቱ ነው እንጂ የሚያሳርር።
መንግሥትም ድሆች በረሃብ ሲነደፉ፥ አይቶ፥ ከፍቶ፥
ማድረግ የሚቻለውን ሳያደርግ ቀርቶ፥
የሙብዛቱን ያህል ሕይወት ጠፍቶ፥
መርዶ ገባ ከቤታችን፥ ልቅሶ በዛ ከቀያችን፥
እጅግ ባሰ ሃዘናችን።
ከዚህም ከዚያም ኃጢአት ይሠራል፤
ቸሩ ፈጣሪያችን የሰውን ድካሙን ያውቃል፤
ሁሉም ነገር ከሰው አቅም በላይ ሲመስል፥
ሰማይ ከምድር የመራቁን ያህል፥
የአምላክ ምሕረቱ ርቆብን ስንማልል፥
እባክሽ ስሚን ስንጮህ፥ “ድረሺልን! ድረሺልን!.....” ስንል።

ከአበቦች መካከል ጽጌረዳ፥
ከሴቶች መካከል ማርያም ፍቁር ወልዳ፥
እባክሽ ተመልከች የልጆችሽን ፍዳ።

እመቤታችን እባክሽ የሰላሙን በር ለኢትዮጵያችን ክፈቺላት፤
በደጁ ወጥቶ ይቅር፥ አይመለስ ጠላት፤
ክፋት ይጥፉ ዘረኞነት።
እባክሽ የፍቅርን በር ክፈቺላት፤
ሕዝቦች ናፍቀዋልና እድገት፥
ኑሮ በነፃነት፥ በእኩልነትና በአንድነት።

እኛ ብንጮህ፡- ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ! እያልን፥
ብንማጸን መሬቱን - አፈር ድንጋዩን፥
ምንድነው ትርፋችን?
ጊዜና ለውጥ ሁሉን አሳይቶን፥
ሥጋ ካለመንፈስ ባዶ መሆኑን አስተምሮን፥
በሚገባን ቋንቋ ተአምረ ማርያም ተነቦልን፥
እኛም ንባቡን ሰምተን፥ ከምድራዊ ስበት ተላቀን፥
ሰማይ ሰማዩን ስናይ በአእምሮአችን የማርያምን ምስል ቀርጸን፥
በጠባዩ መንፈሳዊ ሲሆን ቋንቋችን፥ እንዲሁም ባህላችን።

የማርያም እናትነት፥ ከመለኮታዊ ፍቅር ጋር ተቀናጅቶ፥
ሁለቱን ነጣጥሎ ማያት እስኪያቅተን፤
ታዲያ እንዴት ብለን እኛነታችንን ከእመቤታችን - ከእናታችን እንለያለን?
ሕይወታችን ከማርያም ተነጥሎ እንዴት ሊሆን?
ለዚህ ነው ጸሎታችን፥
መንፈስ አልባ እንዳይሆን ኑሯችን፥
በረከት እንዳያጣ ምድራችን።

ከአበቦች መካከል ጽጌረዳ፥
ከሴቶች መካከል ማርያም ፍቁር ወልዳ፥
እባክሽ ተመልከች የልጆችሽን ፍዳ።

**ቅድስት፥ ድንግል ማርያም ሆይ!**

ካንቺ የተወለደው፥ አልበቃ ብሎት መዳናችን፥
ከመስቀሉ ላይ ሆኖ፥ ፊቱን ዘቅዘቅ አድርጎ፥
አንቺን አየሽ ልጅሽ፥
አልተለወጥሺም አንቺ ያው አንቺ ነሽ፥
ለልጅሽ እናት እንደሆንሽ፥
ለአለም ሕዝብ ሁሉ እናት የመሆን ብቃት ያለሽ።

እንደገናም ከመስቀሉ ላይ ሆኖ፥ ፊቱን ዘቅዘቅ አድርጎ፥
ዮሐንስን ተመለከተ የሚወደውን፥
እንዲሁም አሰበ የምድሪቱን ክፋቷን፥
ጠባቂ እናት ማስፈለጉን።

አንቺን እና ዮሐንስን እናትና ልጅ ያደረገ አምላካችን፥
ያውቃልና ለሚያፈቅር ልጅ የእናት ፍቅር ማስፈለጉን፥
ጌታ ኢየሱስ አንቺን ለእኛ ሰጠን።[65]
"እንኩ ውሰዷት፥ እናት ትሁናችሁ" አለን፥
ይወዳቸዋልና ወዳጆቹን፥ ቤተሰቡን፤
በመስቀል ላይ ሆኖ አይቷልና የምድሪቱን፥ ስቃዩአን፤
ያውቃልና ማስፈለጉን፥
የፍቅር እናት ለኢትዮጵያችን - ለአለማችን።

ማርያም ዳግማዊት ሔዋን - የመዳናችን ምልክት፥
በአንቺ ልጅ - በአምላክሽ - በአምላካችን'ኮ ነው ያገኘነው ድኅነት።
ማርያም፥ ጽዮን፥ አገራችን፥ ከተማችን፥ ታቦታችን፥

---

[65] "ጌታችን ኢየሱስም እናቱንና የሚወደውን ደቀ መዝሙሩን ቆመው ባያቸው ጊዜ እናቱን "አንቺ ሆይ እነሆ ልጅሽ" አላት። ከዚያም በኋላ ደቀ መዝሙሩን፥ "እናትህ እነኋት አለው፤ ከዚያችም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ተቀብሎ ወደ ቤቱ ወሰዳት።" ዮሐ. 19፡ 26፥ 27

አሻጋሪ የኖህ መርከብ - ተስፋችን፥ ባንዲራችን፥
ልጅሽ አምላክሽ ውድድ ቢያደርገን፥
አንቺን እናቱን ለኛ ሰጠን።
ታዲያ፥ ማርያም፥ አንቺን ትተን የት እንደርሳለን?
አምላካችንን ስንጠራ በዘውትር ፀሎታችን፥
ስላመንብሽ እኮ ነው! አማልጂን ማለታችን።
ከጣና ደሴቶች፥ ከባህር ዳር፥
ከሸዋ፥ ከወሊጋ፥ ከሲዳማ እስከ ሐረር፥
ከአስመራና እና ከአክሱም፥
ማን አለ? ያላጌጠ ባንቺ ስም።
ከደቡብ ከሻሸመኔ፥ ከመሃል ከደብረ ብርሃን፥
ከዚያም አልፎ እስከ ሰሜን፥
ማርያም ተስለሻል በአእምሮአችን፤
ምንጊዜም አንረሳም አንቺን።
በኢትዮጵያችን ሰው ቢወለድ፥ ቢሞት፥
አልተለመደም ባይተዋር የሰው ፍጥረት፥
“ማርያም - ማርያም - ማርያም” የማይባልለት።
ማርያምን ሳይዙ ጎዞ፥
ኢትዮጵያ አልለመደባትም፤
ተዘፈነ፥ ተዘመረም፥ ተለቀሰም፥
ማርያም አልባ ስሜት አይታወቅም።
የማርያም ፍቅር የሚያድርባቸው፥
የመስቀሉ ምሥጢር የገባቸው፥
የኢትዮጵያ ሕዝቦቿ ቢለያዩም እንደየመኖሪያቸው፥
ካንቺው ጋር ነው አንድነታቸው፥
መንፈሳዊው ልቦናቸው።
በስደት አለም የአገር፥ የወገን፥ የዘመድ ሃሳብ፥
ናፍቆቱም ሲከብዳቸው፥

ለትልቁም ለትንሹም፥ "እናቴ ባየሺኝ፥..."
"ማርያምዬ ድረሺልኝ..." ማለት ልማዳቸው።
አንዳንዶችም በንስሃ ራሳቸውን እስኪያስተካክሉ?...
ሁሉም እንደየቅሉ፥
አምላካቸውን ሲለምኑ ፈራ ተባ እያሉ (?)
ግን መፍትሔ እስኪያገኙ እየተቻኮሉ፤
ማርያም አንቺን ሲለምኑ፥
እጅጉን ሙጭጭ ይላሉ።
ታዲያ ምንድነው ጥፋቱ? አንቺን መቅረቡ፤
ምድራዊነት ሲያስጨንቀን አይኖቻችን ሲያነቡ።
የልጅሽን ስጦታ መናቅ ነውና አንቺን መርሳት፥
አይሰለቸንም፥ ያንቺንም ስም መጥራት።
አዎን! ስምሽን እንጠራለን፥ ባንቺ አናፍርም፤
የአምላካችን ውለታ ምንጊዜም አይረሳም።
አሁንም፥ ነይ! ነይ! እንልሻለን እምዬ ማርያም፥
ቤዛዊት አለም፥.............
ትንፋሻችን፥ ተስፋችንም ነሽና ለዘለአለም።
ከአበቦች መካከል ጽጌረዳ፥
ከሴቶች መካከል ማርያም ፍቁር ወልዳ፥
እባክሽ ተመልከች የልጆችሽን ፍዳ።
አዬ! ምነው! እመ ብርሃን፥
ምነው ብታሳውቂን የኢትዮጵያን መጻኢዋን፥
ከፋትና ጭካኔ ሲጸናባት፥ ችጋር ሲዘምትባት፥
አዬ! ምነው! እሙብርሃን፥
ምነው ፈጥነሽ ብታስታርቂን ከፈጣሪአችን፥
በረከቱ ርቋልና ከአገራችን፥
ፍቅር ጠፍቷልና ከሕዝባችን።
ማርያም ወዳንቺ ነውና መዝሙራችን፥


በሃዘናችን ፈጥነሽ ድረሺልን፥
ብሷልና ብሶታችን፤
እባክሽ እንባችንን በእጆችሽ አብሺልን፤
እኛም በጸሎት እንበረታልን፤
እመቤታችን፥ እናታችን አማልጂን፤
ጸሎታችንን ወደ ሰማይ አሳርጊልን።
ናስተማስለኪ ብለው ሊቃውንቱ፥
ድብቅ እውነቶችን ሲጎትቱ፥
ጉልህና የሚታየውን ከረቂቁና ከማይታየው እያዛመዱ፥
በመንፈስም አርቅቀው እየሄዱ።
መንፈሳዊ ክስተቶችን በገሃድ ሲያሳውቁ፥
ምስጢራትን ከጥልቁ እየጠለቁ።
ታዲያ ዝም ማለትን ማን ችሎ፥ ማን ይናገር?
ከመሃይሙም ሲወጣ የማርያም ነገር፥
ሲገለጥ የተምሳሌቱ ምሥጢር።
በደብረሲና የነደ እሳት ነበልባል፥
የእጸ ጳጦስን ጫፍ አላቃጠለውም፤
ያ ነደ እሳተ፥ ያ መለኮት፥ ያ የእግዚአብሔር ቃል፥
ማሕጸንሽን አላቃጠለውም።
ባንቺ አድሮ ሰው የሆነ መለኮትም፥
በእውነት አምላክ ነውና አልተለወጠም፤
አንቺም ንፅሕት ነሽና ድንግልናሽ አልተለወጠም።
ማርያምዬ አንቺ ብቻ እኮ ነሽ፥
አንድ ብቻ ወልደሽ፥ እመ ብዙሃን የተባልሽ።
እመቤቴ ያንቺማ ነገር መች ተነግሮ ያልቃል?
ስምሽን ገና ከማሕጸን ስንወጣ ሰምተነዋል፤
በመንፈስ እናትነትሽንም አውቀነዋል።
በጥልቀቱ የማያስብ፥ የማይመራመር፥

አይገባውም ያንቺ ነገር።
ሰማይማ ሳይኖር መሬት እንዴት?
እናትማ ሳትኖር ልጆች እንዴት?
ወዳጆችሽ ከስዕልሽ ፊት ለፊት ቆመው፥
መልክሽን እያዩ ፍዝዝ ብለው፥
እጆቻቸውን እያውለበለቡ፥
እንባቸውንም እያፈሰሱ፥
ማርያምዬ ምነው ጨከንሺብን ሲሉ፥
የሞቱ፥ የረገፉ ዘመዶቻቸውን እያሰቡ።
ተስፋ በልባችን፥ እኛ የምናምንብሽ ሁላችንም፥
እናውቃለን፡- "በቃ! ሃዘን በቃችሁ" ትዪናለሽ ማርያም፤
በኢትዮጵያችን የቁም ስቃይ ሲበዛባት፥
የምድር ችጋር ሲዘምትባት፥
እናውቃለን፡- ስቃይ ፈተናዋን አይተሽ ዝም አትዪም፤
ልጆችሽ "እምዬ፥ እምይዬ" እያሉ ሲጮሁ በአንድነት፥
በእውነት አንቺም ችለሽ መቀነትሽን አታጠብቂም።
ግን አሁንም ምድሪቱ "ዋይ! ዋይ!.." ትላለች፥
"ማርያም እመቤቴ ድረሺልኝ እያለች" ትጮሃለች፤
አንቺ ነሽና፥ ዛሬም ነገም ለሚወዱሽ ልጆችሽ የተሰጠሽ፥
አስችሎሽ ዝም እንደማትዪ የሚያውቁ ሁሉ ተማጸኑሽ?
ከዘመነ ፍዳ ወደ ዘመነ ምህረት ስንሺጋገርብሽ፥
አንቺው ጽላተ ሙሴ፥
የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ ሆነሽ፥
የአምላክ እናቱ ለመሆን በመብቃትሽ፥
እኛም ልጆችሽ በአንቺ ስለተባረክን አፈቀርንሽ፥
ትውልድ ሁሉ ብፅእት ብሎ ስለ ጠራሽ፥
የትህትና፥ የደግነት ተምሳሌት፥ ክብራችንም ሆንሽ።
ማርያም አንቺ በእውነት የጠፈር ንግሥት ስለሆንሽ፥

እናቶች፥ አባቶች፥ ልጆች ሁሉ የጸጋ ስግደት ሰገዱልሽ፥
ስምሽን ስንጠራው ስንለምንሽ፥
ማርያም አስታውሺን በልብሽ።
አንቺ ርህሩህ እናት ሆነሽ፥
የጭንቃችንን ሸክም እያየሽ፤
እንዳመንብሽ አትርሺን እባክሽ።
ከአበቦች መካከል ጽጌረዳ፥
ከሴቶች መካከል ፍቁር ወልዳ፥
እባክሽ ተመልከች የልጆችሽን ፍዳ።
እናውቃለን፥ ከችግራችን አንጻር ልመናችን ሰሚ አለው፤
እርሱ ፈጣሪያችን ነው፥ ችግሮቻችንን ሁሉ የሚያጠፋው፤
እናውቃለን፥ አምላካችን ሰውን ሁሉ ይወዳል፥
ኢትዮጵያንም ዘወትር ይጠብቃታል።
አሁንም፥ እመቤታችን እባክሽ ልጅሽን በርትተሽ ለምኚው፥
“ልጆቼ ጭንቅና መከራው ይብቃቸው፤
ወዳጆቼን ከችግር አውጣልኝ” በዪው።
አሜን።

# ክፍል ሁለት

## ልባዊ እይታዎች - መንፈሳዊ ግንዛቤዎች



# ልባዊ እይታዎች - መንፈሳዊ ግንዛቤዎች


ገጽ

የክፍል ሁለት መግቢያ፡ ........................................................ 239

ምዕራፍ አንድ፡ እውቀትና ሥልጣኔ፥ ማንነትና ድኅነት፡ ............ 241

ምዕራፍ ሁለት፡ እምነት ከትንሽ እውቀት ............................ 281

ምዕራፍ ሦስት፡ መንፈሳዊ ግንዛቤ፡ .................................... 299

ምዕራፍ አራት፡ ምልከታችን - ወደ ምሥራቅ፡ ......................... 331

ምዕራፍ አምስት፡ የሰው ብርታቱ ከመንፈሱ፡ ........................... 351

ምዕራፍ ስድስት፡ ሙሉ ሰው የት አለ?፡ ................................ 377

ምዕራፍ ሰባት፡ ማመን - አለማመን - ማወቅ - አለማወቅ፡ ........ 389

ምዕራፍ ስምንት፡ ማጠቃለያ ሃሳቦች፡ .................................... 401

ዋቢ መጻሕፍት
(ለአራቱም መጻሕፍት)፡ ........................................................... 413

# የክፍል ሁለት መግቢያ

በዚህ ክፍል ውስጥ፥ ልባዊ እይታዎቻችንን በፍጹም ነጻነት ለመግለጽ፤ ከዚያም ጋር ካነበብናቸው መንፈሳዊ ታሪኮች በማቀናጀት መንፈሳዊ ግንዛቤአችንን ለማጋራት ተነሳን። ከአለማወቅም ቢሆንም፥ ጥሩውን ለማድረግ በጽኑ ፍላጎት የተጀመረን ሥራ ፍጻሜውን እግዚአብሔር ያሳምረዋል።

ብዙውን ጊዜ በግልጽ የማይታወቁና የማይነገሩ ጉዳዮች፥ እውነት መሆናቸው አጠራጣሪ ሲሆን ከሚነገሩ ይልቅ አለመነገራቸው ይመረጣል። በትምህርት ቤትም ቢሆን፥ ማስረጃ የማይገኝለትን ሁሉ እንደ ትምህርት አይቀበሉትም፣ በዘፈቀደ አያስተምሩትም። ይህም ሆኖ ሳለ፥ እንዲሁ በእምነት ካልሆነ በስተቀር፥ ሊታወቁ የማይችሉ አያሌ ጉዳዮች እንዳሉ እናውቃለን።

የምናምነውን ስናምን፥ እያንዳንዳችን እንድናምን የሚያደርጉን ለሁላችንም በተለያዩ መንገዶች ነው እንጂ፥ ሰማይ ላይ የተሰቀለችው ጸሐይ እንደሆነች - በእርግጥም ብርሃንና ሙቀትን የምትሰጠን እርሷ ጸሐይ እንደሆነች አይነት፥ ሁላችንም በአንድ አይነት መንገድ አይደለም የምንረዳው። የዚህም ጽሑፍ አላማ፥ አንባብያን በውስጣቸው ያደረውን የእነርሱኑ ልባዊ እይታቸውን እንዲያመሳክሩበት፥ የራሳቸውንም እምነት እንዲመረምሩበትና እንዲያጠናክሩበት እንጂ፥ ልዩና አዲስ እውቀትን እንዲሸምቱበት አይደለም።

የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ በዚህ ክፍል ውስጥ፥ በትንሹ (በሦስተኛውም መጽሐፍ በመጠኑ) ለመተረክ ተሞክሯል።[66]

እንዲሁም በተለያዩ አርእስቶች ከተካተቱት የተለያዩ ሃሳቦች ውስጥ፥ የሚከተለው ሃሳብ ላይ አጽናኦት ተሰጥቷል፦

የሰው አእምሮ አካላዊ ካልሆነው አለም አካላዊ በሆነ መንገድ (በሳይንስ) አካላዊ ያልሆነውን መረዳት አይችልም። ስለዚህ፥ አካላዊ በሆነ መንገድ የማይገለጹትን ኩነቶች ገሸሽ ባለማድረግ እና በመንፈስ ምጥቀት፥ ከማይታየው አለም ጋርም ግንኙነት መፍጠር እንችል ይሆናል።

[66] “ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል።” መዝ. 18(19)፡1

የኪነጥበብ *ሥራ* በአንድ መልኩ የእግዚአብሔርን *ሥራ* የሚያንጸባርቅ ቢሆን፥ በዚህ ደስ የሚላቸው (ከሰዎችም፥ ከመላእክትም) ይኖራሉና፤ በጥልቀት ባንሄድባቸውም፥ አንዳንድ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮችን ለማመልከት ያህል ጠቃቅሰናል።

በዚህ *መጽሐፍ* እንደጀመርነው፥ የምንጨርሰው *መደምደሚያችንም* እንደሚከተለው ነው የሚሆነው፦

*"አማልክት የሚሏችሁ ነገሮች አሉና፤ በሰማይም ቢሆን፥ በምድርም ቢሆን፥ ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች ቢኖሩ፥ ለእኛስ ሁሉ ከእርሱ የሆነ፥ እኛም ለእርሱ የሆን፥ አንድ እግዚአብሔር አብ አለን፤ ሁሉ በእርሱ የሆነ፥ እኛም በእርሱ የሆን፥ አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም አለን።" 1ኛ ቆሮ. 8፡6-7*

# ምዕራፍ አንድ

## እውቀትና ሥልጣኔ፥ ማንነትና ድኅነት



ሄኖክ

## **መግቢያ**

የሰው ኑሮ እንዲህ ርቅቅ ብሎ የሚታየው፥
ከራሱ በመነጨ እውቀቱ ብቻ ነው
ወይንስ ሌላ ተጭማሪ ኃይል - ሌላ የእውቀት ምንጭ አለው?
ስለ ምድራዊ እውቀት አመጣጥና አካሄድ ስናስተውል፥
ባንድ በኩል ምድራዊ ሕይወታችንን ሲያሻሽል፥
በሌላም በኩል መንፈሳዊ ሕይወታችንን ሲያጣጥል፥
ሙሉ ሆኖ የተፈጠረን ሰው እንዲህ ከሁለት ሲከፍል፥
በምድራዊ ምቾት በሚገኝ ደስታ ሰውን ሲደልል፥
ሃሴት ሰማያዊን ሲከልል፤

> ይህ የዘመኑ ሥልጣኔ - በምድራዊ እውቀት ብቻ የመጣ፥
> የሰውን ልጅ መንፈሳዊ ገጽታ እያሳጣ፥
> በሰማያዊ ማንነቱ ወሰከበት ልዩ ጣጣ።

የሰው እውቀቱ በተፈጥሮአዊ ማንነቱ፥
በራሱ እድገት ካልሆነ የተገኘው፥
የውጪ ጣልቃገብነት ካለው፥
እስቲ ይህንን ጉዳይ እናስላው፥
ከጻዲቁ ሄኖክ መልእክትና አቤቱታ ተነስተን።[67]
እንዲሁም እንመርምር ታሪካዊ ሂደቱን፤
እውቀታችን በኛነታችን ላይ ያስከተለውን - ተፅንአውን።

---

[67] "አቤቱ ረድኤቴ መድኃኒቴም፥ የአፌ ቃልና የልቤ ሃሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን።" መዝ. 18 (19)፡ 14

## እውቀትና ሥልጣኔ፥ ማንነትና ድኅነት

በጠፈር ውስጥ፥ ሁሉ ነገር እርስ በርሱ እንደሚያያዝ ይታወቃል፤
እንዲሁም ጊዜ አካልን ተጣምሮታል።
ነፍሳማው ባለ ሕይወት ራሱን ከጊዜ ወደ ጊዜ ሲያሻሽል፥
የከፋት መንፈስ (እርኩስ መንፈስ) ጣልቃ እየገባ የሚያሰናክል፥
የሰው መጨረሻው እልቂት እንዲሆን የሚታገል።

አለም ከተፈጠረች ጀምሮ፥ እንቅስቃሴዎች ሁሉ፥
ከደብዛዛው ወደ ደመቀው አምርተዋል፤
ከጥፋት ውሃ በፊትና በኋላም፥
የተለያዩ ምድራዊ ሥልጣኔዎች ብቅ ብቅ ብለዋል፤
አንድ አይነት ሥልጣኔ ሲወድም፥
ከቀድሞው ለየት ያለ ሥልጣኔ ተተክቷል፤
ሰውም በጊዜ ውስጥ ህልውናው እንዲጸናለት፥
እንደጊዜው ራሱን እየቀያየረ መጥቷል።
ሆኖም ግን፥ ሰው በኑሮው ከፍና ዝቅ ሲበዛበት ይጨነቃል፤
በእውቀት መራቀቅ ሲያበዛም፥ ማንነቱን ይረሳል።
አንድ ትውልድ አልፎ ሌላው እንኳን ሳይከተል፥
እንዲሁ በሁለት አለማት ተጠምዶ ከወዲያ ወዲህ ይማልላል።

እነሆ! ከጥንት ከሄኖክ ጀምሮ፥
በጻድቃን የተላለፈ አንድ መልእክት፥
ለሰው ልጅ የሚሆን ጠቃሚ ትምህርት፡-

በጥንት ዘመን፥ ከኖህ የጥፋት ውሃ በፊት፥
አንድ ኢትዮጵያዊ/ኤርትራዊ ይኖር ነበረ፥ ሄኖክ የሚሉት።
ሄኖክ፥ የያሬድ ልጅ፥ የማቱሳላ አባት፥
የላሜህ አያት፥ የኖህ ቅድመ አያት፤[68]

[68] ዘፍ. 5፡ 18-32

ሄኖክ በጠፈር ተመላለሰ፥ ከዚያም አስተዋለ፥ ተፈጥሮአዊ ክስተት፥
ለእኛም አቆየልን፥ ሞራላዊ ምክር፥ የሚሆነን ትምህርት።
ሄኖክ እኛን ወንዶችን ሴቶችን፥ ወልዶ ተሰወረ፤
በምድራችን በሚሰራው መጥፎ ሥራ ሁሉ እንደተማረረ፥
ለእግዚአብሔር አቤቱታ እያሰማ ከዚያው ቀረ።
እስቲ ለአንድ አፍታ አወቅን የምንለውን ሁሉ እንርሳው፥
ሄኖክ የሚለውን ብቻ እንስማው።

"ሰውም በምድር በበዛ ጊዜ፥
ቆነጃጅቶች ሴቶች ብቅ ብቅ ይሉ ጀመር ከመሃላቸው፤
አንዳንድ መላእክትም ይህንን ክስተት ሲያስተውሉ ቆይተው፥
ሴቶቹን ለማግባት ወሰኑ በውበቶቻቸው ተማርከው።
እነኚህ ከደበረ ቅዱስ የፈለሱ መላእክት፥[69]
ስሙ እስማዚያ መሪያቸው፥
ቆነጃጅት ሴቶችን እየመረጡ አገቧቸው፤
ከነርሱም ወለዱ፥ የሰውን ልጅ ስርዓቱን ጥሰው።
እነኚህ ኃጥአን መላእክት ከፈጣሪያቸው ፈቃድ ወጥተው፥
የራሳቸውን ስሜት በመከተላቸው፥
የተረገሙ ሆኑ ልጆቿቸው፤
እጅጉን ግዙፋን እየሆኑም በማደጋቸው፥
እስከ ሦስት ሺህ ክንድ ይደርስ ነበር ቁመታቸው።[70]
እነርሱም፥ እርስ በርሳቸውም ተበላልተው አለቁ፥
የምድር ምግብ ስላልበቃቸው።"

ካሁን በፊት ግዙፋን (ረዓይት - ኔፈሊም) በምድራችን እንደተመላለሱ[71]

---

[69] ከመጽሐፍ ቅዱስ (የኦርቶዶክስ) መጽሐፈ ሄኖክ ከምዕራፍ ሁለት ጀምሮ..

[70] ሄኖክ 2፡12

[71] ዘፍ. 6፡4

አንዳንድ ምልክቶችን ትተው፥
ይህንን ለታሪክ ተመራማሪዎች ትተን እንለፈው።
ኃጥአን መላእክትን ሄኖክ የከሰሳቸው፥
መጥፎ እውቀትን በማስተላለፋቸው፥
እንዲሁም በብልግናቸው።
ለሰው ልጅ ያስተላለፉትም "እውቀት" እንደየክነታቸው፡-
ሰይፍና ሾተል፥ ጋሻና ጥሩር መሥራትን፥
በዕንቁ ማጌጥን፥ እንሶስላ መሞቅን፥
ዐይን መኳልን፥ ቅንድብ መሸለልን፥
ምታት ማሳየትን፥ ሥር መማስን፥
ጋኔን መሳብን፥ ሟርትና ምታት ማሳየትን፥
የጨረቃን አካሄድ፥ ኮከብ መቁጠርን፥
**"ሌሎችም ለሰው ያልተገለጡ"** - ከምድር የተሰወሩትን።
እንዲህም እያስተማሩ፥ አመነዘሩ፤
ብዙ ዝሙትም አደረጉ፥
በምድሪቱም ደምን አፈሰሱ፥ ግፍን ሠሩ፤
ወደ ጥፋትም ሰውን መሩ፤
ሰዎችም ጮኹ፥ ድምጻቸውም ተሰማላቸው፤
ሚካኤል፥ ገብርኤልና ዑራኤል ደረሱላቸው።
ሆኖም፥ የጥፋት ውሃ ሆነ መጨረሻው።
እንዳው በደምሳሳው ስንመለከተው፥
የሰው እውቀቱም ይሆናል፥
ኃጢአትና ግፍ መሥራትን ያባባሰው፤
ከመንፈስና ከሥጋ የተወለዱ ረዓይት
የከፋት መናፍስት ስማቸው፥[72]

[72] "አሁንም ከመንፈሥና ከሥጋ የተወለዱ ረዓይት በምድር ላይ ክፉዎች መናፍስት ይባላሉ።" ሄኖክ 4፡40

ከፋትን ለሰው አውርሰው፥
በእውቀቱም ውስጥ “ምድራዊነትን” ወስከው፥
ሰውን አልተለዩትም በኃጢአት ሠሪ መንፈሳቸው።
እና፥ የሰው ልጅ የእውቀቱ ምንጭ፥
ከትውልድ ትውልድ የተላለፈው፥
በእውነት ይህ ከሆነ መነሺያው፥
ምን ነበረ፥ ሄኖክ የፈራው?
በእውነት በኃጥአን መላእክት እውቀት፥
በእነርሱ የሥልጣኔ መርህ ተለውጠን ነው ከዚህ የደረስነው?

የከፋት መናፍስትም አብረው፥ ሰውን መስለው፥
የእነርሱን ስነእመክኖአዊ አስተሳሰብ በሰው ጭንቅላት አስገብተው፥
እስከ ዛሬም ካልተለየን ከእነርሱ የተማርነው፥
በጥንቱ ሥልጣኔ የታቀፈ ከፋው መሆኑ ነው፥
ከዘር ዘር ተላልፎ እኛንም ወደ ከፋት የመራው፥
ስለዚህ፥ ይህንን ጉዳይ በጥሞና እናስተውለው።

ከዘመኑ እውቀት ውስጥ በብዛትም ባይሆን በጥቂቱ፥
ከትእዛዝ አፍራሽ መላእክት የተላለፈ ከሆነ ገና ከጥንቱ፥
መንፈሳዊነት የጎደለው፥ ተንኮል አዘል ይሆናል መሠረቱ፥
በእውቀታችን ውስጥም ጣልቃ በመግባቱ፥
ለዚህ ይሆናል፥ በምድራችን የጻድቃን ቁጥራቸው ያልበዛው፥
ለዚህም ይሆናል፥ አንዱ ሲያለማ፥ ሌላው የሚያጠፋው።

የከፋት መንፈስ ባለቤቱ ሰይጣን፥[73]
እኛኑ መስሎ ነገሠ በላያችን፤
በርሱ ጠፋ ሰላማችን።

---

[73] “አንተ በንጋት የሚወጣ የአጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! ወደ አሕዛብም መልእክትን የላክህ አንተ ሆይ! እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቀጠቀጥህ.......” ኢሳ. 14፡12

ሄኖክም እግዚአብሔርን ደስ ስላሰኘው፥
እንዲሁም ምናልባት -  ከሰይጣን ተንኮል ሊጠብቀው (?)
ከምድራዊ ሰዎች ሰወረው።[74]
ሄኖክ ተለየ ከሰው - የሞት ጽዋ ሳይደርሰው።
ኃጥአን መላእክት መንፈስ በመሆናቸው፥
እነርሱ አስተማሪዎች ሆነው - ስናያቸው እኛኑ መስለው፥
እንደ ደግ አሳቢ፥ ሲያበረታቱን በተንኮላቸው፥
ከውስጣችንም ተራብተው፥
እኛም ብዙ ስለቆየን መስለናቸው፥
ስነ አመክኖአዊ አስተሳሰባችንም ተለወጠላቸው፤
አለማችንም በነርሱው አለም ተካተተላቸው።
ክርስቶስም ክፉ አሳቢ ሰዎችን፥
የከፋት መንፈስ ስለ ተጠናወታቸው፦
"እባቦች፥ የእፉኚት ልጆች"[75]
በማለት ስም አወጣላቸው።
"የነቢያት ገዳዮች ልጆች..."[76]
ብሎም ጠራቸው፤
መጥምቀ መልኮት ቅዱስ ዮሐንስም፥
እነኚህኑ ክፉ አሳቢ ሰዎች - የከፋት መናፍስት ልጆች፥
"...እናንት የእፉኚት ልጆች" አላቸው።[77]
በአንድ አለም ሁለት አለም በመኖሩ፥
የሁለት አለም ፍትጊያም ስላልቀረ፥

---

74 "ሄኖክም እግዚአብሔርን ደስ ስላሰኘው አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ሰውሮታልና።" ዘፍ. 5፡24

75 ማቴ. 23፡33፥ ማቴ. 3፡7፥ ማቴ 12፡34

76 ማቴ. 23፡ 41

77 ሉቃ. 3፡7

እኛ በመሃል ተሰቃየን - ችግሮች ተደራረቡብን፤
ባላወቅነውና ባልተገነዘብነው ተንገላታን።
አንዳንድ መንፈሳዊያን ግን፥
ቀጥኛው ትምህርት፥ የሄኖክም አቤቱታ የገባቸው፥
ገዳም ገብተዋል፤ ከፍትጊያው ለማምለጥ ቋምጠው።
ከሩቅ ሆነው ያስተውላሉ፥ ሰብእናቸውን አስከብረው፤
በጾም በጸሎት ይተጋሉ፥ ምድራዊ ኑሮ አስጠልቷቸው።
ተፈጥሮአዊ ክስተት የራሱ ሂደት እንደሌለው፥
ወይንም ተፈጥሮአዊ ክስተትን ተከትሎ የሚሄድ ሰው፥
በራሱ ግፊት ብቻ ስኬታማ እንዳይሆን፥
ተስፋም እንዳይኖረው፥
ጥሩው መጥፎ፥ መጥፎውም ጥሩ እንዲመስለው፥
ክፉ አታላይ አለ በዙሪያው።
ክፉውም መንፈስ ተለሳልሶ፥ እኛኑ መስሎ፥
አብሮን ነው የሚኖረው።
እኛ ዛሬም እውቀታችን ብለን በኩራት የተቀበልነው፥
ማንነታችንን ያሳጣን፥ ሰብእናችንን የቀየረው፥
ያ  የደብረ ቅዱሳን ትምህርት - ሄኖክ ያጥላላው - መጥፎው፥
ከጦር ግንባታ ትምህርት መጥቆ የወጣው፥
ተፈጥሮአዊ ሂደትን በመቀለስ ላይ የሚገኘው፥
እሱን ነው? እኛም፡- “ሥልጣኔ፥ ሥልጣኔ” እያልን ያሞካሸነው።
ከመሠረቱ፥ ለተፈጥሮአችን ባይተዋር የሆነ፥
ከፍቅር ያልተጀመረ፥
ሰዎችን በትእቢትና በትምክህት የወጠረ፥
መንፈሳዊነታችንን የቀበረ፥ ሞራላችንን የሰበረ፤
የልታወቅ ባይነታችንን ስሜት ያሳበጠ፥
ሰብእናችንንም ያጎበጠ፤
እንዲሁም የእርኩስ መንፈስ ሹክሹክታ፥

እንደ ጋኔን መሳብ፥ ሟርትና ምታት ማሳየት፥
እምነትን የሚያሰናክል፥ ልዩነቶችን የሚያበዛ፥
ከብርሃን ወደ ጨለማ የሚከት።

መጥፎውን በመራቅ ጥሩውን ብንቀርበው፤
ሰማያዊ መንፈሳዊ እውቀት - በነእስማዚያ ያልተበከለው፥
ምድራዊ ኑሮአችንን እንዳያሻሽል፥
በገዛ አይምሮአችንስ በራሳችን ለራሳችን እንዳንሠለጥን፥
በመጠናችን ስንኖር፥ መንፈሳዊ ሃሴት እንዳይኖረን፥
ማን ከልካይ አለብን?

ግን በእርኩስ መንፈስ ተንኮል፥
የረከሱ መላእክትንም ወሬ እየሰማን ከሆነ ያደግነው፥
ስንኩል እውቀቶችን ይዘንም ነው የምንጓዘው፤
ይህንን ነው፥ የዘመኑ ሰው ከግንዛቤ ማስገባት የተሳነው።

አይ! ...እኛ ሰዎች ሞኞች ሆነናል፥
ራሳችንን ማየት አቅቶናል፤
በውስጣችን ክፋትና ተንኮል ነግሦብናል፤
አንዳንዶቻችንም፥ ምሁራን የተባልን ሳይንቲስቶች፥
በገዛ እውቀቶቻችን ታውረናል፤
ስነ አመክኖአዊ አስተሳሰባችን ተወላግዷል፤
ከዘለኣለማዊ እውነታዎች ርቀናል፤
አንጻራዊ እውቀቶቻችንን አገዝፈን፥
ለእምነት ሥፍራ ነፍገናል።

የእውቀት አንጻራዊነት የማይካድ ቢሆንም፥
ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን ብናውቅም፥
በእውቀቶቻችን መሃል እየገባ እውነቶችን የሚያዳክም፥
ልዩ ምድራዊ እውቀት መኖሩ አይካድም።



የከሃድያን መንደር

## <u>የከሃድያን መንደር</u>

ከጥንቱም እነኛ የነስማዚያ ተከታዮች

በመንፈሶቻቸው የከበቡን፥

ውሸት እና ኃጢአትን አስተማሩን፤

በምድራዊ ፍልስፍናቸው አጨማለቁን፤

በስግብግብነታቸው አደኸዩን፤

እርስ በርሳችን ሲያገዳድሉንም፥ አንደ በግ ዝም አልን።

ከሳይንስ ተጨባጩን እውነት ባንክድም፥
ወደ ክህደት የሚያመራውን መለየት አላቃተንም።
ለምሳሌ፡- በአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን፥ ቻርለስ ዳርዊን የሚሉት ሰው፥
ሳይንሱን ከፀረ አምልኮ ፍልስፍና ጋር ሲያዋህደው፥
የእርስ በርስ ግንኙነትን በጊዜ ውስጥ ወደኋላ ሲመልሰው፥
የዘር መደቦችን (species) በማመሳሰል አንድ አደረጋቸው፥
ሰውንም ከእንስሳ አዛመደው።
ዳርዊን በጊዜ ውስጥ ነፍሳማ አካላት ሲኖሩ ሲሞቱ ያለፉበትን፥
እያነበበ የቅሪተ አካላቱን፥ በዝቅጠ አለታት የተመዘገቡትን።[78]
እርሱ ራሱ በጀመረው ቅድመ ሁኔታ (premise)
"መለወጥና መገኘት እንጂ፥ መፈጠር የለም" የሚለውን፥
የክህደትን መጀመሪያውን ሲያስተምረን፥
በማናውቀው ውስጥ ሌላ ልዩ እውቀት መኖሩን፥
የተዛባውንም ስነ አመክንዮ የሚያስተካክል፥
የእምነታችን ጉዳይ (ሃይማኖታችንን) ረስተን፥
ያንኑ የውሸት ሳይንስ ተቀብለን ብዙ ቆየን።
የዳርዊን ተከታዮች፥ በተለይም የእነ እስማዚያ ልጆች፥
እጅጉን ደስ አላቸው፥
በሳይንስ የተደገፈ አምልኮ ነውና የመጣላቸው፤
ከሰሜን ያሉትን፥ ነጫጮቹን ለይቶ፥
ወደ ላይ ከፍ ከፍ አደረጋቸው፤
"እናንተስ የ"ዝግመተ ለውጥ (evolution) ቀደምት፥
ከሰውም በላይ፥ ልዩዎች ሆናችኋል" አላቸው።
ከደቡብ ያሉትንም፥ ጥቋቁሮቹን ለይቶ፥
ዝቅ ዝቅ አደረጋቸው - አጣጣላቸው።
ዘረኞችም የጥናቱን ውጤት ተመርኩዘው፥

---

[78] ከምድራዊነታችን ባሻገር፥ ሦስተኛ መጽሐፍ

በአስተሳሰብም አንድነትን መሥርተው፥
ለግድያ፥ ለወረራ፥ ለብዝበዛ ተመቻቸው፤
ያ የርሱ የአንትሮፖሎጂ ጥናት፥ ትንቢቱና ግምገማው፥
የነጭን የበላይነት ነው እንዲህ ብሎ ያበሰረው፡-

“ይህ ብርቱውና ነጩ የሰው ዘር - ሠለጠነ የተባለው፥
እርሱ ነው ምድሪቱን የሚገዛው፤
እርሱ ነው፥ ብዙም ሳይቆይ፥
ኋላ ቀሩን ሕዝብ እጥፍቶ በራሱ የሚተካው”።[79]
ይህንን ነው ዳርዊን አስረግጦ የተነበየው፤
ይህም ትንቢት ለወራሪዎች ተመቻቸው።
ጥቁሮችን እንደ እንስሳ፥ እራሳቸውን እንደ መላእክት ቆጥረው፥
“…እኛ ነን ከሰውም በላይ” የሚሰኝ እምነታቸው፥
የምድሪቱን ሰማንያ በመቶ ለመቆጣጠር ረዳቸው።[80]

በከፊልም ቢሆን፥ የዳርዊን ትንቢቱ ሰመረለት፤
ብዙዎቻችንን ጨረሱን በጦር ኃይል ብዛት፤
ግን ማን መለወጥ ይችላል የተፈጥሮን ሂደት?
በአለም ታዋቂ ሆኗልና፤ የሰው ልጅ ሁሉ ተፈጥሮአዊ እኩልነት።
ሃቀኞች ሳይንቲስቶች ሃቀኛውን ሳይንስ ይዘው ዳርዊንን አጋለጡት፤[81]

---

[79] “……………At some future period not very distant as measured by centuries, the civilized races of man will almost certainly exterminate and replace the savage races throughout the world…….” Charles Darwin, in The Descent of Man, 1871

ትርጉም፡ - ለወደፊት የሰለጠነው የሰው ዘር (ነጩ ማለት ነው) በአለም ዙሪያ ያሉትን ኋላ ቀሮች (ሳቬጆች) ያጠፏቸውል።

[80] European colonialism spread across the globe, conquering more than 80% of the world's land between 1492 and 1914, according to Caltech and Foreign Affairs.

[81] የነኚህን ሃቀኞችና ታዋቂ ሳይንቲስቶች ሥራ (ለምሳሌ - Fazale Rona & Hugh Ross, 2004...) ይመልከቷል።

በዚች ምድር፥ የሚመሳሰል ነገር በበዛበት፥
በማመሳሰል ብቻ አይገኝምና እውነት፤
አብሮ አይሄድምና፤ ሳይንሳዊነት እና ስሜታዊ አስተያየት።
        የዳርዊንን ሥራዎች አንድ ባንድ ለመንቀፍ ሳይሆን፥
        በእውቀቶች መካከል ጣልቃ የሚገባውን፥
        የከፋት መንፈስን ሥራ ለማጋለጥ ስንል ብቻ ይህንን አልን።
ጥሩውና መጥፎው ሳይንስ በውጤቱ ይታወቃል፤
ጥሩው ሳይንስ ደስ ይላል፥
በሥጋ አጥግቦ መንፈስን ያረካል፤
መጥፎው ግን ያስጠላል፥
ከፈጣሪም ያጣላል፤
መንፈስን ያስጨንቃል፥ በመጨረሻም ያጋድላል።
ሰው ከፍቅርና ከእውነት የመነጨ እውቀቱ ሲያስደስተው፥
ከጥላቻና ከውሸት የመነጨ እውቀቱ ነው የቀበረው፤
ጥሩው እውቀቱ ባንድ ጎኑ ራሱን ሲጠቅመው፥
መጥፎው እውቀቱ ነው ወደ ከፋት እየመራ የጎዳው።
        እኛ ግን፥ የሠለጠን መስሎን፥
        ማንነታችንን ወደሚያሳጣ ትምህርት አመራን፤
        ስናድግ፥ የሆነውን ትተን፥ ያልሆነውን ሆን።
        ከትምህርት ቤት በሚመነጭ የዘመኑ እውቀት ተመርቀን፥
        የውጪያዊ ማንነታችን - መታወቂያችንን ይዘን እንዞራለን።
        መንፈሳዊው ማንነታችን (እኛነታችን) እየተናነቀን፥
        በእምነታችንም ውስጥ ጥርጣሬን አስገብተን፥
        ግራ የተጋባን ልዩ፥ ተጨናቂ ፍጥረታት ሆነን፥
        አወቅን ብለን እንደየብጤአችን፥
        እናቅራራለን - እንጮሃለን።
        ከእኛው፥ ከአብራካችን ከወጣ፥
        ከሄኖክም አንሰማ አልን፤

ትምህርት ማሳወቁን አንጂ፥ አላማና ግቡን አላየን፥
የከበረ እውቀታችንን፥
በተገንጣይ መላእክት እውቀት ቀየርን፤
በፀረ ፈጣሪ ትምህርቶቻቸው ሳቢያ፥
መንፈሳችንን ከመንፈሳቸው ቀላቀለን፤
ምድራዊ ብቻ በሆነ ፍልስፍናዎቻችው ተጠመቅን፤
እነርሱን ባሳወቁን አለም ውስጥ፥
አወቅን የምንለውን - እነርሱ ያሳወቁንን፥
መሰልን፥ ተመሳሰልን፥ እንዲሁም ሆነን ቀረን።

ከጥንትም በጦር መሳሪያ ግንባታ ነበር ሳይንሱ ያንሰራራው፤
እስከ ዛሬም ድረስ ከዚሁ የመነጨ ሳይንስ ነው የሚመራው፤
ታዲያ! ምድራችንን አጥፍቶ፥
ወደ ሌላ የጠፈር አካል (ፕላኔት) መዝመት ነው የታሰበው፤
ወይንስ ጥቂት ቱጃሮች፥ ከምርጥ የሰው ዘር በማዘጋጀት ላይ ናቸው፥
ምድሪቱን ለማድረግ የራሳቸው።

*"የእነርሱ ልጆች፥ ኔፊሊም (ግዙፋኖቹ)፥*
*ዘር ተከተው ባያልፉ፥*
*አሁንም ልጆቻቸውን ነጥቀው፥*
*ወደ ራሳቸው ለመውሰድ (?) እንዲህ ባልለፉ።"*

ዘመነ አሪትን ተሻግሮ፤ ዘመነ ሐዋርያትን ነካክቶ፤
ሃይማኖትን አጥፍቶ፥
ወይንም ለተንኮል እንዲመች ተመቻችቶ፥
አለም አቀፋዊ ስርዓትን መስርቶ፥...
ምድሪቱን ለጥቂት ብልጥች፥ ሃብታሞች ሰጥቶ፤..

ይህ ገመድ፥ የአለምን ሕዝብ በተንኮል የሚያስር፥
ይህ ታላቅ ሴራ፥ የእነ እስማዚያ ምስጢር፥
በጥቂት የሃብታሞች ስብስብ (HaKnesset) አለምን ለማስተዳደር፤
ከዚህም አልፎ ከሳይንቲስቶች በመመሳጠር፥

የሚካሄደው ምርምር፥ በላቦራቷር፥
እንደሰው የሚያስብ አንስሳ ለመፍጠር፥
ይህንን ይመስላልና፤
የከፉ ሰውና የከፉ መንፈስ ትብብር፤
ዝም ብለን አንይ፥
ምድራችን በከፉዎች ወደ ከፉው ስትቀየር።
እኛም የመንፈሳዊ መንገዳችንን ሳንለቅ፥
ቢያንስ ነቃ ብለን፥ ምድራዊ - ሰማያዊ ክስተቶችን እንከታተል፤
አይችልም ሰይጣን ምድራቱን ከኛ ሊነጥቅ፤
በእምነት እንጽና፥[82]
ኃይልና ሥልጣን እግዚአብሔር ነውና።

---

[82] እምነትስ ተስፋ ስልምናደርገው ነገር የምታረጋግጥ፥ የማናየውንም ነገር የምታስረዳ ናት። ዕብ. 11፡1

የማይታየውን እንጂ፥ የሚታየውን ተስፋ አናደርግም፤ የሚታየው ኃላፊ ነውና፤ የማይታየው ግን፥ ለዘለአለም የሚኖር ነው። 2ኛ ቆሮ. 4፡18



መገልገያ መሳሪያዎች

## ***<u>መሠልጠን ወይንስ መሠይጠን</u>***

በቀና ልቡና አዳዲስ ግኝቶችን ባመጡ ሳይንቲስቶች
እጅግ ተበራክተው ዘመናዊ መገልገያ መሳሪያዎች፥
የሰው ልጅ ምድራዊ (ሥጋዊ) ሕይወት ሲሻሻል፥
ይህንን ማን ይጠላል?
ነገር ግን፥ በአንጻሩ ክፉ ነገር በዝቷል፤
ሥልጣኔ ለበጎ ነገር ብቻ እንዳይውል፥
በውስጡ ሰይጣናዊ መርዝ ተዘርቷል።
ሰባአዊ እድገትና መሻሻል ያገኘንበትን፥
ስግብግቦች - መጥፎዎች፥

በትምህርትም የዘለቁ ደንቆሮዎች፥
ወደ ሰብአዊ ዝቅጠት መርተውታል።
ሥልጣኔ ጥሩ እና ክፉ ጎን እንዳለው፥
ክፉው ሥልጣን ይዞ - ምድራዊነት አለማችንን ከመራው፥
ክፉ - ሰይጣናዊ ስለሚሆን አቅጣጫው፥
ክፉውን ከጥሩው ሥ**ል**ጣኔ ለይተን፥
“ሥ**ይ**ጣኔ” አልነው።
ምንድነው የሥልጣኔአችንን መልክ የሚቀይረው?
ሰይጣናዊ የሚያደርገው፤
ወይንስ ምን እየጎደለው ነው?
የሰብእናችንን ደረጃ ቁልቁል የሚያድገው።
ሳይንሳዊ እውቀት - የሥልጣኔአችን አንቀሳቃሽ ሞተር፥
ብትንትን አድርጎ ሲያስተምረን የተፈጥሮን ምሥጢር፥
የኛም እምነት ጸንቶ በሳይንቲስቶች ምርምር፥
እነርሱው በቀደዱት ፈር ብቻ መጓዝን መረጥን፤
ለየት ባለ መንገድ - ለብቻ (በነፃነት) ማሰብ መመራመር ተውን።
ከዘመኑ ሥልጣኔ የደረስነውም በአንድ አቅጣጫ እየተጓዝን ነው፡-
በዛው - በእነርሱ መንገድ - ግዑዝ - መንፈስ በጎደለው፥
በዛው - በእነርሱ ስነ አመክንዮ - በቁስ አካላዊ ህግጋት ብቻ በሚመራው፥
በዛው - በእነርሱ እውቀት - ከምድራዊነት በማይወጣው፥
በዛው - በእነርሱ ትምህርት ለሃይማኖት - ለእምነት ክፍተት በማይሰጠው።
ታዲያ አሁን - በሥልጣኔአችን ውስጥ ከጥሩው ክፉው አይሎ አየነው፤
ወይንም ሰው (መንግሥታዊ አስተዳደር) ሥልጣኔን ለሥይጣኔ ሲያውለው፥
“ማንም ሰው ያሻውን ያድርግ..” በሚል መርሆ ከተውነው፥
ከልማት ወደ ጥፋት - ከጥሩነት ወደ ክፋት እየሄድን'ኮነው።

**<u>የምድራዊ እውቀት ሂደት</u>**

የዘመኑን ግስጋሴ እንመርምር፥

ከጥሩ ነገር ጎን ለጎን የሚያድጉ ክፉዎችን እንቆጣጠር፥
የመጥፎነትን ጎዳና በጥሩነታችን እንስበር፤
ወይንም ወደ ጥሩነት የሚመራ አዲስ ሥልጣኔ እንፍጠር.።
ካለማወቅ ወደማወቅ መሸጋገር፥
አውቆም እውቀትን መተርጎም በተግባር፥
ለዚህም የሚያበቃውን ትምህርት መማር፥
እውቀትን ማዳበር፥
የዳበረውንም እውቀት በሥራ መተርጎም፥
በግብርና፥ በቴክኖሎጂ፥ በሶሻል፥ በኢኮኖሚ ፖለቲካም፥
በሁሉም ዘርፍ ግልጋሎት - ለሰው ልጅ የሚጠቅም፥
የነገሮችን ጥሩ ጎን በማየት፥
ጅማሬውን፥ ሂደቱን እና መጨረሻውንም በማጥናት፥
በመንፈሳዊ ቁጥጥር - ከስንፍና ከድንቁርና መውጣት፥
ከምድሪቱ የሚበላና የሚጠጣ- ቆንጆ ነገር ማብዛት፥
በሥጋም በመንፈስም ትልቅ መሆን - አምሮ ደምቆ መታየት፥
ጥሩ ጥሩ ነገር እየፈጠሩ ኑሮን ማመቻቸት..፤
የሰውን ልጅ በቅን ልቦና በፍቅር እና በአንድነት ማሰባሰብ፥
ምድራዊ ኑሮን ከገዳማዊ ኑሮ ማቀራረብ፥
ይህ ከሆነ የሥልጣኔ ሂደቱ እና የመጨረሻ አላማው፥
ይህንን በበጎ አይን ማየት መልካም ነው፤
ሆኖም፥ እንዲህ ያለውን ስርዓት የሚፈጠረው ማነው?
በመለኮታዊ ኃይል የሚመራ አስተዳደር ነው የሚያስፈልገው።
ጥሩ የተባለው ጥሩ ሆኖ ሳለ፥ ሰው ከጠላው፥
ጥሩውን የማይወድ ያ ሰው ችግር አለው።
የቅርብ ጊዜ አባቶቻችን የዘመኑ ሥልጣኔ ጥሩ መስሏቸው፥
ልጆቻቸው ሃብታም ሲሆኑ፥ ተምረውና ሥራ ይዘው፥
አንዳንዶችም ወዳጅ ዘመድ ሲረዱ ራሳቸውን ችለው፥
በዚህ ጥሩ ውጤት ሥልጣኔ ባመጣው፥

ደስታው ለሁላችንም ነበር፥
ከሥልጣኔ ጎን የበቀለውን ሰንኮፍ እስክናየው።
ህብረተሰባችን ድንገት ሲለወጥ፥
ከሰው ልቡ እጁ ሲበልጥ፥
ፍቅር ሲሸረሸር - ትህትና እንደ ሞኝነት፥
ውሸት መዋሸትም እንደ ብልጠት ሲቆጠር፥
ሰውን ማክበር ሲቀር፤
ያ ከአባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የወረስነው መልካሙ ጠባይ፥
ከመንፈሳዊነት ጋር አብሮ ማደግ፥
መልካሙ ባህላችን - ጨዋነት - ደግነት፥
በክፋውም በደጉም አብሮ መሆን - መረዳዳት፥
ሲቀየር በራስ ወዳድነት፥
አባቶቻችን ከሩቅ ያስተዋሉትን መጥፎ ጊዜ “ስምንተኛው ሺ”
እኛም ደረስንበት፤
እኛም አሁን ገባን - የአባቶቻችን ጭንቀት።
ይህ የዘመኑ ሥልጣኔ ሂደት፥
በሃሳብም በተግባርም እጅግ ርቅቅ ማለት፥
በኮምፑተር እና በሞባይል - በኢሌክትሮኒክስ ፍጥነት፥
ይህስ በጣም ደስ ይላል - ልጆቻችንን ፍጥን ፍጥን፥
ጥድፍ ጥድፍ ሲሉ ማየት፤
ለሥራ ከሆነ መልካም ነገር ለማፍራት - ለጋራ ሃብት፥
ብሎም ለፍቅር - አብሮም ለመደሰት።
ግን የዝመኑን ሥልጣኔ በፍርኃትና በጥርጣሬ ነው ያየነው፥
ከእኛነታችን ርቆ የሄደ ባህርይ - መጨረሻው የት ድረስ ነው?
ሥ**ል**ጣኔ ወደ ሥ**ይ**ጣኔ ሲያድግ፥
ማን ሊሆን ነው ተጠያቂው?
ሥልጣኔ ራሱ ወይንስ ተጠቃሚው?
የሰዎች ልዕልና ቢሆን የሥልጣኔ መለኪያው፥

የትኛው አገር ነው ከፍ ብሎ የሚታየው?
አሜሪካ ነው? እጅግ ሥልጡን አገር የሚባለው
ግን በእስረኞች ብዛት አንደኛ የሆነው?
አይ! እንዲሁ አገር ሳንጠቅስ፥
ሥልጣኔ የሚለካ ቢሆን በከተሞች እድገት - በፎቆች ትልቅነት፥
በመሃንዲሳዊ ግንባታዎች ጥራት፥
በቤቶች ትልቅነት - በክፍሎቹ ብዛት እና በእቃው አይነት፥
የተጠቃሚዎቹም የተንደላቀቀ ኑሮ ቢሆን የሥልጣኔ መለኪያው፥
ከእንዲህ ያለ ሥፍራ 'ኮነው፥ ሰው ራሱን ከራሱ ያራቀው፤
ከእንዲህ ያለ ሥፍራ 'ኮነው፥ ሰውና ሰው የማይተዋወቀው።
ታዲያ፡- ማነው ተጠያቂው፥
ለእንዲህ አይነቱ ሥልጣኔ - መንፈሳዊነት ለጎደለው፥
ተጠያቂው - ሥልጣኔ ራሱ ነው? ወይንስ ተጠቃሚው?
ከስነ ምድር እስከ ስነ ጠፈር - እውቀት በእውቀት ላይ ሲዳብር፤
የጠፈር መንኮራኩር - ለበለጠ ምርምር፥
የሰው እውቀቱ - ሥልጣኔውም ከምድራችን አልፎ ሲሻገር፤
እግዚአብሔር አስቀድሞ በፈጠረው አእምሮ
ዘመናዊው እውቀት ተንቆርቁሮ፥
በዚያው ልክ - የሥልጣኔዎች ተውሳክ
ከመሃል እየገባ የሚያውክ፥
ቀና አመለካከቶችን የሚቀጭ፥
ሰባአዊ እድገቶችንም የሚያቀጭጭ፥
ማነው? ምንድነው ለዚህ ተጠያቂው?
የሰው ልጅ ምድራዊ - ሰማያዊ ሲሆን በተፈጥሮው፥
በእርግጥ መንፈሳዊ ሥልጣኔም ነው የሚያስፈልገው።
ቀስ በቀስ ከምድራዊነቱ እንዲላቀቅ፥
ወደ ሰማያዊነቱም እንዲጠጋ የሚረዳው።
የሰው ልጅ፥ ውስጣዊ መንፈሳዊ ተፈጥሮውን የሚቀሰቅስበት ኃይል አነሰው፥

እምነት - ሃይማኖት ጎደለው፥
ምድሪቱም በሰማያዊ ልምላሜ ደስታን የምትሰርጽ እንዳትሆን፥
ከውስጧ መንፈሳዊነትን የሚያመነጭ ኃይል አነሳት፤
ይህቺን አለም ከውስጧ ነፍሳማነቷን የሚሰልብ፥
ዘመናዊው ሥልጣኔ (ሥይጣኔ) ነው የሚያጠፋት።

ጨካኝ በሆነ ሳይንስ ምድሪቱን ለማቃጠል፤
ከእሳተ ገሞራ የበለጠ ኃይል ተዘጋጅቷል፤
መንፈሳዊነት የጎደለው ትምህርት፥
መጨረሻው ይሆናል እልቂት።
ታዲያ ማነው ለሥይጣኔ ተጠያቂው?
ሥልጣኔ ራሱ ወይንስ ተጠቃሚው?

የዘመኑ ሥልጣኔ - እጅግ ማራኪ፥
ሲያዩት ደስ የሚል ግን መንፈስን አዋኪ፤
ሰውንም ያሳብዳል አንዳንድ ጊዜ፥
በእሱነቱ አላስኖር ሲለው፥
በሃሳብም እንዲዋጥ ሲያደርገው፥
አሳልፎም ሲሰጠው ለሃዘን ለትካዜ።

ሰይጣን ተንኮለኛ - ከቶ አይለቃትም ይህቺን ምድር፥
እርሱም እንደ እግዚአብሔር ቢያቅተው መፍጠር፥
ይሁን ብሎ - ካለመሆን ወደመሆን ማሸጋገር፥
ይታገላል - የተፈጠረውን - ፍጥረትን ሊቀያይር፥
ወደራሱ ለማስጠጋት ይሞክራል - እውቀቱን በማካፈል፥
“የራሱንም ሥልጣኔ” በማስተምር።
ግን፥ እንዳው ተስፋ የማቆርጥ መሰሪ፥
ያንኑ የእግዚአብሔርን ፍጥረት ተጠቃሚ፥
ቁስ አካልን አንቀሳቅሶ፥ ሊባል ይፈልጋል ፈጣሪ።

ግን ያም ባይሆን - ስናስተውል፡-
በእውቀት ሳይሆን እንዲሁ በይመስላል - ምርምር፥

የሰው ዘር እንደ አንድ የውሃ ጠብታ ቢቆጠር፥
ሕይወት - ሥልጣኔም ውቂያኖስ ነው፥
ተዘርቷል በጠፈር።
የጥንቱን (የእነ እስማዚያን) እንደ ሥልጣኔ ምንጭ መቁጠር ብዙ አያስኬድም፥
የዘመኑ ሥልጣኔ አመጣጡ ከአንድ ሥፍራ/አካባቢ ቢመስልም፥
በብዙ ጊዜ የእውቀት ድርብርቦሽ እንጂ ባንዴ አልመጣም፤
ጥቅሙና ጉዳቱም ለመላው አለም መሆኑ አልቀረም።

ምድር ስትሆን ጥቂቶች ተንደላቀው የሚኖሩባት፥
ብዙዎችም የሚሰቃዩባት፥
ከምናስበው ሥልጣኔ በስተጀርባ አብሮት ያደገ ክፋት ነው የነገሠባት።
ወደድንም ጠላንም፥ በዘመኑ ሥልጣኔ ሳቢያ ነው፥
የሰው የተፈጥሮ ጠባዩ የተለወጠው - የሦየጠነው፤
ከዚያም ተከትሎ ነው ህብረተሰቡ ኃጢአትን በመሥራት የተራቀቀው፤
ህብረተሰቡ ፍቅረ ሰብን በፍቅረ ገንዘብ ሲለውጠው፥
የዛን ጊዜ ነው የዘመኑ ሥልጣኔ ሰውን ያረከሰው።

የአለም ሕዝብ ወደ ሥይጣኔ የተሳበው፥
በእርግጥ ከትምህርቱ ነው?
ከጥንትም ጥሩነት - መንፈሳዊነት ከጎደለው?
ወይንስ የትምህርቱን አጠቃቀም ባለማወቅ ነው፥
ህብረተሰብ ራሱን ወደ ሥይጣኔ የመራው?
ለጥያቄዎቻችን ብዙ መልሶች ቢኖራቸውም፥
የማናውቀውና ሊገባን የማይችል ቢኖርም፥
የሥልጣኔአችንን መነሻና መዳረሻ መመርምር አይከፋም።

ከማወቅ ጋር ድንቁርናም እንደሚያድግ ካላወቅን፥
መጥፎ መጥፎውን (ጎጂና ጎታቹን) ካላስወገድን፥
ከሰርን እንጂ ምንም አላተረፍን።

**<u>የዘመኑ ሥልጣኔ መንስኤ</u>**

የዘመኑ ሥልጣኔ ምንጩ አንድ - አስተዳደጉም አንድ፥

የብዙ ጊዜ ምርምር ውጤት፥
የእውቀት ግንብ - የዳበረ በትምህርት።
መጀመሪያ አመጣጡ ከጥቂት የሰሜን ሰዎች፥
እውቀት ከተገለጠላቸው ፈላስፎች - ሳይንቲስቶች።

ለሰፊ የእውቀት ግንባታ፥
የሳይንስ፥ የሂሳብ፥ የፍልስፍና፥ ወ.ዘ.ተ. ትምህርቶች፥
መማርና ማስተማር ተጀመረ ሁሉንም በተርታ፥
እስከ ዘመኑ ሥልጣኔም ተደረሰ - ከብዙ ዓመታት ጀምሮ በዝግታ።

የቀድሞ ሥልጣኔ - የግብጽ የኢትዮጵያ፥
የህንድ የቻይና፥ የአራቢያ የፐርሺያ፥
የአዝቴክ፥ የኢንካ፥ የማያ፥
ተዳፍኖ ቀረ - ከፍ ሳይል ባለበት ተቀበረ፤
የአውሮፓው አንሰራራ - ከፍ ከፍ አለ - ተጠናከረ፤
በጥቂት ሩቅ አሳቢዎች አእምሮ የሰረገ እውቀት፥
እርስ በርሱ እየተያያዘ - እየተደጋገፈ፥
ለዘመኑ ሥልጣኔ መሠረት ሆነ።
ከየት መጣ ሳይባል፡-
አጠቃላይ (ሁለ ገብ) የእውቀት ጮራ ፈንጥቆ፥
በእነ አሪስቶትል (384–322 BC) - በፕላቶ (427–347 BC) ተንሰራርቶ፥
በእነ አርቺመደስ (287–212 BC) እና ሌሎችም ማተማቲክስ ቀን አግኝቶ፥
በአይዛክ ኒውተን (1642–1727) የካልኩለስ ግኝት፥
ሳይንስ ኢንጂኔሪንግ እጅጉን ዳበረ፤
እንደ ዘመናችን አይነት የህክምና ምርመራ
በሂፖክራተስ (460–370 BC) ተጀመረ፤
በጆህን ዳልቶን (1766–1844)
በድሚትሪ ሜንዴሌቭ (1834–1907)
እና ሌሎችም የኬሚስትሪ ሊቃውንት፥
ይታወቅ ጀመር የንጥረ ነገር ጠባይ - አይነትና ብዛት።

በሉይስ ፓስተር (1822–1895) ሲታወቅ የባክተሪያ (ጀርሞች) እርባታ፥
እጅግ ተሻሻለ የሃኪም ቤቶች ሥራ።
በማሪ ኩሪ (1867–1934) የበስባሽ ንጥረ ነገሮች ግኝት፥
አዳዲስ መሳሪያዎች ተገነቡ፥ የካንሰር ሴሎችን እድገት ለመግታት፤
በኒኮላስ ኮፐርኒከስ (1473–1543)፥ በጋሊሌኦ ጋሊሊ (1564–1642)፥
ጆሃነስ ኬፕለር (1571–1630)፥ ኤድሞንድ ሃሌይ (1656–1742) ፥
ኢድዊን ኸብል (1889–1953) እና ሌሎችም የከዋክብት ጥናት
በጠፈር መካከል ምድራችንን እንደ አንድ የውሃ ጠብታ አስቀጠራት።
ከአልፍሬድ ኖቤል (1833–1896) የፈንጂ (ዲናሞ) ግኝት ይልቅ፥
በአልበርት አይንስታይን (1879–1955) በንጥረ ነገር ይዘት እና ፍጥነት ጥምረት፥
በትንሽ ነገር - በኃይል በመምታት ታላቅ ጉዳት፤
በሚሳይል በሮኬት ኑክሊየር ቦምብ አስወናጭፎ፥
ከሰማይ እሳት አዝንቦ ሕይወት ማጥፋት፤
ማቃጠል መፍጀት - ማውደም፥  ምድራዊ ገሃነም እሳት...።

በታንክና በመድፍ ወይንም በመትረየስ ጥይቶችን አርከፍክፎ፥
ሰውን ከነንብረቱን አደባይቶ....፥
እንዲህም ሥይጣኔ በራሱ ከበረ፤
የሰው እውቀቱና ክፋቱን አጋምዶ።

ግን ግርም የሚለው፡-
የሰው እውቀቱ ወደ ክፋት ቢወስደውም፥
ወደ ጥሩነት የሚገፋ እውቀትም አላጣም።
በእስቲቨን ሃውኪንግ (1942–2018) እና ሌሎችም የፊዚክ ሊቃውንት፥
በጽልመተ ጥልቀት የጠፈር ውስጥ ግፊት…፥
መዞር መሽከርከር በበዛበት፥
ለጠፈርም ከመዘረጋት ጋር የጠፈር መሰብሰብ እንዳለበት፥[83]

[83] ስለ ጠፈር መሰብሰብ - ከምድራዊነታችን ባሻገር - ሦስተኛ መጽሐፍ https://www.amharicbooksforunity.org/amharicbooksforunity

ይህንንም ተማርን - እጅግ የረቀቀ የፊዚክ ትምህርት፥
ተመስገን፤
የሳይንስ እውቀታችን፥
የስነ ምድር - የጠፈር ምርምራችን፥
የእግዚአብሔርን ሥራ እንድናደንቅለት አደረገን....፤መዝ.8፡ 1-9
ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥
የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል...። መዝ. 18፥1
ከዋክብት አገረ ከዋክብት - እኛም ተደምረን
ተመስገን የእግዚአብሔር ምስክሮች ለመሆን አበቃን። መዝ. 118፡129
በተጠቀሱትና በሌሎችም - በአለም ዙሪያ የነበሩና ያሉ ሳይንቲስት፥
ለአለማችን ስላበረከቱ ታላቅ እውቀት፥
ሲዘከሩ ይኖራሉ - በክብርና በአድናቆት።
ግን ከተጠቀሱት ጎን "እንደ ሳይንቲስይት" የማይቆጠር፥
ዳርዊን የተባለ የሥ**ይ**ጣኔ መምህር፥
የእግዚአብሔርን ዝግመተ ለውጥ፥
በመገኘት እንጂ በመፈጠር እንዳልሆነ ሲያመሳጥር፥
ሳይንስ መሳይ መርዝ እርሱ የነሰነሰው፥
ሃቀኛ ሳይንቶስችንም ነበር ያስደነበረው።

ዳርዊን የከጀለው፥ ሰውን ከዝንጀሮ በሆሚኒድ ሊያዛምደው፥
ዝንጀሮን በፕሪሜትስ ከአንትሮፓይዳ ሊያገናኘው፥
እንዲህ እያለ ወደ አንዲት ህዋስ ሰውን ሊመልሰው።[84]

እንዲህ ሰውን መንፈስ አልባ የሚያደርግ እጅግ በማኮስስ፥
አሁንም በዘመናችን እንደ ትምህርት ይሰጣል፤
አካላዊ ማስረጃዎችም በስነ አመክንዮ ቀውስ ተቀነባብረዋል።
ታዲያ እንዲህ በሁለት ኃይላት የተወጠረ ሰው

[84] ከምድራዊነታችን ባሻገር - ሦስተኛ መጽሐፍ

እንዴት ነው ካለመሰይጠን ኑሮውን የሚመራው?

ህብረተሰብ ሲሠለጥን፥

ከሥልጣኔውም ጋር ሲሠየጥን፥

“ከየት ተነስተን ከዚህ ደረስን?” ብለን መጠየቃችን፥

ያለንበትን አቋማችንን - ሂደታችንን ከወዲሁ ተመልክተን፥

መጥፎውን ሂደት እንድንገታው፥

የተሻለ ሥልጣኔም ቢኖር እንድናስበውና እንድናገኘው፥

ይህ ቢሆን ነው ድካማችን ፍሬ የሚያፈራው።

በማይክሮስኮፕ የማይታዩ ረቂቃን ጀርሞች - የአስተሳሰብ ተውሳኮች፥

አጋንንት ብንላቸው ሰይጣናት ወይንም ጂኒዎች፥

ብን ብን እያሉ በዙሪያችን፥

ቀዳዳ ሲያገኙ እየገቡ ከአእምሮአችን፥

በሳይንሱም ሆነ በሃይማኖት፥

ጥልቅ እያሉ ሳንፈልጋቸው፥

አንዱን እውነት ሺህ እውነት አስመስለው፥

እውነት መሳይ ውሸቶችን ሲሰብኩን፥

እነርሱ ሊያሟሉ እቅዳቸውን - የማሰይጠን ተግባራቸውን፤

እነርሱ እኛን በሳይንሱም፥ በፖለቲካውም፥ በፍልስፍናውም ሲሰብኩን - ሲለያዩን፥

እኛም እኛነታችንን (ተፈጥሮአዊ ማንነታችንን) ረስተን፥

እነርሱኑ መሰልን።

“እባካችሁ - ስለ ፍቅር በስመ አብ ማለት ይቅር”

ይላል ሰይጣን አንዲሉ፥

መጥፎዎች ጥሩ - ጥሩዎችም መጥፎ እስኪመስሉ፥

በሥልጣኔ ስም ኃጢአቶች ይሰበካሉ፤

ኃጢአቶች ሲሰበኩ፥ ሰዎችም በትልቅ በትንሹ ሲጣሉ፥

በዚህ (የንጭንጭ ዘመን) ይታወቃል የሰይጣን ተንኮል ማየሉ።

ወደ ክፋት የሚያመራ ጎዳና ሲቀየስ፥

ሰውን ወደ ክፋት የሚወስድ ፍልስፍና ሲጠነሰስ፥

እውቀትን - ብልሃትን በመንተራስ፥
በዚህ ይታወቃል፥ የሃሳዊ መሲህ ንግስ።
የአስተሳሰብ ተውሳኮች ከጎናችን፥
ጥሩውን እንዳናይ አይነ ጥላ ሆነውብን፥
እንዴት ነው የምንመራው ኑሮአችንን - ካለመሠ**ይ**ጠን?
ሰው እንዴት እራሱን ያድን?
ወይንም እንዴት ወደ ሰይጣን ከመገፋት ይዳን?
ሳይንቲስቶችም በጥቅሉ ይታማሉ፤
"ሰውን ከእግዚአብሔር የሚያርቁ ናቸው..." ይባላሉ።
በእግዚአብሔር የማያምኑትን ከሚያምኑት በደንብ መለየት ባንችልም፥
ከመካከላቸው እንደ ሚካኤል ፋራዴይ ያሉ ሰባኪያን አልታጡም።
ጋሊሊዎ ጋሊሊ "መጽፍ ቅዱስ ዋሾ ሊሆን አይችልም" ሲል፥
"እምላኬ አትተወኝ..." እያለም ይጸልይ ነበር ይባላል።
የታላቁ አይዛክ ኒውተን ካልኩለስ፥
ለውጦችን ከጊዜ ጋር አጣምሮ የማስላት ጥበብ፥
ጥልቅ በሆነ ሃይማኖታዊ ፍልስፍናው ታጅቧል፤[85]
"ሳይንቲስቶች በእግዚአብሔር አያምኑም፥
ሳይንስና ሃይማኖት ይቃረናሉ..." ለሚሉ፥
"ሳይንስ ካለ ሃይማኖት አንካሳ ነው፤
ሃይማኖትም ካለ ሳይንስ እውር ነው" ያለውን
የአንስታይንን አባባል ያስተውሉ።[86]

---

[85]"....The most beautiful system of the sun, planets, and comets, could only proceed from the counsel and dominion of an intelligent and powerful Being." https://en.wikipedia.org/wiki/Isaac_Newton

[86] "Science without religion is lame, religion without science is blind." https://www.biography.com/scientist/albert-einstein

ይህንን አባባል በግርድፉ መቀበል ሊከብድ ይችላል፤
ግን፥ የሳይንስ እውነታዎች እውነት ከሆኑ፥
የሃይማኖትም እውነታዎች እውነት ከሆኑ፥
እምኑ ላይ ነው ጥሉ?
ለብዙ ዓመታት ብዙ እውቀቶች ተደማምረውና ተቀጣጥለው፥
የዘመኑን ሥልጣኔ በመፍጠራቸው፥
ምንም ክፋት ባይኖርም በውስጣቸው፥
መሠረተ ትምህርትን ከምድራዊነት ላይ ብቻ በማንተራሳቸው፥
ለሰብአዊ መንፈሳዊ እድገት እውቅና ባለመስጠታቸው፥
መንፈሳዊነትን በሚሰርጽ ፍልስፍና ላይ ባለማተኮራቸው፥
ሁሉን አቀፍ የሆነ መንፈሳዊ ሥልጣኔን እንዳናየው፥
የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ማንነቱን፥
የእግዚአብሔር ጥበብ በሥፍራዎች ሁሉ መገኘቱን፥
ይህንን ሃቅ በመሳታቸው፥
የቀረብንን ሰማያዊ የእውቀት ጸጋ ሳናውቅ ብዙ ቆየን፥
የጎደለንን ባለማወቃችን ተጎዳን።

ከኃጢአተኛ መላእክት - የአስተሳሰብ ተውሳክ - የማይታዩ ጀርሞች፥
የርዕዮት ጠባብነትን - የስነ አመክዮ ጠማማነትን የሚያስተምሩ፥
ልዝብ ሰይጣኖች - እርኩሶች - ጋኔሎች - ጂኒዎች፥
እንደ ቀሳውስት - እንደ ሳይንቲስትም ሆነው፥
በሰዎች መካከል ጥልቅ የሚሉ የእርጎ ዝንቦች፥
ካሁን በፊት እንደነበሩ አሁንም አልጠፉም።
ትንንቅ - ትግል ቀርቶ አያውቅም፤
ግን ሰብረን ሄደናል ኬላውን፥
አንዳንዴ ስንፈጥን አንዳንዴም ስናዘግም።

እስከ 16ኛው ዘመን ድረስ
ሥልጣኔ በዝግታ እያደገ ቆይቶ፥
ሳይንሳዊ አብዮት ድንገት ፈንድቶ፥

በነሚካኤል ፋራደይ፥ ጀምስ ዋት፥
በነቶማስ ኤዲሰን እና ሌሎችም፥
ጽንሰ ሃሳብና ተግባረ እድ እርስ በርስ ተጋምደው፥
ሲንቀረፈፍ የነበረውን ሥልጣኔ አጣደፈው፤
እውቀትንም ከምቾት ጋር እንዲጣመር አደረገው።
የእንፋሎት ግፊት ሞተር እና ኃማ - የኢሌክትሪክ ሙቀትና ብርሃን፥
መኪና ባቡር ሮኬት አይሮፕላን፥
ሬዲዮ ቴሌቪዢን፥
ስልክ ኮምፑተር ፔኒሲሊን............፥
እንግዲህ ማን ይጠላል ምቾትን?
ገንዘብ ያለው የሚሸምተውን፤
ከድሎትም ድሎት ሥራን የሚያቃልል ፕሮግራም በኮምፑተር፥
ለፋብሪካ፥ ለእርሻ ሥራ - ለትምህርት ለምርምር፤
ሮቦት የኮምፑተር ውጤት - ለሰው አሽከር ይሆን ጀመር።
መቀላወጥ ብቻ አይበቃምና ሌሎቹን እያየን፥
የተደላደለ ምድራዊ ኑሮ እያጓጓን፤
በምድራዊ ሥልጣኔ  የቀደሙንን እየተከተልን፥
እኛም ከዘመኑ ሥልጣኔ ተካፋዮች ለመሆን በቃን።
በጥቂት አስተዋዮች አእምሮ እየተጠነሰሰ፥
ከቶ እማይደርቅ የእውቀት ምንጭ እንደ ውሃ ፈሰሰ፤
ዘመናዊውን ትምህርት ለሚማሩ ሁሉ ተዳረሰ።
የሰው ልጅ አእምሮ (ለክፉም ሆነ ለደግ) አስቀድሞ በተደነገገ፥
የእውቀት ጎዳና እየተመራ፥
በአንድ ውሱን ስነ አመክንዮ እየተገራ፥
እግዚአብሔር አስቀድሞ በፈጠረው
በተፈጥሮ ላይ ተራቀቀና፥
በንጥረ ነገሮች ውስጥ የሚሯሯጡትን ደቂቀ አካላት፥
ከኢሌክትሮን - ፕሮቶን እስከ ኑክሊየስ ያሉትን ሁሉ አስተዋለና፥

እውቀትን በእውቀት አሳደገ - አንዱን ባንዱ እያደራረበ፥
የሰውም ልጅ ሠለጠነ ተባለ፥ ምድራዊ እውቀትን አወቀና።
የዘመኑ ሥልጣኔ መሠረቱ ምድራዊ እውቀት ሆነና፥
በምድራዊ እውቀት ሰው ሥጋዊ ምቾቱን ገነባና፥
በምድራዊ ጎዳና ሲጓዝ፥ ቀኑ እየጨለመ መጣና፥
መንፈሳዊ ጠባይን በሚያርቅ - ሰማያዊ አመለካከትን በሚጋርድ፥
በውስብስብ የእውቀት መንገድ ሲሄድ ሲሄድ፥
ማህበራዊ ጠባይን በሚያስረሳ - የሚያደርግ ራስ ወዳድ፥
ወደ ጠብና ጭቅጭቅ ወደ ጦርነትም በመግባቱ፥
እጅግ መራራ ሆነ ምድራዊ ሕይወቱ።

ከምድራዊነታችን ሕይወትን ዘርተናል፤
እጽዋት እንስሳትም ከኛ ጋር ኖረዋል፤
ማሕበራዊ ኑሮን ተፈጥሮ አስተምሮናል፤
አብሮ ለመዝለቅም - ተደጋግፎ መኖር - መሆኑን አውቀናል፤
በተፈጥሮ ውስጥ የመቆያን ምሥጢር ከሕይወት ቀስመናል፤
ዙሪያችንን ሁሉ አጥንተናል - ጠፈርንም አንኳን ለመዳሰስ ሞክረናል።
በተፈጥሮ ውስጥ የመራቀቅን ጥበብ ከዚህም ከዚያም ሸምተናል፤
በዘመናዊው ትምህርት ቤት ሁሉን ተምረናል፤
እና በዚያውም ሳናውቀው ተለውጠናል፤
ሥልጣኔ (ሥ**ይ**ጣኔ) ቀይሮናል።

የሳይንቲስቶችን ሥራ አድንቀን፥
ምድራዊ ሥልጣኔን ከነ ምቾቱ ወደን፥
ምድራዊ ሥልጣኔ እኛን እየመራን፥
በአድሎአዊ ምቾትና ድሎት ከፋፈለን።
ምን ያህሉን ተለውጠን ከዚህ ደረስን?
ወደ ፈጣሪያችን ተጠጋን ወይንስ ወደ ሰይጣን?
ምድር ስትሆን ጥቂቶች ተንደላቀው የሚኖሩባት፥
ብዙዎችም የሚሰቃዩባት፥

ሥልጣኔ ብቻውን ሳይሆን እንዲህ የለዋወጣት፥
ሥ**ይ**ጣኔም (ሰይጣናዊነትም) ተጨምሮ ነው ጉራማይሌ ያስመሰላት፤
ሥልጣኔ ሳይሆን ሥ**ይ**ጣኔ ነው ቀስ በቀስ የገነነባት።
የዘመኑ ሥልጣኔ ሰውን ወደ ሥ**ይ**ጣኔ ሲገፋፋው፥
የሰውን ዘር ለማጥፋት የረቀቁ መሳሪያዎች ተዘጋጅተው፡-

ሥልጣኔ  አልነው ሥ**ይ**ጣኔውን - ሰውን ወደ ክፋት የሚመራውን።
ሥልጣኔ ምኑን ሥልጣኔ ሆነ የሰውን ካላነጻ ልቦናውን፥
ሥልጣኔ ምኑን ሥልጣኔ ሆነ የሰውን ካላሻሻለ ጠባዩን፥
ሥልጣኔ ምኑን ሥልጣኔ ሆነ የሰውን ካላጎላ ጥሩውን፥
ካልቀበረ መጥፎውን።
ሥልጣኔ ምኑን ሥልጣኔ ሆነ - የሰውን ካላሳደገ ማዕረጉን፥
ካላሻገረ ምድራዊነቱን - ካላስመለከተ ሰማያዊውን።
ሥልጣኔ ምኑን ሥልጣኔ ሆነ - የሰማዩን ቅዳሴ
በምድር እንድንሰማው ካላስቻለ፥
ድሃ ሃብታም ሳይል ሰውን ሁሉ ከመላእክት ጎን ካላስዋለ።
ሥልጣኔ ምኑን ሥልጣኔ ሆነ - በሂደቱ የሰውን ልዕልና ካላጎላው፥
በአቅጣጫው ካልገራው - ሰማያዊ ፍጥረቱን ከቀማው።[87]

ቀደም ሲል - የቄስ ትምህርት ስንጀምር፥
ዛሬ ተገቢውን ሥፍራ ባጣ ፊደል ስንቆጥር፥
ሁሁ - አቡጊዳ ብለን - ወደ መልእክተ ዮሐንስ ስንሻገር፥
ተፈጥሮአዊ ማንነታችን (ጠባያችን) እንዳይቀይር፥
ከሥጋዊነታችን ጎን መንፈሳዊነታችንንም እንድናጠናክር በማሰብ ነበር።
በምድራዊ ሥልጣኔ እጅግ ባንገፋም - ራሳችንን በራሳችን ችለን፥
ኑሮን በአብሮነት - ሃዘን ደስታችንን በጋርዮሽ አድርገን፥

---

[87] “ይህን አለም አትምሰሉ፤ ልባችሁንም አድሱ፤ እግዚአብሔር የሚወደውን መልካሙንና እውነቱን ፍጽሙንም መርምሩ።” ሮሜ.. 12፡2

በመጠኑ እየኖርን፥ ከቁሰካላዊነት የረቀቀ ነበር መመልከታችን፤
ስለዚህም፥ ደስታን ያገኝ ነበር መንፈሳችን፥
ሳይጎዳ ሥጋችን፤
በምድራዊው አለም ሰማያዊም ይመስል ነበር ኑሮአችን።

አሁን (ከቅርብ ጊዜ ወዲህ) ግን፥
እኛም እንዲሁ በምድራዊው ሥልጣኔ ተማርከን፥
የተመቻቸ አለማዊ ኑሮ አጓጉቶን፥
በምድራዊነት ብቻ የተቀየሰ የኑሮ ዘይቤ፥
ወደርሱ የሚያመራውም ትምህርትና እውቀት - አለም ያደነቀው፥
ሥጋችንን ማረከው።
የእኛ የሆነውን በእጃችን የያዝነውን ጣልነው፤
ለኛ የሚሻለንን ለኛ በማይሻለን ለወጥነው፤
በማህበራዊ ኑሮ እርስ በርስ መተሳሰብ፥
በመንፈሳዊነትም መቀራረብ ቀርቶ ግለኝነት የኑሮ ዘዴአችን ሲሆን፥
በክፋት - በኃጢአት (ወይንም በሞኝነት) ብዛት ታውረን፥
በሥልጣኔ ስም ሥይጣኔ ሲሰለጥንብንም አላወቅን።

"እንካችሁ ጥበብ - ከኛ ተማሩ እውቀትን..." ሲሉን፥
"የትኛውን እውቀት - የቱን እንቀበል የቱን ትተን...?
የትኛው ነው እውቀት የትኛው ነው ጥበብ?" ሳንል፥
ተስገብግበን - ሁሉን አግበሰበስን፥
ሳንመርጥ ሳናማርጥ - የሰጡንን ሁሉን ተቀብለን፤
ለውጪ ሥልጣኔ ስንል የኛን የሥልጣኔ በር በራሳችን ላይ ዘጋን።
ትምህርታቸውን ሁሉንም ጠንቅቀን ተማርን፥
በሥልጣኔ ስም የእኛነታችንን ባህሬ በሌላ ቀየርን - ሠየጠንን።

"ሞኝ ውሃ ሲወስደው ይስቃል" እንዲሉ፥
በሥይጣኔ ጎርፍ ስንሄድ ስንሄድ...፥
"የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች" እንዲሉ፥
የተመኘነውን የፈለግነውን አገኘን።

“ሰማይ ይናዳል ብሎ ባላ ተከለ” እንዲሉ፥
የውጪውን የሥልጣኔ ምሰሶ ባገራችን ተክለን፤
የኛን የራሳችንን መንፈሳዊ ሥልጣኔ ጥለን፥
ከነርሱው ተምረን - ተምረን፥
የኛ ባልሆነው አለም ውስጥ መኖር እንደ ጀመርን፥
ሳናስበው እነርሱኑ መሰልን፤
የጣልነውን እኛነታችንን አጎንብሶ መመልከት አሳፈረን።
ለመሆኑ በዛ በቄስ ትምህርት ውስጥ - ንቀን በተውነው፥
በድቁና የሚከፈት የጥበብ በር ሲከፈት ምን ነበር የሚታየው?
ለምንበላው ለምንጠጣው ምሥጋና ቢኖረው፥
ኑሮአችን - እንቅስቃሴአችን ትርጉም ነበረው።
“ለዘብልአነ ዘንተ ሕብስቱ፥ ወለዘአስተየነ ዘንተ ጽውዓ” ሳንል፥
በጸሎተ ማዕድ ማሳርጉንም ተውን።
ግን ከየት ተነስተን እዚህ ደረስን?
ለወደፊትስ ምን ይሆን የሚጠብቀን?
ማንም ህብረተሰብ በራሱ የሚደርስበትን ሥልጣኔ
በራሱ ሥፍራና ጊዜ ማሳደግ ሳያቅተው፥
ከላይ ከሰሜን በመጣው ነው የራሱን ሥልጣኔ የለወጠው።
የቀድሞ ሥልጣኔአችን ሲዳፈን - ሲተካ የኛ ባልሆነው፥
ያኔ ነው የተቀየርነው ቡራቡሬ መልክ የያዝነው።
ሁላችንም - ልጆቻችንን - የልጅ ልጆቻችንንም እየተከተልን፥
ምድራዊ ኑሮን ብቻ የሚያሻሽል - አዲስ እውቀት አይሎብን፥
በመንፈሳዊ ሥልጣኔ ማደጋችንን ትተን፥
ያሳዝናል፤ ሳናውቀው በሥ**ይ**ጣኔ ተጠለፍን።



ባቢሎን

## <u>በቃ የተባለ ሥልጣኔ</u>

ከኖሕ የጥፋት ውሃ በኋላም የሰው ልጅ እንደገና በዛ። በዚያውም ሲቀጥል፥ የሰው ቅራኔ ከፈጣሪው ጋር መከሰቺያው የባቢሎን ግንብ ሆነ፤ እግዚአብሔርም ተቆጥቶ “በቃ!” አለ።

አንድ ቋንቋ የሚናገር የባቢሎን ዘመን ሕዝብ በምድራዊ ጥበቡ ሰማይ ጠቀስ ግንብን ሲገነባ፥ ይህ አካሄድ ወዴት እንደሚያደርስ፥ ሕዝቡ አልተረዳውም ነበር።

እግዚአብሔር የሕዝቡን ቋንቋ ደባለቀው። አንድ ወጥ የሆነ ሕዝብ የተለያዩ ሕዝቦች ሆኑ። ሕዝቦቹንም በምድር ላይ ሁሉ በተናቸው።[88]

መጀመሪያው ትእቢት፥ መጨረሻው ቅጣት፥
የአለማመን ቡቃያ፥ የኃጢአት ምርት።
የተንኮል ሥልጣኔ - የከንቱ ፍላጎት ውጤት፥
እንደ ቁጫጭ እንደ ዘመሚት ሲርመሰመስ፥
በሰማይ ጠቀስ ግንብ ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ፥
ይህንን ለጥቂት ሰዎች ችሎታ መታሰቢያ፣
ለዝናቸውም ማስታወሺያ፥
እንዲህ ያለው ኃጢአት - ገደብ በሌለው እብሪት፥
የክህደት አምልኮን በአንድ ቋንቋና በህብረት፥
በእግዚአብሔር ፊት መገንባት ካለ ሃፍረት።.
ፍጡር ከፈጣሪው አይወዳደርም፤
ምድራዊ ሰው እግዚአብሔርን አያገኝም።
የኩሽ ልጅ የናምሩድ፥
በምድራዊነትህ አትጠመድ፤
በትዕቢት አትወጠር፥
የመጣህበትን አስታውስ - ፈጣሪህን አክብር።
እግዚአብሔር ምድሪቱን ፈጥሮ ባዶዋን እንዳትቀር

[88] “ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ነበረች። ...ኑ ጡብ እንሥራ፥ በእሳትም እንለኩሰው ተባባሉ። ጡቡም እንደ ድንጋይ ሆነላቸው። ...ኑ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ ተባባሉ፤ በምድር ላይ ሳንበተንም ስማችንን እናስጠራው አሉ። እግዚአብሔርም አለ፡- እነሆ እነርሱ አንድ ወገን ናቸው፤ ለሁሉም አንድ ቋንቋ አላቸው። ይህንም ለማድረግ ጀመሩ። አሁንም ያሰቡትን ሁሉ ለመሥራት አይከለከሉም፤ ኑ እንውረድ፥ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው። እግዚአብሔርም ከዚያ በምድር ላይ ሁሉ በተናቸው፤ ከተማይቱንም መሥራት ተዉ። ስለዚህም ስሟ ባቢሎን ተባለ። ” ዘፍ. 11፡ 1-9

“ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት” ያለው እንዲከበር
ሕዝቡን በተናቸው ከዳር እስከ ዳር፤
ሁሉም በየነገዱ እንደያካባቢያቸው፥
የተለያዩ ቋንቋዎች ተሰጣቸው።
ይህ ቅጣት የተሰጠበት ምክንያት፡-
በቋንቋ እና በሥጋ አንድ ከመሆን፥
በሃሳብና በመንፈስ - በእምነት አንድ መሆን እንደሚበልጥ፥
ቀጣዩም ሕዝብ ይህንን እንዲማር፥
እንዲሁም ሌላ ምክንያት ይኖራል፥
ለሰው ልጅ የማይገባ ልዩ ምሥጢር።
ከድሆች የተሠወረ የሃብታሞች መፈንጫ፥
የክህደት አምልኮን መተግበሪያ፥
አውሬውን ለማንገሥ ታላቅ ሩጫ፤
ምርጥ ሥፍራዎች “ለምርጦቹ” መመላለሻ፤
የሃብታሞች መምነሽነሺያ፥
ይህ ነው በሃሳብ እና በመንፈስ የደኸዩ፥
ለሆዳቸው ያደሩ - ምድራዊነታቸው የተጫናቸው፥
በትዕቢትና በኩራት የሚኖሩ፥
የእምነት አልባ ሰዎች ምኞት፥
ወደ ኃጢአት የሚመራ ከንቱ ፍላጎት።
ከፉው ሥልጣን ይዞ - ሥልጣኔን ከፉው ሲመራው፥
ከፉ - ሰይጣናዊ ስለሚሆን አቅጣጫው፥
የሰው ዘር መንፈሳዊ መመሪያን እስኪቀበል ጊዜው ገና ነው።
ምድራዊ ሥልጣኔ ለእምነት ክፍተት አይሰጥም
ምድራዊ ሕይወትን በመንፈሳዊ ሕይወት አያድስም፤
በምድራዊ ሥልጣኔ ብቻ ጥሩው ጎልቶ አይታይም፥
ስለዚህ፥ የሥልጣኔአችንን ሂደት እንድንመረምር፥
ከጥሩ ነገር ጎን የሚያድጉ ከፉዎችን እንድንቆጣጠር፥

የመጥፎነትን ጎዳና በጥሩነታችን እንድንሰብር፥
ወደ ጥሩነት የሚመራ አዲስ ሥልጣኔ እንድንፈጥር፥
ይህንንም ከባቢሎን ግንብ ታሪክ ሕዝበ አዳም እንዲማር፥
ሌሎችም ተከታታይ ትምህርቶች ተሰጥተዋል ለሰው ዘር።
በቃ! በቃ! የሰው ልጅ "በቃ!" በል "በቃ"፤
ምድራችን በምድራዊነት ስትጠቃ፥
ለራሳችን ስንል እንንቃ።
አንተም የኩሽ ልጅ የናምሩድ፥
በምድራዊነትህ አትጠመድ፥
በትዕቢት አትወጠር፥
የመጣህበትን አስታውስ፥ ፈጣሪህን አክብር።
ከእንግዲህ ወደየት ይኬዳል እስክንል ድረስ ተጓዝን፥
እርምጃዎቻችን የትም ካላደረሱን፤
ከእንግዲህስ እናስተውል ቆም ብለን።
ጊዜ ወስደን እናስብ፥ መዳረሻችንን እስክናውቀው፥
እስቲ በአይነ ልቡና እናስተውለው፣
እውቀትና ሥልጣኔ ወሰን ድንበር የለው፤
ለየት ስለሚለው በመንፈሳዊ ሥልጣኔም እናስበው።
ስለ ሁሉም ነገር እግዚአብሔርን በመፍራት ከጀመርነው፤
መላው ጠፈር የኛ ነው የሚሆነው።
ከዘመናዊው ሥልጣኔ ባሻገር፥
ሰውን በክብር የሚያስኖር፥
እውነትን እያነገሠ ውሸትን የሚቀብር፥
ፍቅረ ነዋይነትን ወደ ፍቅረ ሰብ የሚቀይር፥
ግለኛነትን እያጠፉ ማህበራዊ ኑሮን የሚያዳብር፥
ይህ ነው ከፍተኛ ሥልጣኔ ማለት፥
ልዩ ጻድቅ - የፍቅር፥ የሰላምና የአንድነት ምልክት።
አስቀድሞ በተዘረጋ ሥልጣኔ፥

በአንድ መስመር ብቻ መጓዝ አያዋጣም፥
ምድራዊ ሥልጣኔ (ሥይጣኔ) የማይደርስበትን፥
መንፈሳዊ ሥልጣኔን መሻት አይከፋም።
አንድ ብቻ'ማይደል - ያ የጊዜን ሂደት የሚያመላክት ጦር፥
ያ - እኛነታችንን ይዞ የሚጓዘው ባቡር፤
አለ፤ ሌላ ሥልጣኔ በዚችው በምድር፥
ለጋራ ጥቅም የሚውል፥
ወደ ምድራዊነት - ወደገንዘብ የማያዘነብል፥
ለሰላም፥ ለፍቅር፥ ለአንድነት የሚውል።
ሰማይ አንድ ብቻ - ምድርም አንድ ብቻ
ሥልጣኔም አንድ ብቻ አይደለም፤
አደገኛ ሥልጣኔ ይኖራል - ከዚህም ከዚያም አለም፥
በሳይንሱም በሃይማኖት ውስጥም እየገባ ነገር የሚያጣምም።
እውነት ግን አንድ አንጂ፥ ሁለት ሦስት አይሆንም።
እውነት አለ፤ ይኖራል ለዘለአለም፤
ስለዚህ፥ ቅዱስ ትምህርት አይታጣም፥
ከአንድ እውነት የሚመነጭ - በሳይንስም በሃይማኖትም።
ሳይንሳዊ መረጃዎች ቢበራከቱም፥
ሰው አልባ የጠፈር መንኮራኩሮች ቢበዙም፥
ምድራዊ ሥልጣኔ ቢራቀቅም፥
ውሱን የሆነ ሰው ከውሱንነቱ ፈቀቅ አይልም።
በአንጻሩ፥ በመንፈስ መራቀቅ ነገር ይቀይራል፤
መንፈሳዊ ሥልጣኔንም ካለ ገደብ ያሳድጋል።
የጥንቶቹ  እነ ኖህ፥ አብርሃም፥ ሙሴ፥ ኢያሱ፥
ሳሙኤል፥ ዳዊት፥ ዴቦራ፥ ጌዲዎን፥ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ፥
ጴጥሮስ፥ ጳውሎስ፥ ሐዋርያው ዮሐንስ፥
መንፈሳዊ ሕይወታችንን እየመሩ ቢያቆዩትም፥
ያንን እንደሥልጣኔ አልቆጠርነውም።

ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ዘጠኙ ቅዱሳን እና ተከታዮቻቸው ሁሉ፥
እነ ሙሴ ጸሊም፥ ክርስቶስ ሳምራ፥ ወለተ ጴጥሮስ፥
አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ፥ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፥ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፥
ሁሉም በኢትዮጵያውያን መንፈሳውያን በሥራቸው ቢወደሱም፥
ያንን እንደ ሥልጣኔ አልቆጠርነውም።
ከቁስ አካል በተገኘ ኩራት፥
በመንፈስ ኃይል በተገኘው ላይ ንቀት፤
ደፋር ሥይጣኔ በሃይማኖቶች ውስጥም ጥልቅ፥
በሂንዱ፥ በቡድሃ፥ በፕሮተስታንት፥ በኦርቶዶክስ ውስጥም ግብት፥
የዘመኑ ምድራዊ ሥልጣኔ (ሥ**ይ**ጣኔ) ኃያልነት፦
ከሃይማኖተኞች ሳይንስን፥
ከሳይንቲስቶችም ሃይማኖትን ማራቅ።
ልጆቻችን ከእውነትም ከእውቀትም እንዳይሄዱ ርቀው፥
ሳይንስም ሃይማኖትም ይሁን ትምህርታቸው፤
ግን በሁለቱም ውስጥ ሥ**ይ**ጣኔ መኖሩ ገብቷቸው፥
ከሥ**ይ**ጣኔ ጋርም እንዳያድጉ ተቆራኝተው፥
መንፈሳዊ ትምህርትን ይማሩ፥
በመንፈሳዊ አለም ውስጥም እንዲኖሩ፥
እውቀት፥ እምነት፥ ሳይንስና ሃይማኖት በአንድ አላማ እንዲመሩ፥
የሰውም ልጅ ሕይወቱ ለሥጋው ብቻ እንዳይሆን፥
ከምድራዊ ምቾት ጋር ነፍሱም እንዳታዝን፥
መንግሥታዊ አስተዳደር ሕዝባዊ ይሁን።
ሳይንስን ሲያስተምሩ ሃይማኖትን እንደ ጠላት ቆጥሮ፥
ሰው በነፃ እንዳያስብ በእውቀቶችም ላይ ተጽእኖ አሳደሮ፥
ከኪኒኖች ባሻገር - ጸበልም እንዳይፈውስ ጥርጣሬን ፈጥሮ፥
ታዲያ፦ እንዴት ይታወቅ - ከቁስ አካል የረቀቀ የመንፈስ ነገር፥
በምን አይነት ሥልጣኔ - በምን አይነት ትምህርት እውነት ይነገር።
እውነትን እንዳመጣጡ መቀበልና ማስተናገድ ተስኖን፥

የረቀቀውን የመንፈስን ሥራ እንዳንማርበት ተከልክለን፥
ግማሽ ተፈጥሮአችንን (መንፈሳዊነታችንን) እንዳንኖርበት፥
"ያ አለምን ሸሽተው ገዳም ለሚገቡት ብቻ ነው..." አሉን።
በሳይንስ ውስጥ በሃይማኖትም ውስጥ እውነቶች እንዳሉ ይገባናል፤
ግን ከሁለቱም የረቀቀውን እንዳናይ ታውረናል።
ኑሮአችን በተጻጻሪ ኃይላት መሃል ይዋልላል።[89]
በቅድስት ኢትዮጵያችን ውስጥ የሚሠራውን መቆጣጠር፥
የእግዚአብሔርን እና የአጋንንትን አሠራር መለየትም ይገባናል፤
ባለ አንድ አቅጣጫ ሥልጣኔን ለሚጠይቁ፥
ብዙ ገዳማት አሉ ባገራችን፥
የመንፈሳዊ ሥልጣኔ ቀደምት በመሆን የታወቁ።
የቅርቡ ወይንም የሩቁ ወደፊት ሥልጣኔ ከገዳማት የሚፈልቅ ይሆናል፤
የአለም ገዳማት ኃይልና ሥልጣን ይኖራቸዋል፤
የአለም ሕዝቦች ሁሉ መመሪያ ከገዳማት ይሰጣቸዋል፤
እነርሱ ሲመሩን ሰይጣን ምድራዊ ሥልጣኑን ያጣል፤
ጌታችን እና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአሸናፊነት ይነግሳል።

[89] "የእግዚአብሔርን እና የአጋንንትን ጽዋ አንድ አድርጋችሁ መጠጣት አትችሉም። " 1ኛ ቆሮ 10፥21

# ምዕራፍ ሁለት

# እምነት ከትንሽ እውቀት



ሁሉን በፈጠረ አምላካችን እናምናለን

**<u>እምነት ከትንሽ እውቀት</u>**

እውነት እውነት ነው፤ የእውነት እውነትነትም ማመሳከሪያው ስነ አመክንዮ ነው። ብዙ በማሰብ እና ጥቃቅን እውቀቶችን እና እውነቶችን በማሰናሰል መልክ የሚያስይዝ ስነ አመክኖዊ አስተሳሰብ ነው። እውነትም፥ ሃይማኖትም፥ ጠበቅ የሚለው ስነ አመክኖአዊነት ሲኖረው ነው።

አንድ ሰው ብዙ ሊያውቅ ይችላል፤ ነገር ግን በዚያው መጠን ያምናል ማለት አይደለም። በእርግጥ፥ ብዙ ማወቅ እምነትን ማጠናከሪያ ሊሆን ይችላል። ሆኖም፥ አንዳንድ አዋቂዎች የገዛ እውቀታቸው ተጠራጣሪዎችና ወላዋዮች ሲያደርጋቸው ተመልክተናል።

አለማወቅ ኃጢአት አይደለም። በማንም ሰው እውቀት ውስጥ አለማወቅ መኖሩ አይካድም። ስለዚህ፥ ለሚያውቀውም ለማያውቀውም እምነት የጋራ ስለሆነ፤ እምነት ማወቅንም አለማወቅንም ስለሚያቅፍ፥ ምንጊዜም ከእውቀት እምነት እንደሚበልጥ አያጠራጥርም።

እንግዲህ፥ በምናያቸውና በምንረዳቸው ጉዳዮች ሁሉ (ከምድር እስከ ጠፈር) ሁሉን ነገር የምናገናዝበው ከራሳችንም አሰራር ጋር ነውና፤ “ለሰው ልጅ የሚጠቅመው ያለው እምኑጋ ነው?” እያልን በመጠየቅ በጎ በጎውን መከተል ይገባል።

ይኽንን እና የመሳሰሉትን ሃሳቦች ሊቃውንት ጠበብት ተመራምረው በጥልቅ እውቀታቸው የጻፉትን እና የተናገሩትን አይተን ተገንዝበናል። ሆኖም፥ እስካሁን እና ምናልባትም ለወደፊት፥ የማናየውና ልናውቅ ዘንድ የማይቻለን ድብቁን በግልጽ ማየት አለመቻላችን ነው የበለጠ እንድናስብ የሚያደርገን።

ብዙውን በደረቅ አይናችን የምናየውን ነገር፥ በምናውቀው፥ ባለ ሦስት ልኬት (dimension) አለም ብቻ (በሳይንስ/በፊዚክስ) ማገናዘብ አቅቶናል። ብዙ ነገር ከአእምሮ በላይ፥ ረቂቅ ምሥጢርም ሆኖብናል። ዘወትር የማናውቃቸው ጉዳዮች እየከነከኑን፥ በሃሳብ ውጥረት እረፍት ያሳጡናል። ነገር ግን፥ ምንም ይሁን ምን፥ ብናውቅም ባናውቅም፣ የሚመስለንን በስነ አመክንዮ ከመመልከት አልቦዘንም።

ምንም እንኳን፥ በሕይወታችን ሙሉ ያካበትነው እውቀታችን ልንፈታው ወደማንችለው ምድራዊ እንቆቅልሽ እየመራን ቢሆንም፥ የምናምነውን እናምናለን፤ እውነት በሚመስለንም ሁሉ ስለ እውነት መናገርን አንፈራም።

አለማወቃችን አወቅን በምንለው ቢሸፈንም፥
በአለማወቃችን ጠፍተን አልጠፋንም፤
በማወቃችን በሥጋችን ብንረካም፥

በአለማወቃችን በመንፈስ አልተራብንም።

በኃጢአታችን በሃሰት ጎዳና ብንወድቅም፥

የሚያነሳን እምነታችን አልተወንም።

የማናውቀው ከምናውቀው እንደሚበረታ በማወቃችን፤

ከሁሉ በላይ እምነትን (ሃይማኖትን) አስቀደምን፤

በሥጋ ብንጠፋም በመንፈስ ሕያዋን ነን።

መቼም መጥፎው ሳይታይ ጥሩው አይመጣም፤

ጥሩውና መጥፎው አብሮ ብዙ አይዘልቅም፤

ዛሬ ጎላ ብሎ የሚታይ ክፉው ኃያል ሲወድም፥

ለጽድቅና ለእውነት የቆመ ፍትህ መምጣቱ አይቀርም።

ከጊዜያዊ - ምድራዊ እውቀት - ከማይጠቅም፥

ምንም ቢዘገይም፥

ወደ ሰማያዊ እውቀት ሽግግር አይቀርም።



የጥቃቅኖች አለም

## <u>የጥቃቅኖች አለም</u>

የሰማይ፥ የየብስና የባሕር ሕዋሳት ተፈጥረው ሲበዙና ሲባዙ፥ እኛ ገና አልተፈጠርንም ነበር። እኛ ስንጋደል ስንሞት በያለበት፥ ጥቃቅኖቹ እየበዙና እየተባዙ ምድሪቱን ይወርሷታል።

ብዙ ትላልቆች በጊዜአቸው ተሸኝተዋልና፤ ጥቃቅኖቹ (አዋቂዎቹ?) አካላዊ - ምድራዊ ሕያዋን ምድሪቱን ይሞሏታልና፤ አሁንም እኛ በሥጋዊነታችን መቆየትን ከፈለግን፥ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፥ ምድሪቱን "ለጥቃቅኖቹ" ለቀን እንዳንጠፋ ያሰጋል።

በዚህች ምድር ላይ እስከ ሩቅ ወደፊት (በብዙ ሚሊዎን ዓመታት) ብንኖር፥ በአካል እያነስን፥ እየረቀቅን፥ እኛም ከጥቃቅኖቹ መደመር ግድ ይለን ይሆን?

በአካል መተለቅ ወይንም ማነስ አንጻራዊ ቢሆንም፥ አካላዊ ሆኖ ከመገኘት እስከ መጥፋት ድረስ መርቀቅና ማነስ ቢኖርብንስ ማን ያውቃል?[90]

ከጥንቱም ምድሪቱ ለትላልቆቹ፥
ለነዳይናዞር፥ ለነኤፈሊንም አልተመቸች፤
ሁሉንም አንድ ባንድ እንደዋጠች፤
እኛንም ካልወደደች፥ ካስቀየምናት፥
"ተይ" ካልተባለች ካልተገታች፥
ታጠፋን ዘንድ አቅም አላት።
ሆኖም የሰው ልጅ ብልጥነት ወሰን የለው፥
እየተለዋወጠ ነው ከዚህ የደረሰው።
ስለዚህ አሁንም፥ ከትልቅነት ትንሽነት ከሆነ፥
አካላዊ ሆኖ የመቆያ ዘዴው፥
ወደዚያው ይሆናል፥
እድል ፈንታው የሚመራው።
የሰው ልጅ ብልህ ነውና፥ ይህንን ተረድቷል፤
በሳይንስም ሆነ በሃይማኖት፥
በአካልም ሆነ በመንፈስ፥
ተስፋው ጠፈር ሰማይ መሆኑንም ተገንዝቧል፤
ግን፥ ከዚያ ከሰፊው አለም እንዴት ይጥለቅ?፥
በአካል በመርቀቅ? ወይንስ በመንፈስ በመራቀቅ?

---

90 "የማደርገውን አላውቅምና፥ የምወደውንም ያን ምንም አላደርገውምና፥ ያንኑ የምጠላውን ብቻ እሠራለሁ እንጂ።" ሮሜ. 7፡ 15



ዙሪያችን

## <u>ምን አለ በዙሪያችን?</u>

አንዳንድ ጊዜ አናውቅም የምናደርገርውን፤

ሳናስብ እንናገራለን፤ ሳናስብ እናደርጋለን፤

ጥሩ ሰው ግን፥ ጥሩውን ያስባል፤

ጥሩ ይናገራል፤ ጥሩም ይሠራል፤

ከፉ ሰው ከፉ ያስባል፤ ከፉ ይናገራል፤ ከፉውንም ያደርጋል።ቅኔ ናትና ሕይወት[91]

ባለመረዳታችን ብዙ እንዳንቆይባት፥
እርሷ ትወቀን፥ እኛም እንወቃት።
በጥበብ ምርምር ከጠባቡ ወደ ሰፊው፥
ከሚታየው ወደማይታየው አለም ለመዝለቅ፥
ግዴታ ይሆናል፥
ከምድራዊ ምልከታ መላቀቅ፥
ወደ መንፈሳዊ ምልከታ መጥለቅ።

በእርግጥ ያለነው ብቻችንን አደደለም፤
የማይታዩ በደረቅ አይን፥ በማይክሮስኮፕም፥
ጥቂቶች የማይባሉ እጅግ የረቀቁ የሉም አይባልም፤
ሕያዋን በዙሪያችንም ይኖራሉ በእኛው አለም፤
ምድሪቱ የእኛ ብቻ አይደለችም፤
በጋራ የሚኖሩባት ይኖራሉ ሌሎችም፥
እውቅና ብንሰጣቸውም/ባንሰጣቸውም።

የምድሪቱም ትእግስት ወሰን የለውም፥
ከፉዎችን ቶሎ አትገላቸውም።
እኛም የጥበብን ዳርቻ ለመፈለግ አልደከምንም፤
በመንፈሳዊነት ሥልጣኔ መራቀቅን አልተመኘንም፤
መራቀቅም ከየት ወዴት እንደሚወስደን አላወቅንም።

በንቃት ለመመልከት ዙሪያችንን፥
የሩቁን፥ የቅርቡን፥ የሚታየውን የማይታየውን፥
አይኖች ብቻ አይበቁን፤
ማስተዋያ ልቦና ይስጠን ፈጣሪያችን።

---

91 የሕይወትን ፍልስፍና በልጅነት (በወጣትነት) መረዳት (ማጥናት) በኋላ (እርጅና ሲመጣ) “አዬ! ጊዜዬን እንዳው በከንቱ አሳለፍኩ” እያሉ ከመጸጸት ያድናል።



የአራዊት መንደር

## ምን ተማርን ከምድራችን?

እርስ በርስ መጣላት ከመጀመራችን በፊት ከተናካሽ አውሬዎች እየሸሸን ነበር ኑሮአችን። ቀስ በቀስ ምድራዊ እውቀታችን ኃይለኞች፥ አዋቂዎችም አደረገን።

የሰው ዘር እየበዛ ሲሄድ፥ አኗኗሩም ከገጠር እና ከጫካ መሃል እየወጣ፥ ከተሞችንም እየመሠረተ በሕብረት መኖር ሆነ። የራሱንም ዘር እየተካ፥ በቁጥር ሲበዛ፥ የዙሪያውን መቆጣጠር (መግዛት) እንዳለበትም ተማረ። ከዛን ጊዜ ጀምሮ፥ ማህበራዊ ኑሮው እየተጠናከረ መጣ።

የሰው ልጅም ምድራዊ አኗኗርን በቅጡ ሲያውቅበት፥ ከግላዊ ኑሮ ተዛማጅ የሆኑ ራስ ወዳድነት ሕብረተሰባዊ አብሮ የመኖር እሳቤን አሳጣውና፤ የገዢ እና የተገዢ ሕብረተሰብ መመሥረት ተጀመረ። የሕብረተሰብም እድገት ከዚሁ የገዢ ተገዢ ስርዓትን ተከትሎ ሆነ።[92]

ሰው እና ሰው በሃሳብ እየተለያየ ስለመጣ፥ አንዱ ከሌላው በመንፈሱ ተራራቀ። ጦርነቱም ከአውሬዎች ጋር በመሆን ፋንታ እርስ በርስ ሆነ። የሰው ልጅ ታሪክ የጦርነቶች ታሪክ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ሰው እንዴት እርስ በርሱ ይገዳደላል?

ወደ ከፋ የሚመራ መጥፎ መንፈስ እስካለ ድረስ፥ እርስ በርስ መገዳደል ይኖራል፤ ይቀጥላልም። ሆኖም፥ ምድሪቱ ጥሩ (ቀና) ሰው አላጣችምና፤ እርስ በርስ ተገዳድለን ስላላለቅን፥ ይኸው ከዚህ ደርሰናል።

ሰው ምንጊዜም ሕያው ነው፤ በሥጋው ቢሞትም፤

ሥጋችን በከበረ የሬሳ ሳጥን ቢቀመጥም፥

በተወደደ የእጣን ጢስ ታጥኖ ከቤተክርስቲያን ቢገባም፥

ሰዎች ይህንን እያዩ ቢያዝኑ፥ ቢያለቅሱም፥

እውነታው ግን፥ በአይነ ልቦና ለተመለከተው፥

ደስ የሚያሰኝ እንጂ፥

የሚያስከፋ የሚያሳዝን አይደለም።

ወንዶችም ሴቶችም፥

በጅምላ መቃብር የተቀበርን ብንሆንም፥

ቢበሰብሱ ሥጋዊ አብራኮቻችን - አጥንቶቻችንም፥

በታመቀ ኃይል አዲስ መልክ ይዘው ይነሳሉ እንጂ፥

ከምድር ወድቀው አይቀሩም።

ጋደም ብሎ ተንጋሎ - መተኛትም ሲያቅት፥

የተቀመጥንበት፥ የቆምንበት፥ የሄድንበት፥

መሬቱ ሲያነጥር፥ ቁጭ ብድግ የሚያደርግ፥

---

92 Primitive society – slave society – feudal society – capitalist society

ለመቀመጥ፥ ለመቆም፥ ለመሄድ፥ ለመተኛትም ሕግ፥
“ይህንን ብታደርግ ይሄ ይከተልሃል..” የሚልም ሕግ፥
የሰው እና “የተፈጥሮ ሕግ” ሲፈራረቅብን፥
አንዱን ከሌላው መለየት እስኪያቅተን፥
የምዬን ለአብዬ እየሰጠን፥
የመሬት መንቀጥቀጥም “ለእኛ ቅጣት” መሆኑን አላወቅን፥
“አሁንስ የአለም መጨረሻ” ሊሆን ነው እያልን፥
በአለማወቅ ፍርኃት ተዋጥን፥
እምነት አነሰን።
ሰዎች ስለሆንን፥ መገንጠል ባንችልም ከምድራዊነታችን፥
አጭር ብትሆንም፥ ክቡር ናትና ሕይወታችን፤
የረከሱ መናፍስት ሰለባዎች እንዳንሆን፥
እንዳናጣው እኛነታችንን፥
እንንከባከብ ሙሉ ሰብአዊነታችንን፥
እኛን - እራሳችንን - ህልውናችንን፥
ሥጋም መንፈስም የሆነውን።

**<u>እንደ ዙሪያችን</u>**

እኛም ስንሞት - ወደ ሩቁም ሳንሄድ፥ በምድር ሰማይ ሆነን፥
ከዚያው ብናንዣብብ - ብንዞር የቋሚዎችን ዙሪያቸውን፥
በአካል ባንታይም ትልቅ ሁነናል፤
ከምድራችን የተማርነው ብዙ ነገር አሳውቆናል፤
ስለ ብድራት፥ ውለታንም ስለ መክፈል፥
ከቋሚዎች ለየት ባለ መንገድ ተረድተናል።
የሰው ውለታ ያለበት ሰው፥
ውለታውን ሳይከፍለው፥
በሞት ቢለይበት ያ ሰው፥
በምትኩ ውለታን የሚቀበል፥

ሌላ ሰው መች ይታጣል፤
ለአንዱ ያደረጉት ለሌላውም ይሆናል፤
የሞቱትም ያልሞቱትም፥
በማይታይ ቀጭን ሃረግ ተሳስረዋል።
ለማንም ሆነ ለማንም፥
በምድር ክፋትን ያበደረ፥ በሰማይ ያንኑ ክፋት ይቀበለዋል፤
በምድር ደግነትን ያበደረ፥ በሰማይ ያው ደግነት ይከፈለዋል።[93]
ሕይወት ሲዘራ በምድራችን፥
የነፍሳችን ግኝት  በሥጋችን፤
የሥጋችንም ግኝት በነፍሳችን፤
ብንሞትም ሕያዋን ነን።
በምድር ከሞት ጋር ፍጥረታችን፥
ሞት ሲለቀን ነጻነታችን፥
በምድርም በሰማይም ያው እኛው ነን።
ስለዚህ፥ ማንም ሰው መልካም ሥራን ቢሠራ ለማንም ሰው፥
ያ መልካም ሥራ በሰማይ ለሚኖሩትም ሳይቀር ነው
ትሩፋት የሚሆነው።

---

[93] “ከዚህም በኋላ ንጉሡ መልሶ እንዲህ ይላቸዋል፦ እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ ካመኑ ከእነዚህ ከታናናሾች ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁትን ሁሉ ለእኔ አደረጋችሁት።” ማቴ. 25: 40



እውነትን ፍለጋ

## <u>እውነትን ፍለጋ</u>

ገና በልጅነት ተነጥቀን ለምድራዊነት ተሰጠን፤

ምድራዊነትም የማናውቀውና፥ ልናውቀውም የማንችለው፥

ጭራሽ የማይገባን ሆነብን።

በእኛና በቤተሰቦቻችን መካከል፥

የስነ አመክንዮ ልዩነት ተፈጠረ፤

የሰው አብሮ የመኖር ተፈጥሮአዊ ጠባዩ ተቀየረ።

ሰው በሰው ላይ ጠላት ሲሆን አይተን ደነገጥን፤
በሄድንበት የምናየው ግፍና ኃጢአት መሥራት አስፈራን።
ስናድግ የፈራነውን፥ ከሰማዩ የሚለየውን - ይህንኑ ምድራዊውን መሰልን፤
ሳንወድና ሳንፈቅደው የገባንበት በመሆኑ ምንም አልተመቸን።
በምድራዊ እውቀታችን ገንዘብ ተከፍሎን፥
በድሎት መኖር ሲቻለን፥
ደስ አልተሰኘም መንፈሳዊ- ሰማያዊ ልቦናችን።
መሆን ከነበረብን ውስጣዊ ማንነታችን ጋር እየታገልን፥[94]
አንዳንዴ አውቀን፥ አንዳንዴም ሳናውቅ ኃጢአት እየሠራን፥
እንዲሁ እንኖራለን፥ ማንነታችንን በምድራዊነት ቀይረን።
አንድ ልዩ ሕያው ይኖር ይሆን በውስጣችን?
ሲከፋው የሚያስከፋን፥ ደስ ሲለውም ደስ የሚያሰኘን።
ውስጣዊ ማንነታችንን በፍለጋ ሆነን፥
እራሳችንን ስላጣን፥
በመንፈስ መታወክ፥ እስከ አእምሮ ህመም እንደርሳለን፤
ካለ ቅዱስ መንፈስ ምንም መድኃኒት የለም የሚያድነን።[95]
እስቲ ማን ያውቃል?
በውጪ ኃይላት (በመናፍስት) ካለማቋረጥ እየተሰበከን ቢሆን?
ማን ያውቃል፥ በአስተሳሰባችን ውስጥም ጣልቃ እየገቡ ቢጨቀጭቁን፤
በብቸኝነት የማሰብ ነጻነታችንንም ቢያሳጡን።
እስቲ ማን ያውቃል?
ከምናየው (ከምድራዊነታችን) ባሻገር፥
አካላዊ ያልሆነ - እኛ የማናውቀው - ሌላ አለም ቢኖር።

---

94 "ድካምንና ጣርን አይ ዘንድ፥ ዘመኔም በእፍረት ታልቅ ዘንድ፥ ስለ ምን ከማኅፀን ወጣሁ?" ኤር. 20፡18

95 "አቤቱ ተመለስ፥ ነፍሴንም አድናት፥ ስለ ቸርነትህም አድነኝ።" መዝ. 6፡4

እስቲ ማን ያውቃል? የኛ አካላዊ ሆኖ መኖር፥
ለእነርሱም ቢሆን ነፍስ የሚዘሩበት፥ እንደሚተነፈስ አየር።
ለእኛ መሞትና መቀበር፥
ለእነርሱም ካልሞትንላችው የማይኖሩበት - የህልውናቸው ድንበር።
እውቀታችን (በተለይ ዘመናዊው) ከአንጎላችን ሰፊውን ሥፍራ ስለያዘብን፤
መታየት፥ መታወቅ ያለበትን ሁሉ ነው የሰወረብን፤
የገዛ እውቀታችን ነው መንፈሳዊነታችንን ያሳጣን።
ይልቁንም በዘመኑ ምድራዊ ትምህርት ብቻ ተወስነን የቀረን፥
በመናፍስትን አሰራር  ውስጥ እኛም ገብተን፥
እነርሱኑ እንደመሰልናቸው አላወቅን።
አእምሮስ ምንድነው ካለመንፈስ ብቻውን፥
እንዴት ሊያውቅ ይችላል ሁሉን?
አንጎልም ነገር የሚቋጥር ጎተራ፥
የሚመመገበው እውቀት ካልጠራ፥
ወደ ጥፋት፥ ወደ እርኩሰት ነው የሚመራ።
የአንጎል ሕዋሳትም፥  ጠባየ ፍጥረታቸው ልክ እንደ ጠፈሩ፤
ግሊአል የተባሉ ሙጫዎች፥ እርስ በርሳቸው የተጣመሩ።
አንጎል፡- በመልእክት አስተላላፊዎች፥ የነርቭ ሕዋሳት ሰራዊቱ፤
ኢሌክትሮ ኬሚካል ንዝረቱ፥
የሚገመት፥ የሚለካ፥ እድገቱ፥ ውፍረቱና ክሳቱ፤
ቢበላ አይታይ መብላቱ፥ ቢተፋ አይታይ ትፋቱ፥
እሳተ ገሞራ ስሜቱ፥ የምድር ተምሳሌት በማንነቱ፤
አቤት! ጥልቀቱ፥ የእውቀቱ! የቃላቱ፥ ብዛቱ፥
የቋንቋው ስፋቱ፥ በዳግማዊ ባቢሎን ቅዠቱ፥
ባርነቱ፥  በራሱ፥ በምድራዊው እውቀቱ፤
ነፃነቱ - ሕሊናው ንቃቱ - እስከ ጠፈር ግዛቱ።
መጫወቺያ ኳስ የሌላት ድመት፥
በገዛ ጭራዋ እንደምትጫወት፥

ሰውም ከራሱ እውቀት ጋር  በጫወታ ብዛት፥
ልዩ እውቀት በውስጡ ነገሠበት።
ታዲያ፥ የሰው አእምሮ ብቻውን፥
የድርጊቶች ሁሉ ተጠያቂ ቢሆን፥
ማን አወቀ፥ ክፉውንና ደጉን፥
በራሱ ለይቶ ማወቅ መቻሉን።
ከሰው ልጅ ከጎኑ መካሪ ባይኖር፥
በራሱ ፈቃድ ብቻ ያን ያህል ክፉ ይሆን ነበር?

ግዙፉን ከደቂቁ አገናኝተን፥
ሁሉ ነገር ከሁሉ ነገር ይያያዛል ካልን፥
የመንፈስንም ከአካል ጋር መጣመር፤
ሁለቱን የሚያቆራኛቸው ምን እንደሆን፥
የፍላጎታዊነት እና የግዴታዊነትን ባህሪ፥
የአጣብቂኝነቱንም አባዜ፥
የመቀላቀልና የመዋሃድ ምሥጢር፥
በእውነት፡- አእምሮም "አይዞህ..." እያለ ከሚሰብከውም ጋር ቢተባበር፥
ስለ እውነት መሞት፥
እስከ ሰማዕትነትም መድረስ ነው የሰው ልጅ ክብር።



የክርስቲያኖች ስነ አመክንዮ

## ክርስቲያኖች የመባላችን ስነ አመክንዮ

ምንም ሳናውቅ፥ ገና በሕጻንነታችን ተጠመቅንና ክርስቲያኖች ተባልን። ክርስቲያኖች ስለተባልን፥ ስለ ሃይማኖታችን ብንማርም፥ ባንማርም፥ ክርስቲያኖች ሆነን ቀረን። ግን፥ እንዲሁ በስነ አመክኖአዊ አስተሳሰብ፥ ክርስቲያናዊነት እጅጉን ጥሩ ነገር መስሎ ይታየናል። ለምን? አሁን ብዙ ስላወቅን? ወይንስ በማወቅ ውስጥ ካለው እውቀት፥ በእምነታችን (በአለማወቅ ውስጥም ቢሆን) የምናውቀው እንደሚበልጥ ስለምናምን ይሆን?

ምድራችን ስትፈጠር እሳታማ የነበረች፥
እስክትቀዘቅዝ ብዙ ዘመን እንደፈጀች፥
ክርስቲያናዊነትንም በቀላሉ አላገኘናትም፥

ያሳለፍነው መከራና ስቃይ አይረሳም።
በብሉይ ኪዳን እንዲሁም በወንጌል፥
ተስተካክሎ የተቀመጠ፥
ሰማያዊ ቃል - ለሰው ልጆች ሁሉ የተሰጠ፥
መጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ የማይሽረው እውነት፥
ስህተት (መዛነፍ) የማይገኝበት፤
ከዚያ የመነጨ ነው የክርስትና እምነት፤
የእውቀት እና የስነ አመክንዮ ጥምረት፥
የፈጣሪ ቃል ኪዳን ያለበት፥
ታዋቂ ነብያት የተነበዩበት፤
ትንበያውም እውነት ሆኖ የታየበት፤
በማስረጃ የተደገፈ እውነት፥
የተስተካከለ፥ አንዳች ክፍተት የሌለበት።
የአርኩስ መንፈስም የተረጋገጠ ነውና ሕልውናው፥
የቀደሙ ክርስቲያኖችን እጅጉን አወካቸው፤
የውሸታምነቱን ስነ አመክንዮ እየሰበከ ከፋፈላቸው፤
የነስማዚያ መንፈስ በጠበጣቸው፤
ታላቅ ትግል ተካሂዶ አንድነትን አሳጣቸው።
በአንድ በኩል ቅዱስ አትናቴዎስ፥
በሌላም በኩል እርኩስ አርዮስ፥
ይኸው እስካሁን አልጠፋም የጠላት ጦስ፤
ሁላችንም በአንድ ላይ ሆነን እንዳንቀድስ።[96]
በክርስቲያኖች አለም የክህደት ሃይማኖት - የሚመስል እውነት፥
ለያይቶ አስቀመጠን እንዳይኖረን ህብረት።
የራሳችንን ክርስቲያንነት (ተኦ) - የብዙ ዘመን የትግል ፍሬ፥

[96] አባ ጎርጎርዮስ፥ 1978፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ


እስካሁን አልተነጠቅንም - በዚያ ክፉ - ሰይጣን አውሬ፤
ይኸም "በእንተዝ ናፈቅረኪ....." እያልን የቆየንበት፥[97]
የስነ አመክንአዊ አስተሳሰባችን አንድ ወጥነት፥
ስለሆነ ነው እንጂ፥ በእውነት እና በቅንነት መጽናት፥
አይደለም - የእውቀታችን ብዛት ውጤት።
እናቱን የማይወድ ማን አለ ከሰው?
ፈጣሪዋን የወለደች እናትስ እንዴት ነው የማትወደደው?
ፈጣሪስ እንዴት ነው እናቱን የሚወዱለትን የማይወደው?

---

[97] ማርያም ሆይ! ስለዚህ እንወድሻለን፥ ከፍ ከፍም እናደርግሻለን፤ እውነተኛ የጽድቅ መብልንና እውነተኛ የሕይወት መጠጥን ወልደሽልናልና። (የኢት. ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች፥ በቅዳሴና በሁሉም ሥፍራ)

# ምዕራፍ ሦስት

## መንፈሳዊ ግንዛቤ



እምነት

## ***መግቢያ***

ከሁሉ አስቀድሞ እግዚአብሔር በዘለአለማዊ ሕያዊነቱና እና ክብሩ በመንግሥቱ ይኖር እንደነበረ፥[98] በጊዜና በቦታ የማይወሰን አልፋና ኦሜጋ እንደሆነም፥ ሁሉን የጀመረ፥ ሁሉን የያዘ፥ ሁሉን የሚፈጽም እርሱ እግዚአብሔር አምላካችን መሆኑን እናምናለን፤ በዚሁ አምነታችን ጸንተን፥ የተሠጠንን ሥራችንን በትጋት እንቀጥላለን።[99]

## ***መንፈሳዊ ግንዛቤ***

ተፈጥሮ ለእኛም አይነ ልቦና እንደሰጠን አወቅን፤
እውነት የመሰለንን ካለ ፍርኃት ልንናገር ተነሳን፡-
    እግዚአብሔር ሲፈጥረን እንድናመልከው እርሱን፥
    በመጠናችን - እንደየችሎታችን - አስተማረን፤
    እርሱ ራሱ ማንነቱን - እንደየችሎታችን - በመጠኑ አሳወቀን።
እነኛም የድሮ ሰዎች - አባቶቻችን፥
ያልተማሩ - የኛን ያኽል እውቀት የሌላቸው ያልናቸው፥
ፈጣሪያችንን  የተረዱ ናቸውና አስቀድመው፥
በእነርሱ አረዳድ - በልዩ እውቀታቸው፥
በእምነት የጠነከረ ነበርና መንፈሳዊ ሕይወታቸው፥
ከእነርሱ አኗኗ - ከእውቀት እምነት እንደሚበልጥ ነው የተማርነው።
    ዘመኑ ከፍቶ እኛጋ ሲደርስ ትምህርቱ፥
    ፍልስፍናው ምድራዊነቱ፥
    እውቀት ወደ አለማመን ሲያዘነብል፥
    ማቃናት አስፈልጓል በእምነታችን ኃያል።
እስቲ ማን ያውቃል ምክንያቱን፥
ክርስቶስ ለምን እንደ መረጠ፥
ከአለም ሕዝብ መካከል፥

---

98 “እርሱ ከሁሉ አስቀድሞ ነበረ፤ ሁሉም በእርሱ ጸና።” ቆላ. 1፡17

99 “እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፤ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች።” መዝ. 102 (103)፡19

ከአይሁዶች መወለድን፥
እያወቀ ከፉዎች አሰቃይተው የሚገድሉትን?
እርሱ ንጉሥ ገድሎ መንገሥ ሲቻለው፥
ወደ ጥቁሮች አገር መሰደድን ነው የመረጠው፤
ፍሳድቃን ከሚባሉ - ከታዋቂዎች መከከል መገኘት ሲቻለው፥
ከኃጥአን ቤት ገብቶ መብላትን ነው የመረጠው፥
እንዲህ ዝቅተኛውን የሕብረተሰብ ክፍል ያልተጸየፈው፥
ሰውም አምላክም የሆነው፥
በፍጹም ልባችን የምናምነው
ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችን አምላካችን ነው።
እስቲ ማን ያውቃል ምክንያቱን ላልነው፥
ከጥንትም እግዚአብሔር እስራኤላውያን ቢረዳቸው፥
ከግብጽ ምድር አውጥቶአቸው ነጻነትን ቢሰጣቸው፥
ጥቂቶች[100] ስለሆኑ፥ በእጅጉም ስለተጨቆኑ አዝኖላቸው።
ጌዲኦንን የእግዚአብሔር መንፈስ ስለረዳው፥[101]
በ300 ወታደሮች ብቻ ነበር ምድያማውያኑን ያሸነፈው፤
ለዚህም እስቲ ማን ያውቃል ምክንያቱን ላልነው፥
በዳይ ተበዳይን ፈጽሞ እንዳያጠፋው፤
እውነትን አንግቦ፥ በእግዚብሔር ኃይል ለሚታመን፥
ምንጊዜም አሸናፊ እንጂ ተሸናፊ አይሆን።
ከእመቤታችን ማርያም ቃል አንዱም ስለማይጣል፤
የወደፊቱም በርሷ መዝሙር ተቀምጧል።[102]

---

100 እግዚአብሔርም የወደዳችሁና የመረጣችሁ ከአሕዛብ ሁሉ ስለበዛችሁ አይደለም፤ እናንተ ከአሕዛብ ሁሉ ጥቂቶች ነበራችሁና። ዘዳ። 7፡7

101 መሳፍንት 7 በጠቅላላ

102 “ኃያላኑን ከዙፋናቸው አዋረዳቸው፤ ትሑታኑንም ከፍ ከፍ አደረጋቸው።” ሉቃ. 1፡ 46 55

ላይ የተቀመጠው (ዛሬ) ታች (ነገ) ይወርዳል፤

ከታች ያለው (ዛሬ) ላይ (ነገ) ይወጣል።

ስለዚህ ሰው ሆይ አትኩራራ ይበቃሃል፤

የነገ ተራው ለጭቁኑ ለተጠቃው ይሆናል።

በሚታየውም በማይታየውም አለም፥

በሳይንስም በሃይማኖትም፥

ብዙ ነገር አለ በጥያቄ እና በግርምት የምናልፈው፦

እስቲ እሱው ያስተምረን፥

እርሱ ሁሉን ይግለጽልን።

ከእንግዲህስ፥ ከግላዊ እሳቤዎቻችን ፈቀቅ ብለን፥ በማወቅ ብቻ ከሚመጣ እውቀት ሳይሆን፥ ካለማወቅም በሚመነጭ - በፍጹም ልብ ከማመን ከሚከሰት እውቀት እንጀምር። ከሥጋዊ አስተሳሰብ ወጣ በእንበልና፣ መንፈሳዊ ግንዛቤአችንን እናጠናከር። መልካሙን እንድናስብ  በሚረዳን በእግዚአብሔር ተመክተን በፍጹም እምነት እንነሳ።

ሥራችን ሁሉ የተባረከና የተቀደሰ እንዲሆን፥ ፍጻሜውንም እንዲያሳምርልን፥  በጎውን መንፈስ በሁላችንም እንዲያሳድርልን፥ መንፈሳዊ ብርታቱን እንዲሰጠን፤ ወደ ቅዱስ መንፈስ የሚያቀርበንን መንፈሳዊ እሳቤ እንድናመነጭ፥ የእርሱን ፍቃድ ለመፈጸም ይረዳን ዘንድ፥ ፈጣሪ አምላካችንን እንለምነው።

## ጸሎት

አቤቱ አምላኬና ፈጣሪዬ፥ የሚታይና የማይታየውን ሁሉን የፈጠርክ፤ የሁሉን አካሄድ እና አፈጻጸም የምትወስን፤ አንተ እግዚአብሔር ኃያል፥ ቸር እና ይቅር ባይ እንደሆንክ አምናለሁ።

አቤቱ አምላኬና ፈጣሪዬ፥ የማየውም የማላየውም፥ የአንተ የክብርህ መገለጫ ነውና፤ ድንቅ ሥራዎችህን ባሰብኩ ጊዜ እደነቃለሁ፤ እኔም ባቅሜ ያንተን ገናናነት ለመመስከር እጓጓለሁ።

አቤቱ አምላኬና ፈጣሪዬ፥ አንተ ያለህና የምትኖር መሆንክን ባሰብኩም ጊዜ፥ ስለ ነፍሴ ዘለአለማዊ ሕይወት ተስፋ አደርጋለሁ። ከምድራዊ ጭንቀት የምታወጣኝ፥ የምታድነኝም አንተ እንደሆንክ፥ ይህንን በሕይወቴ ተረድቻለሁና፤ አንተን ከማመስገን አልቦዝንም።

አቤቱ አምላኬና ፈጣሪዬ፥ በማየውም በማላየውም፥ በማውቀውም በማላውቀውም፥ በአንተ ያለኝ እምነት የጸና በመሆኑ፥ በሰማያዊ መንግሥትህ እንድኖር አብቃኝ።

አቤቱ አምላኬና ፈጣሪዬ፥ በኑሮዬ ክብርህን የሚገልጽ ሥራን እንድሠራ ፍቀድልኝ፤ ለምድራዊ ሕይወቴ መመሪያ፥ ቅዱስ ቃልህንም መተግበሪያ ይሆን ዘንድ፥ መንፈሳዊ ብርታትና ብቃቱን አድለኝ። አሜን።



እምቅ ኃይል

## እምቅ ኃይል

ፍጥረታት ሁሉ በውስጣቸው የእግዚአብሔርን ኃይል ይገልጣሉ። ያለና የሚኖር ሁሉ (ሕይወት ያለውም የሌለውም) ይንቀሳቀሳል (ከመኖር ወደአለመኖር፥ ከአለመኖርም ወደ መኖር ይጓዛል)፤ ይህም፥ በሁሉም አቅጣጫ የእግዚአብሔር ኃይል መኖሩን ያረጋግጣል።[103]

እንደ ንጉሥ ዳዊት ውስጣዊ ስሜታችንን ብንገልጠው፥


በተመሳሳይ ቃላት አምላካችንን ብናወድሰው፤

ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር እንደሚናገሩ፥

---

[103]“አቤቱ ፍጥረትህ ሁሉ ያመሰግኑሃል፤ ጻድቃንህም ያመሰግኑሃል፤ “ለመንግሥትህ ክብር ይገባል” ይላሉ። ኃይልህንም ይነጋገራሉ።” መዝ. 144(145)፡10 -11

የሰማይ ጠፈር የእጁን ሥራ እንደሚያወሩ (መዝ. 18፡1)
ለዚህ ያበቃንን - የተዘመረለት አምላካችንን - እንድንቀድሰው፥
እኛም እንዲህ እያልን በምሥጋና እንቅረበው፡-
አቤቱ ሥራህን ሁሉ የፈጠርካቸው ይመሠክራሉ፤
የማእድናት አለም በድንጋዮች ውስጥ እንዳሉ፥
የእነርሱን ሕልውና ታሪካቸውን ሁሉ ጊዜያት ይመሰክራሉ፤
ሰው ግን፥ በችሎታው እነርሱን አጎንብሶ ያያል፤
ወደ ሰማይም ያንጋጥጣል።
እነሆ! ከሰማይ ከዋክብት፥ እስከ ምድር ጠጠር፥
አንድም የለም የማይንቀሳቀስ፥
በለውጥ በክንውን ያንተን ሥራ የማይናገር።
አቤቱ አምላካችን፥ የአንተን ኃያልነት ለመግለጽ፥
የሰው ልጅ አቅመ ቢስ - እድሜውም አጭር፥
የሚያምንብህ የሰው ዘር ሁሉ ከመላእክት ጋር፥
ከምድር ዳርቻ እስከ መላው ጠፈር፥
ምስጋና ይድረስህ - ከትውልድ ትውልድ የሚሸጋገር።
አሜን።



የኃይል ስርጭት

## የኃይል ስርጭት በየቅጣጫው

ሁሉም የሚታየውም የማይታየውም (በአካልም በመንፈስም) በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠረ እናምናለን።[104] ከአምላካችን የሚመነጭ የኃይል ስርጭት በየአቅጣጫው ብዙ ድንቅ ድንቅ ሥራዎችን እንደሚሠራ እናምናለን። የእግዚአብሔርም ቃል ኃይል

---

104 “የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም ሁለት ልሳን ካለው ሰይፍም ይልቅ የተሳለ ነው፤ ..” ዕብ. 4፡12

“ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴም ብርሃን ነው።” መዝ. 118 (119)፡105

“የቃልህ መጀመሪያ እውነት ነው፤ የጽድቅህም ፍርድ ሁሉ ለዘላለም ነው።” መዝ. 118 (119)፡160

ነውና፥ ጊዜ የማይገድበው ዘለአለማዊ ስለሆነ፥ ይሠራል፤ ሁልጊዜ ይንቀሳቀሳል፤ ይፈጥራል፥ ሁሉን ያደርጋል። ሰው እና ጊዜ ተዛማጅ በመሆናቸው፥ ለእኛ እንዲገባን ያህል ነው እንጂ፥ "እግዚአብሔር በዚህን ጊዜ ውስጥ ይህንን ሥራ ሠርቶ አገባደደ" ማለት አይቻልም።

ትልቅነት ምንድነው? ትንሽነትስ ምንድነው? እንደ እኛ ነፍስ ያላቸውም የሌላቸውም ይንቀሳቀሳሉ። ፈጣኖቹ ቶሎ ይሞታሉ፤ ቀርፋፎቹም ይቆያሉ። ዝሆን ሲረግጣት ለምተፈርጥ አይጥ፥ መሬትን ለምትዞር ጨረቃ፥ ለነ ጁፒተርም ለፀሐይም ለከዋከብትም ተስተካክለው የሚንቀሳቀሱበት አውድ ተዘጋጅላቸው፤ የዑደታቸውም መሥመር ለሁሉም መገኛ ሥፍራቸው ነው። ከተፈጠሩ ጀምሮ፥ በዚሁ እንቅስቃሴአቸው ህልውናቸው ይረጋገጣል።

የእግዚአብሔር ቃል ኃያል ኃይል ነውና፥ ከእግዚአብሔር አንድ "በቃ" የሚል ቃል ቢወጣ፡- ጠፈራዊ ስበት (gravity) ይናጋል። ሁሉም ከሁሉም ይጋጫል፥ ይጨፈላለቃል፤ በመጨረሻም፥ ሁሉም ወደ ምንምነት ይለወጣል።[105]

የእግዚአብሔር ቃል አይገታም፤[106]

እርሱ ዘለአለማዊ እንደሆነ፥

ዘለአለማዊ ነው ቃሉም።[107]

የእግዚአብሔር ቃል ኃይል ነው። እኛም በእግዚአብሔር እምነት፥ ጽድቁን እንድንሠራ ብቁዎች ያደርገን ዘንድ፥ መንፈሳዊ ብርታቱንም ይሠጠን ዘንድ እርሱን እንለምነው።

*አቤቱ በቃልህ እንደ ፈጠርከን፥*

*ቃልህንም እንደሰጠኸን፥*

*አቤቱ በቃልህ አጽናን።*


*አሜን።*

---

105 ስለ ምንምነት ከምድራዊነታችን ባሻገር የተሰኘውን (ሦስተኛውን) መጽሐፍ ይመልከቱ።

106 "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።" ዮሐ. 1፡1

107 "ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ነው፤ የሚሻውን እስኪያደርግ ድረስ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም፤ መንገዴንና ትእዛዜን አከናውናለሁ።" ኢሳ. 55፡11



ምድራችን

## ***ምድራችን - መነሻችን***


የእግዚአብሔር ፍጥረት ምን ይረቅ! የጠፈር አካላት የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ይመሠክራሉ።[108]

በእግዚአብሔር ቃል የተጀመረ ሁሉ (ነፍስ ያለውም የሌለውም) በአንድ በተወሰነ መልክ (ህልውና) ይከሰታል። አካላዊ የሆኑ ሁሉ የተለያየ ቅርጽ እና መልክ አወጡ። ኢአካላዊ የሆነውም በራሱ በተወሰነ መልክ (ህልውና) ይከሰታል፤ ሁሉም በውስጣዊ ኃይሉ ይንቀሳቀሳል፤ ይህም ክስተት ዘለአለማዊ ስለሆነ ይቀጥላል (በእንቅስቃሴ ያድጋል፤ ይለወጣል)።

---

[108] "ምድርን እዩአት፤ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ፥ በሷ ላይ ከሚሠራው ሥራ የተነሳ የሚታይ የአምላክ ሥራው ሁሉ፥ እንዳይለወጥ ልብ አድርጉ።" ሄኖክ 1፡11

የአካል የት ድረስ እንደሆነ የትልቅነቱ መጨረሻው፥
የት ድረስ እንደሆነ የትንሽነቱንም መጨረሻው፥
ይህ ነው ሳይንሳዊ ምርምሮችን ያዘናጋው።
በትልቅነቱ የጠፈር ያለማቋረጥ ስፋቱን ማን ይገታዋል?
በትንሽነቱ የአካል ያለማቋረጥ ጥበቱን ማን በቃህ ይለዋል?
ሙቀት ያገዝፋል፥ ቅዝቃዜም ያጠባል፤
አካል በትልቅነቱ በትንሽነቱም ከሰው ግንዛቤ በላይ ይረቃል፤
በሁለቱም አቅጣጫ የመኖርና አለመኖር ትርጉም ያጣል።
የት እና መቼ ነው ከሰው አእምሮ አካል የሚሠወረው?
ወደ ኢአካላዊ አለም የሚሸጋገረው፤
ከዚያም ሁለመናው ወደ ሌላ የሚለወጠው።
ለሰው ጎልቶ ወይንም ረቅቆ ያልታየ፥
ሁሉም አለመኖሩን አይደለም የሚያሳውቀው፤
የአካልን የህልውናውን ወሰን፥
ወደ ኢአካላዊ አለም የሚወስደውን፥
ያንን ስውሩን መንገድ ነው ያልተረዳነው።
እኛ ግን፥ በምድሪቱ እንደ ቁሜጭ እንደ ዘመሚት ሆንባት፤
እንደ ራስ ላይ ቅማል፥ እንደ ቂሜምም እየሆንን በላናት፤
እኛ ስንተነፍስ እርሷ እንደማትተነፍስ፥
እርሷ ነፍስ እንዴሌላት፥
የእኛም መኖር ለእርሷ እንደማይበጃት፥
መስሎን - ለሆዳችን ብለን ሆድ ልናሳጣት፥
ቆፈርናት፥ ቆረጥናት፥ ሰረሰርናት፥ ሸነቆርናት፤
አረስናት፥ ገዘገዝናት፥ ፈለጥናት፥ ሰነጠቅናት።
መቼም እርሷ አፍ አውጥታ አትናገር፥
ብቻ አንዳንድ ጊዜ ስትናደድ ስታማርር፥
ታራግፈናለች፤ ወደውስጧ መልሳ ትከተናለች፥
እኛ እንደበላናት እርሷም ትበላናለች።



የሓይል መገለጥ

## የኃይል መገለጥ

አካላዊ ያልሆነውን አለም ባናውቀውም፥ እንዲሁ (ካለ ምንም ሳይንሳዊ ማስረጃ) መኖሩን እናምናለን። ሆኖም፥ እጅግ በተወሰነ ደረጃ፥ አካላዊ ገጽታ - በሦስት ልኬት (dimension) የማይገለጽ፥ በጠፈር ሁሉ አካላዊ ያልሆነ ኃይል ስለመኖሩ ታዋቂ ነው። በደረቅ አይን የማናያቸውም ኃይላት በጠፈር ውስጥ ስለመኖራቸውም በሳይንስም ታዋቂ ነው።[109]

[109] 1) Cosmic Microwave Background Radiation (CMB), 2) Dark Energy; 3) zero-point energy; 4) Electromagnetic Radiation

የኛ እምነት ከምናየው እና ከምናውቀው (ልናውቅ ከምንችለው) ውጪ መሆኑ እምነታችን **ከማንነታችንም በላይ** መሆኑን ይገልጻል፤ "ሁሉን አውቀን ሁሉን ተገንዝበን እናምናለን.." የሚሉ ግን ግብዞች እንጂ፥ እውነተኛ አማኞች ሊባሉ አይገባም።

*"ከዙፋኑም መብረቅና ብልጭልጭታ ይወጣል፥ ነጎድጓዱም ይወጡ ነበር፤ በዙፋኑ ፊትም ሰባት ሰባት የእሳት መብራቶች ይበሩ ነበር። ይኸውም የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ነው።" ራዕይ* 4:5

"የእግዚአብሔር ዙፋን በመብረቅና በነጎድጓድ የተከበበ ነው.." ተብሎ ቢነገረን፥ ይህንን በምናስብበት ጊዜ፥ ዘወትር ከምናየውና ከምናውቀው አካላዊ መብረቅና ነጎድጓድ ጋር ለማዛመድ እንዳዳለን። ይህስ እንዲገባን በምሳሌ ተነገረን እንጂ፤ እኛ ይህንን ልናውቅ አንችልም። የአለማወቃችንም ምክንያቱ በዚያው ጥቅስ ውስጥ *"ይኸውም የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ነው፣"* በሚል ተገልጿል።

ለአንድ ሰው የተገለጠ መገለጥ ለሁሉም አንድ አይነት ስለማይሆን፥ ሰው ሁሉ ወደ ሰማይ አንጋጦ በአንድ አይነት አረዳድ የሚረዳበትን መንገድ ወደፊት ይከሰታል፤ ይኸውም፥ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ እንደሆነ ይመለከቷል።

*"በዚያም ወራት የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፤ ያንጊዜም የምድር አሕዛብ ሁሉ ያለቅሳሉ፤ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል።" ማቴ. 24:30*

አጋንንትም እርኩሳን መናፍስት ስለሆኑ በሰዎች ላይ ስነአእምሮአዊ ተጽእኖ በማሳደር ሰውን ወደ መጥፎው ይመሩታል እንጂ፥ የሰው ልጅ በራሱና ከራሱ በሚመነጭ ክፉ ባሕሬ ብቻ ክፉ ሥራን ሲሠራ አልቆየም።

*"ሰልፋችሁ፡- ከጨለማ ገዢዎች ጋርና ከሰማይ በታች ካሉ ክፉዎች አጋንንት ጋር ነው እንጂ፥ ከሥጋዊ ደማዊ ጋር አይደለምና።" ኤፌ. 6:12*

ይህም ቁሳዊ ባልሆነ ልኬት (dimension) ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች (ጉልበቶች) እንዳሉ ያመለክታል። በማይታየውና በማይታወቀው አለም ውስጥ፥ የእግዚአብሔር ባሕርይ ፍጹም ልዕልናን የተጎናጸፈ፥ ከሰው አእምሮም በላይ የሆነ ነውና፤ ፀሐይን በቀጥታ ማየት እንደማንችል፥ ነገር ግን ሙቀቷ እንደሚሰማን፥ የማናውቀውና የማናየው ኃይል እንዳለ ለእያንዳንዳችን፥ እንደየብጤአችን ልባዊ

---

(Light, Radio Waves, etc.); 5) Gravitational Waves; 6) Black Hole Thermodynamics & Hawking Radiation

አይታዎች ተሰጠን። በዚህም (እንደየችሎታችን) በመንፈስ አርቅቀን ስንሄድ (ስንጸልይ) የእግዚአብሔር ኃይል በውስጣችን ይሰርጻል፤ ቅዱስ መንፈሱ ያድርብናል፤ መንፈሳዊ ብርታትና ጽናትም ይኖረናል።

በቴሌስኮፕ ከሚታየው ጉልህ፥ በማይክሮስኮፕ ከሚታየውም እስከ ደቂቅ አካል ድረስ፥ ሁሉንም በስርዓቱ አስተካክሎ የፈጠረ አምላካችን እግዚአብሔር፥ እኛ ከምናየውም ባሻገር እጅግ የረቀቁ ህያዋንን ፈጥሮም እንደሆነ ስናስበው፤ እኛም ወደ መንፈስነት ተቀይረን፥ አስገራሚ የሆኑትን ድንቅ ድንቅ ሥራዎቹን ወደምናደንቅበት አለም  መሄድን ያስመኘናል።

ይህንን እና የመሳሰሉ ጉዳዮችን ስናስብ ወደ ሌሎች ትኩረት የሚስቡ ጉዳዮች ውስጥም እንሳባለን። ሆኖም፥ ሁሉም (የምናስበውም የማናስበውም) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቃሎ ተቀምጧልና፤ ትኩረታችን ከዚያው በመነጨ ንባብ፥ ትርጓሜ እና ፍልስፍና ቢሆን ይሻላል።

መንፈስ ቅዱስ ያበረታል፤ ያጽናናል፤ ያጸናል፣ ይመራል። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በቀጥታ  ከብርታትና ከችሎታ ጋር የሚዛመድ በመሆኑ፥ ለውጥን ያመጣል፤ ለምሳሌ፡- ሙሴ እግዚአብሔርን ከተገናኘ በኋላ ፊቱ አበራ።[110]

በታቦር ተራራ የኢየሱስ ክርስቶስም መለወጥ ለእኛ መለኮታዊ ክብሩን እንድናገናዝብ አደረገን።[111]

ከየት ይምጡ ከየት የማይታወቅ ሁለት ሰዎች ከኢየሱስ ጋር መገኘታቸውም ቁሳዊ ያልሆነ መንፈሳዊ ዓለም መኖሩን ያረጋግጣል።[112]

ኃይል በአካል ይገለጣል፤

አካላዊ ያልሆነም በሚያመነጨው ኃይሉ ይታወቃል፤

መንፈስ ቅዱስ ኃይልን የሰጣል፤

---

110 “.....ሙሴም ከተራራው በወረደ ጊዜ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር ፊቱ እንዳንጸባረቀ አላወቀም ነበር...።” ዘፀ. 34:29

111 “.....ሲጸልይም የፊቱ መልክ ተለወጠ፤  ልብሱም ነጭ ሆነ፤ እንደ ሙብረቅም አብለጨለጨ...።” ሉቃ. 9:29

112 “እነሆም ሁለት ሰዎች መጥተው ከእርሱ ጋር ይነጋገሩ ነበር። እነርሱም ሙሴና ኤልያስ ነበሩ።” ሉቃ. 9:30

ለሚቀርበው ይቀርባል።[113]

ለሚርቀውም ይርቃል።

እና ታዲያ፡- በልቡ ለእውነት የቀረበ፥

ትንሽ የተባለችዋንም፥ እውቀቱን ይዞ የመጠቀ፥

በትንሿ እውቀቱ ፈጣሪውን ያወቀ፥

ትንሿ እውቀቱ በጸሎቱ፥

ወደ መንፈስ ቅዱስ ከሳበችው፥

ያቺ ትንሿ እውቀቱ ከፈ ከፍ ካደረገችው፥

ስለቀረው በዝሃ እውቀት ምን አሳሰበው?

ብዙ አውቆ ከማያምን፥ ትንሽ አውቆ የሚያምን ይበልጣል፤

"ብዙ" ማወቅ ያጠራጥራል፤

የብዙ አንጻራዊነትን ሳያስተውል፥

ብዙ አወቅሁ ለሚል፥

የገዛ እውቀቱ ይሆነዋል መሰናክል።

እምነት ያጠናክራል፤ ብዙም ያሠራል፤

ከአለማወቅም ቢሆን እምነት ይበልጣል።

አዎ! ጨው ለራሱ ሲል ይጣፍጥ፤

አያውቀውምና ማንን እንደሚያጣፍጥ።

---

[113] "…..መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ…" ሐዋ. ሥራ 1:8



የስሜቶች ምንጭ

## የስሜቶች ምንጭ

ስሜቶቻችንስ እንዴትና ከወዴት ፈለቁ? በአፈጣጠሩ ቀጥ ብሎ ቆሞ የሚሄድ ሰው፥ ሰማይን እንደልቡ ቀና ብሎ ያስተውላል፤ ወደ መሬትም ያቀረቅራል። ቀና ብሎ ከዋክብትን ሲመለከትና አቀርቅሮ መሬት መሬቱን ሲያስተውል የሚሰማው ስሜት አንድ አይነት አይሆንም። እንስሳትና አራዊት ግን፥ ይህ የሰው ችሎታ አልተሰጣቸውም። ስለዚህ፥ እነርሱም እንደየተፈጥሮአቸው እንስሳዊና አራዊታዊ ስሜት ቢኖራቸውም፥ የእነርሱ ስሜት ከሰው ስሜት ጋር አንድ አይሆንም። የኛ ስሜቶቻችን እንዴትና ከወዴት ፈለቁ?

አካላዊ ያልሆነው አለም ውስጥ እንደ ሙቀት እና ቅዝቃዜ የመሰለ ስሜት ቢኖር፥ ያንን ስሜት አካላዊ የሆነ የሰው ልጅ በአካላዊ ተፈጥሮው ሊረዳው አይችልም። እንዲሁም፥ እኛ ገሃነም እሳት የምንለው አካላዊ ለሆነውም ላልሆነውም አንድ አይነት ስሜትን ይሰጣል ማለት አይቻልም።

አካላዊ ባልሆነ ነፍሳችን ላይ የሚያመጣውን ስሜት፥ እንዲሁ መጥፎ ነው እያልን እንገልጸዋለን እንጂ፥ እኛ አናውቀውም (ልናውቅና ሊገባን ዘንድ አይቻለንም)።

በማይታይ አለም ውስጥ ሕያዋን ቢኖሩ፥ ደስታና ሃዘናቸውም በማይታይ ሰውነታቸው (አካላዊ ያልሆነ ማንነታቸው) ለነርሱ የሚሰማቸው ስሜት ምን አይነት እንደሆነ ማን ያውቃል?

እንግዲህ፥ ነፋስ ሲነፍስ መኖሩን እንደምናውቅ፥ መንፈስ መኖሩን እንጂ አኗኗሩን እኛ ልናውቅ አንችልም።[114]

እግዚአብሔር ዓለምን የሚገናኝበትን መንገድ ባናውቅም፥ በእኛ መንፈሳዊ ግንዛቤ አኳያ፥ በምናመልከው አምላካችን እግዚአብሔር ኃይል፥ በመንፈስ ቅዱስ እና በመላእክት እንቅስቃሴ እየተመራን እንኖራለን፤ ስንሞትም ሥጋችን መሬት ሲቀር፤ የተቀረው ነፍሳችን/መንፈሳችን ወደማይታየው አለም ይዘልቃል።

ቅዱሳን አባቶቻችን በጸሎት፥ በጾም እና በአርምሞ ብዛት፥ በእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ውስጥ እስከ መሳተፍ ሲያደርሳቸው፥ ለኛ ከውጪ ለምናያቸው ግራ እንጋባለን። ለምሳሌ፡- የአባታችን የቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አኗኗር ለኛ ለምድራውያን የማይገለጽ፥ ከአእምሮ በላይ የሆነ ምሥጢር እንዳለበት እሙን ነው።

እኛ ማነን? ትንሽ ምድራዊ እውቀትን ይዘን፥

በመንፈሳዊ መንገድ የሚመላለሱትን የአስቸገርን፥

ምድራዊ ስነ አመክኖአችንን ሁለንተናዊ ያደረግን፥

እኛ ማነን? ለአማኞች ግራ ያጋባን፥

አንዳንዴም በምድራዊ አንደበታችን

በነዝናዛ ደረቅ እሳቤአችን፥

ለአማኞች መሰናክል የሆን።

አዋቂው ፍጡር (sapiens) የተባልን፥

ከተገለጠው የተደበቀው የሚበልጥ መሆኑን አላወቅን፥

ምሥጢራቱን እንዳያመሰጥሩልንም ተከላከልን፥

ሁሉም ግልጥልጥ እስኪል መታገሱ ሰልችቶን፥

በደብዛዛው ስንሰነካከል አረጀን።

---

[114] ዮሐ. 3፡ 6 - 12



የመላእክት መንደር

## <u>የመላእክት መንደር</u>

የሰማይ መላእክት ከኛ ጋር ናቸውን? ሁሉም በእግዚአብሔር እንደተፈጠረ ካመንን[115]፥ የሰማይ መላእክትም እንዳሉ ካመንን፤[116] የሰማይ መላእክትም በዙሪያችን እንደሚኖሩ መረዳት ያን ያህል ከባድ አይሆንም።

---

115 “.........ሁሉም በእጁ ሆነ፤ ሁሉም በእርሱ ለእርሱ ተፈጠረ።” ቆላ. 1፡16 (ነህሚያ 9፡6፥ ወ.ዘ.ተ.)

116 “መላእክቱ ሁሉ ያመሰግኑታል፤ ሠራዊቱ ሁሉ ያመሰግኑታል።” መዝ. 148፡2

የመላእክትን መኖሪያ፤ አኗኗራቸውን፥ መውጪያ መግቢያቸውን፥ ባሕሪአቸውን እና ድርጊቶቻቸውን ማወቅ ባይቻልም፥ እግዚአብሔር የፈጠራቸው ቅዱሳን መላእክት በዙሪያችን እንዳሉ፥ ከእነርሱም ጋር፥ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ፥ መገናኘት እንደሚቻል እናምናለን።[117]

የመላእክትን ስማቸውን ስንጠራ ይሰሙናል፤

እናውቃቸው ዘንድ፥ አውቀንም እንዲራዱን፥

እንዲህ ብለው ስማቸውን አሳወቁን፡-

ሚካኤል፤ ገብርኤል፤ ሩፋኤል፤ ዑራኤል፤ ራጉኤል፤ ሱሪኤል፤ ራሚኤል፤

እነዚህ ሰባት መላእክት በሰው ተመሳሌት ታይተው፥

ወይንም ሳይታዩ በአራቱም ማዕዘናት አለምን ዞረው፤

ለሚጠሯቸው ሁሉ ተስፋን መግበው፤

ክፉ መናፍስትን ተቋቁመው፥

በፈጣሪያቸው ፈቃድ በየሰዉ ቤት ተገኝተው፥

ለተጨነቁት፥ ለተጎዱት ሁሉ በጎ ሥራን ሠርተው፥

ባለ ውለታችን መሆናቸውን እንኳን ሳናሳውቃቸው፥

ፍጥነው ይኼዳሉ - የታዘዙትን ብቻ ፈጽመው፥

ወደ ሌላ በጎ ሥራ ይሠማራሉ - በቶሎ ውልብ ብለው።

117 “ስለ መላእክቱም፥ መላእክቱን ነፋሳት፥ የሚላኩትንም የእሳት ነበልባል የሚያደርጋቸው እርሱ ነው።” ዕብ. 1፡7



ልዩ ፍጥረታት በጠፈር

## የተለያዩ ሥጋውያን ነፍሳት

በጠፈር ውስጥ ሌሎች ሥጋውያን ነፍሳት[118] ቢኖሩ፥ እኛ አናውቅም (ልናውቅ አንችልም)፤ ነገር ግን፥ እንደሚኖሩ ሳይንሳዊ እና መንፈሳዊ ስነ አመክኖአችን ይነግረናል።

[118] እንደኛው አይነት ሥጋውያን ቢሆኑ፥ የእነርሱ ሕልውናቸው የሚገለጽበትን አካል ከእኛ አካል ልዩ መሆኑን ለማስረገጥ "ሚሻከል" በሚል ቃል መጠቀም ይቻላል፤ ይኸውም፥ የእነርሱ አካል በፍጥረቱ (በይዘቱ) ከእኛ አካል መለየቱ ስለማይቀር ነው።

በሌሎችም እኛ በማናውቃቸው አለማት ውስጥ ከእኛዎቹ ጋር የሚመሳሰሉ (ወይንም የማይመሳሰሉ) የተለያዩ ፍጥረታት ተፈጥረው ይሆናል (አናውቅም)።

በዚህች ታናሺቱ በምድር ያለውን የፍጡራን ብዛት ባሰብንበት አእምሮአችን፥ ሰፊውንም ጠፈር በምናብ ስንዳስስ፥ ሌሎችም በእኛ ምድር ካሉ ፍጡራን ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው (ወይንም የሌላቸው) ሌሎች ፍጡራን እንደሚኖሩ ይታሰበናል።[119]

የግለሰብ እምነት የሚጸናው በሥጋዊ አይኑ በሚያየውና በሥጋዊ አእምሮው በሚያውቀው ላይ ብቻ አይደለምና፤ "እንይና እንወቅ፥ እንወቅና እንመን" ብንል፥ ስንቱን አይተን ስንቱንስ አውቀን እንዘልቀዋለን?[120]

የአእምሮአችን ተመራማሪነት ሩቅ አልወሰደንም፤

በጠፈር ስለሚኖሩ ሥጋዊ ሕያዋን - ሚሻክላውያን፥

ምንም አዲስ አይነት እውቀት አላፈለቀም፤

ስለመኖራቸውም ጉዳይ ሳይንስ ምንም አላበሰረም።

ሁሉም በእውቀት ብዛት አይገለጽም፤

ሁሉም እውነት በእውቀት አይገኝም፤

በመንፈሳዊነት እና በእምነት ውህደት ብዙ ነገር ይገለጣል።[121]

---

119 "ዓለም በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠረ፥ የሚታየውም ነገር ከማይታየው እንደሆነ፥ በእምነት እናውቃለን" ዕብ. 11:3

120 "ጌታችን ኢየሱስም፥ "ስለአየኸኝ አመንህ? ብጹአንስ ሳያዩ የሚያምኑ ናቸው" አለው።" ዮሐ. 20:29

121 "ከዚህም በኋላ አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን አየሁ፤.......።" ዮሐ. ራዕ. 21:1



የጠፈር ሕያዋን

## የጠፈር ሕያዋን

በጠፈር ውስጥ አያሌ እንደ መሬት ያሉ ሥፍራዎች እንደሚኖሩ፤ በእነዚህ ሥፍራዎች ውስጥም፥ ነፍስ ያላቸው ተንቀሳቃሽ ሕያዋን፥ በአንድም ሆነ በሌላ መልክ፥ ሊኖሩ እንደሚችሉ ይገመታል።

ሕይወት የተዘራው በመላው ጠፈር ሁሉ ከሆነ፥ የጠፈራዊ ሕያዋን (ፍጥረታት) አኗኗርና ስሜት የኛኑ ቢመስል ማን ያውቃል?

አካላውያን (ሚሻከላውያን) የሆኑ የጠፈር ሕያዋን፥ ሁሉም እንደ ብጤያቸው፥ ደስታቸውን የሚገልጹበት ዘዴ ቢኖር፤ ምናልባትም፥ እንደኛው አይነት ዘፈን እና መዝሙር፥ እንደኛው እልልታ እና ጭፈራ ቢኖራቸው ማን ያውቃል?

ከጠፈራዊ ሕያዋን መካከል፥ የአንዳንዶቹ (ወይንም የሁሉም) አኗኗር፥ መንፈሳዊ ቢሆን እና፥ እንደኛ የሚቀድሱና የሚዘምሩ ቢሆን፥ ማን ያውቃል?

በጠፈር ውስጥ ሕያዋን ነፍሳት ካሉበት ሥፍራ ሁሉ ቅራኔዎችም ስለሚኖሩ፥ ልክ እንደኛ ምድር፥ ጠብና ጭቅጭቅ፥ ጦርነትም ቢኖር - እነርሱም እንደ እኛ፥ በውስጣቸው ጉራማይሌ ስሜት (ሃዘንና ደስታ) ቢኖርባቸው ማን ያውቃል?

እኛ ግን፥ በእምነታችን፥ ሰማያዊ አለም አለ የምንለው ከአንድ አካል ወደ ሌላ አካል የምንሸጋገርበት ምድራዊ/አካላዊ ሥፍራ አይደለም። ስላልሆነም፥ ከዚያ ቅራኔዎች እንደማይኖሩ እናምናለን። ከዚያ (ከሰማይ) ፍጹም ደስታ (ሃሴት) ይኖራል ብለን እናምናለን። የእኛ ምድራውያን ሰዎች ፍጹማዊ ደስታ የሚከሰተው ሞተን ስንነሳ፥ ፈጣሪ አምላካችን እግዚአብሔር ባለበት በሰማይ እንደሚሆን እናምናለን።

በአካላዊው አለም የአካልና የጊዜ አብሮነት፥

የሕይወት ውሱንነት፥

መሞትና መበስበስ - ጊዜ መቁጠር ያለበት።

ሰማያዊው አለም ነው ይህንን የመሰለ ውዝግብ የሌለበት፤

ለነፍሳችንም ሰማያዊ ሕልውናችንን የምናገኝበት (ዮሐ. 3)።



እንቅስቃሴዎች በምድር

## ምድራዊ ዝግጅቶች

እግዚአብሔር ለሁሉም ነገር ስርዓት ስላበጀለት፥ ለእኛም ከዚህ መድረስ የብዙ ሚሊዎን ዓመታት ክንውኖች በማስፈለጉ፥ ምድሪቱን ለእንስሳት ለሰውም ምግብነት ሲያዘጋጃት ቆይቷል።

ጥቃቅን የየብስ እና የባህር ሕያዋንም ከመፈጠራቸው በፊት፥ ለመኖር የሚያስፈልጋቸው ሁሉ ተስተካክሎላቸዋል። እግዚአብሔር ምድሪቱን ለምድራዊ ሕያዋን ሁሉ (እነደየጠባያቸው፥ ሁሉንም በሰማይ በመሬት እና በባሕር) ተስማሚ አደረገ። ይህቺን ምድራችንን (መላ ሰውነቷን) ስንቃኛት፥ በውስጧ ብዙ ሥፍራ አለ ሰው የማይኖርባት።[122] ታዲያ ማን ያውቃል፥ የማይታዩ (ስውራን) ፍጡራንም በውስጧ ቢገኙባት?

---

[122] ከምድራችን ምን ያህሉን እንደምንጠቀም ይመለከቷል፦ ባሕር፡-71%፤ ደረቅ መሬት፡-29%፤ ሰው ሊኖርበት የሚችል ደረቅ መሬት፡-.6%፤ በበረዶ የተሸዕፈነ፡-3%፤ በረሃ፡-10% ፤የማይኖርበት ጫካ፡-3%፤ ሌሎች ተራራማና የማይኖርበት ሥፍራዎች፡-7%

እውቀት እንደ ውሃ ምንጭ ከያለበት ይመነጫል፤ ጥራቱን ብዛቱን፥ አካሄዱን ሁሉ፥ ጊዜና ሥፍራ ይወስነዋል። ወደ ባህር የሚገባ፥ ወደ መሬትም የሚሰርግ ውሃ አለ። እንዲሁም የሰው ልጅ እውቀቱ ምድራዊም ሆነ ሰማያዊ፥ ልክ እንደ ወንዝ ውሃ ሲፈስ ቆይቷል። አካሄዱን እና አቅጣጫውን የሚያይ አይነ ልቡና ይስጠን።

የሳይንስ ሊቃውንት እንደነገሩን፡- ከጠፈር ውስጥ፥ እኛ ልናውቅ የምንችለው (በማየት ብቻም ቢሆን) 5% ነው፤ የተቀረው (95%) አይታወቅም።[123]

የማያቋርጥ፥ ዘለአለማዊ ሃሴት የሚኖረው በማይታየው ሰማይ ውስጥ ቢሆን እና፥ ከዚህች ምድራዊ ደስታ ጋርም ቢወዳደር፥ “በእውነት ይህች ምድር 5% ያህል እንኳን ደስታ ይገኝባታል ወይ?”

አዬ! ይህስ ምድራዊ ደስታ እኛ ደስታ የምንለው፥

እውነት ቢሆን እንኳን፥ ፍጹም ደስታን የሚሰጠው፥

ከ 24 ሰዓታት ውስጥ ምን ያህሉን ጊዜ ነው፥

ሰው ሳይከፋው ሙሉ ደስታን የሚያገኘው?

ለብዙሃኑ 2% እንኳን ሙሉ ደስታ በዝቶባቸው፥

ሆድን ለመሙላት መድከም ብቻ ሆኗል ኑሮአቸው።

ደስታን ከሰው እየነጠቁ፥ ደስታን የፈለጉ ለራሳቸው፥

ከአለመደሰትም በላይ ሲያዝኑ ሲተክዙ ነው ያየናቸው፤

በእውነት ደስ የሚላቸውስ፥

ሌሎችን ለማስደሰት የሚተጉ ናቸው።

---

[123]በጠፈር ውስጥ 95% የሚሆነው በማናያቸው ክፍሎች የተመላ ሲሆን፥ ከዚህ ውስጥ 68% ጨለማ ኃይል (dark energy) የተቀረውም 27% ጨለማ ነገር (dark matter) እንደሆነ ይነገራል።



## ጊዜ ምንድነው?

ጊዜ ምንድነው? ጊዜ ድርጊትን የሚያመለክት የአንድ እንቅስቃሴ ጅማሬን፥ ሂደትን እና ፍጻሜን የሚያመለክት ጽንሰ ሃሳብ (መለኪያ) ሲሆን፤ የመፈጠር፥ የመወለድ፥ የማደግ እና የመሞትን ክስተት - ታሪክ ለመተረክም እንዲያመች የተስተካከለ መቁጠሪያ ቀመር ነው።

ጊዜ እና እንቅስቃሴ አይለያዩም። በእንቅስቃሴ (የመርገብገብ ማዕበል) ብዛት የሚለወጡ፥ የሚያረጁ፥ ነፍሳማዎች ብቻ አይደሉም። በድን አካላትም (ቤቶች፥ ድንጋዮም፥ ተራሮችም) ስለሚንቀሳቀሱ ያረጃሉ፥ ይፈርሳሉ፥ ይበሰብሳሉ፥ በመጨረሻም ይቀየሩና የቀደመ ህልውናቸውን በሌላ ይተካሉ ያጣሉ።

በእኛ የመፍጠንና የመንቀርፈፍ - ከትውልድ እስከሞት ባለው የእንቅስቃሴዎች ተመን ሲታሰብ፥ ግዑኡዛን አይን ኖሮአቸው ቢያዩን፥ የእኛ እንቅስቃሴ ቶሎ ለማይሞቱቱ፥ እጅጉን ፍጥን ፍጥን የሚል ይሆንባቸዋል።

እኛ ቶሎ የማንሞት ቢሆን ኖሮ (እድሜአችን በሺዎቹ ቢሆን ኖሮ) ሁሉ ነገር ባይናችን ላይ ሲያልፍ ፍጥን ፍጥን ይልብን ነበር (ለሕጻናት ጊዜ ረጅም ነው፤ ለሽማግሌዎች ደግሞ ጊዜ ቶሎ ቶሎ ያልፋል)።

ሁሉም ነገር እንደ ነፍሳማ (ሕያዋን) አንዱ ሌላውን ተከትሎ፥ እንደ ወራጅ ውሃ ይፈሳል (ይለዋወጣል)። ሆኖም፥ ፍጥነት እና ጊዜ በሰው ግንዛቤ እንጂ፥ ዘለአለማውያን ለሆኑት ምንም ትርጉም አይኖረውም።[124]

ጊዜ ለእግዚአብሔር ምኑ ነው? እግዚአብሔር ዘለአለማዊ ስለሆነ፥ ዘለአለማዊ ለሆነ እግዚአብሔር ጊዜ ምንም ትርጉም አይኖረውም።

ለእግዚአብሔር ቅርብ የሆኑ፥ ሱራፌልም (ኢሳ. 6፡2) ካለማቋረጥ አምላካቸውን ሲያመሰግኑ ለእነርሱም ጊዜ ምንም ትርጉም አይኖረውም።

ሰው ግን፥ መንፈሳዊ ቢሆንም አካላዊም ነውና፤ በጊዜ ቀመር መጠቀም አስፈልጎታል፤ ምክንያቱም፥ ጊዜ የሚለካው የአካልን እንቅስቃሴ ስለሆነ፤ አካልና ጊዜም የማይለያዩ ስለሆነ ነው።

በቅዳሴ ዜማን የሚያስረዝሙ ቀዳሾች ለእነርሱስ ጊዜ ምንድነው? እነሱማ በመንፈሳዊ ስሜት፥ ከምድር እየተነጠቁ ወደ ሰማይ የሚገቡ፥ ከዚያም ከሰማይ አቻዎቻቸው ጋር በሰማያዊ ቅዳሴ ሲቀድሱ (ሲያዜሙ) ጊዜን ቀጥ የሚያደርጉ ናቸው።

"አሐዱ አብ ቅዱስ፤ አሐዱ አብ ወልድ ቅዱስ፤ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" በማለት፥ ጥዑም ሰማያዊ ዜማን ለሚያሰማ ምድራዊ ቀዳሽ ጊዜ ምኑም አይደል። እኛም ምእመን ረጋ ብለን፥ ቀልባችንን ሰብሰብ አድርገን፥ አብረን ስንሳተፍ፥ ጊዜ እጅግ አጭር (ወደ ዜሮ የተጠጋ) ነው የሚሆን።

በአጠቃላይ፥ የሰማይና የምድር ጌታ ለሆነው ጌታችን፥ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ለአምልኮ መቆም ማለት በመንፈስ መጥቆ፥ ሰማይ ደርሶ፥ ከአምላክ ፊት በመቆም ፍጹም ደስታ (ሃሴት) ውስጥ መገኘት ስለሆነ፥ ጊዜ ይሽማቀቃል - ፍጹም ደስታን ከሚሰጡ ኩነቶች ውስጥ ስንገኝ ጊዜ ወደምንምነት

---

124 ሺህ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደ ትላንት ቀን፥ እንደ ሌሊትም ሰዓት ነውና። ዘመኖችህ በፊትህ የተናቁ ናቸው፤ በማለዳም እንደ ሳር ያልፋሉ። መዝ. 89፡4-5

በተጨማሪ ትንቢተ እንባቆም ምዕራፍ 3፤ እንዲሁም መጽሐፈ ኢዮብን ያንብቡ።

ይጠጋል ማለት ነው። ይህንን ለምድራዊነታችን አስፈላጊ የሆነ ጊዜ ከሰማያዊነታችን ጋር አነጻጽረን መመልከትን በመሻት ጠልቅ ብለን ስንመራመር አያሌ ኩነቶች ያስደንቁናል። ለምሳሌ፡-

አንድ መንፈሳዊ ሰው በጊዜ ውስጥ ሲመላለስ እንደ አንድ አለማዊ ሰው አይደለም። ምናልባት አንድ አለማዊ ሰው በጊዜ ውስጥ ሲመላለስ፥ በልጅነቱ የሠራቸውን የእናትና አባቱን፥ የአጎቶቹንና የአክስቶቹን፥ የባልንጀራዎቹን (ክፉውንም ደጉንም) ያስታውስ ይሆናል። ሌላ መንፈሳዊ ሰው ደግሞ፥ ፈጣሪ አምላኩ ያደረገለትን ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ ያስታውሳል፤ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ከአዳምና ሔዋን ጅምሮ የተተረከው ለሰው ልጅ መንፈሳዊ ታሪኩ ነውና። እና፥ አሁንም የጠቀስናቸው ቀዳሾች "ወ..ን..ጌ..ል.." በማለት ዜማን የሚያስረዝሙት እኛ ምእመን፥ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት፥ እስከ ሞቱ እና መነሳቱ፥ ሁሉንም በአንድ ጊዜ በአእምሮአችን እንድንቀርጽና በመንፈሳዊ ስሜት እንድንመጥቅ ሊሆንም ስለሚችል (ግላዊ አስተያየት)፤ የዚያን ጊዜ ለአንዳንዶቻችን ጊዜ ምንም (ዜሮ) ይሆናል ማለት ነው።

የጊዜ መርዘምና ማጠር አንጻራዊ መሆኑን፥ በሕይወታችን ሥጋዊና መንፈሳዊ ኑሮ እንረዳለን። በሥጋዊ አመለካከት ጊዜ አካልን ይገልጠዋል። አንድ እሁድ ይመጣል፤ ሌላ እሁድ ይተካል፤ እንዲሁም፥ አንድ መስከረም ሌላውን ይተካዋል። ታዲያ፥ እኛም "ኢ..ት..ዮ..ጵ..ያ.." ብለን፥ ጊዜን ድምስስ አድርገን፥ የኢትዮጵያችንን ሥጋዊና መንፈሳዊ ማንነቷን (ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ) ያሳለፈችውን ታሪኳን (የሆዷን ክፉና ደጉን ሁሉ) ብናስታውስ! ቀጣዩ እድል ፋንታዋ ወደ ጥሩው እንጂ፥ መልሶ ወደከፋው እንደማይወስዳት እንረዳ ይሆናል።

ጊዜ ልክ እንደ ጅረት ውሃ ይግተለተላል፤ በዛውም መጠን አካል ይለዋወጣል። በዚህ አንጻር ሲታይ፥ መንፈስና ጊዜ አይተዋወቁም ማለት ይቻላል።

በእግዚአብሔር ቃል የተፈጠረ አካል ሁሉ መነሻና መድረሻ ስለሚኖረው በመካከሉ የጊዜ መኖር አስፈልጓል የሚል ሰው ነው። ስለዚህ፥ ያንን ጊዜ ሰው ልቀምር ብሎ ይነሳል። ለምሳሌ፡-

"መሬት በዚህ በአሁኗ ቅርጿ ከተገኘች 4.5 ቢሊዎን ዓመት ይሆናል። በመጀመሪያ የነበሩ ነፍሳትም (stromatolites) በምድር ላይ ከተፈጠሩ 2.5 ቢሊዎን ዓመት ይሆናል.." ብለን እንድናስብ የሚያደርጉ ምልክቶችን (Carbon Isotopes ($\delta^{13}C$) በግልጽ ተመልክተናል።

እነሆ! የእግዚአብሔር እና የሰው (ሰማያዊ እና ምድራዊ) ምልከታ ምንኛ የተራራቀ ነው።[125]

እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር የፈጀበት ጊዜ፥ ምናልባት አንድ ሰኮንድ ላይሞላ ይችላል፤ ይህ እሳቤ እኛጋ ሲደርስ ግን ሌላ ነው። እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር የፈጀበት ጊዜ አንድ ቀን፥ አንድ ሳምንት፥ ወይንም ብዙ ሚሊዎን ዓመታት ቢሆን፥ ይህንን ማሰብ ለእኛ ምን ይጠቅማል? ነገር ግን፥ የሰው ልጅ በምድር መኖር ከጀመረ ከመቶ ሺህ ዓመታት በላይ ይሆናል ለማለት የሚያበቁ መለኪያዎችን ባስተዋልን ጊዜ፥ ለእኛ የሚጠቅመን እግዚአብሔር ለፍጡራኑ ያለውን ፍቀር ማሰላሰል ነው። እግዚአብሔር ለእኛ ምድራዊ ሕይወት የሚያስፈልገውን ሁሉ ሲያዘጋጅ የቆየበትን ረጅም ሰዋዊ ጊዜ (በእኛ የጊዜ አቆጣጠር) ስናስበው፥ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ፥ ክቡር፥ ተወዳጅ ፍጥረት መሆኑን እንረዳለን፤ በዚህም ደስ ይለናል።

ጥንት ተፈጥረው የነበሩ፥ አሁን የማይታዩ - የጠፉ፥
በዝቅጠ አለቶች ውስጥ ይታያል ሬሳቸው - አካለ ቅሪታቸው፤
የእድሜአቸውም ተመን ይታወቃል (ይገመታል) ከአጽማቸው፤
እንደነሉሲም (ድንቅነሽ) በሚሊዎን የሚቆጠር፥[126]
የሌሎችም አጽም ተመዝግቧል በሳይንስ ምርምር።

በመላምት ሳይሆን ማስረጃን ‘ሚያቀርበው፥
የእግዚአብሔርን ሥራ በቅጡ ‘ሚያብራራው፥
አንጻራዊ ሳይሆን ከእውነት ያልራቀው፥
ሳይንስ (ጂኦሎጂ፥ አንትሮፖሎጂ..) ለሃይማኖት አጋር ነው።

የእግዚአብሔርን ሥራ የምናደንቅ፥
በምድር ተደሳቾች በጊዜያዊ ደስታም የምንፈነድቅ፥
ከፉ ጊዜ አልፎ መልካም ጊዜ ውስጥ የገባን፥

---

[125] “ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የነበረውና ያለው፥ የሚመጣውም፥ ሁሉንም የሚገዛ አምላክ” እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም።” የሐ. ራዕ. 4፡8

[126] "Lucy" — the famous Australopithecus afarensis fossil — is about 3.2 million years old.

ጊዜአዊ ደስታን (pleasure) እንደ ሎተሪ ያገኘን፥
እና ዘላቂ ደስታን (hapiness) ማጣጣም ያቃተን፥
ክረምት በልባችን በጋ ከፊታችን፥
ያሳለፍነው የክፉ ጊዜ ቅርሻት ከአፋችን፥
እናስተውል፥ ሕይወት ቅኔ ናት፥
ትርጉም (ፍልስፍናም) የሚያሻት፤
ሃዘን በደስታ ባይለወጥም፥
ተስፋ አንቁረጥ፥
ተረጋግቶ መኖር ይቻላል በምድራቱም፤
በምክንያት እንጂ፥ ካለ ምክንያት ከዚህ አልደረስንም።
በምድርም ሳለን እንደየእምነታችን ደስታን እናገኛለን።[127]
መናፈቅ መከጀል፥ መጓጓት፥
ከዚህ ሳሉ ወዲያ መንጠራራት፥
ብቅ ጥልቅ፥ አንድ ቦታ አለመርጋት፤
በሃሳብ መቃተት፥ ወዲያ ወዲህ ማለት፥
የመጥፎን መጥፎነት - የጥሩን ጥሩነት አለመለየት፥
አንዱን አለመምረጥ፥ መርጦም አለመርጋት።
የወሬ ነፋስ በአንድ በኩል በጧት፥
ሲነፍስ በተሲአት፥ በምሽት እና በሌሊት፥
ብዙ ነገር ሲተራመስ አብሮት፥
በሽውታም ቢሆን በማፏጨት፥
በሹክሹክታም ቢሆን በጩኸት፥

---

127 "የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ፤ ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ፤ በቀኝህም የዘለአለም ፍሥሐ አለ።" መዝ. 15፡11

"..ነፍሴም በእግዚአብሔር ሐሴት ታደርጋለች፤ ሸልማትን እንደለበሰ ሙሽራ፥ በጌጥ ሸልማቷን የማዳንን ልብስ አልብሶኛልና።" ኢሳ. 61፡10

ከአራት አቅጣጫ ንግግሩ ከሰው ጆሮ ሲደርስ፥
ከተሳታፊው፥ አሳታፊው ሲብስ፥
ሰውም ከአየሩ ጋር አብሮ ሲነፍስ...........፤
ይገርማል! ለምንድነው?
ሰው እውነትን የሚሸሽ ልክ እንደ ባይተዋር?
ለምንድነው እውነቱን እውነት፥
ውሸቱንም ውሸት ለማለት የማይደፍር?

## መደምደሚያ

በመንፈሳዊ ሥልጣኔ ካልሆነ በስተቀር፥ ሳይንስ አካላዊ ያልሆነውን አያውቀውም። ሰይጣን ይህንን የኛን የችሎታ ማነስ በመጠቀም፥ ሳይንሳዊ ስነ አመክንዮአችንንም መቀማት ይፈልጋል። ስለዚህ፥ እኛ ማድረግ ያለብን፥ በችሎታችን የምናውቀውን አውቀን፥ ማወቅ በማይቻለን ሁሉ በእምነት መጽናት ነው።

የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ሥራ እንዲሁ ከማድነቅ አልፎ፥ ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ በመግባት ሁሉን ልወቅ ቢል፥ አይችልም። ሳይንቲስቶችም ሞከሩ እንጂ፥ በተፈጥሮአቸው ውሱን መሆናቸውን ይረዳሉ።

እኛ ምድራውያን ሰዎች ፍጹማዊ ደስታ የሚከሰተው ሞተን ስንነሳ ቢሆንም፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ከውስጣችን ካለ፥ ከዚሁ ሥቃይ በበዛበት በምድራችን ውስጥም ቢሆን በደስታ ልንኖር እንችላለን።[128]

ምድራዊ ሃብትን ያካበተ፥
ምድራዊ ደስታን በገንዘቡ የሸመተ፥
ለጊዜው መሆኑን ሲያስበው፥
በምትኩ ሃዘን ይጎበኘው፤

---

128 "ቃልህ ሐሴትና የልብ ደስታ ሆነኝ።" ኤር. 15፡16


"ወንድሞች ሆይ! ልዩ ልዩ መከራ በሚመጣባችሁ ጊዜ በሁሉ ደስ ይበላችሁ።" ያዕ. 1፡2

ደስታ በምድራችን ምንጊዜም አይጸዳም፤
ኃጢአት እየሠሩም ደስታ አይገኝም።

ስናምን፥ ሳናምንም፥ ስናውቅ ሳናውቅም፥
የእግዚአብሔር መንፈስ አለ ፈራጅ ሁሉን የሚወስን፤
ስለዚህ፥ የፍጥረታትንም ነገር ከመንፈሳዊ አቻቸው ሳንለይ፥
እንድንረዳቸው ተመራማሪ አእምሮ እግዚአብሔር ይስጠን።
ከሳይንሳዊ ብቃት ጋር የሚሄድ ጎን ለጎን፥
መንፈሳዊ እውቀትን (ብቃትን) ይለግሰን፤
ዐይነ ልቡናችንንም ያብራልን።
አሜን።

# ምዕራፍ አራት

## ምልከታችን - ወደ ምሥራቅ



ወደ ምሥራቅ

## መግቢያ

አንድ ሰው ጥሩ ሰው (ጥሩ ዜጋ) ቢሆን ራሱን እና ሕብረተሰቡን አገሩንም የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ አይሆንም። ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ እድገትም ቢሆን፥ መንፈሳዊነት ሲታከልበት ነው ሕብረተሰቡን የሚጠቅመው፤ አስተዳደሩም ጥሩ መልክ የሚይዘው።

በቅድስት አገራችን በኢትዮጵያ (ኤርትራንም ጨምሮ) ሕዝብ እና መንግሥት "ተፈጥሮን በቁጥጥር ውስጥ እናውላለን.." የሚል መፈክር ይዞ በተነሳበት ወቅት የት እንደደረሰ፥ የዛን ጊዜው የክፉ መንፈስ ሰንኮፉ እስካሁን እንዳልተነቀለ አስተውለናል።

ይህች ምድራችንም እውነትና ውሸት፥ እውቀትና ድንቁርና፥ ክፋትና ደግነት፥ ጥሩና መጥፎው ሁሉ አብረው የሚኖሩባት ጉራማይሌ አለም ናትና፦

ልቦናችንን ከፍ ከፍ እናድርግ፥

ከጉልሁ ወደ ረቂቁ እንደግ፤

ከረቂቁም ወደ ግዙፉ እንሰወር።

## ምልከታችን - ወደ ምሥራቅ

በብዙ ዓመታት የሚቆጠረውን ዘመን አሳጥረን፥

እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ ደረስን፤

ከዚያም በኋላ በትክክል ዘመን መቀመር ስንጀምር፥

"እመጣለሁ..." እያለ ሲያባብለን የነበረ ክርስቶስ ዘገየብን፤

ክርስቶስ ናልን (ማራ ናታ) እያልን ብንማጸን፥

የረሳን እስኪመስለን፥ አምላካችን ቆየብን፥

የተሸከመችን መሬት የተሸከምናትን ያህል ስለከበደችን፤

መጨረሻው (የጌታችን መምጫያው) ጊዜ ረዘመብን።

በምድራዊነታችሁ ምድሪቱን ያልለቀቃችሁ፥

በሥጋዊ ፍላጎት ተጠምዳችሁ፥

ኑሮአችሁን አለማዊ ያደረጋችሁ፤

ከተቀመጣችሁበት ተነሱ፤


ብድግ ብላችሁ ቁሙና አስተውሉ፤

ወደ ምሥራቅም ተመልከቱ፤
በሰማይ ከዋክብት የደመቀ ጠፈር ሁሉ የሚሰግድለትን
ከድንግል ማርያም ሰው ሆኖ የተመወለደውን፥
ስለኛ ስለ ሰዎች የተሰቀለውን፥ የሞተውን፥
ከሙታን ተለይቶ የተነሳውን፥ ያረገውን፥
ዳግመኛም ተመልሶ የሚመጣውን፥
በተመስጦ አስቡት ኢየሱስን።
ይመጣል ተመልሶ፥ እንደሄድ አይቀርም፤[129]
እግዚአብሔር በግልጥ ይመጣል፤ ዝም አይልም።[130]
እግዚአብሔር ሲፈጥረን እንድናመልከው፥
እኛ ስናፈነግጥ፥ ስንሸሽው፥
እርሱ ሲያስተምረን፥ ሲመልሰን በየጊዜው፥
ይህንን ነው ከታሪክ የተማርነው።
አንድ እውነት ብቅ ሲል፥ ቢከተልም አጥፊው፥
ከሰማይ በመጣ ትምህርት ነው ክፉውን የምንቋቋመው።
ተመስገን፤ ለዚህም ነው እስካሁን ሳንጠፋ የቆየነው።
"እውነት እና  እምነት ከወዴት አለ?" ብለን ስንጠይቅ፥
ሲነገረን ቆየ፥ እንድናስተውል ወደ ምሥራቅ፤
እሺ እንግዲህ አእምሮአችን ይንቃ፥
አይነ ልቦናችንም ይመልከት፥
አቅጣጫው ተነግሮናልና ጌታችን የሚመጣበት።
ከእንግዲህስ መንፈሳችን ይረጋጋ፥
ወደ ጥሩው እንዲጠጋ።

---

129 "........ከእናንተ ወደ ሰማይ ሲያርግ ያያችሁት ኢየሱስ፥ ከእናንተ ወደ ሰማይ ሲያርግ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ዳግመኛ ይመጣል" አሏቸው። የሐ.ሥራ 1፡11

130 መዝ. 49፡3



አንድነታችን

## <u>አንድነታችን</u>

እኛ በኋላ ተፈጥረን፥ ገና በጨቅላነታችን ግራና ቀኝ ተመልክተን፥ በቅርባችን ያለውን ምድራዊ/አካላዊ የሆነውን ሁሉ ስንነካካ ብዙ ተማርን። በዙሪያችን ያየነው የሰማነው ሁሉ የእኛኑ ምድራዊነት መልሶ ይነግረናል።

አስተሳሰባችንን ወደ ሰማይ ስናመጥቀው፥ በአይነ ሕሊናችንም ስናስተውል፤ ከዚያም ቆይተን ስለ መንፈሳዊነታችን ነገር በማሰላሰል፥ ብዙ ቆይታዎች ባደረግን ጊዜ፦ “አየር ከሌለበት የድምጽ ሞገድ እንደማያስተጋባ ሁሉ፥ ባዶ ከሆነ ሥፍራ ምንም አዲስ ነገር አታገኝም። ከምድራዊነትህ ወጥተህ የምትሄድበት ሥፍራ ባዶ ነው፤ ድምጽ የለም፤ ምንም ነገር የለም። ስለዚህ፥ በከንቱ በሃሳብ አትባዝን፤ ከአንተነትህ ርቀህ አትሂድ፤ ልታገኝ የማትችለውን አትሻ፤ ወደ ምድራዊነትህ ተመለስ፤..” የሚል ሃሳብ ይጫነናል።

ቀጥሎም፥ ውስጣዊ መንፈሳዊ ተፈጥሮአችን ሌላ የተለየ ተስፋ ይሰጠናል። አየር በሌለበትም ሥፍራም ቢሆን፥ አልፎ አልፎ “የሕሊና ጭውታ” ይሰማናልና፤ በአእምሮአችን ከምድራዊነት አስወጥቶ ወደ ሌላ ሥፍራ በሚወስድ የሃሳብ መንኮራኩር እንደምንጓዝ፤ አንዳንድ ጊዜም፥ በአካል ወደማይገለጽ ሰማያዊ አለም ውስጥ እንደምንገባ ይታወቀናል። ስለዚህ፥ አሁንም ራሳችንን ከምድራዊነታችን እየገነጠልን፥ ወደ ውጪ ከመመልከት፥ በራዕይም ሆነ በእውን፥ በቅዠትም ሆነ በሕልም፥ በአይነ ልቡናችን ከማስተዋል አልቦዘንም፤ የመንፈሳዊነታችን ነገር ከአንድ የተወሰነ ኃይል እንጂ፥ ከምንም አልተቀሰቀሰምና።

መንፈሳዊ ሥልጣኔ ከዘመናችን ምድራዊ ሥልጣኔ እጅጉን የረቀቀ ስለሆነ፥ ሁላችንንም የሚያስተሳስረን እርሱ ነው። ፍቅር፥ ስላም እና አንድነትን በመንፈሳዊ ስልጣኔ ብንሻ፥ የማንደርስበት ሥፍራ፥ ፈልገን የማናገኘው ነገር አይኖርም። እግዚአብሔር እውነት ነው።

በመጥፎው መንፈስ ተከበናልና ዙሪያችንን፣

በጊዜ እንንቃ፤ ይገለጥ ዐይነ ልቡናችን።

ሰይጣን አይኖቻችንን ወደ ብልጭልጭ ነገሮች

ጆሮዎቻችንንም ወደ አሳሳች ውሸቶች፥

አእምሮአችንንም ለአለማዊ እሳቤዎች፥

አብራኮቻችን ሁሉ ለጊዜያዊ ግልጋሎት፤

እግዚአብሔር በፈጠረው ላይ ሥልጣኑን እንድናይለት፥

ስነ አመክኖአችንን ያወላግዳል፤

ስሜቶቻችንንም ሊቆጣጠር፥

የእርሱም ባሪያዎች ሆነን እንድንቀር፥

እግዚአብሔር የሰጠንን በጎ ፈቃድ ሊነጥቀን ይወዳል፤

የእርሱን እውነት መሳይ አሳሳች እውቀቶቹን ይሰብከናል፤
የእርሱን ጊዜያዊ ደስታን ይሰጠናል፤
የአምላካችንን ዘለአለማዊ ደስታ ያሳጣናል፤
የእርሱን ደስታ (ሃዘን መከራውን) ለኛ ሰጥቶ እርሱ በዚያ ይደሰታል፤
ከራር እንደሚከር፥ በእርሱ ቅኝት ይቃኘናል፤
የእርሱን ዘፈን (ግጭት፥ ስድብ፥ ውሸት፥ጦርነት..) ይዘፍነናል፤

እኛ ግን፥ ደስታን ካለቦታው ስንፈልግ አጣነው፣
የምንፈልገውን ነው ያላወቅነው።

የት ነው እውነተኛ ደስታ (ፍስሓ) የሚገኘው?
የሚያስደስተንስ ምንድነው?
ዘላቂና እውነተኛ ደስታን የሚሰጠን ማነው?[131]

የሚጠቅመንን ትተን፥ ስንፈልግ ማይጠቅመንን፥
በጊዜአዊነት ተጠመድን - ኑሮአችንን በአላስፈላጊ ነገሮች አጣበን፥
ስግብግብ - ምድራዊ ደስታን አሳዳጅ (pleasure monger) ተብለን፥
ሰማያዊ ፍቅር፥ ዘላቂ ሰላም (ፍሥሓ)፥
ለሕሊናችን ምግብ - እውነተኛ ደስታ አጣን።
ዐይነ ልቡናችንን በሚያሳውር ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ገባን፤
ልባዊ ሳቅና ጨዋታን ተነፈግን፤
እርስ በርሳችንም ተኮራርፈን - ሻኩራዎች ሆንን፤
እርስ በርስ መፈራራት፥ መነካከስና መበላላት፥
እንደ አውሬዎችም መገዳደል አብዝተን፥
ሃዘን፥ ጭንቀትና አለመደሰት ሆነ እድል ፈንታችን።

በምድራዊ የቴክኖሎጂ እድገት ጊዜአዊ ደስታን ፈልገን አገኘን፤
ይኸው ጊዜአዊ እድገት ሰማይ ላይ ሰቅሎ ከመሬት ፈጠፈጠን፤

---

131 “ዮም ፍሥሓ ሆነ በእንተ ልደታ ለማርያም” እመቤታችን ቅድስት ማርያም ልደትሽ ልደታችን ነው።

በፍቅር አልባ ሕይወት ምድሪቱ አልበቃ አለችን፤
የተትረፈረፈው ተፈጥሮአዊ ሃብት አጣላን፤
ከእርስ በርስ ሰዋዊ ግንኙነቶች አላቀቀን።

አብሮ የመኖር ምሥጢር፥ እንደ ገዳም አይነት የኑሮ ስርዓት፥
በመንፈሳዊ አንድነት  ማሕበራዊ ደስታና ፍቅር የበዛበት፤
ሁላቸውም በፍቅር ጥግትግት ብለው፥
የጋርዮሽ ሕይወትን ከአንድ መቅደስ ቀድተው፥
ከውስጥ ለየብቻ - ከውጪም በጋራ ልብስ (መንፈሳዊ) ተሸፋፍነው፥
በአንድ ገዳማዊ በቅዱሳን ስም ተጠርተው፥
እነርሱ እና እነርሱን ለሚመስሉ ጻድቃን ነው
እግዚአብሔር እውነተኛ ደስታውን ‘ሚሰጣቸው።[132]
የእኛነታችን መለዮ - መተሳሰራችን በፍቅር ሰንሰለት፥
ማህበራዊ ኑሮአችን - አንድነታችን፥
ኢትዮጵያዊነታችን - አብሮ የመሆን ጸጋ በሠፊዋ አገራችን፥
ይህ መልካሙ - ልዩ ጠባያችን፥
ተገንጥሎ ከሄደ ከላያችን፥ ባዶነት ነው ትርፋችን።

የገዳም አይነት ኑሮ - የጋራ ብልጽግና፥
የጋራ ደስታ (ፍሥሐ) በጋራ ሕይወት
በምድር እየኖሩ አለመከፋት፥
ይህ ነው ዘላቂና ዘለአለማዊ ደስታ - ታላቅ ስጦታ - የሚሰጥ ለሚሹት፤
ይህ ነው ጊዜአዊ ያልሆነ - እውነተኛ ደስታ - የሚገኝ በመንፈሳዊነት፤
ምድራዊ ያልሆነ - ሰማያዊ - የፈጣሪያችን በረከት።[133]

---

[132] “በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፤ የልብህንም መሻት ይሰጥሃል። መንገድህን ለእግዚአብሔር ግለጥ፤ በእርሱም ታመን፤ እርሱም ያደርግልሃል።” መዝ. 36፡ 4-5

[133] “የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ፤ ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብከኝ፤ በቀኝህም የዘለዓለም ፍሥሓ አለ።” መዝ. 15፡ 11



መጠበቅ እና መጠባብበቅ

## <u>መጠበቅ እና መጠባበቅ</u>

በምድራችን አንድ ትንሽ ልጅ እናትና አባቷን ከውጪ እስኪመጡላት ድረስ በጉጉት እንደምትጠባበቅ፥ በነቢያቶች ትንቢት መሠረት፥ የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት በናፍቆት የሚጠባበቁ ነበሩ። ለምሳሌ፡- ሳሙኤል ለአምስት መቶ ዓመታት

የክርስቶስን ከድንግል ማርያም መወለድ ሲጠባበቅ ነበር። ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መወልድና የሰውን ልጅ ከዘመነ ፍዳ ወደ ዘመን ድኅነት ማሸጋገር ጉዳይ በተደጋጋሚ የተነበዩ ነብያት ብዙሃን ናቸው።

ከንጉሥ ዳዊት ጀምሮ ብዙሃን ነብያት የተነበዩለት፥
የትንቢቱንም መፈጸም አለም የመሰከረለት፥
እንግዲህ ይህ ነው የእውነታ እና የስነ አመክንዮ ውህደት፥
የክርስቲያናዊነት መነሻው፥
ላለማመን የማይቻል ንጹህ ልብ ብሩህ አእመሮ ላለው።

ይህንን አንቀበልም አናምንም ብለው የቆዩትም፥
በጊዜ ውሰጥ አምነው ተቀብለዉ ስናያቸው፥
የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ከዚያ ተማርነው።

አንድ ሰዉ በልቡ ክፋት ከሌለዉ፥
ከሚያዉቁትም በላይ በመንፈስ ስለሚታየው፥
አለማወቁ እምነቱን አይገታው፤
የርሱ እውቀቱም እምነቱም የበላይ ነዉ የሚሆነዉ።

***"ሰው እናታችን ጽዮን ይላል፤***
***በውስጧም ሰው ተወለደ፤***
***እርሱ ራሱም መሠረታት" መዝ. 86፡5***



እናታችን

## **እናታችን**

ሰው እናታችን ይላል፤
በጉጉት ልጇንም በጉጉት ይናፍቃል፤
ሰው ጽዮንን ይጣራል፥

የሕጻኑን መወለድ ይጠባበቃል።

ናፍቆት የነቢያት ናፍቆት፥
ናፍቆትስ እንዴት አይናፈቅ?
ሰው ከፈጣሪው ሲታረቅ።

ሰው ናትና ጽዮን - ፈጣሪም ሰው ሲሆን፥
ትላንት መጥቶ ሄዷል አሉን፥
መመለሺያ ጊዜውን አላወቅን።
የመጠባበቂያችን ዑደት፤
እስኪወለድ ናፍቆት፥ እስኪመለስ ናፍቆት፤
ናፍቆትስ እንዴት አይናፈቅ፥
እውነተኛውን እስክናገኝ ስንጠብቅ፥
ለኛ ለበሽተኞች መድኃኒት፥
ናፍቆት የፍቅር ናፍቆት፥
ናፍቆት ለኛ ለኃጢአተኞች፥
ምድራዊነትም ላስጨነቀን ህመምተኞች።

ሰላም ለዝክረ ስምኪ፥
ዘመንከረ ጣዕሙ፥ ለወልድኪ አምሳለ ደሙ፤
መሠረተ ሕይወት ማርያም
ወጥንተ መድኃኒት ዘእምቀዲሙ፥
ኪያከ ሰናይተ ዘፈጠረ ለቤዛ አለሙ፤
እግዚአብሔር ይትባረክ
ወይትአኮት ስሙ።

## ***ያምላካችን እናት ለእኛም እናት ሆነችልን***

የእግዚአብሔርን ደግነት - በራሳችን ማየት የማንችለውን፥
የፈጣሪአችንንም ማንነት - በራሳችን መስማት የማንችለውን፥
ሁሉንም በመምህራችን በኢየሱስ ክርስቶስ አየነው ሰማነው፤

ይህንን ያዩ አይኖቻችን፥ የሰሙም ጆሮዎቻችን ምንኛ እድለኞች ናቸው![134]

በአንድ ቦታ እንደተቀመጠ፥

በአንድ ሥፍራም እንደሚኖር፥

እንደዚያ አይደለም፥

የማርያምና የልጇ ነገር።

ማርያምና ልጇ አሉ፤

ይኖራሉ ለዘለአለም።

በሁሉም ሥፍራ ይገኛሉ፥

በአንድ ሥፍራ ብቻ አይደለም።

ምን አይነት አይን ነው የሚያያቸው?

እንዴትስ ችሎ ነው፥

የሰው አእምሮ የሚስላቸው?

በምድር እንደተከሰቱ ሄዱ፦

አሁንም - አሁንም እኛን ሰዎችን እንደወደዱ።

የፍቅራቸው ኃይል ቢያስገድደን፥

በጸሎት፥ በዝማሬ እንጣራለን፥

"እባካችሁ እዩን እንያችሁ - እዩን እንያችሁ" እያልን።

ይህም የዳዊት መዝሙር ትዝታን ጫረብን፦

*"...ታቦርና አርሞንኤም በስምህ ደስ ይላቸዋል፤ ስምህንም ያመሰግናሉ። መዝ. 88፡ 12*

የዚህ ጥቅስ ፍቺው ትርጓሜው፦

"እንዲህ ነው..." ብለው አስረዱን - ነገሩን - ብዙ ተረኩልን፤

እኛ ግን፥ ፍጹም ስላልገባን፥ እንዳው ዝም ብለን፤


---

[134] "እውነት እላችኋለሁ ብዙዎችን ነብያትና ጻድቃን እናንተ የምታዩትን ሊያዩ ተመኝተው አላዩም፤ እናንተ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ተመኝተው አልሰሙም።" ማቴ. 13፡ 17

የአለማወቃችንን ማወቅ በጉያችን አምቀን፥
እምነታችንን አጠናክርን፤
መቼም በአምላካችንና በመድኃኒታችን፥
በስሙ የማይደሰቱ ፍጡራን ከቶ አይኖሩም ብለን።
መሬት ስትርድ፥ ከከርሷ እሳት ስትተፋ፥
የጠፋው ሲገኝ፥ ያለው ሲጠፋ፥
እንቅስቃሴ በሂደት፥ ሲጮህ፥ ሲዘመር፥
የፍጡራን ሁሉ እልልታ ሰው ሲፈጠር፥
ሰው እንዴት ይችላል ሊረዳው - በዚች በሰባ ዓመታት እድሜው፥
ሥፍራና ጊዜን ቆርሶ ከዘለአለማዊው።
የሰው አእምሮ ማገናዘብ ባይቻለውም፥
በስሙ ደስ የሚላቸው *ታቦርና አርሞናኤም*፥
ምንጊዜም ደስ ይላቸዋል - ለደስታቸው ወደር የለውም።

*አቤቱ አምላካችን የአንተን እውነት እንድንገነዘብ፥ የሕይወታችንን ትርጉም እንድናውቅ፣ የፊትህንም ብርሃን እንድናይ፥ ዐይነ ልቡናችንን አብራልን፣ አሜን።*[135]

[135] ኤፌ. 1፡18፥ 2ኛ ቆሮ 4፡16...




## ያንን ጊዜ አንረሳውም

ጌታችንና መድኃኒታችን፥ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ሁሉን የያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የፈጠረ፥

እርሱ ራሱ በፈጠረው እጅ ተያዘ፤
ዓለም ሳይፈጠር ከአባቱ ጋር የነበረ፥
እራሱን ማዳን ሲችል፥ ለገዳዮቹ ታዘዘ።
አምላካችንን ያዙት፥ እያንገላቱም ወሰዱት፤
ከጲላጦስም ፊት አቀረቡት፤
"ይህ ሰው ኃጢአት ሰርቷልና ፍረድበት" አሉት።
ኃያል ንጉሥ፥ ሰማይና ምድርን የሚገዛ ጌታ፥
መሬት ወርዶ፥ ሲያስተምር፥
ሲፈውስ በመድከሙ ፋንታ፥
እንደ ወንጀለኛ ተንገላታ፤
እርሱም ኃይሉን፥ ማንነቱን በማሳወቅ ፋንታ፥
በፈቃዱ አንደበቱን ገታ።
ጲላጦስም አንዳች ጥፋት ስላላገኘበት፥
ሕዝቡን ተማጸነ በነጻ እንዲለቁት፤
ሕዝቡ ግን አስቸገሩት በጩኸት፤
"ስቀለው፥ ስቀለው" በማለት።
እርሱም የሕዝቡን ቁጣ የሚያበርድ መስሎት፥
በድጋሜ ተማጸነ፥ ክርስቶስን እንዲተዉት፦

"ይህንን ሰው መረመርኩት፥
ምንም ጥፋት አላገኘሁበት፤...
እንዳስለመድኳችሁ፥ በየዓመቱ አንድ እስረኛን መፍታት፥
ከባራባስና ከዚህ ሰው ማንን እንድምርላችሁ ነው የምትሹት?"

ሕዝቡም፥ "ባራባስን ማረው፥
ኢየሱስን ስቀለው" ብለው ፈረዱበት።
ጲላጦስ አልቻለም የሕዝቡን ፍላጎት ለመግታት፤
ቆርጠው ተነስተዋልና መድኃኒታችንን፥
አሰቃይተው ሊገሉት፤
ጲላጦስም እጁን ታጠበ ከሕዝቡ ፊት፤

“እኔ ከደሙ ንጹህ ነኝ” በማለት።

ፈራጅ በሆነ አምላክ ላይ፥ ሕዝቡ ፈረዱበት፤
በግርፋት አደከሙት፥ አቆሰሉት፥ አደሙት፤
በመስቀል ላይ አጋድመው፥ በምስማር ቸነከሩት፤
በእራሱ ላይ የእሾክ አክሊል ጫኑበት፤
በሁለት ወንበዴዎች መካከል ሰቀሉት፤
ቀለዱበት፥ አፌዙበት፥ ሰደቡት፥ ጎኑን በጦር ወጉት፤
“ተጠማሁ” ባለ ጊዜም፥ መራራ እሬት በሰፍነግ ነክረው ሰጡት።
ጌታችንና አምላካችን፥
እኛን ሊያድን
“ተፈፀመ” ብሎ ሞተ፥ ሄደ ወደ ሲዖል በር፤
ጥንትም ከሴቲቱ (ከሔዋን) ዘር፥
የኢየሱስ ከድንግል ማርያም መወለድ ተወስኖ ነበር።[136]
የሰይጣን እራስ ሲቀጠቀጥ፥[137]
የሰይጣን እጅ በኢየሱስ ሲታሰር፥
የቀድሞው እባብ ሲጣል[138]፥
እኛም ነፃ ወጣን ከእስር፤
“ተፈጸመ”።
ይህ ነው የእግዚአብሔር ቃል የማይሻር፥

ኢየሱስ ክርስቶስ - በዚያች ሌሊት፥ ተንበርክኮ በጸሎት፥
ያውቅ ስለነበር ሁሉን ነገር፥

---

[136] “በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል፥ ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኮናውን ትነድፋለህ።” ዘፍ. 3፡15

[137] “...የብዙዎችን ራሶች ይቀጠቅጣል፡፡” መዝ. 109፡6

[138] “..ዲያቢሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ፥ እርሱም የቀድሞው እባብ ተጣለ፥...የመሲሁም ሥልጣን ሆነች...”ዮሐ ራዕ. 12፡10

“የአንተ ፈቃድ ይሁን” አለ፥
የእግዚአብሔርን ፍቅር ሲያበስር።
ሕዝቡን ለመታደግ የተወለደ፥[139]
ኢየሱስ ነጻ አወጣን፤[140]
በሞቱና በትንሳኤው ልዋጭ፥
አለሙን ድል ነሳልን፤[141]
ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥
ሕመማችን በሕመሙ ለወጠልን፤[142]
በስቅላቱ ተቀደስን፤[143]
በደሙ ድኅነትን አገኘን።[144]

---

[139] “ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች፥..” ኢሳ. 7፡14


[140] “ሕዝብህን ለመታደግ፥ የቀባኸውንም ለማዳን ወጣህ።....” ዕንባቆም 3፡13

[141] “...ጽኑ፤ እኔ አለሙን ድል ነስቼዋለሁና።” ዮሐ. 16፡33

[142] “..እርሱ ግን ስለ ኃጢአታችን ቆሰለ፥ ስለ በደላችንም ታመመ፥ የሰላማችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን።” ኢሳ. 53፡5

[143] “ስለዚህ ኢየሱስ ሕዝቡን በደሙ ይቀድሳቸው ዘንድ ከከተማ ውጪ ተሰቀለ።” ዕብ. 13፡12

[144] “በእርሱም እንደ ቸርነቱ ብዛት፥ በደሙ ድኅነትን አገኘን፥ ኃጢአታችንም ተሰረየልን።” ኤፌ. 1፡7




## ዝማሬ ሰማያት

በ5ኛው ምእተ ዓመት፥ አክሱማዊው (ኢትዮጵያዊው) ቅዱስ ካሌብ፥
ወደ ናግራ (የመን) ዘመተ ክርስቲያኖችን ለማዳን ከአይሁዳዊው ንጉስ ፥
የክርስቲያን ሀገር በኢትዮጵያ እንዲጽና አደረገ አሸንፎ ሲመለስ።
ለእግዚአብሔር በገባውም ቃል ኪዳን መሠረት፤

መንኖ ገዳም ገባ ሥልጣኑን ለልጁ ተወለት።
ልጁ አጼ ገብረመስቀልም ከቅዱስ ያሬድ ጋራ በአንድነት፥
ኢትዮጵያን አሠለጠኗት ቅድስት የክርስቲያን ሀገር አድረጓት።

ዋይ ዜማ - ውይ ዜማ፥
ምድር ያላየችው፥ ለጆሮ 'ሚስማማ፥
መንፈስን የሚያድስ፥ ልብን የሚያረካ፥
ዋይ ዜማ - ውይ ዜማ
ከሰማይ የመጣ፥ ገጸ በረከት ለኢትዮጵያ።

ዋይ ዜማ የፍቅር አይነት የሚዘመር፥ ጥዑም ዜማ ሰማያዊ፤
የጸሎት አይነት የሚቀደስ፥ ሁሉን አቀፍ መንፈሳዊ።
የምስጋና አይነት የሚወደስ፥ የሃሴት አይነት የሚያስደስት፥
ከቅዱስ ያሬድ የተገኘ ገጸ በረከት።

*"ዋይ ዜማ ዘሰማዕኩ በሰማይ እመላእክት ቅዱሳን እንዘ ይብሉ፡-*
*ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር መልአ ሰማያተ ወምድረ ቅዱሳተ ስብሐቲከ..."*።[145]

የኢትዮጵያ ዜማ - ምንጩ ከግዕዝ፥ ከዕዝል እና ከአራራይ፥
ሁሉም የተቀዳ ከኢትዮጵያ ሰማይ፥
የቤተ ክርስቲያን ደወል ሲደወል፥
ከበሮ ሲመታ፥ ቃጭሉም ሲያቃጭል፥
የውስጡን ዜማ የውጪው ሲቀበል፥
አዝማሪም ቅኝቱን ሲያስተካክል፥
በማሲንቆ፥ በክራር፥ በዋሽንት፥
አይ የኛ ነገር፡- የሁለመናችን ምንጩ ቤተ ክርስቲያን፥
መጀመሪያችን ጥምቀት፥ መጨረሻችን ፍትሃት።

አንቺ ኢትዮጵያ እጅጉን የታደልሽ፥
ምድራዊ ምግብ ቢያንስሽ፥
የማይጠገብ የማይሰለች፥ ሰማያዊ ምግብ አልተለየሽ፤

---

145 ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ

ይኸው እየበላሽ እየጠጣሽ፥ በመንፈስሽ ፋፍተሽ አምሮብሽ፥
አምረሽ፥ ድምቅ ብለሽ ትታዩያለሽ፥
እግዚአብሔር ያዝልቅልሽ።

## *መደምደሚያ*

*የሚሆነው ይሆናል፣ መሥራት ያለበት ኃጢአት ይሠራል፤*
*መንገሥም ያለበት ሰይጣን ይነግሣል።*
*ግን ጊዜን ጊዜ ይሽረዋል፤*
*ንጉሳችን አምላካችን ክርስቶስ ተመልሶ ይመጣል፤*
*የሰይጣንን ወንበር ይሰባብረዋል፤*
*የእግዚአብሔር ፈቃድ*
*በምድራችን ይሆናል።*

*ሲንቀጠቀጥ መሬት፥*
*ከመቀመጫ ቁጭ ብድግ የሚያደርግ፥*
*ተነስቶ መራመድ፥ መተኛትም እስኪያቅት፥*
*መሬቱ ሲያነጥር፥*
*የተቀመጥንበት፥ የቆምንበት፥ መሬት ሲርድ፥*
*ይህንንም በመቁጠር እንደ ቅጣት፥*
*አይቋረጥ የዘወትር ጸሎት፤*
*ይነጋል - ቢመሽም፤*
*ጨለማ ብርሃንን አያጠፋውም - አይውጠውም፤*
*ብርሃን ግን፥  ጨለማን ያጠፋዋል፤ ይውጠዋል።*
*ከጠፈራዊ ሕግ ወጥቶ ማን - ምን ማድረግ ይችላል?*

*ተመስገን፤ በኃይለ መስቀሉ እንደተጠበቅን፤*
*የ"አንድ ኣድርገን" ጸሎታችንን የሚሰማን፣*
*የፈጠረን አምላካችን ጠብቆ ከዚህ አደረስን።*

*እኛም እንጠብቃለን እኛነታችንን፤*
*በሚገባ እንከውናለን ኃላፊነታችንን፤*

ስለዚህ፥ ሸብረክ አንልም ከመንፈሳዊ አላማችን።

# ምዕራፍ አምስት

## የሰው ብርታቱ ከመንፈሱ



## መግቢያ

ተጋድሎ ይባላል፥ ትግል ከማይታየው፥
ምድራዊነትን ከዶ፥ በልዩ ዓለም ለሚኖረው።
የባህታውያን ተጋድሎ፥ ስውር ትግል፥
ነወይ? አንድም ቅራኔን ከራስ ለማቃለል።
ምንድነው ይህ መንፈሳዊ ሥልጣኔ?
ምድሪቷን የሚያስከድ በምናኔ።
ለመንፈሳዊም ቢሆን ለአለማዊ፥
እነሆ አንድ ታሪክ፡-
ስለ አንድ መነኩሴ፥ ገብረ ክርስቶስ የተባሉ ባህታዊ፥
አል ሃበሺ፥ አብደል መሲህም ብለው የሚጠሯቸው አረጋዊ፥
በ1898 የተወለዱ፥ አንድ ምስኪን ኤርትራዊ/ኢትዮጵያዊ።
ቅራኔዎችና ትግሎች ናቸውና ከዚህ ያደረሱን፥
እስቲ ይህንንም ታሪክ እንመርምረው፥ በጥቅሉም ቢሆን፥
ለመንፈሳዊ ብርታታችን፥ ለተስፋችንም እንዲሆነን።
አካለዊው የሰው ጥንካሬ ከእምነቱ ጋር መያያዙን፥
በግልጽ ለማየት ከበቁ ግብጻውያን፥
በደዊ ከተባሉ የበረሃ ነዋሪዎች፥
እንዲሁም ኢትዮጵያውያኖች፥
ታሪካቸውን በዝርዝር ጽፈው ካቆዩልን ተቆርቋሪዎች፥
የተነገረን ከመነኮሳት፥ ከዶክተሮች፥ እንዲሁም ከፕሮቴስታንቶች።[146]

[146] የፕሮቴስታንት ተከታይ ከሆኑት ከዶክተር ኦቶ ሜይናሩድስ ከጻፉት፡- "The personality of Abuna Abd el-Mesih reveals many characteristics of Oriental psychology, and it is not easy for the Western Christian to understand the dynamics of this solitary monk. That these however, are real, …" Bishop Macarius H.G., 2009. pp.123

## የገብረ ክርስቶስ ተጋድሎ

አብደል መሲህ (ገብረ ክርስቶስ ) ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ፥
ትውልዱ ከኤርትራ፥
ባራሙስ ወደሚባል የግብጾች ገዳም መንገዱን አመራ።
ጥንትም በኢትዮጵያ ገዳም የኖረ፥
ከሃብታም ቤተሰቦች የበቀለ፥
ለርሱ የሚስማማውን ሲፈልግ፥
ከቤተ ዘመዶቹ ሁሉ ተነጠለ፤
ገብርዬ ሁሉን ትቶ ወደ ሱዳን ኮበለለ።
ከሱዳን ጠረፍ ወታደሮች ቢያገኙት፥
አልቻሉም ሊከለክሉት፥
እንዳይሄድ ቀልቡ ወዳረፈበት፤
በረሃውን ሲያቋርጥ በረሃብና በውሃ ጥም፥
ተስፋ ቆርጦ ወደኋላው ዞር አላለም።

ከባራሙስ ገዳም እንደደረሰ፥ ሲገናኝ ከሽኑዳው፥
ሃሳቡን በቶሎ እንዲረዱለት በጸሎት ነበር የጀመረው።
"ባህታዊ፥ መነኩሴ ነኝ" ማለት ራስን ከፍ ማድረግ መስሎት፥
ሽኑዳውን ቢጠይቅ በገዳሙ ኑሮ እንዲፈቅዱለት፥
"ይህ ገዳም ለመነኮሳት ብቻ ነው" አሉት።
እርሱም፡- "ታዲያ ለመመንኮስ የፈለገ ወዴት ይሂድ?" ቢላቸው፥
ቶሎ አንብበው ገባቸው፥ መንፈሱን በመንፈሳቸው፤
ሳያመነቱ ፈቀዱለት፥ "እንደፍላጎትህ ይሁንልህ" ብለው።

ገብርዬ ከባራሙስ ገዳም ገብቶ፥
ለዓመታት ሲያገለግል አንገቱን ደፍቶ፥
ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል፥ በጾም በጸሎት ተግቶ፥
የገብርዬ እጅግ ሲያይል መንፈሳዊ ጥንካሬው፥
ሥጋ ሰውነቱን ተራምዶት ሄደ እርሱ ሳያስበው፤
የገዳሙም ኑሮ አልበቃህ አለው፤

በዋሻ ውስጥ የብቸኛ ገዳም አሰኘው።

አዎ! የሰውን ተፈጥሮ ብርቱ የሚያደርገው፥
ከመንፈሱ እንጂ አይደለም ከጡንቻው።
ገብርዬ ሳያጓድል የገዳሙን ሥርዓት፥
እየሠራ፥ በቃሉ እየደገመ፥ እየጸለየ ከኖረበት፥
በአክብሮት ቢጠይቅ ከገዳሙ ለመውጣት፥
"አይሆንም፥ ከዚህ ገዳም አትወጣም፥
በረሃ ከገባህ ትሞታለህ.." አሉት።
እርሱ ግን አሸንፏቸው ሄደ፥ ከገዳሙ ወጥቶ፥
ከዋሻ መኖርን ጀመረ፥ የብቸኛ ገዳምን መሥርቶ።

ጥንትም በሥጋው ሞቶ በመንፈሱ መኖሩን ያላወቁ፥
አውሬ ይበላዋል ብለው እጅግ ተሳቀቁ።
ገዳም እየገቡ፥ ከዛም እየወጡ የሚያስተምሩ፥
እንደ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ የተከበሩ፥
አንድ ነገር ብቻ በጽንአት ያስተምራሉ፥
"እናንት ጳጳሳት፥ መነኮሳት፥
በልብስ ደምቃችሁ አትታዩ፥
ምድራዊነታችሁን ካዱ..." እያሉ።

በገንዘብ፥ በሃብት እና በንብረት፥
በአጠቃላይ በምድራዊነት ላይ የሙጥኝ አለማለት፥
ይህ ነበር ከገብረ ክርስቶስ የተሰጠ ታላቅ ትምህርት፥
መነኮሳት፥ ጳጳሳትም ከዋሻው ድረስ እየመጡ የተማሩት።
በምድራዊ ሕይወት ምንምነት፥
ለሰማይ አንዳችነት፥
ይህ ነበር የመነኩሴው ሃይማኖታዊ ርዕዮት።

ለገብርዬ ገንዘብ ቢሰጧቸው፥
ለበረሃ መንገደኞች ያከፋፍላሉ፥
የዳቦ ፍርፋሪ ከአውሬዎች ጋር አብረው ይበላሉ።

አውሬዎችን ያስተናግዳሉ፥ እባቦችን ያቅፋሉ፥
እንስሳቱም እንዲህ ከሰው ፍቅርን ሲቀበሉ፥
እነርሱም በተለየ መንገድ ያፈቅራሉ።
　　“ለዋሻዎ መዝጊያ ይበጅለት፥
　　ተኩላዎች እየገቡ ይቸገራሉ...” ሲባሉ፥
　　“እኔም እኮ ተኩላ ነኝ” ይላሉ።
ገብረ ክርስቶስ የሥጋ ሕመም ሲሰማቸው፥
እንስሶች ነበሩ ጠያቂዎቻቸው፥
ዝንጀሮዎችም በሕብረት አድመው፥
ከተፈጥሮ ሁሉ ጋር ተነጋግረው?
ይመክሩ ነበር (?) ዶክተሮች መጥተው እንዲወስዷቸው?
　　አባ ገብረ ክርስቶስ በአባትነት ታውቀው፥
　　መጽሐፍ ቅዱስን ሲወጡት በቃላቸው፥
　　ጸሎት ልብሳቸው፥ ጸሎት ምግባቸው።
የባራሙስ መነኮሳት፡- “እባክዎት ይመገቡ” እያሉ ቢማጠኗቸው፥
“መጋቢዬ እግዚአብሔር ነው፤ አታስቸግሩኝ፤..” ነበር የሚሏቸው።
“ለጤንነትዎ ሲሉ ይመገቡ፥ አለዚያ ይታመማሉ..” ሲሏቸው፥
“ሲያመኝ እግዚአብሔር ይጠብቀኛል፤
የበለጠም ይባርከኛል” ነበር መልሳቸው።
　　ሰዎች በከንቱ ተጨነቁላቸው፥
　　እያለ፥ ከጎናቸው፥ የሚያረጋጋቸው - ውስጣዊው ሰላማቸው።
ያማረ ልብስ ቢልኩላቸው፥
በመቀስ ቆራረጡት፥ “ቀጭን ልብስ” ለኔ አይገባም ብለው፥[147]
አባ ቄርሎስ አርባ ፓውንድ ቢሰጧቸው፥
ወዲያው ለአሽከሮቻቸው አከፋፈሏቸው፥

---

147 “ወይስ ምን ልታዩ ወጥታችኋል? ቀጭን ልብስ የለበሰ ሰውን ነውን? እነሆ ቀጭን ልብስ የሚለብሱስ በነገሥታት ቤቶች አሉ።” ማቴ. 11፡8

“እኔስ ከአርባ ጋኔሎች ጋር አንድ ቀን አላድርም..” ብለው።

ይህንን እና የመሳሰሉትን ድርጊቶቻቸውን፥
በምድራዊ ዓይን ለተመለከተው፥
ፍጹም ሞኝነት ነው የሚመስለው።

አዎ! ይህንን ይመስላል ገድል፤
ከማይታይ ባላጋራ ትግል፥
በአሸናፊነት ምድራዊ ክፍያ የማይገኝበት፥
ግን ሰማያዊ ደስታን የሚሰጥ፥
በመንፈሳዊ አይን ለሚመለከት።

ቁስም ቢሆን ወታደር፥
የልቡን ጥሩነት ያይለታል እግዚአብሔር።
ባህታዊነት ባይሰጥም ለሁላችን፥
መንፈሳዊ ተጋድሎ አልቀረልን፥
ከክፋት ጋር እየታገልን፥ በቀን ተቀን ኑሮአችን።

አባ ገብረ ክርስቶስ የብቸኛ ገዳም መሥርተው፥
ለ36 ዓመታት በግብጽ ዋሻ ውስጥ ኖረው፥
እየጾሙና እየጸለዩ፥ ከተፈጥሮም ጋር ስምም ሆነው፥
ግን ይህ ሥፍራ እንዳይሆን በስተእርጅና
መሞቺያና መቀበሪያቸው፥
እጅግ ተቸገሩ፥ በየቀኑ ኢየሩሳሌም እየታያቸው።

ከግብጽ ወደ እስራኤል ለመግባት፥
መጥፎ ስለነበረ ጊዜው፥
ስላልበረደ የአረቦችና የእስራኤሎች ግጭቶቻቸው፥
ጳጳሳቱና የኢትዮጵያ ኢምባሲም ተባብረው፥
እንደምንም ሊባኖስ እንዲገቡ ረዷቸው።
ከዚያም ሦሪያን አቋርጠው፥
ምናልባትም በዮርዳኖስ ዘልቀው፥
ከኢየሩሳሌም ሳይገቡ አልቀረም ተብሎ ነው የሚወራው።

በትንሹ እየበላ፥ በትንሹም እየጠጣ፥
ከአውሬዎች ጋርም እየተነጋገረ ከዋሻው ሲወጣ፥
“ይህ መነኩሴ የት ገባ?” እያሉ ሰዎች ይንጫጫሉ፥
ግብጻውያን መነኮሳት፥ ጳጳሳቱም ይጸልያሉ፥
ሞቶ ተቀብሮም ከሆነ፥ መቃብሩን ለማየት ይጓጓሉ፥
እግዚአብሔር እውነቱን እንዲገልጥላቸው ይማጸናሉ።

ኦ! አብዱል መሲህ፥ አብዱል መሲህ፥
እባክህ አጫውተኝ ልጠይቅህ፥
ከትውልድ አገርህ ከኤርትራ ወጥተህ፥
በኢትዮጵያ ገዳማት ተመላልሰህ፥
ከሱዳን በረሃ ተሻግረህ፥
በግብጾች አገር ከባራሙስ ገዳም ሰንብተህ፥
ከዚያም ወጥተህ፥ ከዋሻ ገብተህ፥
የብቸኛ ገዳምን መርጠህ፥
ረቂቅ የሆነ መንፈሳዊ ተጋድሎህን ፈጸምህ።
እንግዲህ ምንድነው ይህ ያንተ ሃይማኖት፥
ምንድነው ይህ - በተለይም ያንተ - የባህታዊነትህ፥
የእምነትህም መመሪያ፥
ምንድነው መሳሪያው ምድራዊነትን መግደያ፥
ምንድነው ይህ መነኩሴነት ወደ እግዚአብሔር መቅረቢያ።
ምንድነው ገዳም፥ ይህ አምባ መሸሸጊያ፥
ምንድነው ይህ ሥፍራ፥ የሰውን መንፈስ መቀየሪያ፥
አዲሱን ሰው መፍጠሪያ።
እባክህ ተጠየቅ ልጠይቅህ፡-
የብቸኝነትህ ምሥጢሩ ምንድነው፥
ረሃብና ጥማቱንስ እንዴት ቻልከው?
አውሬዎችን በምን ቋንቋ አናገርካቸው?
ከየት አገኘኸው ይህንን ታላቅ የፍቅር ስበት፥

ተናካሽ የዱር አራዊትን በፍቅር የሚጎትት፥
ተስማምቶ ኑሮ ከመላው የእግዚአብሔር ፍጥረት።
አዎ! እንግዲህ መሆኑ ነዋ!
ላመኑበት ዋሻም የሚሆን ቤት፥
በፍቅር ከያዙት፥ አውሬም የሚሆን ጎረቤት።
አንተ መነኩሴ፥ በህመምህ የምትደሰት ጤነኛ፥
በመራብህ የማትደከም ጉልበተኛ፥
የእንስሳት ፍቅረኛ፥
የፍጥረታት ጓደኛ።
ምንድነው ይህ ጉዳይ፥
ለሰው ሁሉ የማይታይ፥
በድህነትህ የሚያስከብርህ፥
ምንም ሳይኖርህ ሁሉን ያገኘህ፥
በሄድክበት ተፈጥሮ የታቀፈህ።
ምንድነው ይህ የመነኮሳት ሕይወት?
እንዲህ ለሰው ልጅ ጥንካሬን የሚሰጥ እምነት።
ይህ ኑሮ የባህታውያን፥ የመነኮሳት፥
የሰው ናሙና፥
ለሚያዩት ብቻ የሚታይ በምሳሌያዊነት፥
በጣት ቆንጥረው የሚወስዱት።
የትና የት ናቸው እነኚህ ሁለት አለማት?
እንዲህ ቅርብ ነወይ? ሰማያዊው አለም ለሚቀርቡት?
ይቻላል ወይ እንዲህ?
ሥጋዊነትን ሙሉ በሙሉ መተካት፥ በመንፈሳዊነት።
አዎ! ሐዋርያው ጳውሎስም፡-
"ሰውነቴን አስጨንቃታለሁ፥
ሥጋዬንም አስገዛዋለሁ.." ሲል፥..1ኛ ቆሮ. 9፡27
ይህና ይህንን የመሳሰለ ገድል አስፈልጓል።

ትግል፥ አስፈልጓል ከምድራዊነት ተጽንኦ የሚያስወጣ፥
በሥልጣን ጥም ሰላምን ከሚነሳ፥
በሃብትና በንብረት ከሚያስመካ፥
አዎ! ትግል አስፈልጓል፥
የምድሪቱንም መንፈሳዊ ህልውና ከሚነሳ፥
በምድራዊ እውቀት፥ ፍቅር በጎደለበት፥
የሰዎች ኑሮ ሂደት፥ ሲያመራ ወደ ጥፋት፥
ትግል፥ ከራስም ከተፈጥሮም ጋር  ከሚያጣላ፥ የውስጥ ጠላት።
ገድል፥ በግልጽ የማይታይ ትግል፥
ትግል አስፈልጓል፥ ለመንፈሳዊ ጥንካሬ፥ ገድል የሚሉት፥
ሰው በመንፈሱ ሲጠነክር ራሱ መንፈስ እንደሚሆን አይነት።



ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት

## ጻዲቁ አባት ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት

ጻዲቁ አባታችን ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በብዙ የኢትዮጲያን ሥፍራዎች በመመላለስ፥ በወንጌል ትምህርት እያስተማሩ ወደ ክርስትና ሕይወት የመለሱ ቅዱስ አባት ናቸው። አንድ ሰው ክርስቲያን ሆኖ እንዲህ እንደርሳቸው ለደግ ሥራ ቢተጋ፥

ሁሉን ማደረግ እንዲቻለው፥ ልዩ መንፈሳዊ ኃይልም እንደሚያገኝ (እንደሚሰጠው) ከእርሳቸው የሕይወት ገድል መረዳት ይቻላል።

ቅዱሱ አባት አቡነ ተክለ ሃይማኖት "አትታበዩ፥. ወዳሴ ከንቱንም አትመኙ፥ እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ...." እያሉ፥ አምልኮተ ጣኦታትን ከህብረተሰቡ ያስወገዱ፥ በሰዎች እያደሩ የሚያስጨንቋቸውን ክፉ መናፍስትን እያሳድዱ፥ ለሕብረተሰቡ ወንጌልን በመስበክ፥ ወደ ክርስትና ሃይማኖት እየመለሱ የሚያጠምቁ፤ ለነፍሳቸው እንጂ ለሥጋቸው ያልኖሩ፥ ሰው በዐይነ ሥጋ እንደሚመለከታቸው ሳይሆን ከላይ ከሰማይ በተሰጣቸው የእግዚአብሔር ጸጋ የኖሩ ናቸው። እኚህን ቅዱስ አባት መምሰል ማለት በምድራዊነት ከሚገኝ ጥቅማጥቅም ገሸሽ ብሎ ሰማያዊውን ሕይወት መገንባት ይሆናል።

እኛ ቅዱሳኑን ብንመስላቸው በመልካም ሥራቸው ምሳሌ ብናደርጋቸው፥ እነርሱን በማስታወስ ከክፉ ሥራ እንቆጠባለን። መንፈሳዊ ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን እነርሱ በሚያሳዩን አቅጣጫ ብንመራ፥ ምድራዊ መሰናክሎችን በቀላሉ በማለፍ ወደ ፈጣሪያችን እንጠጋለን።

ከቅዱሳን ገድል፥ እንደየአቅማችን የመሰለንን ብንቀበል፥ በእርግጠኝነት በመንፈሳዊ ሕይወት እናተርፋለን እንጂ አናጎድልም፤ እንጠቀማለን እንጂ አንጎዳም።

ቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት በ12ኛ መቶ ዓመት፥
በደብረ ዳሞ ገዳም (ትግራይ) ቆይተው ለአንድ አመት፥
ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ
ከገደሉ ቁልቁል ሲወርዱ፥
ወገባቸውን ታሥረው በገመድ፥
ገመዱ ተበጠሰ በድንገት፥
የአምላካችን ፈቃዱ አይደለምና፥
ሕይወታቸው ያልፍ ዘንድ በዚያን ወቅት፥
እንዳይሞቱ፥ እንዳይቆስሉም መሬት ወድቀው፥
በአየር ላይ እንዳሉ የጸጋ ክንፎች ተሰጣቸው፥
ኢየሩሳሌምም ደርሰው ሲመለሱ፥
"እኛ መነኩሴ መጡ ክንፍ የተሰጣቸው" እየተባሉ ሲወደሱ፥
ይህንን ውዳሴ ከንቱ በመጥላታቸው፥
ወደ ደቡብ ዘመቱ የወደዱትን ገዳም ትተው፤

ከዚያም የወንጌል ሥራቸውን ተያያዙት።
የደቡብን ሕዝብ ጣኦታቱን እያስጣሉ አጠመቁት - ክርስቲያን አደረጉት.
ቤተ ክርስቲያናትን እያሠሩ አስገቡ ታቦታቱን፤
ይህ ሥራቸው ግብጽ አገር ገነነ እጅጉን።
አቡነ ቄርሎስም የፓትሪያርክነትን ሥልጣን ፈልገውት ሳለ፥
ፈቅደው ነበር ሊሰጧቸው ለአባታችን፥
ሙሉ ኢትዮጵያን - ባይሆንም የደቡቡን፥
አባታችንስ የሥልጣን ፍላጎት የላቸው፣
ምድራዊነትን በቃኝ ብለው፥
የመነኑ ቅዱስ አባት ናቸው።

**<u>አጭር ታሪክ</u>**

በታህሳስ ወር በሃያ አራት፥
ከአባቱ ከጸጋ ዘአብ እና ከእናቱ ከእግዚእ ሃረያ
ተወለደ አንድ ሕጻን፥
መጠሪያ ስሙ ፍስሐ ጽዮን።
ካደገ በኋላ በጉልምስናው ወቅት፥
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገለጠለት።
የኢትዮጵያ ሐዋርያም ይሆን ዘንድ፥
ሹመትን ሰጠው እንዲህ በማለት፦
"የኃጢአተኞችን ነፍስ የምታጠምድ፥
ወደ ሕይወትም የምትመራ፥ እንደ ኤርምያስና አጥማቂው ዮሐንስ ትሆናለህ፤
ከአሁን በኋላም፥ ተክለ ሃይማኖት ተብለህ ትጠራለህ፤
ርኩሳን አጋንንትን ታሳድዳለህ፤
በሽተኞችን ትፈውሳለህ..።"[148]

ተክልዬ ይህንን ከፈጣሪው እንደሰማ፥ ወደ ቤቱ ፈጥኖ ገሰገሰ፤

---

[148] ከግድላቸው የተወሰደ።

ሃብቱን ንብረቱን ሁሉ ለድሆች ለገሰ፤
ቤቱን ክፍቱን ትቶ እንደወጣም አልተመለሰ፤
ግዳጁንም በመፈጸም ተክልዮ ለኢትዮጵያ የሠራው፥
ውለታው ብዙ ነው በገድሉ የተጻፈው።[149]

አቡነ ተክለ ሃይማኖት እንደኛ ሰው ናቸው፤
ግን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ስላናገራቸው፥
በልዩ ተልዕኮ መንፈሳዊ ኃይል ስለተሰጣቸው፥
ከምድራውያን ፍጹም የተለዩ ቅዱስ አባት ናቸው።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሲጾሙ ሲጸልዩ፥ እስኪቆስል ሥጋቸው፥
ሳይሞቱ ሥጋቸውን ከምድራዊነት አላቀው፥
በነሐሴ 24 አረፉ፥ በንዳድ በሽታ ታመው፤
በተወለዱ በ99 ዓመታቸው።


እግዚአብሔር ለተክልዩ የጸጋ ክንፎች ቢሰጣቸው፥
ለእኛም አስቦልን እንደሆነ ይታወቃል - ከታሪካቸው፤
አሁንም አልተለየንምና - የእርሳቸው ጾምና ጸሎት - በረከታቸው።

**“ቅዱሳኑን”** እግዚአብሔር ስለሚወዳቸው፥
ለእኛም ተክልዩን ሰጠን እንድንመስላቸው።
ቅዱሳኑን “**ምሰሏቸው**” መባላችንንም አንርሳው።[150]

---

[149] አቡነ ተክለ ሃይማኖት በነበሩበት በዚያን ዘመን፥ መነኮሳቱ ምድራዊ (ሥጋዊ) ሰውነታቸውን ከመርሳታቸው (ከመልቀቃቸው) የተነሳ፥ የየግል ጾታቸውን እስከ መርሳትና፥ ወንዱም ሴቱም ካለ ልዩነት ከአንድ ሥፍራ ቆመው እንደሚጸልዩ ከገድላቸው ተጽፏል።

[150] የእግዚአብሔር ቃል የነገሯችሁን መምህሮቻችሁን አስቡ፤ መልካም ጠባያቸውን አይታችሁ በእምነት ምሰሏቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናና ዛሬ እስከ ዘለአለም የሚኖር እርሱ ነውና። ዕብ.13፡7-8




## የበረሃዋ እመቤት

እነሆ! አንድ ምሳሌ ከቅዱሱ መጽሐፋችን፥
ምሳሌነቱ፡- ትኩረት በራስ ላይ ብቻ እንዳይሆን፥
የአገር ፍቅር - ሕብረት - አንድነት እንዲኖረን፤
ምንጊዜም እንድናስብ ለአገራችን - ለወገናችን።

ሱቱኤል የተባለ ዕዝራ ከዱር ከበረሃ ሲንከራተት፥[151]
የተፈጥሮን ነገር ሲያሰላስል፥ ሱባኤ በመግባት፥
በሃሳቡም ከእግዚአብሔር ጋር ሲሟገት፥
በድንገት ታየቸው አንዲት ቆንጆ ሴት፤
ያዘነች - የተከዘች - ቆንጆ - የተዋበች እመቤት፥
ጎስቆል ብላ፥ ቀሚሷንም ቀዳ፥
እያነበነበች ታለቅሳለች፥ ምርር ብላ በጩኸት፥
ዕዝራም ከሩቅ አይቷት በችኮላ ተጠጋት፥
እንዲህም ብሎ ጠየቃት፡-

“ለምን ታለቅሺያለሽ? ምን ሆነሽ ነው የኔ እመቤት?
ምክንያቱን ነገሪኝ፥ ከዚህ ምን አመጣሽ ድንገት፥
እንኳን ሰው የዱር አውሬም ከማይታይበት።”

እርሷም ልቅሶዋን ሳታቋርጥ መለሰችለት፥ እየተነፋረቀች።
“ሃዘኔስ እጅግ ከባድ ነው፥
ከሰው የተፈጠረ የማይችለው፤
ከዘመድ ከወዳጅ ኮብልዬ ከዚህ እንደመጣሁ፥
እንዲሁ እንደምታየኝ እንባዬን እያፈሰስኩ አለሁ።
እባክህን ተወኝ!” አለቺው፥
“ተወኝ ላልቅስበት” ብላ ተማጸነችው።

ዕዝራም መልሶ፡- “ተይ አታስጨንቂኝ፥
የሆንሺውን ንገሪኝ፤
ባታውቂኝ፥ ባላውቅሽም ወገንሽ ነኝ።
እባክሽን ንገሪኝ እባክሽን፥
አካፍሊኝ ጭንቀትሽን፥

---

[151] መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል - ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መፅሐፍ ቅዱስ - ተጨማሪ (ዲዮትሮካኖኒካል)

እባክሽ ንገሪኝ የሆንሺውን።”
ሴቲቱም ተናገረች እንባ እየተናነቃት፡-
“መካን በነበርኩበት ዘመን ሁሉ፥ ለሰላሳ ዓመታት፥
ፈጣሪዬን ሳላቋርጥ አጥብቄ ለመንኩት፤
ልጅ እንዲሰጠኝ ብቻ ነበር የኔ ጸሎት፤
እግዚአብሔር ድካሜን አየልኝ፤
ጸሎቴንም ሰማኝ፤
እጅግ ያማረ ወንድ ልጅ ሰጠኝ።
እኔም ልጄን አሳደግሁ፥
ልክ እንደራሴው ነፍስ፥ እየተንከባከብሁ።
ለአቅመ አዳምም ሲደርስ፥
ሚስት አጋባቼው፥ ሲለኝ ደስ ደስ፥
ሠርግ ደግሼ፥ በታላቅ ድግስ፥
በዛች ባንድ ቀን በጫጉላው ሰዓት፥
ወድቆ ሞተብኝ፥ በድንገት።
ይኸውልህ፥ የኔ ጌታ! ስማኝ፥
ውዱ ልጄ እንዲህ ሳላስበው፥ ድንገት ሲሞትብኝ፥
እኔም የሞትኩ ነበር የመሰለኝ፤
ታዲያ፥ አለአሞቴ ሲገባኝ፥
በልቅሶ ብዛት ነፍሴን ሳትኩኝ፤
ወገኖቼም ብዙ ደከሙ ሊያረጋጉኝ፤
በቃሽ፥ በቃሽ እያሉ ሲጨቀጭቁኝ፥
በንዴት ብዛት ራሴ ዞረብኝ።
ግን የነርሱ ምክር፥ ሃዘናቸውም ሲሰማኝ፥
ተለይቻቸው መጥፋትን አሰኘኝ።
እህህህህ!....ልጄ ሲሞት፥ የኔም ሕይወት ተሰበረ፥
ልቅሶዬ ጩኸት ሆነ፥ ልቤ በሃዘን መረረ።
ለብቻዬ ሆኜ ማዘንን ስ - ለ - መ - ረ - ጥ - ሁ፥


ጨለማ ሲሆን ወ - ደ - ዚ - ህ በረሃ መ - ጣ - ሁ፤
ዳግመኛ ወደ አገሬ ላልመለስ ቆርጫለሁ፤
ሃዘኔን ለብቻዬ እንድወጣው፥ ከዚሁ ሆኜ አለቅሳለሁ፤
ከ -  ዚ - ሁ፥ ከ - በ - ረ - ሃ - ው፥ እየጾምኩ፥ እየጸለይኩ፥
እስከሞት ድረስ ከዚሁ ለመቆየት ወስኛለሁ።
ከእንግዲህ አያሻኝም ወዳጅ ዘመድ፥
ይህ ብቻ ነው፥ ልጄን በቶሎ ለማግኘት የሚረዳኝ መንገድ።”

የበረሃዋ እመቤት ይህንን ስትናገር፥
ዕዝራ በስሜት አለ ኩምትር።
የሴቲቱ ሁኔታ አሳሰበው፤
የቀድሞ ሃሳቡንም አስረሳው።
ሁኔታዋ እንዳሳዘነው፥ እርሷም እንዲገባት፥
የተሻለውን እንድትመርጥ እንዲህ እያለ መከራት፡-

“የኔ እመቤት የመረረው ሃዘንሽ ልቤ ገብቷል፥
ልጅ ከቤት ሲጎል እጅጉን ያስጨንቃል።
ግን ሃዘንሽ እጅግ የከፋ ቢመስልም፥
እስቲ ላንድ አፍታ ቢሆንም፥
ካንድ እራስሽ ወጣ ብለሽ ተመልከቺ ሁላችንንም፤
ከመጣሽበት ምድረበዳ ጠይቂያት ምድሪቷንም፤
እርሷም ትነግርሻለች፡- የዘውዳችንን ውድቀት፥
የመንግሥታችንን ማጣት፥
የቤተ መቅደሳችንን መፍረስ፥
የሕዝቦቻችንን ስደት፥
የታቦተ ጽዮንን መማረክ፥
የኢየሩሳሌምን ውድቀት፥
የነዋየ ቅድሳትን መመዝበር፥
የሚስቶቻችንን መቀማት፥
የሴትና የወንድ ልጆቻችንን፥

የጀግኖቻችንን መገደል፥
የሌዋውያንን መማረክ፥
የካህናቱን መቃጠል፥
ይህ ሁሉ መከራ በባቢሎን ሰዎች ሲደርስብን፥
በተድላ ደስታ ፋንታ የጋራ ሃዘን ተጭኖብን፥
እስቲ ከራስሽ ወጣ ብለሽ ተመልከቺ ሁሉን።
“አምጬ ባሳር የወለድኩት ልጄ ሲለየኝ በድንገት፥
የኔ ሃዘን የመረረ ነው ተወዳዳሪ የማይገኝለት፥”
በማለት ያንቺን ሃዘን አጉልተሽ ብታይው፥
ካላግባብ ያለቁትን ወገኖችሽንም እስቲ አስታውሺያቸው።
አሁንም፥ ቋሚ ዘመዶችሽ የደረሰብንን የጋራ ሃዘን በልባቸው ይዘው፥
ሊያረጋጉሽ የደከሙትን እስቲ አስቢያቸው።
አንቺም እንደገና ተደርበሽ፥ ጥፍት ስትዪባቸው፥
በሃዘን ላይ ሃዘን፥ ድንጋጤና ፍርኃት እንዳያገኛቸው፤
እባክሽ ለነሱ ብለሽ ተመለሺ፥ አትጥፊ ከጎናቸው።
የአለም አህጉራት ሁለት መልክ ቢኖራቸው፥
አንዱ ከምድራዊነት ነው የሚመነጨው፥
ድሎታቸው፥ ወይንም ጭንቀታቸው፥
ግን ከምድራዊነት ባሻገር፥
ቀሪውም መንፈሳዊነታቸው ብቻ ነው፥
በጉስቁልናም ደስ ሊያሰኝ የሚችለው።
ስለዚህ ከራስሽ ወጣ ብትዪ፥ ወገንሽንም ባትርሺው፥
በመንፈሳዊነት ነው እንባሽ የሚደርቀው፥
በሃዘንም በጉስቁልናም ተስፋሽ እርሱ ብቻ ነው።”
ዕዝራ እንዲህ ሴቲቱን እየመከረ ሲያባብላት፥
እርሷም አልመለስም ብላ ስትሟገት፥
ከልቡ ሲጨነቅላት፥ እጅግ ግራ ገብቶት፥
ሴቲቱ በድንገት ከፊቱ ልውጥ ብላ፥

እንደ ጸሐይም እያበራች ቀረበችው፥
እንደ አንድ የታነጸ ከተማ፥
እንደ አንድ ታላቅ አገር ሁናም ታየችው፤
ከዚያም፥ ምድር እስኪናወጥ ተናግራ ተሰወረች።
　　ዕዝራም በድንጋጤና በፍርኃት ግራ ገብቶት፥
　　እንደወትሮው መልአኩ ዑራኤል ደረሰለት፤
　　ከዚያም ብዙ ብዙ ነገር ገለጠለት።
　　እኛም ኢትዮጵያኖች፥ ዕዝራዎች ነን ለአገራችን፥
　　እንቅልፍም አይወስደን፥ ሳናይ ሰላም፥ ነፃነቷን፥ አንድነቷን።
ይህች የበረሃዋ እመቤት የተባለች፥
በዚህ ታሪክ እጅግ የምትደንቅ የተዋበች፤
ውድ ልጅዋን ብታጣ ከበረሃ ገብታ የአነባች፣
እስራኤል ሀገር እንጂ ሰው አይደለች።
　　ግን፥ ይህ ታሪክ የሚያስተምረን፥
　　አንድም ከራስ ወጣ ብሎ መመልከትን፥
　　ምንጊዜም በአይነ ሕሊና ሠፊውን አገር ማስታወስን።
ለሌላው በማሰብ፥ ሃሳብ ይቃለላል፤
ግላዊነት ሲቀር፥ ጭንቀትም ይጠፋል።
　　የሚያዝኑ፥ የሚተክዙ፥
　　በበዙበት በዚህ በዘመናችን፥
　　እኛም እናተኩር ወደ አገራችን፥
　　ወጣ ብለን፥ ከግላዊነታችን።
የራሱን ትቶ ለአገሩ ስላሰበ ነው፥
ዑራኤል ዕዝራን የቀረበው፥
ለሕዝቦች በማሰብ፥ ራሱን በጾምና ጸሎት ለሚያደክም፥
ከሰማይ ምላሽ ሳይሰጥ አይቀርም።




## <u>*መድኃኒተ ነፍስ - ከቤተ ክርስቲያን*</u>


ቤተ ክርስቲያን ስሄድ ይቀለኛል፤

ከዚያ ስመለስ ይከብደኛል፤

ዲያቆናትና ቀሳውስት ያስቀኑኛል፤

የእነርሱ ጥንካሬ ይገርመኛል።

ለሰማይም ሳይሆን ወይም ለመሬት፥
በጅምር የቀረ፥ ቀዥቀዥ ያለ ሕይወት፥
ካለ ቅዱስ መንፈስ ከቶም እንስሳዊነት።
መቼም ሰው አንዳንድ ጊዜ - ወይንም በድግግሞሽ፥
ሳያጋጥመው አይቀርምና መጠቃት፥
በተለይም መንፈሳዊ ለሆነ - ለሚተጋ በጸሎት፤
የታመመ መዳኛውን፥
የጤንነት ምንጩን፥ እውነት መድኃኒቱን፤
ከሁሉም በላይ ሰው ይመርምር ራሱን፥
መምረጥ ይበጃል፥ ከሁለት ሃሳብ አንዱን፥
ወደ ጥሩ የሚመራውን።
የአለሙን ነገር ያልወደደዱ፥
እነርሱ ብጹአን ናቸው፤
ለመንፈሳዊነታቸው ቅድሚያ በመስጠታቸው፥
በምድራዊ ሕይወታቸው ምንም ሳይጎድልባቸው፥
ዘለአለማዊ ሕይወት ነው የሚጠብቃቸው።
የዋሆች፥ ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ፥
የሚምሩ፥ የሚያስታርቁ፥
ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ፥ ማቴ. 5፡5-9
ለተጎዱ፥ ለተበደሉ ሁሉ የሚያዝኑላቸው፥
እነርሱ ብጹአን ናቸው። ማቴ 5፡4
እግዚአብሔር አምላካቸው የሆነላቸው፥
ለእርስቱ በመመረጣቸው፥
እነርሱ ምስጉን ናቸው። መዝ. 33፡12



## ገዳማት በኢትዮጵያ

ሰዎች በእኩልነትና በነጻነት፥ በሰላምና በፍቅር የሚኖሩባቸው፥
ገዳማት በኢትዮጵያችን በእውነት ልዩዎች ናቸው፤
ይኸም የደብረ ዳሞ ገዳም አንዱ ነው።

በኢትዮጵያ ምድር - እጅግ በታጣበት ሰላም፥
አያሌ ማረፊያ ሥፍራዎች ተዘጋጅተዋል በገዳም።
ጫካ ውስጥ ገዳም፥ ዋሻ ውስጥ ገዳም፥
በእግር ተጉዞ፥ በገመድ ተስቦ፥ ከተራራው ጫፍ ገዳም።
ገዳማውያን - መንፈሳውያን ከምድራዊነታችን መላቀቅን ሽተው፥
የሰማዩን መንግሥት ናፍቀው፤
ወደ ገዳም ሲሄዱ በመንፈስ ተስበው፥
ወደ ላይ የመውጣት ተስፋቸውንም ሽከፈው።[152]
ከገዳም ሲኖሩ በጥቂቱ ተደስተው፥
ባላቸው ብቻ ረክተው።
በመሬት ላይ የጸኑ እንደ ሰማያውያን አህጉራት፥
ነዋሪዎቹ እንደ ሰማይ መላእክት፥
አስተዳደሩም እንደ መንፈሳዊ ኮሙኒስት።
ስብግብነት፥ አልጠግብ ባይነት፤
ለኔ ለኔ ብቻ ማለት የሌለበት፥
ለሌላው በማዘን፥ ራስን እስከ መርሳት፥
ገዳማውያን ሁሉም ለሁሉም ነው የሚያስቡበት፤
ተካፍለው የበሉት፥ ጥቂቱ በረከት።
ኢትዮጵያችን እና ገዳማት - ምድራችን እና ሰማያዊ ስርዓት፥
የመንፈሳውያን ርቀት - እስከ መሰወር በጸሎት ብዛት፤
የፈላስፎች ብስለት - ከሳይንስም ባሻገር - የጥበብ ምጥቀት፤
የወደፊቱ ምድራዊ አኗኗር - እንደ ሰማይ ስርዓት፤
ከገዳማት ይሆናል፥ ስልጡን ሥልጣኔ የሚፈልቅበት።

---

[152]“በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና፤ እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል። በተኵላና በእባብ ላይ ትጫማለህ፤ አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ።” መዝ. 90/91፡ 11-13

## ማጠቃለያ

ምድራዊ እውቀት የጎደለው "ደንቆሮ" ይባላል፤ ከእምነት አልባ አውቂ በምን ያንሳል? ትሁት ሰው ግን፥ ስለ እምነቱም እርዳታ ይጠይቃል። አዎ! ማመን በማወቅ ብቻ አይደለምና፤ እኛስ አወቅን/አላወቅን ማመን የሚገባንን የሚሰጠን አምላክ ስለአለን፥ ረዳታችንም እርሱ ስለሆነ፥ "አቤቱ! አለማመንን አስወግድልን" እያልን እንጸልያለን።

በጽንፍ ሃሳቦች የተወጠረች ምድራችንን ከሁለት አቅጣጫዎች የሚያዩአት ሳያውቋት አረጁባት። ቀኑ ሲመሽ፥ ሌሊቱም ሲነጋ፤ ይህንንም ያንንም እየመሰሉ ሲኖሩ፥ የሁለት አለማት ሰዎች አንድ ወጥ ሰላም አላገኙም።

እያየናት ከምንደነጋገር፥ ከሁለቱ አንዱን ገጽታዋን መምረጥ እና ረጋ ያለ፥ ሰላማዊ ኑሮን መኖር ይቻላል፤ ይኸም በመንፈሳዊ አስተሳሰብ እንጂ፥ በምድራዊው አይደለም።

የምድራችን ነገርማ፥ ቢወራም/ባይወራም፥ ቢጻፍም/ባይጻፍም፥ ግራ የሚያጋባ እየሆነ ነው የመጣው፤ በውስጧ ያለውን ሁሉ እየነካካ የሚያተረማምሳት ኃይል ወደ አህጉራቱ ሁሉ ሰተት ብሎ ገብቷልና።

በዚህች ምድር (በተለይም በኢትዮጵያችን) ጩኸት በረከተ፤ ሁከት፥ ጫጫታ እና ትርምስ በዛ። እስቲ እራሳችንን ከምድራዊነታችን እናግልል - እና በሃሳብ እንምጠቅ።

የኃያላን ጌታም ሁሉን ማድረግ ሲችል፥
ደግ ሰው ሲበደል ክፉው ሲሸነገል፥
ጌታችን ፈጣሪያችን ዝም ያለውን እኛ ምን እንበል?
በስፋት እንዳንናገር፣ ሃሳብ ይጠባል፤
ሃሳብም ሲሰፉ፥ መናገር ያቅታል፤
ንግግርም ሲረቅ፥ ሰሚ ሰው ይጠፋል፤
እንዲሁ ዝም ብለንም ዝም እንዳንል፥
አይነ ልቦናችን ብዙ ነገር ያሳየናል፤
ዕዝነ ሕሊናችንም ብዙ ነገር ያሰማናል፤
በልቅሶና በጩኸት፥ በሁከት እና በግርግር መሃል፤
ጭራሽ ዝም ብሎ ዝም ማለት እንዴት ይቻላል?

ኃያል ድምጽ ሲያስተጋባ፥
የ “ኑ እንሰብሰብ” ጥሪ ደወል ሲደወል፥
አንዳንዱ በግራ ጆሮው ያዳምጠዋል፤
እንደ ንግግር፥ እንደ ማስፈራራት አይነት፥
“ሂዱ ከእኔ ራቁ..” የሚል ይመስለዋል።
ሌላውም በቀኝ ጆሮው ይሰማዋል፤
እንደ ማደፋፈር፥ እንደ ማጽናናት፥
ዶሮ ጫጩቶቿን እንደምትሰበስብ፥
ኑ ወደ እኔ እያለ - እንደ ናፍቆት፥
መልካም ዜና እንደሚያበስር፥
የሰላም ጥሪ - እንደ ፍቅርም አይነት።
ለሚያምን ሁሉ እንደ እምነቱ፥
ፍቅር ነውና መሠረቱ፤
የአንድ ክርስቲያን ሃይማኖቱ፥
መሄጃ አያሳጣውም፥ መንፈሱ ነውና ብርታቱ።
መልስ የማያገኝ ጸሎት የለም፤
ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥም፥
እግዚአብሔር አያዳላም - መልስ ይሰጣል ለሁሉም።[153]
የተቸገሩ፥ የተጨነቁ በተስፋ ይጸናሉ፤
ከቤተ ክርስቲያን ሄደው ይጸልያሉ፤
ምድራዊ ሰው ተለምኖ ከሚሰጠው ብዙ፥
እነርሱ ከሰማይ ቤት የበለጠውን ያገኛሉ።
ከእንባዎችም እውነት ይፈልቃል፤
አይንም ሲጨፈን ልዩ አለም ይታያል።

---

[153] “በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፤ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፤ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።” 2ኛ ዜና መዋዕል 7፡14

በአርምሞ በተመስጦም ኃያል ድምጽ ይሰማል፤
ከድምጹም ብዙ እውቀት ይገኛል፤
እውቀት በእምነት ይበለጽጋል፤
ፍቅርም ሁሉን ያቅፋል።
በመንፈሳዊው መንገድ ከተጓዝን፥
የልባችን ተስፋ (እምነት) ይሆነናል ብርሃን።[154]
ወደ ገዳም የሄዱ፥
ራሳቸውን ረግጠው ተራመዱ፥
ከተፈጥሮ ጋር ተዋሃዱ፥
በአዲስ ሕይወት ጎለበቱ፥
በፍቅር አለም ሰነበቱ።
እነርሱ እንደ ኮሙኒስቶች፥
ሰውን ከሰው የማያበላልጡ፥
በሰው እኩልነት የሚያምኑ፥
ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባቸው፥
በምድር ሲኖሩ እንደ መላእክት ናቸው።
እነኛ ግን፥ ጠፊውን አለም የወደዱ፥
እድሜአቸውን አባከኑት በከንቱ።
በመሰላቸው ምድራዊ ሕይወት ሲነጉዱ፥
የጎደለባቸውን መንፈሳዊ ሕይወት ሲረዱ፥
በቁጭት እና በንዴት ነደዱ። -

---

[154] "እርስ በርሳችሁ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ፤ እንድትድኑም ለወንድሞቻችሁ ጸልዩ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎቱ ብዙ ትረዳለች፤ ግዳጅም ትፈጽማለች።" ያዕ. 5፡16

# ምዕራፍ ስድስት

## ሙሉ ሰው የት አለ?



## ሙሉ ሰው የት አለ?

*ያንን መልካም መንገድ ትቼ፥ ያንን ማድረግ ስችል፥*

*ይህና ያ ሁሉ ተጠራቅሞ ያሳስበኛል፤*

*ሃሳብ ማብዛትና ጸጸት ብቻ ሆኖብኛል፤*

*ሳልወዳት ሳልፈቅዳት ከመሬት መጣበቁ፥*

*እኔው የእኔ ቁራኛ ሆኜ፥*

*እኔን በእኔ አስሬ እንዳልቀር፥*

*መንፈሳዊነቴ ይመራኛል;*

*ነጻ ሆኜ እንድኖር*

*ገዳማዊ ኑሮን ያስመኘኛል።*

*ሙሉ ሰው የታለ?*

*ፈጣሪውን የመሰለ።*

*አዬ! አምላኬ አንተም ለኔ አስብልኝ፥*

*ከችሎታዬ በላይ ሳስብ አትተወኝ።*

*ባቢሎን ጋለሞታ፥ ተለዋዋጭ እንደ እስስት፥*

*እያታለለች፥ በሃብት በንብረት፥*

*እያጠመደች በአለማዊነት ስሜት፥*

*ሰውን ትመራለች ወደ ኃጢአት።*

*ታዲያ፥ በዚህች ምድር የ<u>ሚሠ</u>ራውን ሁሉ እየጠላን፥*

*እንዴት ይሁን ኑሮአችን?*

*ምን ይሁን? የሕይወት መመሪያችን?*

*ሙሉ ሰው የታለ?*

*ፈጣሪውን የመሰለ።*

*ሁሉም ከኛው ጋር ሲሆን፥*

*የሚያስቀን፥ የሚያስለቅሰን፥*

*የሚያስወድደን የሚያስጠላን፥*

*ከራስ ጠጉራችን እስከ እግር ጥፍራችን፥*

*ከሥጋችን ወይም ከአጥንታችን፥*

ከደማችን ወይም ከነርቮቻችን፥
እኛው በእኛው ተጠቃለን፥
ካለ መንፈስ ቅዱስ ባዶ እኮ ነን።
ታዲያ፥ ሳንመነኩስ፥ ገዳም ሳንገባ፥ ሳንመንን፥
እኛነታችን ወደ ጥሩው ካልመራን፥
ማን ይሁን መካሪያችን?
ወደ በጎ የሚያስገባን።

ሙሉ ሰው የታለ?
ፈጣሪውን የመሰለ።

ጥበብን መሻት ባያስገኝም እውነትን፥
እስቲ መስመር እናስይዘው፥
በዳበሳ የነካካነውን።
የትንሽነት ትንሽነት እጅግ መርቀቅ፥
የትልቅነትም ትልቅነት፥ እጅጉን መተለቅ፥
አካል አካልነቱን እስኪያጣ፥
እጅጉን ቢያንስ እስከ መጥፊያው፥
አካል አካልነቱን እስኪያጣ
እጅጉን ቢተልቅ እስከ መጥፊያው፥
ምንድነው የትልቅነትና የትንሽነት ልዩነቱ፥
ለሁሉም መጥፋት ከሆነ መጨረሻው?

አዎ! ቶሎ ሲመሽ ቶሎ ይነጋል፤
ቶሎ ሲነጋም ቶሎ ይመሻል።
የቱጋ ነው የነፍሳችን ውል?
ጫፍና ጫፉ የጠፋብን፥
እኛ ሥጋ ነን ከመሃል፤
ጥፍት ግኝት የምንል።

ጊዜ እኛን ለማስደሰት ሲል ራሱን አያሳጥርም፥
የሩቁን ለማቅረብ ሲል አይጎብጥም፥ አያጎነብስም፤

ነፍሳችን በሥጋ ተጠርንፎ አይቀርም፤
መውጪያ መንገድ አናጣም።
ስለዚህ፥ ጊዜ እንዲያጥርልን ከምንመኝ፥
ለምን እኛው ራሳችንን አናሽማቅቅም?
የሥጋን ብቻ እያሰብን ከምንኖር፥
ለምን በመንፈስ አንኖርም?
　　ምንም ነገር በፍጹም ጥልቀቱ አይታወቅም፤
　　እግዚአብሔርም አይመረመርም።
ሳይንስ የአጽናፈ ሰማይን ውጫዊ ገጽታ ይገልጻል፤
መንፈሳዊ ማስተዋል የውስጣዊውን ገጽታ ያሳያል፤
ንቃተ ህሊና ለሁለቱም ይጠቅማል።
　　ከሳይንስ ተመራማሪዎች እውቀት ይልቅ፥
　　የሃይማኖት አባቶች እንዲልቅ፥
　　የእነርሱው ወደማይተየው ስለሚጠልቅ፥
　　እኛም እነርሱን ተከትለን እንጥለቅ፥
　　እስቲ ወደ ጥልቁ እንግባ፥
　　በማስተዋል እናጠናቅ፥
እኛ ማነን - ሙሉ ሰው የታለ?
ኃጢአት የሌለበት - ክርስቶስን የመሰለ።
መንፈሳዊ ማንነታችንንስ እንዴት እናግኘው?
ፀሐይ፣ ፕላኔቶችና ጨረቃዎቻቸው
ይመሳሰላሉ በተገነቡበት ንጥረ ነገሮቻቸው[155]፥
ሰውም ከመሬት በተገነባ ሰውነቱ፥

---

[155] ጸሐይ በሃይድሮጂን ንጥረ ነገር የበዛባት ስትሆን፥ ሌሎች ንጥረ ነገሮችም በጥቂቱ ይገኙባታል። መሬት፥ ጨረቃ እና ማርስም በብዛት ኦክሲጂን፥ ሲሊኮን እና ማግኔዚየም በውስጣቸው አሉባቸው። በጠፈር ውስጥ ያሉ አካላት ውስጥ ያሉ ንጥረ ነገሮች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ናቸው።

አፈር፥ ውሃ፥ ነፋስና እሳት ፍጥረቱ...፥
ከአካላውያን ሁሉ ጋር ሲዞር ሲሽከረከር፥
ይንቀሳቀሳል፤ "ቁም" እስኪለው እግዚአብሔር።

የከዋክብት ንጥረ ነገሮች በሰውነታችን፥
የፍጥረት ትቢያ በአጥንቶቻችን፥
በዚህ አንድነታችን ልዩ ልዩ ሆነን ታነጽን፤
ግን'ኮ የሁላችንም አንድ ነው መሠረታችን።

ቤቶች ቢለያዩ በአሰራራቸው፥
ሁሉም ይገናኛሉ፥
በአንድ መሬት መቀመጫቸው፤
ስለዚህ፥ ቤትና መሬት በዚህ አንድነት ስለአላቸው፤
አንድላይ ይኖራሉ ከአፈጣጠራቸው እስከ ጊዜ ሞታቸው።
እኛም ሁላችንም ተፈጥሮአዊ አንድነት ስላለን፥
በአካላዊ ስበት ተሳስበን፥
በአካላዊ ሃረግ ተዛመድን፥
በሚታይ ወይንም በማይታይ ኃይል፥
እርስ በርሳችን እየተነካካን፥
ሳንነጣጠል እንኖራለን።

ማንኛውም አካል - ነፍስ ያለውም ነፍስ የሌለውም፥
ካለ ተፈጥሮአዊ ሕግ በዘፈቀደ አይንቀሳቀስም፤
ይህ ስርዓት የጸና ነውና ለሁላችንም፥
ለግዑዛን፥ ለሰው፥ ለአንስሳት እና ለእጽዋትም፥
ካለ እግዚአብሔር ማንም ሊሽረው አይችልም።

አካል አካልን ሲስበው፥ ሲጎትተው፥
ሲያሽከረከረው ሲያዞረው፥
ይህ እንዲህ ከሆነ፥ ትስስሩ እና ዝምድናው፤
ይህንን የሚታየውን አለም በዚህ መልክ ከተረዳነው፥
በማይታየው ዓለም ያለውን እንዴት እንወቀው?

አ! የማይታየው መንፈሳዊ እንደ አውታር
የሚታየውም በዚያ እንደ አጋር፥
ሁሉም እርስ በርስ ተያይዞ ተሳስሮ አብሮ ሲኖር፥
የአካልም የመንፈስም አመንጪ በሆነው፥
በአንድ ማእከል ሲመራ ሁሉም፥
የሁሉም ፈጣሪ ቅድስት ሥላሴ - አንድ እግዚአብሔር።
ከመሪው የተለየ በሥጋው ብቻ የኖረ፥
ሞቶ በስብሶ መሬት ቀረ።
ከመሪው ያልተለየ፥
ሥጋና ደሙን እየተቀበለ፥
ከመላእክት አለም ተቀላቀለ።
መሪውን የማያውቅ ቀውላላ ይሆናል፤
ጠላት ከጠለፈውም ሞትን ይኖራታል፤
ከመሪው ያልራቀ መሪውን ስለሚያውቅ እርጋታን ያገኛል፤
መላእክትንም ስለሚያገኛቸው በሕይወት ይኖራል።
የምድር አበባ ሲደርቅ እንደሚረግፍ፥
ሥጋዬም ሲያረጅ ይከዳኛል፤
የተሠወረ መንፈሴ፥ ከሥጋ ቁራኛ ነጻ ያወጣኛል።
በክርስትና ስሜ ሰማያዊ ዜግነቴ ተመዝግቧልና፤[156]
ሕይወቴ በመንፈሴ ማበብ ይጀምራል፤
ሰማያዊ ፍጥረቴ ዘለአለማዊ ያደርገኛል።
ግን፥ ይህንን አእምሮ የተባለ ነገር፥
እንዴት በራሴ ልመርምረው እላለሁ፤
ግን በድፍረቴ፥ በውስጤም ቢሆን በላዩ፥
ከሥጋዊነቴ ወጥቼ፥ በሌላው ማንነቴ፥
በመንፈሴ መኖርን እለማመዳለሁ፤

156 ኤፌ 2፥6፣ ቆላ 3፥1-3፣ ፊል 3፥20፣ ዮሐ 17፥16

ለዚህም ገዳም ባለበት (በተገኘበት) እጠጋለሁ፤
እኔም እንዳባቶቼ ከምድራዊነት ወጥቼ የምሸሸግበት
ዋሻ እፈልጋለሁ።
ምድሪቱን ሳንለቅ፥ ነፍሳችን ተጣብቃ ከሥጋችን ካለች፥
በበጎ ሥራ፣ በጸሎትና በምስጋና ካኖርናት፥
እርሷም ወደ ፈጣሪዋ ትወስደናለች፤
ስንሞት መጠጊያዋን ፈጣሪዋን ታገኛለች።
ነፍሳችን እንደነበረች፥ ስንሞትም ለዘለአለም ትኖራለች።[157]
ሰማያዊ ፍጥረቴ ዘለአለማዊ ያደርገኛል።
በክርስትና ስሜ ሰማያዊ ዜግነቴ ተመዝግቧል።[158]
ሙሉ ሰው የታለ?
ፈጣሪውን የመሰለ።
አዬ! አምላኬ አንተም ለኔ አስብልኝ፥
ከችሎታዬ በላይ ሳስብ አትተወኝ።

---

157 "ይህ የሚፈርሰው የማይፈርሰውን፥ ይህም የሚሞተውን የማይሞተውን ይለብስ ዘንድ አልወና።" 1ኛ. ቆሮ. 15፡53

158 ኤፌ 2፥6፣ ቆላ 3፥1-3፣ ፊል 3፥20፣ ዮሐ 17፥16



## ሰው እንዴት በራሱ ያውቃል ራሱን?

ሰው እንዴት ያውቃል ራሱን?

ሌላውን ሳይመስል፥ ወይም ሳይሆን።

ሰውማ ብቻውን፥ መሪ ያጣ ደንባራ፥

ተከትሎ ሌላውን፥ ሰው የመሰለውን፥

እጁን አይቶ - ሰጪውን፥
እግሩን ተከትሎ - መሄጃውን፥
ንግግሩን ሰምቶ - ልፈፋውን፥
መጽሐፉን አንብቦ - ፍልስፍናውን፥
ትምህርቱን ተከታትሎ - ያስተማሪውን፥
እንደ ትያትረኛ እንደ ተዋንያን፥
ራሱን ጥሎ ሌላውን እንደሚሆን፥
እንደ ሕልም አላሚ - ከራሱ ተነጥሎ እንደሚኳትን፥
ልዩ አለም ውስጥ እንደሚገባ - ብኩን፥
መጨረሻያውን ሳያውቅ የሚፋጠን።

የአንጎል ህዋሳት መረጃዎችን በማስተላልፍ ሥራቸው፥
ቢደክሙም፥ እርጅና እና ሞት እስኪያጋጥማቸው፥
ወይንም ቢደነዝዙ፥
መሥራት እስኪያቅታቸው።
በኢሌክትሮ ኬሚካሎችም ንዝረት፥
ከወዲያ ወዲህ የሃሳቦች መተራመስ፥
ቅራኔ ከአንጎል ሲጠነሰስ፥
በምድራዊነቱ ችግር ውስጥ ሲነከር፥
በውስጡ ምንም ሰማያዊ እሳቤ ባይኖር፥
የሚያሳዝን ነገር እጅግ ያሳዝነው፥
በጭካኔም ብዛት - ሰው ሁሉ እንደ አውሬ ይሆን ነበር።

በእንግልት ብዛት
አንጎል ወቅታዊ ችግሮችን መፍታት ሲያቅተው፥
ቀኑ መሽቶ እንቅልፍ ሲወስደው፥
በእውን የተደበቀውን ሁሉ ህልም ሲገለጠው፥
ግን ያ ሁሉ ምሥጢር ጥፍት ሲል በነጋታው፥
በእርግጥ፥ የትኛው አለም ውስጥ ነው ያለነው?

የሰው መንፈሱ፥ ለራሱ አቻ 'ሚሆነውን ሲፈልግ፥

ምድራዊነት ሲያርቀው፥
ሰማያዊነት ሲያቀርበው፥
ወይንም በተቃራኒው፥
ልክ በቀን እንደሚታየው፥
ሥጋዊነት - ምድራዊነት - ብቻውን ተፈጥሮአዊነት ሲመስለው፥
ሁሉም ከሁሉም ጋር እንደሚነካካ፥[159]
ይኸንን ነው'ኮ በቅጡ ያልተገነዘብነው።

በአንድ አለም የሰማይና የምድር አብሮነት፥
ምን ይሆን ይህ ጉራማይሌ - ዝብርቅርቅ?
በዚች ምድር፥ የተጣመመ እውነት፥
የተቃና ውሸት የበዛባት፥
ያልጠራ ሕይወት፥ ግማሽ ጤንነት፥
ግማሽ እብደት - ጭንቀት።

አንድ ሰው በአካሉ አንድ ቢባልም፥
በውስጡ ያለው ሌላው ሰው አካል አይደለም።

በፍጥረቱ እንደ ከዋክብት - ባለ ደመ ነፍስ - እንደ እንስሳት፥
ሙሉ ሰው - ሲሆን ሁለት፥
አንዱ ባለ መንፈስ ነው - እንደ ሰማይ መላእክት።

አዬ! ሳይንሳዊ ምልከታ ነው የጎደለን?
ወይንስ መንፈሳዊ ምልከታ ነው የጎደለን?
ለምንድነው?
የሰው ልጅ በአንድ አይነት ምልከታ ያልተመራው?

ምድራዊ፥ ሰማያዊ ጠባያችንን ይዘን በመቆየታችን፥
ሰው ተባልን።

---

[159] አካል ሁሉ ከአካል ሁሉ ጋር በአንድም ሆነ በሌላ ይነካካ ይሆናል። ምናልባትም መንፈስ ሁሉ ከመንፈስ ሁሉ ጋር ይነካካ ይሆናል። አካል ሁሉ ከመንፈስ ሁሉ ጋር የሚነካካ መሆኑን ማን ያውቃል?

ይህ የቅራኔዎች መነሻችን - ፍጥረታችን ባይሆን፥
አንዱ ሰው እንደ ሁለት አይሆን።

ጥሩ ሆኖ በገነት የተፈጠረ፥
ከምድር ሲገባ፥ በላና በጠባዩ ተቀየረ።
ምንድነው ይህ የሰውን ሰማያዊ ጠባይ የሚቀይር፥
የምድራችን እሳት፥ ውሃ፥ አየርና አፈር?
ከየት መጣ ክፋት፥ ሰይጣናዊ ልባምነት?
ሌላው ይሙት፥ እኔ ብቻ ልኑር ማለት?

ገና ድሮ፥ ድሮ፥ የሰው ልጅ በጠላቱ ሲመከር፥
ተጠምዶ ነበር በሁለት ነገር፤
በ“አትብላ” እና በ“ብላ” መካከል ክርክር።
ምድራዊ ታሪካችን ከዚህ መነሻችን ሲጀመር፥
ተነግሮ፥ ተነግሮ የማያልቅ ሆነ - የሰው ነገር - የምድራዊነት ነገር።
ሰው እና ምድራዊነት አብሮ ሲኖር፦
ሰብአዊነት ተቆራረጠ በሞት፥
ግን፥ ጭራሽ እንዳይጠፋ በኃጢአቱ ብዛት፥
ዘለአለም እንዲኖርም በመንፈሳዊው ሕይወት፥
ከላይ ወደታች ወረደ የእግዚአብሔር ምሕረት።
ምንጊዜም መፍትሄው ከላይ ነው የሚመጣው።
የእግዚአብሔር ልጅ (ክርስቶስ) ነው ሰውን ያዳነው።


ሲሮጡ ባንድ ላይ፥ ፈረስ፥ ፈረሰኛው፤
ሲደብቅ፥ ሲገለጥ እስካሁን የቆየው፤
ግቡ ያው፥ ግቡ ያው፥
የመንፈስና የሥጋ ባንድነት ማደግ ነው።
ተመስገን፤
ይህ እድል በአለማችን ሁሉ ተዳርሷል፤
ተመስገን፤ የምድራችን አይኖች ተከፍተውላታል፤
ምድራችን ጠባቂዎቿ በዝተውላታል።

ቅዱስ እውቀትን ሽተን፥
ከቆየንበት አለማመንም ተነቃቅተን፥
ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄድን፤[160]
ከቅዳሴውም ተሳተፍን፤
ከጭለማው አለም ወጥተን፥
ከብርሃናማው አለም ተቀላቀልን፤
መንፈሳዊ አንድነታችንን ስለተጠማን፥
እየወደቅንም እየተነሳንም ብዙ ስለተጓዝን፤
በሃሳብ ብዛት ብንንገላታም፥
አተረፍን እንጂ ምንም አላጣንም።

[160] "መቅደስ ትሥራልኛለህ፤ በመካከላቸውም አድራለሁ። ዘጸ. 25: 8

# ምዕራፍ ሰባት

## ማመን - አለማመን - ማወቅ - አለማወቅ



## መግቢያ

በአሁኑ ጊዜ የመናፍስት ኃይላት ምድሪቱን እያናወጧት ስለሆነ፥ ከእንግዲህ ወደ ከባባድ ጦርነቶች ውስጥ ስለምንገባ፣ ሰዎች አውቀውና አምነውበት ከሚወግኑት ጋርም እንዲወግኑ ለማደፋፈር፤ ሰውም ባለማወቅ ወይንም በሞኝነት ተታሎ፥ ወደ እርኩስ መንፈስ እንዳይጠጋ መምከርና መመካከር አስፈልጓል።[161]

## ማመን - አለማመን - ማወቅ - አለማወቅ

እምነት የእውነት ነጸብራቅ ነው። ከማመን አስቀድሞ ማወቅ ያስፈልጋል ቢባል፥ "ለማመን ምን ያህል እውቀት ያስፈልጋል?" የሚለውን ጥያቄ ያስከትላል። ሰው አውቆም ሳያውቅም ያምናልና፤ ቢያንስ ቢያንስ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ያለውን ልዩነት አውቆ፥ በፈጣሪው የሚያምነውን ሰው አዋቂ ብንለው አይከፋም፤ ከዚያ በላይ የሚያውቀውም ሰው በማወቅ ብዙም አይበልጠውምና።

እውቀት እና እውነት ሁል ጊዜ አብሮ አይሄድም፤ አንዳንድ ጊዜ፥ እውቀት እውነትን ይደብቃል (በተለይ አንዳንድ ዘመናዊ እውቀቶች ብዙ እውነቶችን ሳይከድኑብን አልቀረም)።

ጠቢባን በትላልቅ መጻሕፍቶቻቸው ያሰፈሩትን ሳይሆን፥ በራሳችን አእምሮ መርምረን፥ እንዳውም ከራሳችንም ወጥተን ወደማናየው አለም በምናብ ስንጓዝ፥ በሃማኖት (በእምነት) የምናየው ብዙ ነው፤ ድንቅ ነው፤ ግሩም ነው።

የሰው ልጅ የሚያውቀውን (የሚያውቅ የመሰለውን) ሁሉ ሲሞክር፥ ሲሞካክር ከዚህ ደረሰ። ግን'ኮ፥ የማያውቀውንም (ሳይታወቀው) መነካካቱ አልቀረም። "ከአለማወቅም" በመነሳት አንዳንድ ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች ተሠርተዋል (ተፈጥረዋል)። የሰው ልጅ በራሱ አይምሮ ሳይሆን፥ ከውጪው አለም እውቀቶችንና ሥልጣኔን አግኝቶ እንደሆንስ ማን አወቀ?

አባት እና እናት የሚወልዷቸው ልጆቻቸው ሁሉም ጥሩዎች እንዲሆኑላቸው እንጂ፥ ከልጆቻቸው መካከል አንዱ እንኳን የተበላሸ ባህሪ ይዞ እንዲያድግ አይፈልጉም። እግዚአብሔርም ሰውን በአምሳሉ ሲፈጥር፥ እንደ እሱው ጥሩ እንዲሆንለት እንጂ፥ ብልሹ እንዲሆን አይደለም።

---

161 "የሰው ከንፈሩ ጽኑ ወጥመድ ነው፤ በአፉ ቃል ይጠፋል።" ምሳሌ 6:2

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ዮሐንስ ራእይ ድረስ ያለው ሁሉ፥ የእግዚአብሔርን ፍላጎት እና ተጻራሪ የሆነውን የሳጥናኤል ፍላጎት የሚያሳይ ሲሆን፥ በዚሁ ቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ፥ የሰው ልጅ በራሱ በጎ ፈቃድ ተነሳስቶ፥ መልካሙን እንዲመርጥ የሚያስችለውን፥ በቂ (ከበቂ በላይ) መንፈሳዊ (ሃይማኖታዊ) ትምህርቶች ተቀምጠውለታል። በአንጻሩ፥ የሰው ልጅ በማህበረሰብ ተደራጅቶ ሲኖር፥ ለራሱ የሚበጀውን፥ ለምድራዊ ኑሮው ይጠቅመኛል የሚለውን፤ በሙታን ትንሳኤም የሚያምን ከሆነ፥ ለሰማያዊ ኑሮው ይጠቅመኛል የሚለውን፤ በራሱ በጎ ፈቃድ የተሻለውን ይመርጥ ዘንድ ተነግሮታል (ተሰብኳል)።

ሌሎችም፥ አያሌ መንፈሳዊ/ሃይማኖታዊ፥ ወይንም እንደ ስነ ልቡና፥ ፍልስፍና፤ ምድራዊም፥ መንፈሳዊም የሚመሳሰሉ መጽሐፍት የሚያስተምሩት በመጽሐፍ ቅዱሳችን ካለው እምብዛም አይለይም። ሆኖም፥ በአፈጣጠራችን ከምናውቀው እና ልናውቅ ከምንችለው በላይ የማናውቀው እና ልናውቅ የማንችለው መኖሩን በመዘንጋት፥ ብዙውን ጊዜ የማያምኑ ሰዎች፥ ወይንም ለማመን የሚያመነቱ “ሁሉን አውቄና ተረድቼ እንጂ፥ እንዴት ሳላውቅ ልመን?” እያሉ ነው።

የሰው ልጅ ሁሉን ማወቅ እንደማይችል ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ለምሳሌ፦ መልአክ ጴጥሮስን ከወህኒ ቤት እንዴት እንዳወጣው፥ በሰንሰለት የታሰሩትን ሁለት እጆቹን እንዴት እንደፈታለት፥ የእስር ቤቱም የብረት መዝጊያ እንዴት በራሱ እንደተከፈተ፥ (ዮሐዋ. ሥራ 12፡ 6 - 18) ይህንን ክስተት በእምነት ከመቀበል በስተቀር፥ ማን ሊረዳ ይችላል? ይህን እና ይህንን የመሳሰሉ እውነታዎች መፈጸማቸውን እናስተውላለን። ነገር ግን፥ በእምነት ካልሆነ በስተቀር፥ በምድራዊ እውቀትና ግንዛቤ ብቻ ልናውቅ አንችልም።

ማንም ሰው የሚያምነውን እና የማያምነውን በአቅሙ ልክ መጥኖ ይቀበላል እንጂ፥ ይህ ልክ ነው፤ ይህ ልክ አይደለም ማለት ከአቅም በላይ ይሆናል። ሁሉም በተቀበለው መክሊት የሠራበት ይሸለማል። ማቴ. 25፡ 14-30

እውነት መኖሩን ካወቅን፥ የእውነትን ነጸብራቅ የምናየው በእምነት እንጂ በእውቀት ብዛት አይደለም። ብሩህ ልቦና ይስጠን።

እውነት በሰዎች ቢታወቅም ባይታወቅም፥ ምንጊዜም እውነት ነው። ጊዜ ከማይሽራቸው ፍጹማዊና ዘለአለማዊ እውነቶች መካከል የእግዚአብሔር መኖርና ዘለአለማዊነት እምነታችን ነው። ይህንን ነው፤ እምነት የእውነት ነጸብራቅ ያልነው።

ከፍጹማዊና ሁለንተናዊ እውነት ትንሹን ያወቀ ሰው አዋቂ ይባላል። ከዚያቺም ከታወቀችው ትንሺ፥ እርሷንም ትንሿን ሙሉ በሙሉ የሚያውቃት ግን፥

ማንም የለም። ምንጊዜም በሚታወቀው ውስጥ ሌላ የማይታወቅ ስለሚኖር፥ እውቀት (በተለይም ምድራዊ እውቀት) ፍጹማዊና ሁለንተናዊ ሊሆን አይችልም።

እውቀት በየጊዜው እያደገ ስለሚሄድ አንጻራዊ ነው የሚሆነው። አንድን እውቀት ከኋላው ሌላ እውቀት ሲገፋው፥ ከአንድ ዝቅተኛ አንጻራዊ እውቀት ወደ ሌላ ከፍተኛ አንጻራዊ እውቀት ያሸጋግረዋል። እውነቶች በእውነትነታቸው ለኛ ለሰዎች ሲገለጡ ታወቁ እንላለን እንጂ፥ እውነቶች በራሳቸው ማንነት እንዳሉ ያሉ፥ ህልው ናቸው።

እኛ የማናውቀው እና ሊገባን የማይችለው ከምናውቀው እና ልናውቅ ከምንችለው እጅጉን ይልቃል። አንዳንድ ሰዎች ግን፥ እነርሱ ከሚያውቁት ወይንም ከራሳቸው ስነ አመክንዮ (logic) በላይ፥ ሰፊ እውቀት፥ ሌላ እውነት፥ ረቂቅ ስነ አመክንዮም ሊኖር እንደሚችል አይገነዘቡም።

ማወቅ በማየት እና በመስማት ከሆነ፥ የሰው ልጅ በሁለቱም ውሱንነት አለበት። ፍጹም ማየትን አያይም (ብዙ የማያየው አለና)። ፍጹም መስማትን አይሰማም (ብዙ የማይሰማው አለና)። ስለዚህ፥ ለማመን ማወቅን የሚያስቀድም፥ እስኪያውቅ ሲጠብቅ፥ እስከ ጊዜ ሞቱ ድረስ ላያምን ይችላል። በአንጻሩ፥ ምንም ሳያውቁ ወይንም ባወቁት መጠን ከትንሿ ተነስተው የሚያምኑ፥ እነርሱ ወደ እውነት የሚጠጉ ናቸው፤ እነርሱ፥ በሰው አእምሮ ሊታወቅ ከሚችለው (ከሰው ግንዛቤ) በላይ ወደ ሆነው መጠጋታቸው በውስጣቸው ሊሰማቸው ይችላልና። ሉቃ. 10፡42

ስለዚህ፥ የሰውን እምነቱን ብዙ በማወቁ እና ባለማወቁ አንመዝነው።[162] ምድራዊ እውቀትም ቢሆን ቁልጭ ብሎ ምድራዊ እውነታን ያሳየን ዘንድ ሙሉ አቅም ያንሰዋልና።

ሰውም "ምድሪቱ የኛ ናት፤ በውስጣቸው ያሉትም ሁሉም የኛ ናቸው.." እያለ መደንፋት የለበትም፤ ሁሉም የእግዚአብሔር ነውና። ለእኛ ከሆነውና ከተሰጠን እንድንቋደስ እና መንፈሳዊ አንድነታችንን እናጠነክር እንጂ፥ ማንም ሰው ከገዛ ራሱ ርቆ መሄድ የማይችል፤ እሱነቱ የራሱ ብቻ እንዳልሆነ እና ለሌላም የተሰጠ መሆኑንም እንዘንጋ።

ሃይማኖት ሰዎች በመሰባሰብ በአንድ የጋራ ትምህርት ጥሩዎች እንዲሆኑ፥ በፈጣሪያቸው በእግዚአብሔርም አምነው እርሱን እያመሰገኑና ስሙንም እየጠሩ


---

[162] "ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ፥ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ።" ዮሐ. 3፡ 12

(እየጸለዩ) እንዲኖሩ የሚያደርግ እንጂ ሌላ አይደለም። እኛም አንድ ወጥ ሃይማኖት ያለን የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች የምናምነውን ሲነኩብን አንወድም። እኛ በአለም ዙሪያ ከነበሩና ካሉ መንፈሳውያን ሊቃውንት፥ ጻድቃንና ቅዱሳን ብዙ ተምረናል፤ እነርሱን እንመስላቸውም ዘንድ እንተጋለን።

ሰዎች በመንፈሳቸው፥
ጊዜና ቦታ አይገድባቸውም፤
ይመላለሳሉ፣ የትም የትም።
በመንፈስ አንድ የሆኑ፥
ዘወትር በሃሳብ ይገናኛሉ።
አካላዊ ሁሉ ሲንቀሳቀስ፥
ወደ መጥፊያው ሲገሰግስ፥
ማስተዋል ይገባል፥ መጨረሻው ሳይደርስ።

የተራራውን ስብከት ቢከተሉ ኖሮ ሰዎች፥ ማቴ. 5፡1-16
ተስማምተው ይኖሩ ነበር ተደስተው፥
ምንም ምንም ሳይጎድልባቸው።



**ጥያቄና ተስፋ**

እኔ በእግዚአብሔር አምሳያ እንደ ተፈጠርኩ፥
ትንሽ ትንሽም ቢሆን ከእርሱ ባህሬ ተካፋይ ነኝ።
ታዲያ፥ ከሰው ፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ፥
እኔም በአንድ መልክ የነበርኩና የምኖር ነኝ?

በውስጤ እየፈራሁ ለመናገር እጓጓለሁ፤
ግን ለአፍታ ቆም እላለሁ።
ምናልባት ይህንን አእምሮ የተባለ ነገር፥
ይህንን ሰፊና የተደበቀ ቤት፥
እንዴት በራሴ ልመርምረው እላለሁ፤
ግን በድፍረቴ፥ በውስጤም ቢሆን በላዩ፥
ከሥጋዊነቴ ወጥቼ፥ በሌላው ማንነቴ፥
በሃቀኛው መንፈሳዊነቴ አነበንባለሁ፡-
እንዲህም እያልኩ በደመ ነፍስ አንሾካሽካለሁ፡-
አካል አካልን ሲስበው፥
ይህ እንዲህ ከሆነ፥ ትስስሩ እና ዝምድናው፤
ይህንን የሚታየውን አለም በዚህ መልክ ከተረዳነው፥
በማይታየው ዓለም ያለውን እንዴት እንወቀው።
በአለማወቃችን ውስጥም ትንሽ ማወቅን ብናውቅ፥
ከማይታየውም አለም የሚኖረን ጥምረት፥
ስለራሳችን ከምናስበው በላይ የከበርን ነን።

በመንፈሳዊነት ካልሆነ በስተቀር፥ በምድራዊነት የማይዘገን ሠፊ እውቀት አለ። ይህ እውቀት ለተማሩትም ላልተማሩትም (መሃይማን) ፍንትው ብሎ በየጊዜው ይገለጻል። ዳሩ ግን፥ ይህንን እውቀት ምድራዊ በሆነ መንገድ መግለጽ ስለማይቻል፥ ለተቀረው ሕዝብ ማስተላለፍ ያስቸግራል። ሆኖም፥ በተወሰነ ደረጃ፥ ከማይታወቀው እውቀት ውስጥም፥ ሌላ ልዩ እውቀት እንደሚኖር ከተገነዘብን በቂ ነው።

ከምድራዊነት በመላቀቅ መንፈሳዊ ባህሬን የገነቡ ጻድቃን በሥጋዊ ሕይወታቸው ባይደላቸውም፥ ምንም የቀረባቸው ነገር ያለ መስሎ አይታያቸውም። ሆኖም ሰው ሁሉ እንደነርሱ ጻድቅ ለመሆን ባይችል ወይንም ባይፈልግ፥ ሁሉም የራሱን መንፈሳዊ ሕይወት ቢገነባ፥ ሥጋዊ/ ምድራዊ ኑሮው እንደየባህሬውና ችሎታው ይስተካከልለታል እንጂ፥ ወደ ልዩ ጭንቀትና መከራ አይከተውም።[163]

---

[163] “በእውነት ያለ ጥቂት፥ ከብዙ የኃጣን ሀብት ይበልጣልና።” መዝ. 36፡16

እስቲ ረጋ ብለን ራሳችንን እንጠይቅ፤
ያለንበትን የምንሄድበትንም እንወቅ፡፡
ወዴት ነው የሰው ልጅ በመጓዝ ላይ ያለው?
የት ነው መጨረሻውና መዳረሻው?
ወዴት ነው የዚህ ሥልጣኔ ብለን የጠራነው
አጠቃላይ ሂደቱና አቅጣጫው?
ወደ እግዚአብሔር ነው የሚመራው?
ወይንስ ወደ ሰይጣን ነው የሚያስጠጋው?
አዳምና ሔዋንን ያስከዳ፥
ሰውን ከፈጣሪው የለየ በኃጢአት ግርጊዳ፤
የሰውን ተፈጥሮኣዊ ማንነቱን እያሳጣ፥
ሳያቋርጥ የሚሠራ፤
ብሎም የራሱ ዜጋ ሊያደርግ፥
ወደ ልዩ አለም እየመራ፡፡
ከየአቅጣጫው፥ ከህጻን እስከ አዛውንት፥
የከፋ የከረፋ ምክሩን የሚሰማ እንዲበዛለት፥
ሰይጣናዊ አለምን ለመመሥረት፤
ተፈጥሮአዊ ሂደትን መቀለስ፥
ይህስ እንዳይሆን 'ማይደል ጸሎታችን፥
የሰማዩን መንግሥት መማጸናችን?
ለይተን ባላወቅነው አለም፥
እየታየን ሳይሆን እየመሰለን፥
በብኙታ እንኖራለን፤
በስመ ሥልጣኔ ውስጣዊ ብርሃናችንን አጣን፤
ከባእዳኑ የወረስነው እውቀታችን፥
የማናመልጠው ወጥመድ ሆነብን፤
በውስጡም ብዙ ስለቆየን፥
ከጥንት በተፈጥሮ ሂደት የመጣ፥

የኑሮ ባህሬአችን፡-
ቋንቋችንን፥ ባህል፥ ወጋችንን፥
ዘፈን፥ መዝሙራችንን፥ እንዲሁም ውዝዋዜአችን፥
ፊደላችንን ሳይቀር ትምህርታችን፥
ሁሉም እያየነው ተቀየረብን፤
ማንነታችን ተለወጠብን፤
ስለዚህም፥ ከራሳችን ተደበቅን፤
በሁለት አለም ፍትጊያ ተወጥረን፥
የራሳችንንን ጥለን፥ ስንወርስ የሌላውን፥
አተርፍ ባይ አጉዳይ ሆነን ቀረን።

ኑሮ (ደስታም ሃዘንም) የግል በሆነበት፥
ከእውነት ይልቅ ውሸት በነገሠበት፥
የተዛባ ስነ አመክንዮ - የአስተሳሰብ ጎዶሎነት፥
የቀጨጨ እምነት - የሞራል ልፍስፍስነት፥
የጥላቻ ጀግንነት - የፍቅር ድህነት፥
የአብሮነት - የአንድነትና የሕብረት ፍርኃት፥
የፍቅር ማጣትና የብቸኝነት ናፍቆት፥
በቁስ አካል ቁንጅና መርካት፥
የሰውን ተፈጥሮአዊ ማንነቱን በማይመጥን
ከመሠይጠን የተገኘ ቅሪት፥
እጅግ ሲበዛ ሃብት፥
ለማይገኝ ደስታ - ድካም ካለ እረፍት፤
ወሰን ድንበር የሌለው ምኞት፤
የማይጠረቃ ፍላጎት፤
ቢበላ አይጠገብ - እንዳው መስገብገብ ለምኞት፥
ከሰው መራቅ፥ ወደ ገንዘብ መጠጋት፥
መቀናጣት - ከድሎት ወደ ድሎት፤
አይ! ... የሰበአዊ ልዕልና ማጣት፥

በመንፈስ ወደኋላ ጉትትትትትት.....፥
ሰው ሰው ሆኖ የዘለቀበትን ዘመን እድሜዬ ነው አለ፤
ፊቱ ሲጨማደድ - የመከፋት ምልክቶችን ሁሉ ከፊቱ እያስተዋለ፥
ለመኖር ሲንገታገት - የሚያጠፋውን ጊዜ ኖርኩበት አለ።
ሙብረድ እንዳይኖር ማድረግ ያልቻለ፥
በሥልጣኔ ራሱን ከብርድ ተከላከለ፤
ቃጠሎ እንዳይኖ ማድረግ ያልቻለ፥
በሥልጣኔ ራሱን ከሙቀት ተከላከለ፤
ረሃብ እንዳይኖር ማድረግ ያልቻለ፥
በሥልጣኔ ራሱን ከረሃብ ተከላከለ፤
ታዲያ፥ ሰው በሥልጣኔ ራሱን ቢያደላድል፥
ተፈጥሮን መቀየር አይችል።
የሰው ልጅ ይዘፍናል፥ ይጨፍራል፥
ደስ የሚያሰኘውን ሁሉ ያደርጋል፥
ግን ደስታን መፍጠር አይችል።
ህጻን ልጅ ሲወለድ ያለቅሳል፥
“አትውለዱኝ አትቀስቅሱኝ፥
ልኑርበት እዛው ልሁን..” ይላል፤
ታዲያ፥ ለምን ሲያድግና ሲሸመግል
ከመጣበት ተመልሶ መሄድን - ሞትን ይፈራል?
ሰው ሲሞት ይለቀስለታል፥
ግን ሞትን ሰው ራሱ እንደፈጠራት፥
የገዛ ሥልጣኔውም ራሱን ማጥፊያ እንደሆነ ይዘነጋል።
እውቀቶች በምድራዊ ስነ አመክንዮ እየተመሩ፥
አዳዲስ እውቀቶችም በአሮጌው ላይ እየተደመሩ፥
እየተቀየሩ - እየተሻሻሉ - የዘመኑን ሥልጣኔዎች በያለበት አዳበሩ።
“ፍሬ በፍሬ ላይ ተደራርቦ ጎተራ ሞላ” እንዲሉ፥
በእውቀቶች ላይ እውቀቶች ተደራርበው፥ በምድራችን ሞሉ።

ሆኖም ግን፥ በየሥፍራው ሲያጨናንቅ የሥ**ይ**ጣኔ መንፈስ፥
ኅተራው በጥላቻ ፍሬ ሞልቶ ሲፈስ፥
እውነትም "ሥ**ይ**ጣኔ"፡-
በምድራዊ ድሎት፥ ፍቅረ ነዋይ፥
ወንድም ወንድሙን እስኪሸጥ፥
ሰው በገዛ ወገኑ ላይ ሲጨክን፥
እንዲገዳደል - እንዲጨራረስ።

ከእንግዲህ ተያይዞ መጥፋት ከሆነ መጨረሻችን፥
ምን አይነት ትምህርት - ምን አይነት እውቀት?-
ምን አይነት ሥልጣኔ ነው እኛን ከጥፋት የሚመልሰን?
ምን አይነት ኅተራ ነው፥ ከፍሬዎች መካከል፥
ብልሹውን የሚተፋ - መልካም መልካሙን ብቻ የሚቀበል።
ልዩ ሥልጣኔ ከወዴት ይፈልቃል?
ለመንፈስም ለሥጋም የሚሆን፥
አዲስ ትምህርት (አዲስ እውቀት) ከወዴት ይገኛል።

ከጥንቱም ገበሬው (አስተማሪው) ችግኞቹን (ትምህርት) እየመረጠ ቢተክል፥
ከምድሪቱ ለምድሪቱ (ለሰውም) የሚስማማው ነበር የሚበቅል።

ሳይንቲስቶች የአለም አቀፍ አርኪዎሎጂ ጥናቶችን አካሂደው፥
ከዘቀጡ አለታት ውስጥም ቅርሳ ቅርሶችን ሰብስበው፥
የአትላንቲስን ሥልጣኔ፥ የሳሃራንም ሥልጣኔ፥
የሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃንም ሥልጣኔ አገናኝተው፥
የምድራችን ሥልጣኔ የተሰባበረ መሆኑን ተናግረዋል አጽንተው።
ያም ሆነ ይህ፥ ለምድራችን የሚያስፈልጋት የሥልጣኔ አይነት፡-
ውሃ፥ አፍርና አየር፥ እጽዋት፥ እንስሳና ሰው በአንድነት፥
ባለ ሕይወት፥ ሕይወት አልባም ተስማምቶ የሚኖርባት፤
ለጥፋት የማይውል ሳይንስንም የምንማርበት፥
በመንፈስም ሥራ ምድሪቱን የሚያለመልማት፤

ሁሉም በተናጠል ሳይሆን፥ በተዋህዶ እውቀት፥
ተፈጥሮአዊ ማንነቷን የሚጠብቅላት፥ የሚንከባከባት፤
አዎ! እንዲህ ነበር መሆን ያለበት።

የሰው ልጅ በችሎታው ከጥሩ ተነስቶ መራቀቅ ሲቻለው፥
ወደ ክፋት ማምራቱ ነው እጅግ የሚያሰጋው።
ግን፥ እግዚአብሔር ለጠፈር ሕሊናን ሰጥቶታል፤
በጊዜ ውስጥ የመንፈስና የአካል ሽርሽሩ ይቀጥላል፤
ጥሩው ወደ ምድራችን ይዘልቃል፤
መጥፎውም ከምድራችን ይራገፋል። አላጣንም።

# ምዕራፍ ስምንት

## ማጠቃለያ ሃሳቦች



## ማጠቃለያ

ሰው ሲወለድ ሲሞት፥ እውነቶች ብቅ ብቅ ሲሉ፥
ሃሳቦች ሲነጥሩ፥ ሲጠሩና ሲፈኩ፥
ፍቅር ሲደምቅ፥
ከምድራዊነታችን ባሻገር ለሚሰማን ስሜት፥
የእግዚአብሔር መንፈስ ይታከልበት።

እውቀት እምነትን ማጠናከሪያ ሲሆን ያድናል፤
እውቀት እምነትን ሲያላላ ይገድላል።
የሰው አንጎል ማወቅ የሚችለውን ያህል ያውቃል፣
ማወቅ ብቻውን ጥበብ እንዳልሆነም ይረዳል፤
ጥበብ ከምድራዊነት የሚገኘውን እውቀት ይመረምራል፤
ጠቃሚውን ከማይጠቅመው ይለያል፤
ሳያውቁም ማመን እንደሚቻል ያስገነዝባል።[164]

*********************************************************************

በዘመናዊ ትምህርት - በምድራዊ እውቀት አንጎላችንን አጣበብን፥
የማንነታችንን ሰፊ ድርሻ ምድራዊው ወሰደብን፤
ህልውናችንንም ስላሳጣን፥
መንፈሳዊ እውቀትን እንደ ተራ አስመሰለብን።
የሀገራችንን እሴት እንዳናይ፥
ቅድስት ኢትዮጵያን እንዳናውቃት አደረገን።

ሰማያዊ አሰራር ሳይገባን፡-
"ይህማ ሊሆን አይችልም..." እንላለን፤
በቅድሚያ አምነን ሁሉን ማወቅ ሲቻለን፥

---

164 *"የሥጋ ሃሳብ ሞትን ያመጣብናል፤ የመንፈስ ሃሳብ ግን፥ ሕይወትን እና ሰላምን ይሠጠናል።"* ሮሜ. 8፡6

በዚሁ በምድራዊ አመለካከታችን ተወስነን፥
በክህደት አለም ውስጥ ብዙ ቆየን።
እነርሱን (የክፋት መናፍስትን) ግን ዝም አልን፤
እነርሱም በእጅ አዙር ጠቀለሉን።
እስቲ ማነው?
ማነው ኢትዮጵያዊ?
በአለም ዙሪያ ተመላልሶ ሁሉን ያስተዋለ፤
የራሱን የሆነውን ሁሉ ጥሎ፥ ሌላውን መሆን የቻለ።
ይህንንስ እንኳን እኛ ከኢትዮጵያ የተወለድን፤
ከውጪ የተወለዱትም አልቻሉትም ልጆቻችን፥
ራስን ከድቶ ሌላ መሆንን።
የኛ የኔታ ተግተው ያስተማሯቸው፥ ጠግበዋል በጾማቸው፤
ተደስተዋል በማጣታቸው፥ አጊጠዋል ባላቸው።
ካለ ሥጋ ተጉዘዋል - ተመላልሰዋል - በአይን ቅጽበት ደርሰዋል ከግባቸው።
*********************************************************************
ሰውም በፍጥረቱ ገና ከጥንቱ፥
ከአንድ ሥፍራ (ኢትዮጵያ) ጀምሮ፥
በአህጉራት ሁሉ ሲሰደድ፥
በየብስ፥ በባህር - እዚያና እዚያ ተዘዋውሮ፥
በንግድ ልውውጥና በመቀራረብ አንዱ ከሌላው ተምሮ፥
የሰው ማንነትም እንደየሁኔታው ተለዋውጦ፥
በምድራዊነቱ፥ በኢኮኖሚው ይዘት፥
ወይንም በጉብዝናው፥ ሰላሙን ማስከበሩ በጦርነት፥
መንፈሳዊ ሥልጣኔ ሲጀምር
እና ሲያንሰራፋ በኢትዮጵያችን፥
ጸንቶና ተጠብቆ፥ ቆየ መልካሙ ባህላችን - ህልውናችን።
መንፈሳዊ የእውቀት ጮራ በፈነጠቀበት ዘመን፥
የተባረከ የተቀደሰ ነበር ማህበራዊ ኑሮአችን።

ከውሃዎችም ልዩ ውሃ የሚፈልቁበት የጸበል መገኛዎች፥
የሥጋም የመንፈስም ፈውስ የሚሰጥባቸው ሐኪም ቤቶች፥
ገዳማት እና ቤተ ክርስቲያናትም የበዙባት ስለሆነች፥
ስለተጸለየባት፥ ስለተጸለየላትም ምድሪቱ የተባረከች ነበረች።
የክርስቲያናዊነታችንም ጅማሬም እጅጉን የሚደንቅ፥
የጃንደረባው መንፈሳዊ እድገት - ክርስቲያናዊነት፥[165]
አንድ ሺውን ዓመት፥ እንደ አንድ ቀን የመንገደኛ ሕይወት፥

ጥበብን ፍለጋ ሳይደክሙ፥ ሳይወጡ ሳይወርዱ ካጠገባቸው፥
ከንጉሥ ሰለሞን የሚበልጥ፥ ፈጣሪያቸው መሆኑ አልገባቸው።[166]

እኛስ እንዴት ነው ቶሎ የገባን?
ወይስ ምንድነው ያልገባን?
በየገዳማቱ ትምህርት ቤቶች
መንፈሳዊ ሊቃውንት በዝተውልን፥
የትኛውን አይነት ጥበብ ነው ፈልገን የቀረብን።
ለዘመናት ወደ ውጪ ያስመለከተን።

በሥ**ይ**ጣኔ የማንነታችንን ይዘት - ስለ መቀየራችንም ነገር፥
እስቲ ሁላችንም በእውነት እንመስክር፤
የትኛው ህልውናችን ይሻለን ነበር?
መንፈሳዊነታችን ያመዘነበት፥

---

165 “ፊሊጶስም አፉን ከፈተ፤ ስለ ኢየሱስም ከዚያው መጽሐፍ ጀምሮ አስተማረው። በመንገድ ሲሄዱም ወደ ውሓ ደረሱ፤ ጃንደረባውም “እነሆ ውሓ፥ መጠመቅን ምን ይከለክለኛል? አለው። ፊሊጶስም “በፍጹም ልብህ ብታምን ይገባሃል” አለው፤ ጃንደረባውም መልሶ፥ “ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እኔ አምናለሁ” አለው።” የሐዋ. ሥራ 8፡35-37

166 “የአዜብ ንግሥት በፍርድ ቀን ከዚች ትውልድ ጋር ተነስታ ትፋረዳቸዋለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ ልትሰማ፥ ከምድር ዳርቻ መጥታለችና፤ እነሆ ከሶሎሞን የሚበልጥ በዚህ አለ።” ሉቃ. 11፡31

ወይንስ ምድራዊነታችን ያመዘነበት?
ያኔማ! አሁንም በገጠር እና በየገዳማቱ ያሉ፥
ልጆቻችን ፊደል ቆጥረው “ መልእክተ ዮሐንስን” ያነባሉ፤
የፈጣሪያቸውን አንድነትና ሦስትነት ይማራሉ፤
የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት መሆኑን ያውቃሉ።
በመንፈሳዊነትታቸው የጸና ነውና ኑሮአቸው፡-
ግዕዝ፥ ትግርኛ፥ አማርኛ፥ ኦሮሚኛም ቢሆን ቋንቋቸው፤
ማንነታቸው ታንጿል በእምነታቸው።
ቢደኸዩም፥ ባለጸጎች ባይባሉም፥
ከሰማይ እንጂ ከምድር አይገኝም፥
እርካታቸው፥ ሰላማቸው፥ ደስታቸው፥
ፍቅራቸው፥ አንድነታቸውና ሕብረታቸው።
**********************************************************************
ከአድማስ አድማስ የሚሰማ፥ የቤተክርስቲያን ደወል፤
ተነሱ እንጸልይ የሚል በጧት፥
እኛም ተነስተን ስንጸልይ “በሰላም አውለን” ጸሎት
ማታ “በሰላም አሳድረን” ጸሎት፥
ከምግብ በፊት ከምግብም በኋላም ጸሎት።
ከእንግዲህ ከዚህ የለም ባቢሎን ሰይጣን ይቅና፤
ኢትዮጵያችን ሕዝቦቿም የእግዚአብሔር ናቸውና።
የዘመኑ ሥልጣኔ መረን ለቀቀ፥ ቅጥ አጣ፤
መገታት አለበት መዘዝ ሳያመጣ።
የሰውም ልጅ ከፋትን - ጥፋትን በመካከሉ እያስፋፋ፥
ጊዜው እጅግ አስጊ ሆኗልና - እራሱን በራሱ እንዳያጠፋ።
በእምነት እንኑር - በፍቅርና በተስፋ።
በእግዚአብሔር እስትንፋስ ነፍስ ዘርተን፥
ለሰይጣን እንዳይሆን ሕይወታችን
አቅጣጫንን መቀየስ ያስፈልጋል እንደገና፥

ፈጽሞ አያዋጣምና የያዝነው ጎዳና።

የወደፊቱ ትውልድ እራሱን የሚያድነው፥

በተፈጥሮአዊ ማንነቱ የሚያቆየው፥

ሳይንስም ሆነ ማንኛውንም እውቀት፥

ለጋራ ጥቅም (ምድራዊ/ሰማያዊ) ሲያውለው ነው።

ከምድራዊ ሥልጣኔ ጋር መንፈሳዊነትን አክሎ፥

ክፋት ምቀኝነትን ደምስሶ - ጦርነትን በሰላም ተክቶ፥

ድሎትና ምቾትን አስተካክሎ፥

ፍቅር ደስታን አጎናጽፎ፥

አዲስ ሥልጣኔ ካለ መሠይጠን፥

ምኞታችን ይሄ ቢሆን፥ ስንፈልገው ይገኛል፤

ከውስጣችን ይፈልቃል።

*******************************************************************

አውቃለሁ ብሎ ሌላውን ከሚንቅ፥

አለማወቁን የሚያውቅ ይልቅ።

በእውቁልኝ ራሱን የሚያተልቅ፥

ከእርሱ መታጀል ምንም ቁምነገር አይፈልቅ።

"እኔ አላውቅም.." ብሎ ወደ እምነት የሚጠጋ፥

የማያውቀውንም ለማወቅ የሚተጋ፥

እርሱ ወደ እውነት ስለተጠጋ፤

ይሰጠዋል ሰማያዊ ጸጋ።

*******************************************************************

አዎ! እኛ ሁላችን፥ አላዋቂዎች የተባልን፥

የአምላካችን ጸጋ በዙሪያችን መኖሩ የሚሰማን፥

ጽኑ እምነት አለን - የማይሸከመው አእምሮአችን፤

የማንገልጸው በአፋችን - ጽፈንም የማንዘልቀው በጣቶቻችን።

የሚደግፈን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፥

መንፈሳዊ ክስተቶችም አሉ በዐይነ ልቡናችን የሚታዩን።

ታዲያ፥ የኛ የምንጊዜም ተስፋችን
የምናመልከው እግዚአብሔር ነው አምላካችን።
ጊዜ እውነትን ሲገልጠው፥
የኛ እግዚአብሔር፥ መድኃኒ አለም፥
ክርስቶሳችን፥ ከኛ ጋር ነው ያለው፤
ሰውን እንደገና የሚፈጥረው፥
ሰላሙንም የሚሰጠው - ከመጠፋፋት የሚያድነው፥
ቀድሞም ከሰማይ የወረደው፥
ተመልሶም የሚመጣው - እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
*******************************************************************
ምናልባት ባይኖር ኖሮ ሃይማኖት፥
ደጋጎቹ ይሆኑ ነበር እንደ መላእክት፥
ክፉዎቹም ይሆኑ ነበር እንደ አጋንንት።
የሃይማኖት መኖር ሳይሆን አይቀርም ከመጠፋፋት ያዳነን፥
ደግሞም የሃማኖት ልዩነት ነው አንዱ፥
እርስ በእርሱ የሚያበጣብጠን።
ከምድራዊ ችግሮቻችን ሁሉ ባሻገር፥
ይህ ትውልድ አያልፍም፥ ሰው ሁሉ ሳይዘምር፥
የዲሞክራሲ፥ የነፃነትና የእኩልነትን መዝሙር።
ይህ ትውልድ አያልፍም፥ አለም ሳይመሰክር፥
የኢትዮጵያኖችን መንፈሳዊ አንድነትና ፍቅር።
ከምድራዊ ችግሮቻችን ሁሉ ባሻገር፥
ይህ ትውልድ አያልፍም፥
የኢትዮጵያችንን አንድነት - እድገቷንም ሳናይ፤
ሳናውለበልብ ባንዲራችንን ከሰማዩ ላይ፤
የልምላሜ፥ የብልጽግና፥ የጀግንነታችን ምልክት፥
አረንጓዴ፥ ቢጫና ቀይ።
*******************************************************************

በዚህ መጽሐፍም የተካተቱ ቁምነገሮች
ጊዜ የማይገድበው ኃይል አላቸው፤
በእውነት ኃይልና ሥልጣን የእግዚአብሔር ነው።
ድኅነትን ለሚሻው፥
ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምላሽ አለው።[167]

ስለዚህ፡- የዘወትር ጸሎታችንን[168] እየጸለይን፥
ጠላታችንን፥ የክፋት መንፈስን "ሂድ፥ ከእኔ ውጣ" እንላለን፤
ስንጸልይ የምትጸልይ አብራን፥
የምታማልደን ወላዲተ እምላክ፥ እምዬ ማርያም አለችልን፤
ተራዳኢ መላእክትም አሉ ከጎናችን።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ድኅነትን፥
መንፈሳዊ አንድነትንም አግኝተን፥
ውስጠ ማንነታችን አስከብረን እንኖራለን።

*******************************************************************

እግዚአብሔር የሕዝቦችን ጩኸት ያዳምጣል፤
ጉልበተኛው ሲያይል፥ እጅግ ሲበዛ በደል፥
ማነው ልክ፥ ማነው ሃሰተኛ ሳይል፥
ጻድቁን ከኃጢአተኛው ሳይለይ፥
ወደርሱ የጮኸውን ሁሉ ይሰማዋል።

ሰማያዊውን እውነት የፈለጉ፥
እውነትን ሲሹ ከልባቸው፥
ጥሩውን የሚመክር አጋር ከውስጣቸው፥
ሁሉም እንደየእምነታቸው፥

---

167 "ለምኑ ይሰጣችኋልም፥ ፈልጉ ታገኛላችሁም፥ ደጅ ምቱ ይከፈትላችሁኣልም። " ማቴ 7፡7

168 http://media.wix.com/ugd/a268ea_a1aef37949e4480b9eb4220b3f25afd9.pdf

የመንፈስ ሰላምን አግኝተዋል በአምላካቸው።

**********************************************************************

ከእንግዲህ ሰው ሆይ! እራስህን አታሳንስ፥
እውቀት የለኝም ብለህ፥
እውቀትና ኃይል የእግዚአብሔር ነውና፤
ሁሉንም ከእርሱ ታገኘዋለህ።
የመንፈስና የሥጋ ሚዛን ካንዱ ወዳንዱ ቢያዘምም፥
በምድር ላይ ሥጋ የበላይ ሆኖ መንፈስን አይገዛም፤
ነፃ ፈቃዳዊ ፍላጎት ተሰጥቷልና በዚች አለም፤
እውነተኛው እውነት ይኖራል ዘለአለም።
እውቀትን ተሸካሚ አንጎል ነው ይባላል፥
እርጅና ሲመጣ፥ እውቀትም ይጎድላል፤
እምነት ከልብ ነው፥ ሲያረጁ 'ማይደክም፥
አሻጋሪ ድልድይ፥ የውስጣችን ብርሃን፥
ምንጊዜም 'ማይጨልም።

**********************************************************************

ብቻውን አንድ ሰው ሕይወቱን አይኖርም፤
የማንም ሰው ሕይወት ነውና የሁሉም።
ስለዚህ፥ የሰው ልጅ ተበታትኖ እንዳይቀር፥
ከፋፍሎ የሚያጠቃ ጠላት እንዲባረር፥
ለአንድ አላማ ቆመን እንተባበር።
በዚህ ችግር በበዛባት አለማችን፥
ያበረታናል አዎንታዊነታችን፤
ያድነናል እምነታችን፥ ይጠብቀናል ጸሎታችን[169]።

---

[169] "እንግዲህስ ወዲህ በእግዚአብሔርና በኃይሉ ጽናት በርቱ። የሰይጣንን ተንኮል መቋቋም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ጋሻ ልበሱ። ሰልፋችሁ ከጨለማ ገዦች ጋርና ከሰማይ

ከእንግዲህ፥ እንሰብስብ እራሳችንን፥

ከፍ ከፍ እናድርግ ልቦናችንን፤

አለን ጥበብ በየአይነቱ፥ ከቤታችን፤

ቆንጆ ነው ባህላችን፥

ጨዋነት፥ ደግነት፥ አንድነት ፍቅራችን፤

በቅድስት ኢትዮጵያ/ኤርትራ ሀገራችን።

እግዚአብሔር ቀሪ ዘመናችንን ይባርክልን፤

ምንጊዜም፥ የእግዚእብሔር መንፈስ አይለየን።

*******************************************************************

በእውነት ፈጣሪ አምላካችን እግዚአብሔር ፍጹምና ኃያል፥

ስሙ ክቡር፥ ለዘለአለምም የተመሰገነ ነው።

አስጀምሮ ላስጨረሰን ለፈጣሪ አምካችን ታላቅ ምስጋና ይድረሰው። አሜን።

*******************************************************************

**ተፈጸመ**

*በመቀጠልም፥ "ከምድራዊነታችን ባሻገር"*
*የተሰኘውንም ሦስተኛ መጽሐፍ እንዲያነቡ ተጋብዘዋል።*

---

በታች ካሉ ከክፉዎች አጋንንት ጋር ነው እንጂ፥ ከሥጋዊና ከደማዊ ጋር አይደለምና።" ኤፌ. 6፡ 10 – 12

**ጸሎት**

አቤቱ አምላካችን፥ ፈጣሪያችን፥

ማረን፥ ይቅርም በለን፤

ያንተን እውነት ስጠን፥ ብርሃንክን አብራልን።

ስቃይ መከራ ከመላበት፥

ከረግረጉ ከኃጢአት ጭቃ ውስጥ መንጥቀህ የምታወጣን፥

የፈጠርከን አምላካችን አንተ እንዳለኸን እናውቃለን (እናምናለን)፤

ስለዚህም አንተን ለማመስገን እንደተነሳን፤

አንተም እንድትቀርበን እንደተማጸንን፥

እባክህ አምላካችን፥

በእምነታችን አጽናን፤

ፍቅርህን እውነትህን ግለጽልን።

በስመ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ ብለን፥

እያማተብን በእጃችን፥

ወደ አንተ ስንማጸን፥

ጸረ ሰውን የሚያባርር ኃይልህን ስጠን፤

ምን ጊዜም መንፈስ ቅዱስ ይከበበን።

**<u>የምስጋና መዝሙር</u>**

አምላኬ ሆይ ይድረስህ ምስጋና፤
ከመከራ ስቃይ ጠብቀኸናልና፤
ብርታትና ጽናት፥ አሁን እንድትሰጠን፥
ባንተም ደስ እንዲለን በተስፋ መግበን።

**<u>አዝማች</u>**

በምን ቋንቋ ልግለጽ የአምላኬን ፍቅር፥
እምነቴን እንድገልጽ በውስጤ እንዳይቀር፤
አንተ ነህ አምላኬ፤ ባንተ ነው ሕይወቴ፤
አንተን አልረሳህም እስከ ጊዜ ሞቴ።

ፍቅር እንድንቸር፥ ፍቅርህን አብዛልን፤
ሰላም እንድንሰጥ ሰላምክን አድለን፤
ደስታን እንድንሰጥ ደስታን ጨምርልን፤
ይቅርም እንድል ይቅርታህ አይራቀን።

**<u>አዝማች</u>**

በምን ቋንቋ ልግለጽ የአምላኬን ፍቅር፥
እምነቴን እንድገልጽ በውስጤ እንዳይቀር፤
አንተ ነህ አምላኬ፤ ባንተ ነው ሕይወቴ፤
አንተን አልረሳህም እስከ ጊዜ ሞቴ።

አቤቱ አምላካችን፥ አስባት ኢትዮጵያን፤
የሕዝቦቿን ጩኸት፥ ተመልከት ፍዳዋን፥
ምንጊዜም በጸሎት፥ ስንለምን አንተን፥
አትርሳት ጠብቃት፥ መመስገኛህ ትሁን።

**<u>አዝማች</u>**

በምን ቋንቋ ልግለጽ የአምላኬን ፍቅር፥
እምነቴን እንድገልጽ በውስጤ እንዳይቀር፤
አንተ ነህ አምላኬ፤ ባንተ ነው ሕይወቴ፤
አንተን አልረሳህም እስከ ጊዜ ሞቴ።

# ዋቢ መጻሕፍት

## (ለአራቱም መጻሕፍት)


Abdullah Yusuf Ali (Translation by), 2002: **The Qur'an**, Published by Asir Media.

Bartusiac Marcia (edited and with Introduction), 2006: **Archives of the Universe**, Vintage Books, A Division of Random House, INC. New York.

Bhaktivedanta Swami Prabhupada A.C (His Devine Grace), 1972, 1983: **Bhagavad Gita As it is,** The Bhaktivedanta Book Trust.

Charles Darwin, 1958: **The Origin of Species**, Signet Classics.

Close Frank, 2009: **Anti Matter,** Oxford University Press.

Coogan Michael D., 2003: **World Religions,** Duncan Baird Publications, London.

Davidson Basil, 2005: **Africa in History**; Touchstone, Rockfeller Center, New York, N.Y.

Drage Hale Rosemary, 2004: **Understanding Christianity**, Duncan Baird Publishers, London.

Ehrlich Carl S., 2003: **Understanding Judaism**, Duncan Baird Publishers, London.

Elain Murray Stone, 2004: **A Saint and His Lion, the Story of Tekla of Ethiopia,** Paulist Press.

Francene Dufresne, 1985 : **L'Ethiopie se meurt!** Mais renaîtra, Louise Courteau éditrice

Hammond, 2002: **Concise Atlas of World History**, 6th Edition, Map Makers for the 21st Century; HarperCollins Publishers.

Hausman Gerald, 1997: **The Kebra Nagast**: St. Martin's Press, New York

Hawking W. Stephen And Leonard Mlodinow 2010: **The Grand Design**; Bantam Books, New York.

Hawking W. Stephen, 1988: **A Brief History of Time**, From The Big Bang to Black Holes; Bantam Books, New York.

Hawking W. Stephen, 2005: **The Theory of Everything**, Fate of The Universe; Phonix Books.

Houston Drusilla Dunjee, 2007: **Wonderful Ethiopians of The Ancient Empire**; Nuvision Publications, LLC, Sioux Falls, SD, USA.

Jackson G. John, 1939 And 1985: **Ethiopia and the Origin of Civilization**; Nuvision Black Classic Press, Baltimore, MD. USA.

John Brockman (Editor), 2010: **This Will Change Everything**, Ideas That Will Shape The Future; Harper Collins Publishers, New York, NY. 10022.

Laszio Ervin, 2006: **Science and The Enchantment of The Cosmos**; The Rise Of The Integral Vision Of Reality, Inner Traditions, Rochester Vermont.

Leslau Wolf, 1976: **Concise Amharic Dictionary**, Amharic - English, English - Amharic, Otto Harrassowitz – Wiesbaden, Commercial Printing Press, Adds Ababa, Ethiopia

Mary And John Gribbin, 2003: **From Atoms to Infinity**; Icon Books.

Muhaiyaddeen Bawa M.R., 1987, revised 2004: **Islam and World Peace, Explanations of a SUFI,** The fellowship Press, Philadelphia, PA.

Oldstone Moore Jennifer, 2003: **Understanding Confusianism**, Duncan Baird Publishers, London.

Rana Fazal & Ross Hugh 2004: **Origin of Life**; Navpress, Colorado Springs, CO80920.

Ross Hugh 2010: **Beyond the Cosmos**, **What Recent Discoveries in Astrophysics Reveal About the Glory and Love of God,** 2010:Signalman Publishing, Orlando, Florida.

Southwood, Richard 2002: **The Story of Life**, Oxford University Press.

Steinberg Milton, 1975: **Basic Judaism**, Harcourt Brace Jovanovich, Publishers. San Diego, New York, London.

Vorilhon Claude, 1983፡ **Le Livre Qui Dit La Verite**

Wallis Budge (1932): **The Kebra Negast,** Oxford University Press, London, Humphrey Milford.

ልዑለ ቃል አካሉ (መምህር)፥ 1994፤ ***ሥርአተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ***፥ አትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፥ ዩ ኤስ ኤ፥ አታሚ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።

ልዑለ ቃል አካሉ (መምህር)፥ 1994፤ ***ሥርአተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ***፥ አትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፥ ዩ ኤስ ኤ፥ አታሚ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።

መሪራስ አማን በላይ፥ 2007፤ **ሕይወት እንደገና በሦስት አለሞች**።

ሰሎሞን ይርጋ፥ 1992፤ **ህልውና**፥ አታሚ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ቦጋለ ተፈሪ በዙ፥ 2011፤ **ትንቢት ሼህ ሁሴን ጂብሪል**።

ተስፋ ገብረ ሥላሰሴ (አዘጋጅ)፥ 1978፤ **ገድለ አቡነ አረጋዊ**፥ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1951)፤ ***የኢትዮጵያ ታሪክ*** 2ኛ መጽሐፍ።

ትንሳኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት (አሳታሚ)፥ 1990፤ **ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው**፥ ትንሳኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

አቡነ ሽኑዳ 3ኛ የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ (ውርስ ትርጉም በዲያቆን ታደሰ ወንድም አገኘሁ)፥ 1993፤ **የንስሐ ሕይወት፥** ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፤ አዲስ አበባ።

አባ ኤልያስ ሊቀ ጳጳስ፥ 2009፤ **በአዲስ መሠረት ላይ የነበረው ጥረት፥** Washington D.C. 20018 USA.

አባ ጎርጎርዮስ፥ 1978፤ **የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፥** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

አባ መልከጼዴቅ፥ ሊቀ ጳጳስ፥ 2011፤ **የቅዳሴያችን ይዘት፥** አክላንድ፤ ካሊፎርኒያ-አሜሪካ፤ ጣና ማተሚያ ቤት፥ ቶሮንቶ፥ ካናዳ።

አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር)፥ 1998፤ **ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት፥** ኅትመት ብራና ማተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

አንዱ ዓለም አባተ (የአጸደ ልጅ)፥ 2010፤ **ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ፥** እና ሌሎች ግለ-ወኅች።


አንዱ ዓለም አባተ (የአጸደ ልጅ)፥ 2010፤ **ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ፥** እና ሌሎች ግለ-ወኅች።


አባ ፊሊጶስ፡ 1992፡ **ገድለ ክርስቶስ ሠምራ፡** ተስፋ ገብረ ሥላሰሴ (አዘጋጅ)

ብሩህ ዓለምነህ፥ 2010፤ **የኢትዮጵያ ፍልስፍና የዘርርዓ ያዕቆብና የወልደ ሕይወት ሐተታዎች ትንታኔ (ከነሐተታቸው)**

ዓባይነህ አስፋው፥ 2012፤ **መጽሐፈ ሔኖክ ግዕዝ እና አማርኛ ከአንድምታ ማብራሪያ ጋር።**

ዐቢይ አሕመድ፥ 2012፤ **መደመር፥**

ኢንተርናሺናል መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር፥ 2001፤ **መጽሐፍ ቅዱስ፥** አዲሱ መደበኛ ትርጉም፥ International Bible Society.

ዓሥራት ገብረ ማርያም፤ 1991፤ **ትምህርተ መለኮት፥** ሁለተኛ እትም፥ ንግድ ማተሚያ ቤት ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

ዓባይነህ ካሴ፥ 1992፤ **የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥** ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አንደኛ መጽሐፍ፥ አሳታሚ ማሕበረ ቅዱሳን፥ አዲስ አበባ።

ኤፍሬም አሰፋ ወረደወርቅ፥ 1992፤ **አዲሱ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፥** ሁለተኛ እትም።

ኤፍሬም አሰፋ ወረደወርቅ፥ 1995፤ **ሚሊንየም እንግሊዝኛ-አማርኛ መዝገበ ቃላት፥** Revised Edition.

እሸቱ ታደሠ ወንድም አገኘሁ (ዲያቆን) እና ደጀኔ ሽፈራው በላቸው (ዲያቆን)፥ 1991፤ **ወላዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ፥** ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፤ አዲስ አበባ።

ወሰኔ ይፍሩ፤ አዘጋጅ፤ 1990፤ **ሄኖክ**፤ በየዓመቱ የሚታተም የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር መጽሔት፥ 1101 S.W. Washington St. Suite 129 Portland, OR 97205

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር (አሳታሚ)፥ 1980፤ **መጽሐፍ ቅዱስ**፥ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፥ መጀመሪያ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፥ United Bible Societies Africa Regional Centre, Nirobi, Kenya

የጥንት ሊቃውንት እንደ ጻፉትና እንደተረጎሙት፥ 1983፤ **ተአምረ ማርያም፥** አንደኛ መጽሐፍ፥ አዘጋጅና አከፋፋይ ተስፋ ገብረ ሥላሰሴ፥ አዲስ አበባ።

የጥንት ሊቃውንት እንደጻፉትና እንደተረጎሙት፥ 1946፤ **ገድለ ተክለ ሃይማኖት፥** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ዲበኩሉ ዘውዴ፥ 1986፤ **ፍትሐ ነገሥት ብሔረ ሕግ ወቀኖና**፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ዘበነ ለማ (መምህር/ዶክተር)፥ 2019፤ **ምንትኑ ውእቱ ሰብእ ሰው ምንድን ነው? የማንነትን ትርጉም ፍለጋ፥** አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ

ጥዑመ ልሳን ካሳ (ሊቀ ካህናት - ርዕሰ ደብር)፥ 1981፤ **ያሬድና ዜማው፥** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።